

አዲስ የተቋቋመው የሚንስትሮች ካቢኔ

ከንጉሡ የሚመነጨውና በማዕከል ከሚኒስትሩ ቢሮ ወደታች የሚተላለፈውን የስራ አመራር በክፍለ አገር ደረጃ በተግባር ላይ የሚያውሉ የአገር ግዛት ሚኒስትር ባለሥልጣናትና ሠራተኞች፤ 1. ጠቅላይ አገር ገዢዎች፣ 2. ዳይሬክተሮች፣ 3. ፀሐፊዎች፣ 4. የአውራጃ፣ የወረዳና የምክትል ወረዳ ገዢዎች፣ 5. ዳኞች፣ 6. የኃይል አዛዦች፣ 7. ወታደሮች፣ የፖሊስና የፀጥታ ተወካዮች፣ 8. ሌላ አግባብ ያላቸው፣ ለምሳሌ የገንዘብና የጤና ሚኒስቴር መስሪያቤቶች ተወካዮች ናቸው፡፡

የአገር ግዛት ሚኒስቴር መስሪያ ቤት ሁለት ዋና ተግባራት አሉት፡፡ በአንድ በኩል በፀጥታ፣ በፖሊስ፣ በወህኒ ቤት፣ በጠረፍ ጥበቃና በኢሚግሬሽን ክፍሎች አማካኝነት የመንግስትን ደህንነትና ፀጥታ መጠበቅ፤ በሌላ በኩል በልዩ ልዩ የግብር፣ የቀረጥና የብድር ምንጮች የመንግስትን የገንዘብ ገቢ መጠን ማሳደግ ናቸው፡፡

በአዲሱ መንግስታዊ አወቃቀር ላይ ታማኝ ባለሥልጣናትን እየሾሙ፤ የሁሉም የበላይ ንጉሥ ነገስቱ ሆነው ሚኒስትሮች እስከ ቀበሌ ድረስ ስራው በተዋረድ እንዲቀጥል እያደረጉ በደሞዝ መስራት ጀመሩ፡፡እንደተባለውም የመንግስት ገቢ በግብር፣በቀረጥ፣በአገልግሎት ክፍያዎች ላይ ተመሰረተ፡፡የገቢ አሰባሰብን በተመለከተም በተለያዩ ጊዜያት ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች እየወጡ ተግባራዊ ተደረጉ፡፡

ከ1928 - 33 የነበረው የፋሽስቶች ቆይታ የንጉሡን ስልጣን ለማጠናከር ረድቷል፡፡ ለአብነት ያህል አንዳንድ ተቃዋሚዎቻቸው ተደምስሰዋል፣ የየመኳንንቱና መሳፍንቱ የግል ጦር ፈርሷል፡፡ ምንም እንኳን ጣሊያን ዝሙትን አስፋፍቶ፣ ባህልን በርዞ፣ አንድ ህዝቦችን ለራሱ



በሚያመች መንገድ በብሔር፣ በጎሳ፣ በሃይማኖት ለመከፋፈል የሸረበው ሴራ ባይዘነጋም፤ አንዳንድ የመሠረተ ልማት ዝርጋታዎቹን ለራሱ መጠቀሚያ ሲል ለማከናወን እንቅስቃሴ ጀምሯል፣ በሕግ ሸረው ያልሻሩትን የባሪያ ስርዓት ሙሉ ለሙሉ እንዲደመሰስ አስችሏል፡፡በዚህም በገንዘብ ተቀጥረው የሚሰሩ ሰዎች በመበርከታቸው ጅምሩን ካፒታሊዝም አጠናክረው እንዲቀጥሉበት ረድቷል፡፡

ከጦርነቱ በኋላ በእንግሊዝ ተፅዕኖ ስር ቢሆንም፤ በትምህርት፣ በአስተዳደር፣ በጦር፣ በፖሊስ፣ በፀጥታ፣ በቢሮክራሲ፣ በመንገድ፣ በመገናኛ በንግድና በገንዘብ ስራዎች፣ ድርጅቶችን መልሶ ለመገንባት በተወሰዱ እርምጃዎችና ኤርትራ ወደ እናት አገሯ የመቀላቀሏ ጉዳይ ተደማምረው የጃንሆይን ስልጣን የበለጠ ሲያጠነክሩ፤ በሌላ በኩልም የካፒታሊዝሙ ስርዓት የበለጠ እያደገ እንዲሄድ በር ከፍቷል፡፡

ንጉሡ ከእንግሊዝ በኋላ በአሜሪካ፣ በስዊድን፣ በስዊዝ፣ በፈረንሣይ፣ በህንድ፣ በዩጎዝላቪያና በጃፓን አሰልጣኞችና አማካሪዎች፤ እንዲሁም እርዳታና እገዛ እየተደገፉ ሁሉንም ነገር በቁጥጥራቸው ስር ለማድረግ ችለዋል፡፡

የጃንሆይ መንግስት ቢሮክራሲ ላዕላይ መዋቅሩ በተለያዩ በአዋጅ በሚቋቋሙ መስሪያ ቤቶች እየደረጀና ሕግ እየወጣለት ሲቀጥል፣ ታህታይ መዋቅሩ በልዩ ልዩ የገቢ አሰባሰብ መሰረቱን ጥሎ በየእለቱ እየዘመነና እየጠነከረ እንዲቀጥል ሆነ፡፡

በወቅቱ የእንግሊዝ የበላይነት ጠንከር ያለ ነበርና የገንዘብና የወጪ ንግድ ቁጥጥሩ በእንግሊዞች የበላይነት ስር ነበር፡፡ ኢትዮጵያም የራሷ የሆነ የመገበያያ የወረቀት ገንዘብ አላሳተመችም፡፡ የእንግሊዝ የሁለት ዓመት ውል ካበቃ በኋላ ግን ነገሮች መልካቸውን ቀየሩ፡፡

ከዚህ ቀደም የኢትዮጵያ የመገበያያ ገንዘቦች የማሪያ ትሬዛ፣ የኢጣሊያ ሊሬ፣ የእንግሊዝ ፓውንድ ስተርሊንግና የምስራቅ አፍሪካ ሽልንጎች ነበሩ፡፡ የገንዘብ ቦርዱም በእንግሊዝ ለንደን የነበረ ሲሆን፣ ከሦስቱ የቦርድ አባላት ሁለቱ እንግሊዛውያን አንዱ ኢትዮጵያዊ ናቸው፡፡

በ1937 ዓ.ም ኢትዮጵያ የራሷን "የኢትዮጵያ ብር" አሳተመች፡፡ ስርዓት ያልነበረው የኢኮኖሚ መዋቅር ዘመናዊ እየሆነ ሄደ፡፡ እጅግ ዘመናዊ የተባለው የግብር አሰባሰብና አጠቃላይ የበጀት ስርዓቱ ተግባራዊ መሆን የጀመረው በ1953 ይሁን እንጂ ከነፃነት በኋላ ዘመናዊ የበጀት ስርዓትን ተግባራዊ ማድረግ ተችሏል፡፡

ከነፃነት በኋላ ንጉሡ ኢትዮጵያዊ ምሁራንን ያሰማሩት በአምባሳደርነት እየሾሙ ነበር፡፡ አገር ውስጥም በትልልቅ የመንግስት ተቋማት ታማኞቻቸው የሆኑ ምሁራንን መድበዋል፡፡ የእንግሊዞች የበላይነት በነበረ ጊዜ የውጭ ግንኙነቱን በአምባሳደሮቻቸው አማካይነት እንዲከናወን

አድርገዋል፡፡ በዚህም ጥረት ለምሳሌ በሰኔ ወር 1936 ዓ.ም ቁጥራቸው ከ250 በላይ የሆኑ አሜሪካውያን የልዩ ልዩ ሙያ ባለቤቶች በፍራንክሊን ሩዝቬልት መልካም ፈቃድ ወደ ኢትዮጵያ መጥተዋል፡፡ እነዚህም በሲቪሉ ዘርፍ እንጂ በፖለቲካው ጣልቃ ገብነት አልነበራቸውም፡፡ ኢንጅነሮች፣ የቴክኒክ አማካሪዎች፣ ነርሶች፣ ዶክተሮች፣ መምህራን፣ አናፂዎችና የልዩ ልዩ ዕደጥበብ ባለሙያዎች ነበሩ፡፡

ከ1937 በኋላ ግን ንጉሡ በነፃነት ከተለያዩ ስልጡን አገራት መንግስታት ጋር ግንኙነት በመመስረት አገር ግንባታውን በኢኮኖሚ፣ በጦር፣ በፖለቲካ፣ ወዘተ በስፋት ተያያዙት፡፡ ወደፊት እንደምናገኘው ሰፋ ያለው እገዛ ከአሜሪካ ነበር የተገኘው፡፡ የሚገርመው ግን ጃንሆይ አገር አይመርጡም፡፡ በአሜሪካ ድጋፍ ስራቸውን እየሰሩ በጎን ደግሞ የሶሻሊስቷን የዩጎዝላቪያን ድጋፍ ፈለጉ፡፡ አገኙም፡፡ ማርሻል ብሮዝ ቲቶ ምርጥ ወዳጅ ሆነው ተገኙ፡፡

የዩጎዝላቪያ እገዛ በኢኮኖሚው ዘርፍ ነበር፡፡ በተለይ በ1949 ዓ.ም የመጀመሪያውን ዘመናዊ የ5 ዓመት የበጀት እቅድ ነድፈው አበረከቱ፡፡ በዚህም ጥሩ የሚባል ኢኮኖሚያዊ እመርታ ታዬ፡፡ ከዚህ በኋላ በተከታታይ በወጡ የበጀት እቅዶች ዘርፈ ብዙ ስራዎች ተሰሩ፡፡ ይህም ከከፍተኛው የነዳጅ ማጣሪያ ፋብሪካ ጀምሮ እስከ አነስተኛ ተመሣሣይ የኢንዱስትሪ ዘርፍ፣ ከትልልቅ የትራክተር እርሻዎች እስከ አነስተኛው ተመሣሣይ የግብርና ዘርፍ፣ ከተራ አውራ ጎዳናዎች እስከ ዘመናዊ አየር መንገድ፣ በጦሩም ረገድ ከእግረኛ እስከ ታንከኛ፣ ከአየር ኃይል እስከ ባህር ኃይል በስልጡን አገሮች ድጋፍ ያቀላጥፉት ጀመር፡፡ እነዚህንም በአጭሩ በተከታታይ ለማየት እንሞክራለን፡፡

የጃንሆይ መሬትና እርሻ

‹‹በ1930ዎቹ አጠቃላዩ የኢትዮጵያ የህዝብ ቁጥር የኤርትራን ህዝብ ሳይጨምር 20 ሚሊዮን ያህል ነበር፡፡ አጠቃላይ የኢትዮጵያ የመሬት ቆዳ ስፋት ደግሞ 120 ሚሊዮን ሔክታር ሲሆን፤ ከዚህ ውስጥ 80 ሚሊዮን ሔክታሩ ለግብርና ስራ ተስማሚ እንደነበር ተገምቷል››(ፕ/ር ላጵሶ 1983)

በ ፕ/ሩ ጥናት እንደተመለከተው በዚያ ወቅት 57 ሚሊዮን ሔክታር በመንግስት ይዞታ ስር የነበረ ሲሆን፤ ከዚህም ውስጥ 40 ሚሊዮን ሔክታሩ የሚገኘው በደቡብ፣ 15 ሚሊዮን ሔክታሩ በመሐልና በምዕራብ፣ 2 ሚሊዮን ሔክታሩ በሰሜን ነበር፡፡ ከ1933 - 1966 ዓ.ም የኢትዮጵያ ዋና ዋና የመሬት ይዞታ አይነቶች ደግሞ 1ኛ. የመንግስት ይዞታ፣ 2ኛ. የታላላቅ ጉልተኛ መሳፍንቶች፣ መኳንንቶች፣ ባላባቶች፣ ነጋዴዎች፣ የቤተ-ክርስቲያን፣ የጦርና የፖሊስ ሹማምንቶች ይዞታ፣ 3ኛ. የአርሶ አደሮች



የማሳ ይዞታ ተብለው ይታወቃሉ፡፡ ንጉሡ በተለይ ከስደት መልስ ለታላላቅ ሹማምንት በልዩ ሁኔታ የመሬት ችሮታ አድርገዋል፡፡

ከ1933 ጀምሮ 5 ሚሊዮን ሔክታር መሬት ለሹማምንቶቻቸው በስጦታ በርስትነት ለግሰዋል፡፡ እነዚህም የመንግስት ባለሥልጣን እንደመሆናቸው መጠን በከተማ እየኖሩ በተቀጣሪ ያሳርሳሉ፡፡ በዚህም ላይ ግብር አይከፍሉም ነበር፡፡ በተጨማሪም የመሬት ስጦታው ወደ ደቡብ ነበር፡፡ 20 ከመቶ ያህሉ የቤተ-ክርስቲያን ርስት ነው፡፡ ቤተ-ክርስቲያንም ለመንግስት ግብር መክፈል አታውቅም፡፡ አልለመደችም፡፡

ቀደም ባለው ጊዜ በኢትዮጵያ ለቤተ-መንግስት፣ ለቤተ-ክርስቲያን፣ ለጦርና ለጉልተኛ ባለሥልጣኖች የገባሩ አገልግሎት የምግብ ግብር፣ የምርት ስፍር፣ የአስራት መዋጮ እየተባለ በአይነት ነበር የሚገበረው፡፡ በኃይለስላሴ ጊዜ ግን በገንዘብ እንዲለወጥ ሆኗል፡፡ ሙሉ ለሙሉ የነበረ ባይሆንም፡፡

ጃንሆይ "የ1923ቱን ሕገ-መንግስት መሠረት በማድረግ የመንግስት ገቢ በገንዘብ ግብር እንዲሆን አውጀዋል፡፡ በአዋጁም መሠረት ከ1926 ፣ 1927 ዓ.ም ድረስ ከአገሪቱ መኳንንት፣ ሻለቃና ባለማደሪያ ሹማምንቶች፣ ከከተማ ነዋሪዎችና ከገጠር ገባሮች በአንድነት ለመንግስት የገንዘብ ግብር 2.5 ሚሊዮን ብር ገቢ ተሰብስቦ እንደነበር" የፕሮፌሰሩ ጥናት ያመለክታል፡፡

ንጉሡ በ1934 በታወጀው የመሬት ግብር አዋጅ መሠረት ከወረራው በፊት በመሬት ላይ ተጥሎ የነበረው ግብር ህዝቡ በጦርነቱ ስለተጎዳ በሚል በግማሽ ቀነሱት፡፡ በ1927 በአንድ ጋሻ መሬት 30 ብር ይከፈል የነበረውን 15 ብር እንዲሆን ተደርጎ ነበር፡፡ በአዲሱ አዋጅ መሠረትም አንድ ወጥ ብሔራዊ የመሬት ግብር ሕግ ሲደነገግ ከአፈሩ ልማት አኳያ "ለም"፣ "ለምጠፍ" እና "ጠፍ" ተብሎ በሦስት ተመደበ፡፡ በአገር አቀፍ ደረጃ ለአንድ ጋሻ ለም መሬት በአመት 15ብር፣ በለምጠፍ 10 ብር በጠፍ 5 ብር እንዲሆን ተወስኖ የነበረ ቢሆንም፤ በተሻሻለው በ1937ቱ የመሬት ግብር አዋጅ ግን ለለም በዓመት 50 ብር ለለምጠፍ 40 ብር፣ ለጠፍ 15 ብር እንዲሆን ተደርጓል፡፡ ይህ የሆነውም በአይነት ይከፈል የነበረውን ተጨማሪ የአስራት ግብር በጥሬ ገንዘብ ለመተካት ሲባል ነው፡፡ የዋጋ ተመኑ በስራ ላይ የዋለው በሸዋ፣ በሐረር፣ በወሎ፣ በወለጋ፣ በአርሲ፣ በሲዳሞ፣ በኢሊባቡር፣ በጋሞ ጎፋና በከፋ በሚገኙ የተለኩ መሬቶች ላይ ነበር፡፡

በሸዋ የርስት መሬት ላይ ዝቅ ያለ ተመን ሲጣልበት፣ የጎጃምና የበጌምድር መሬት ግን ግብሩ በቀድሞው ተመን ሆኖለት በአስራት በተገመተው እንዲከፍል ተደረገ፡፡ ከዚሁ አዲስ እርምጃ ጋር በተያያዘም

ቀደም ሲል በገበሬው ላይ ተጭነው የነበሩት ልዩ ልዩ ክፍያዎችና የጉልበት ስራዎች ተሽረዋል፡፡

ነገር ግን አዋጁ በበታች ሹማምንት እየተጣሰ ገበሬው ሕገ-ወጥ ጭቆናው አልቀረለትም፡፡ የንጉሡ ስርዓት ያለው የግብር አሰባሰብ ዓላማም ግቡን ሊመታ አልቻለም፡፡ በስተመጨረሻ ከፍተኛው ዓመታዊ ግብር 80 ብር የደረሰበት ሁኔታ ሲኖር፤ በ1958 ዓ.ም በታወጀው 3ኛው የመሬት ግብር አዋጅ መሠረት ባለመሬቶች ግብሩን እንደቀድሞው ለጉልተኛ ሳይሆን በቀጥታ ለመንግስት እንዲያስገቡ ተደነገገ፡፡

ፐ/ር ባህሩ ዘውዴ "ይህ እርምጃ ተፈፃሚነት ቢያገኝ ኖሮ ርስተጉልትንና ሲሶ ጉልትን የመሻር ያህል ነበር፡፡ ነገር ግን እንዲህ አይነቶቹ ባለመብቶች በተለይም ርስተ ጉልተኞች ከፖለቲካ ስልጣን ጋር ባላቸው የተሳሰረ ግንኙነት ተጠቅመው የአዋጁን ተግባራዊነት ለማሰናከል ችለዋል፡፡ የቤተ-ክህነትን የጉልት መብት የመንካቱ ጉዳይ እንደሆነ ከቶም አልታሰበም" በማለት ያብራሩታል፡፡

የአፄ ኃይለስላሴ መንግስት ሲነሳ የመሬት ግብርና የገበሬ አመፅ የሚሉ ቃላቶች አብረው ይጠቀሳሉ፡፡ ነገር ግን የኢትዮጵያ ዋናው ሀብት ምናልባትም ብቸኛው ያኔ መሬት ነው፡፡ ሹመትና ሽልማት መሬት፣ የገቢ ምንጭ መሬት፣ ሁሉም ነገር መሬት ነውና የንጉሡ ዘመናዊ አስተዳደር ዝርጋታም ሆነ የመንግስት ገቢ በመሬት ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ የመንግስትን ገቢ ለማሳደግ የመሬት ግብር ግድ ነው፡፡ ንጉሡን ወደ መሬት ያወረዳቸውም መሬት ነው፡፡ ጥፋታቸው የመሬት ግብር መጣላቸው ሳይሆን ሰፋፊውን መሬት ለሹማምንቱ መስጠታቸው፣ ሰጥተውም ግብሩን አለመጣላቸው፣ በክልሎች ደረጃ ከዘመኑ ፖለቲካ ጋር በተያያዘ ችግር ፍትሐዊ የግብር አጣጣል ማድረግ አለመቻላቸው ነው፡፡ ሆኖም በተደጋጋሚ የተለያዩ እርምጃዎችን ወስደዋል፡፡በ1960 የመጨረሻውን የእርሻ ገቢ ታክስ አወጁ፡፡ እስከዚህ ጊዜ ድረስ ከግብርናው የሚገኘው ገቢ እጅግ ዝቅተኛ ነበር፡፡

የመጨረሻው አዋጅ እጅግ ፍትሐዊ የተባለና ሁሉንም ያማከለ፤ በመሬቱ አይነት ሳይሆን በምርት መጠን የሚለካ፣ ከፍተኛ ገቢ ያላቸውን በርከት ያለ ግብር የሚጠይቅ ሆኖ ቢታወጅም ማን ይፈፅመው? ገማች ኮሚቴዎች ማዳላት ጀመሩና አበላሹት፡፡ ምንም እንኳ ሰፊው መሬት ለግብርና ምቹ ሆኖ ቢገኝም፤ በተለያዩ ችግሮች ምክንያት በግብርናው ዘርፍ ተጨባጭ ለውጥ ሊመጣ አልቻለም፡፡ ለዚህ ደግሞ ዋናው ችግር ዘመናዊ የማምረቻ ግብአት አለመኖር ነው፡፡ ስለዚህ በውጭ ንግድ ላይ ያተኮረ ከፍተኛ የትራክተር እርሻ ተመራጭ ነበርና እሱኑ ተግባራዊ አስደረጉ፡፡



የዚህ ተሳታፊዎች መንግስት፣ የውጭ ባለሃብቶችና የአገር ውስጥ ባለሃብቶች ናቸው፡፡ ባለመሬቶች የራሳቸውን መሬት ሲያርሱና ሲያሳርሱ፣ ሌሎች መሬት ተከራይተው ማረስ ጀመሩ፡፡ እነዚህ በሰፊ የእርሻ ልማት የተሰማሩ ባለሃብቶች በዋናነት በደቡብ ሸዋና በሁመራ አካባቢ ነበር፡፡ ለአብነትም በእንግሊዛዊው ሜቼል ኮትስ ኩባንያ የተቋቋመው የተንዳሆ የጥጥ እርሻ ልማት በአዋሽ ሸለቆ፣ በኤርትራ የጣሊያን ከበርቴዎች ያቋቋሙት የኤላበረድ እርሻ፣ በመንግስት በኩል በ1954 በአዋሽ ሸለቆ ባለስልጣን አማካኝነት የእርሻ፣ የአግሮ ኢንደስትሪና የሐይድሮ ኤሌክትሪክ እንቅስቃሴዎች ይካሄዱ ነበር፡፡

ለተራው ገበሬም "ሁለገብ የእርሻ ልማት" በተሰኘ ፕሮግራም ምርጥ ዘርና ማዳበሪያ በማደል ግብርናውን ለማሳደግ ተሞክሯል፡፡ ይህም የእርሻ ዘዴና ጥቅም ማስፋፊያ በሚባለው የመንግስት ተቋም አማካይነት ይከናወን ነበር፡፡ ከዓለም ባንክ በተገኘ እርዳታ የተቋቋመው የወላይታ እርሻ ድርጅት "ዋዱ" በሰፈራ ፕሮግራሙ አማካይነት የመሬት መጣበብን ለማቃለል በመቻሉ ደሃውን ገበሬ በማገዝ ውጤታማ ነበር፡፡

የስዊድን ዓለም አቀፍ የልማት ድርጅት /ሲዳ/ ገበሬውን በልማት ሊያግዝ ቢቋቋምም ሐብታም ባለመሬቶች እነሱን የሚያግደውን ሕግ ጥሰው ዋና ተጠቃሚዎች ሆኑበት፡፡ ይህም የጭላሎ እርሻ ልማት "ካዱ" በመባል የሚታወቀው ነው፡፡ ድሆችን ሊረዳ ተቋቁሞ ማናለብኞች ተሻሙት ማለት ነው፡፡ ይሄው ነው፡፡ ፍትህ ከሌለ እርሻ ብቻ ሳይሆን "መና"ም ቢወርድ አይሳካልንም፡፡

የትራክተር እርሻ በተስፋፋበት ጊዜ ለበርካታ ጭሰኞች መፈናቀል ምክንያት ሆነ፡፡ ምክንያቱም ባለመሬቶች በጭሰኛ ከማሳረስ ይልቅ መሬት ማከራየቱን አዋጭ ሆኖ አገኙት፡፡ እለት እለት የጭሰኛው ችግር እየተባባሰ ስለሄደም መንግስት የተለያዩ የመፍትሄ እርምጃዎችን ለመውሰድ ቢሞክርም አጥጋቢ አልሆነም፡፡

በዚህ ረገድ መንግስት የጭሰኛውን ሁኔታ በሚመለከት በ1954 አንድ ኮሚቴ እንዲቋቋም አድርጎ ነበር፡፡ ይህ ኮሚቴ በ1957 ወደ "የመሬት ይዞታ ማሻሻልና ልማት ባለስልጣን" አድጎ ከዓመት በኋላ የመሬት ይዞታና አስተዳደር ሚኒስቴር መስሪያ ቤት ለመሆን በቃ፡፡ በሂደቱም የጭሰኛውን ችግር ለመፍታት ተንቀሳቀሰ፡፡ "ነገር ግን የሚወጡት ረቂቅ ሕጎች /የጭሰኛውን ጥቅም በሚመለከት/ የባለመሬቱን መደብ ጥቅም ስለሚፃረሩ ምክር ቤቱና አባላቱ እያደናቀፉና እያንተቱ አዘገዩት፡፡ የጭሰኛውን ችግር ይፈታል ተብሎ የታመነበት የ1957ቱ ረቂቅ ሳይፀድቅ በመቅረቱም ነው የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች "መሬት ላራሹ" ብለው ሰልፍ የወጡት" እንደ ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴ

አገላለፅ፡፡ ከዚያ በኋላ ባሉት ዓመታትም ተመሣሣዩ የመጨረሻ እቅድ /ረቂቅ/ ሳይሰምር ቀርቷል፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለም ድርቅ፣የአንበጣ መንጋና ሌሎች የተፈጥሮ አደጋዎች ባደረሱት ቀውስ በ1950 በትግራይ፣ በ1958 በወሎ፣ ጥቂት ቆይቶ በ1965ም በዚያው በወሎ ተደጋጋሚ ድርቅና ረሃብ ተከስቶ የብዙ ዜጎችን ህይወት ቀጠፈ፡፡

ተሸፋፍኖ የቆየው ረሃብ በዩኒቨርስቲው ማኅበረሰብና በውጭ ጋዜጠኞች ተጋለጠ፡፡ የተፈጥሮ አደጋው እንዳለ ሆኖ፤ ዋናው ተጠያቂ ሙስና ነው፡፡ ሙስና ጉቦ መቀበል ብቻ አይደለም፡፡ ይህን ጉዳይ በስተመጨረሻ በሰፊው እንቃኘዋለን፡፡ የጃንሆይ አስተዳደርና መሬት በጣም በአጭሩ ያየነውን ሲመስል፤ በአጠቃላይ የግብርናው ዘርፍ በየጊዜው እየተስፋፋ ሄዶ በ1966 ዓ.ም ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ጠቅላላ የአገር ውስጥ ምርት የመጀመሪያውን ደረጃ ይዞ 49.3 በመቶ ቢደርስም በውጤቱ ህዝብን መመገብ የሚችል አልሆነም፡፡

### ጃንሆይና ንግድ

ንግድ በጃንሆይ ዘመን ነው የዘመነው፡፡ አብዛኛው ወደ ውጭ የሚላኩ ሸቀጦች የእርሻ ውጤቶች ነበሩ፡፡ከጠቅላላው የውጭ ንግድ 60 በመቶውን የሚይዘው በዘመናቸው ግጥም ተገጥሞ በጅማ ወጣቶች ዜማ የተሰራለትና ዛሬም ድረስ የሚዘመርለት ቡና ነው፡፡ ቀጥሎ ቆዳና ሌጦ ነው፤ ከዚያም ጥራጥሬና የቅባት እህሎች ይከተላሉ፡፡

የወጪና ገቢ ንግዱ ከወደመጀመሪያ ተመጣጣኝ ስላልነበረ የውጪ ንግዱ ውጤት እዚህ ግባ የሚሉት አልነበረም፡፡ ከውጭ የሚገቡ ሸቀጦችን አገር ውስጥ ማምረት ሲጀመርና ኢንዱስትሪዎች ሲስፋፉ ግን መጠነኛ ለውጥ ታይቷል፡፡ የንግድ ሂደቱ የአገሪቱን የዓለም አቀፍ ግንኙነት አቅጣጫ የተከተለ በመሆኑ 40 በመቶው ከአሜሪካ ጋር ሲሆን በተለይ የቡና ንግድ 70 በመቶው በአሜሪካ ገበያ የሚጣራ ነበር፡፡

በገቢ ንግድ ረገድ ደግሞ በቅደም ተከተላቸው ጣሊያን፣ ጃፓንና አሜሪካ በዋናነት ይጠቀሳሉ፡፡ ንግዱ ኪሣራ መሆኑ ሲታይም ነው የኢንደስትሪ ፖሊሲው ላይ ማተኮር ያስፈለገው፡፡ የውጪ ሸቀጦች ዋጋ እየወረደ፣ የገቢ ሸቀጦች ዋጋ እየናረ ብዙ ኪሳራዎች ታይተው ነበር፡፡ የአገር ውስጥ ንግድን በሚመለከትም ቀደም ሲል በወደቦች አቅራቢያ በሚገኙ የኢትዮጵያ ከተሞች ተጧጡፎ በመሐል ከተማው የቀዘቀዘ የነበረው የአገር ውስጥ ንግድ ወደ አዲስ አበባ አተኩሯል፡፡

የቀድሞው የምኒልክ የአራዳ ገበያ ከወረራው ጊዜ ጀምሮ "ፒያሣ" በሚል አዲስ ስም ተሰይሞ የነጮች መገበያያ ሆኖ ነበር፡፡መርካቶን ለሐበሻ መከለላቸውም ይታወቃል፡፡ ስለዚህ የችርቻሮው ንግድ ከፒያሣ ወጥቶ ወደ መርካቶ ተዛወረ፡፡ ፒያሣ ላይ ሰፍረው ይነግዱ የነበሩ የውጭ



ዜጎች የበላይነታቸው በታታሪው የጉራጌ ብሔረሰብ እየተሸረሸረ ከስሟል፡፡ የመርካቶ ጉራጌዎች በየመን ዓረቦች ቁጥጥር ስር ሆኖ የነበረውን የችርቻሮ ንግድ ለመቆጣጠር የቻሉትም ከነፃነት በኋላ ነው፡፡

አንዳንድ የላይኛው መደብ አባላትም አስመጪና ላኪ በመሆን አንዳንዴ በግላቸው፤አንዳንዴ በመንግስት ሽፋን ተሰማርተውበታል፡፡በመንግስት ደረጃም ብሔራዊ ኮርፖሬሽን የተባለው ድርጅት ተቋቁሞ የእህል ምርትን ለአገር ውስጥ ዜጎችም፣ ለውጭ አገር መንግስታትም ይሸጥ ነበር፡፡ ይህ ድርጅት በ2ኛው የዓለም ጦርነት የኢኮኖሚ ቀውስ ለደረሰባቸው ለአውሮፓውያን ጦርነቱ እየተካሄደ በነበረባቸው ተከታታይ 4 ዓመታት የእህል ምርቶችን በመላክ በሚሊዮን የሚቆጠር ትርፍ አግኝቷል፡፡ ከዚያም የኮርፖሬሽኑን ተሞክሮ መሠረት በማድረግ የውጭ ንግዱን ለመቆጣጠር ወይም ለማመጣጠን ሌሎች ተመሣሣይ የንግድ ተቋማት በመንግስት ደረጃ ተመስርተዋል፡፡ ከእነዚህም ውስጥ "የንግድና የትራንስፖርት ማኅበር" ተብሎ የተሰየመው ድርጅት በቀድሞው አጠራር "ማኅበር ቤት" የሚባለው የተለያዩ የውጭ ሸቀጦችን ወደአገር ውስጥ የማስገባት ሞኖፖል የነበረው ይጠቀሳል፡፡ ሌሎችም ቡና ቦርድ፣ እህል ቦርድ ... ወዘተ ቦርድ የሚባሉ ነበሩ፡፡ የጃንሆይ ዋና የገቢ ምንጭ ጉምሩክ ነው፡፡ የወጪና የገቢ ንግድ ቀረጥ ድንጋጌዎች በተለያዩ ጊዜያቶች ተደንግገዋል፡፡

የአዋጆቹ ትኩረት ከሚወጡት ይልቅ በሚገቡት ላይ ነበር፡፡ በውጪ ንግድ በኩል ታሪፋቸው የተደነገገው ቆዳና ሌጦ፣ ቡና፣ ሰም እና ዝባድ ነበር፡፡ ይህም ዘመናዊ የሆነ አሰራር እስኪዘረጋ ድረስ የቆየ ነበር፡፡ ከገቢ ንግድ የሚገኘውን ቀረጥ ከፍ በማድረግም የመንግስትን ገቢ ማሳደግ ተችሏል፡፡ሆኖም ከወጪ ንግዱ የሚገኘው ገቢ አናሳ ስለሆነ በንግዱ ዘርፍ ተጨባጭ ለውጥ ሳይታይ ቀርቷል፡፡

በጥቅሉ አዲሱ የብሔራዊ ባንክ በገንዘብ ሚ/ር አጠቃላይ መመሪያ ስር የአገሪቱን የውጭ ምንዛሬ፣ የገንዘብ ሕትመት፣ የባንክ ብድርና የወለድ ፖሊሲ በሚመለከት ሃላፊነት ነበረበት፡፡ በ1935 የትራንስፖርት ሕግ ደግሞ በአገሪቱ ታሪክ ለዘመናት በንግድና በመገናኛ ስራዎች እድገት ላይ ተፅዕኖ ሲያደርግ የኖረውን የኬላ ስርዓትና ቀረጥ አስቀርቶ፣ በማዕከላዊ የመገናኛ መስሪያ ቤት ስር ዘመናዊ የሞተር ተሽከርካሪ ስርዓትና አሰራር በመፍጠር በአገራችን የንግድና የመገናኛ ታሪክ አዲስ የእድገት ምእራፍ ከፈተ፡፡ የ1935ቱ የጉምሩክ ሕግ የኢትዮጵያ መንግስት የገንዘብ ገቢ ዋናው ምንጭ የውጭ ንግድ እቃ ቀረጥ እንደሆነ አሳየ፡፡

ነገር ግን ምንም እንኳ እነዚህ መሠረታዊ የባንክ፣ የመገናኛ፣ የጉምሩክና፤ የገንዘብ ድርጅቶችና ስራዎች በአገሪቱ ለዘመናዊ የንግድና የመገናኛ እድገት አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታዎች ቢሆኑም፤ የኢትዮጵያ

ቁልፍ የእርሻና የእደ ጥበብ ክፍለ ኢኮኖሚዎች ኋላቀር በመሆናቸው ለንግዱ ክፍለ ኢኮኖሚ እድገትና መስፋፋት ሊያደርጉ የሚችሉት አስተዋፅኦ በአይነትም በመጠንም የተወሰነ ሆነ፡፡

ቢሆንም የንግድና የመገናኛ ክፍለ ኢኮኖሚው ዘርፍ ከኪሣራ ተነስቶ በየእለቱ እያደገ ሄዶ በአብዮቱ ዋዜማ ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ጠቅላላ የአገር ውስጥ አመታዊ ምርት /ገቢ/ 15.6 በመቶ ሆኖ ነበር፡፡ ይህም ከእርሻ፣ ከአገልግሎት፣ ከኢንደስትሪ ዘርፎች ቀጥሎ የመጨረሻ ደረጃ ላይ የሚቀመጥ ዘርፍ ሆኗል ማለት ነው፡፡

**ጃንሆይ እና ኢንደስትሪ**

የኢንደስትሪው ዘርፍ ከወረራው በፊት ከነበረው ጋር ሲነፃፀር ከነፃነት በኋላ የታየው ለውጥ ከፍተኛ የሚባል እንደነበር ብዙዎች ያምናሉ፡፡ የዚያ ዘመን ንግድና ኢንደስትሪ እንደ አቅሙ መስፋፋት የቻለው ንጉሡ አገሪቱን ለኢንቨስተሮች ምቹ በማድረጋቸው ነው፡፡ ለምሳሌ በ1941 ዓ.ም የተደነገገው የገቢ ቀረጥ አዋጅ ከ2 መቶሺህ ብር በላይ ካፒታል ያለውና በማዕድን፣ በኢንደስትሪና በትራንስፖርት ዘርፍ የተሰማራ ማንኛውም ኢንቨስተር በመጀመሪያው 5 ዓመት የሚያገኘው ትርፍ ከቀረጥ ነፃ ነበር፡፡ በንግድ ኩባንያዎች ትርፍ ላይ የሚሰበሰበው ቀረጥም ከ15 በመቶ እንዳይበልጥ ተደርጎ ነበር፡፡ በሦስተኛው የበጀት ዓመትም ትራክተሮችና ልዩ ልዩ ኬሚካሎች ከቀረጥ ነፃ ሆነው ነበር የሚገቡት፡፡

የንጉሡ አስተዳደር የኢንደስትሪ ፖሊሲ ወጪና ገቢው ይመጣጠን ዘንድ "ከውጭ የሚገቡ ሸቀጦችን በአገር ውስጥ ምርት መተካት" የሚል ነው፡፡ በዚህም መሠረት መጀመሪያ ጨርቃጨርቅ ትኩረትን አገኘ፡፡ አቃቂ ጨርቃጨርቅ ፋብሪካና ባህርዳር ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ በዋናነት ይጠቀሳሉ፡፡

በኢንደስትሪ መስፋፋት ትልቅ ድርሻ የሚሰጠው በሆላንዱ ኩባንያ ፀኤች.ቪ.ኤ ይካሄድ የነበረው የስኳር ኢንደስትሪ ሲሆን፤ ከነፃነት በኋላ ምቹ ሁኔታ ተፈጥሮለት በ1946 ዓ.ም ሁለት የስኳር ማምረቻ ፋብሪካዎች ማለትም ወንጂ እና መተሐራን አቋቋመ፡፡ የወንጂ ስኳር ፋብሪካ መሠረቱ የጣሊያን ነበር፡፡ ጣሊያን በአዋሽ ሸለቆ የሸንኮራ ተክል ማሳ መስርቶ ነበር፡፡ በ1953 ዓ.ም ኤች ቪ ኤ ተብሎ የሆላንድና የኢትዮጵያ ተብሎ ተሰየመ፡፡ በርካታ ኢትዮጵያውያንም በሥራ ተሳታፊ ነበሩ፡፡ በኩባንያው አክሲዮንም ኢትዮጵያ አንድ ሦስተኛ ድርሻ ነበራት፡፡ በ1959 ከፍተኛ የተባለውን 10 ሚሊዮን ብር ትርፍ ያስገኘ ኩባንያ ነበር፡፡ ለሸማቹም ትልቅ ለውጥ ነበረው፤ ቀድሞ ስኳር ከውጭ ይገባ ስለነበር፡፡

ሌላው መጠጥ ሲሆን፣ የመንግስት የገቢ ምንጭ በመሆን ሰፊ ድርሻ ነበረው፡፡ ከወረራው በፊት የተመሠረተው የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ



ፋብሪካ የረጅም ዘመን ሞኖፖሉን ከሜታ አቦ ቢራ ፋብሪካ ጋር መጋራት ጀመረ፡፡ ኮካ ኮላና ፔፕሲም አገር ውስጥ መዘጋጀት የጀመሩት በንጉሡ ዘመን ነው፡፡

የማዕድን ኢንደስትሪን በተመለከተም ከነፃነት በኋላ በአዶላ የተጀመረው የወርቅ ማዕድን ቁፋሮ እጅግ የላቀውን ገቢ ያስገኘ ሆኗል፡፡ ለምሳሌ በ1937 ዓ.ም ከመንግስት ገቢ አንድ አምስተኛ የተገኘው ከአዶላ ወርቅ ነው፡፡ ይህ ዘርፍ መንግስትን ስላከበረ አዶላ የሚለው የአገር ስም በክብረ መንግስት ተቀየረ ይባላል፡፡

በጥቅሉ የኢጣሊያ መሠረት ያላቸውን ጨምሮ የጨርቃ ጨርቅና ሲሚንቶ ፋብሪካዎች፣የዘይት መጭመቂያዎች፣የእንጨት መሰንጠቂያዎችና የእህል ወፍጮዎች በእጅጉ ተስፋፍተዋል፡፡ የቆቃ ግድብም በ40 ሚሊዮን ብር ተሰርቷል፡፡ ይህ 40 ሚሊዮን ብር የኢትዮጵያ መንግስት ከኢጣሊያ ማግኘት የነበረበትን ካሳ ሳያገኝ ቀርቶ፤ነገር ግን 40 ሚሊዮን ብር ብቻ በሰጠው ካሣ የተሰራ ነው፡፡ የኢጣሊያ መንግስት ለሊቢያ ተገቢውን የጦር ካሣ በቢሊዮን የሚቆጠር ዶላር ቢከፍልም፤ኢትዮጵያ የጠየቀችውን ገንዘብ ግን አልከፈለም፡፡ከ40 ሚሊዮን ብር ውጪ፡፡

ሌላው የኢጣሊያ ጅምር ኢንደስትሪ የአዲስ አበባው የቃጫ ፋብሪካ የሚጠቀስ ሲሆን፤ አባ ሳሙኤል ተብሎ ከሚጠራው ግድብ የተጠለፈው የመብራት ኃይል ምንጭም የእነሱው አሻራ ነው፡፡ በንጉሡ ጊዜ ባየነው መልኩ ከውጭ በሚገቡ ምርቶች ላይ ከፍተኛ ቀረጥ በመጣል ያገር ውስጡን ኢንደስትሪ ለማስፋፋት ተሞክሯል፡፡

የኢንደስትሪዎች ማዕከል በአብዛኛው በአስመራ፣ በአዲስ አበባና በድሬዳዋ ከተሞች ሲሆን፤ በተለይ በአገሪቱ ካሉ ፋብሪካዎች ውስጥ ግማሽ ያህሉ በአዲስ አበባ ይገኙ ነበር፡፡ ለአብነት ያህል የተነሱት ዘርፎችና መሰል የኢንደስትሪ ተቋማት እየተስፋፉ በመሄዳቸውም የሰራተኛው ገቢ የጨመረበት ሁኔታ ከመፈጠሩም በላይ፤ በአብዮቱ መዳረሻ የሰራተኛው ቁጥር 54 ሺ ያህል ደርሶ ነበር፡፡

የዜጎች አማካይ የዓመት የነብስ ወከፍ ገቢም 72 ዶላር ከሃምሳ ሣንቲም ደርሶ ነበር፡፡የሰራተኛው መደብ ከየክልሉ መጥቶ ኢንደስትሪ በተቋቋሙባቸው ቦታዎች በጋራ ሲሰራም የመሰብሰብ እድሉን አግኝቶ በእድርም፣በእቁብም መልክ የተለያዩ ማኅበራትን መመስረት ጀመረ፡፡የክፍያ መሻሻልና የመሣሠሉት ጥያቄዎች በአቤቱታ መልክም በአድማ መልክም መካሄድ ሲጀምሩ፤ መንግስት በ1954 ዓ.ም የመጀመሪያውን የሠራተኛ ማኅበር አዋጅ ደነገገ፡፡ በዓመቱ የኢትዮጵያ ሰራተኞች ማኅበር ኮንፌዴሬሽን ተቋቋመ፡፡ የወንጂ አድማ በ1953 ነበር የተቀጣጠለው፡፡ የመጀመሪያው የስራ ማቆም አድማ በወንጅ ሠራተኞች


ተጀምሮ ወደሌሎችም በመዛመቱ ወደኋላ ላይ ለንጉሡ ውድቀት ዋናውና አንዱ ግብአት ሆኗል፡፡

ባጭሩ በኢንደስትሪው ዘርፍ የታየውን መሻሻል ስናይ በ1966 ዓ.ም 436 ፋብሪካዎች፣ 54 ሺ 816 የፋብሪካ ሠራተኞች ነበሩ፡፡ አጠቃላይ የክፍለ ኢኮኖሚው የብሔራዊ ምርት ድርሻ ከመቶ 16.1 ሆኖ የታየው በ1966 ዓ.ም ነው፡፡ ዘርፉ "ከባድ" በሚባሉት ሳይሆን አነስተኛና መካከለኛ የሚባል ሆኖ፤ የምግብ፣ የመጠጥ፣ የትምባሆ፣ የጨርቃጨርቅ፣ የቆዳና የጫማ፣ የእንጨት፣ የሲሚንቶ፣ የሸክላ፣ የመስታወት ስራዎች፣ የሚጠቀለሉ ብረት ነክ ያልሆኑ የማዕድኖች ስራ፣ የማተሚያ፣ የኬሚካል፣ የብረታ ብረትና የመሳሰሉትን የሚያካትት ነው፡፡

በአጠቃላይ በአብዮቱ ዋዜማ በኢኮኖሚው በኩል ግብርናው 49.3 በመቶ፣ የአገልግሎት ዘርፉ 19 በመቶ፣ ኢንደስትሪው 16.1 በመቶ፣ ንግድ 15.6 ከመቶውን ሸፍነው ነበር፡፡

የጃንሆይ የጦር ግንባታና የመሠረተ ልማት ዝርጋታ

ኢትዮጵያ ከጦርነቱ በፊት ዘመናዊ ጦር አልነበራትም፡፡ የሆለታ ገነት ጦር ትምህርት ቤትም የመጀመሪያ ሰልጣኞችን ሳያስመርቅ ነበር ጦርነቱ የተነሳው፡፡ "ነጭ ለባሽ" በሚል መጠሪያ የሚታወቁ ጥቂት የከተማ ፖሊሶች ነበሩ፡፡ ከነፃነት በኋላ ግን ዘመናዊ ፖሊስ ማግኘት ችላለች፤ በ1934 ዓ.ም በእንግሊዞች፡፡ እንግሊዞች ከመልቀቃቸው በፊትም 5 ሺህ የሰው ኃይል ያለው "የክቡር ዘበኛ ጦር" የተባሉት ወታደሮች በስዊዲናውያን መኮንኖች እንዲሰለጥኑ ተደረገ፡፡



የክብር ዘበኛ ጦር፣1928

በ1937 ዓ.ም ንጉሡ አሜሪካዊው አይዘንሐወር ግብፅ ውስጥ በነበሩበት ጊዜ ወደ ግብፅ አምርተው ተገናኟቸውና በኢትዮጵያ ስላለው



ወቅታዊ ሁኔታ ተነጋገሩ፡፡ ስለ ኤርትራ፣ ስለኦጋዴን፣ ስለምድር ባቡር አጠቃላይ ሁኔታውን አስረዱ፡፡

የአሜሪካው የፔትሮሊየም ኩባንያ "ሲንክልየር ሊዉስ" በኦጋዴን የነዳጅ ዘይት ፍለጋ ጥናት ቢያካሂድ ኢትዮጵያ ፈቃደኛ እንደሆነች ንጉሡ ያስረዱትም፡የኦጋዴን ግዛት የይገባኛል ጥያቄ መፍትሄ እንዲያገኝና፣ በዚያውም ከአሜሪካ ጋር ጥብቅ ቁርኝት ለመመስረት ነበ ፡፡

ከ1937 ዓ.ም በፊት የአሜሪካውያን ተሳትፎ በሲቪሉ ዘርፍ ነበርና አሜሪካ በወታደራዊው መስክ ልዩ ድጋፍ እንድታደርግ ንጉሡ ተማፀኑ፡፡ ሆኖም አሜሪካ ለዘብተኛ አቋም ይዛ ጥቂት ጊዜ ቆየች፡፡ ከ1938 ዓ.ም ጀምሮ የተወሰኑ ወታደራዊ እገዛዎችን ስታደርግ ቆይታ፣ በ1945 ዓ.ም ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር በፌዴሬሽን ስትተሳሰር ግን አሜሪካም አስመራ ባላት የመገናኛ ጣቢያ ምክንያት የመካከለኛው ምስራቅ ስትራቴጂካዊ ጥቅሟ ከኢትዮጵያ ጋር ተያያዘ፡፡ ወዲያውም የእንግሊዝ ወታደራዊ ተራድኦ ቡድን ከኢትዮጵያ ሲወጣ ኢትዮጵያ የተሟላ ድጋፍ ከአሜሪካ ማግኘት ቻለች፡፡

በ1944 ዓ.ም በገማል አብደል ናስር አማካኝነት በግብፅ የተካሄደው አብዮትም አሜሪካ በመካከለኛው ምስራቅና በቀይ ባህር ዳርቻ ያላትን አቋም በደንብ እንድታጤን አስገደዳት፡፡በእነዚህ ሁኔታዎች መነሻነት አሜሪካና ኢትዮጵያ ኢኮኖሚያዊና ወታደራዊ ስምምነት ተዋዋሉ፡፡

"የአሜሪካ ተፅዕኖ ከሁሉም ጎልቶ የታየው በስልጠናና በትጥቅ መስክ ነበር፡፡ ከ1938 እስከ 1964 ድረስ አሜሪካ ያደረገችው ወታደራዊ እርዳታ በ180 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር የሚገመት ነበር፡፡ ከ1945 እስከ 1960 ባለው ጊዜ ከ5 ሺ 500 በላይ የሆኑ ኢትዮጵያውያን በአሜሪካን አገር የተለያዩ ወታደራዊ ስልጠና አግኝተዋል፡፡ ከዚህ በተረፈ ጀቴ፡ፀረ-አውሮፕላን መቃወሚያው፣ የባህር ኃይል መርከቡና ጀልባው፣ የእግረኛው መሣሪያና አንዳንዴ ዩኒፎርሙም ሳይቀር የሚመጣው ከአሜሪካ ነበር፡፡ በትጥቅም ሆነ በስልጠና የአሜሪካ ወታደራዊ እርዳታ ቁንጮ ውጤት ተብሎ የሚገመተውና በዘመናዊነቱና በቅልጥፍናውም ዝናን ያተረፈው የአየር ኃይሉ ነበር፡፡" (ኘ/ር ባህሩ ዘውዴ2002)

አሜሪካ በ1945ቱ ስምምነት መሠረት በአስመራ የሚገኘውን የመገናኛ ጣቢያዋን ማለትም በመካከለኛው ምስራቅ ኮሚኒስት አገሮችን ለመከታተል የሚያስችላትን የስለላ ጣቢያ "ቃኘው ጦር ሠፈር" በሚል ስያሜ በመሰየም ይዞታዋን ስታረጋግጥ፣በምላሹም "ማግ" በሚል ምህፃረ ቃል በሚታወቀው የወታደራዊ እርዳታ አማካሪ ቡድን አማካይነት ሦስት ክፍለ ጦር ሠራዊት ለኢትዮጵያ አሰለጠነች፡፡ አሰልጥናም አስታጠቀች፡፡የኢትዮጵያ የምድር ጦር ቀደም ብሎ ከሰለጠነው ጋር

ተዳምሮ በአራት ክፍለጦሮች ተደራጀና አንደኛው ክፍለ ጦር /ክቡር ዘበኛ/ በአዲስ አበባ፣ ሁለተኛው ክፍለ ጦር መጀመሪያ ደሴ፣ ቀጥሎ ኤርትራ፣ ሦስተኛው ሐረር፣ አራተኛው ከፊሉ አዲስ አበባ ከፊሉ ነገሌ ቦረና ተመደበ፡፡

በየክፍሉም አሜሪካውያን አማካሪዎች ተመደቡ፡፡ የምድር ጦሩን በዘመናዊ መንገድ ካደራጁ በኋላም በስዊዲኖች ተጀምሮ የነበረውን የአየር ኃይልና በኖርዌጆያኖች እየተደራጀ የነበረውን የባህር ኃይል ተሳትፈውበታል፡፡ በእንግሊዝ ስር በነበሩት ህንዶች ይተዳደር ለነበረው የሐረር ጦር አካዳሚም የማቴሪያል ድጋፍ ያደረጉ ሲሆን፤ የአሜሪካውያን አሻራ ያላረፈባቸው የጦር ክፍሎች ተብለው የሚጠቀሱት ክቡር ዘበኛና ፖሊስ ናቸው፡፡

በጃፓን አማካሪነትም ባፋጣኝ የማዕረግ እድገትና ሹመት ብዙ ከፍተኛ መኮንኖች ሊፈጠሩ ችለዋል፡፡ "ከ1939 እስከ 1948 ድረስ በዘጠኝ ዓመታት ውስጥ አራት ብርጋዴር ጀኔራሎች ብቻ የነበሩ ሲሆን፤ ከ1949 እስከ 1959 ድረስ በአስር ዓመታት ውስጥ 42 ብርጋዴር፣ ሜጀርና ሌተናል ጀኔራል መኮንኖች ተፈጥረዋል፡፡" (ፐ/ር ላጺሶ1983)

አጠቃላይ ጦር ኃይሉም በአንድ የጦር ሚኒስቴር ስር እንዲተዳደር ተደርጓል፡፡ ኢትዮጵያ ከ1940ዎቹ ጀምሮ በተከታታይ በአሜሪካውያን ሰፊ ድጋፍ በባህር ኃይል፣ በአየር ኃይል፣ በምድር ጦር በኩል በደንብ የተደራጀ የምርጥ ዘመናዊ ጦር ባለቤት ሆነች፡፡ ከባድ የጦር ካሚዮኖች፣ ታንኮች፣ ወዘተ አሜሪካውያን ለገሱ፡፡ ምንም እንኳ የ2ኛው የዓለም ጦርነት ቅሪት ቢሆንም፡፡

በጥቅሉ አሜሪካ ኢትዮጵያ ለኮሚኒዝም ጥቃት እንዳትጋለጥ በደንብ አዘጋጅታታለች ለማለት ይቻላል፡፡ (የሚገርመው ኮሪያ የዘመቱትና ከአሜሪካውያን ወታደሮች ጎን ተሰልፈው የተዋጉት ቃኘው ሻለቃ በአሜሪካውያን ካልሰለጠኑት ከክቡር ዘበኛ የተመለመሉ መሆናቸው ነው፡፡)

የአሜሪካ ድጋፍ በጦር ኃይሉ ብቻም ሳይሆን በአየር ትራንስፖርት በኩልም አለ፡፡ በ1938 ዓ.ም ከኢትዮጵያ ወደ አሜሪካ ያቀናው ልዑክ በኢትዮጵያ የአየር መንገድ ለማቋቋም የአሜሪካን እርዳታ ጠየቀ፡፡ በሚቀጥለው አመትም በኢትዮጵያ መንግስትና በትራንስኮንትኔታል ኤንድ ዌስተርን ኤር ላይን /T.W.A/ መካከል ስምምነት ተደርጎ የኢትዮጵያ አየር መንገድ በ1939 /1946 እ.ኤ.አ/ ተቋቋመ፡፡

ዋና ስራ አስኪያጆችና የቴክኒክ ተቆጣጣሪዎች አሜሪካውያን ሆነው ከቀጠሉ በኋላ፤ በ1964 ዓ.ም የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ስራ አስኪያጅ ተሾመ፡፡ ለየብስ መንገድም ቢሆን አሜሪካ ዋናውን ድርሻ



ትይዛለች፡፡ ቀደም ሲል በወረራው ጊዜ ተሰርተው የነበሩ መንገዶች በጦርነቱ ፈራርሰው ነበር፡፡አዳዲስ መንገዶችም በብዛት አልነበሩም፡፡ በ1943 ዓ.ም የአውራ ጎዳና ባለስልጣን ተቋቁሞ የኢትዮጵያን መንገዶች ለመጠገንና አዳዲስ መንገዶችን ለመገንባት እንቅስቃሴ ተጀመረ፡፡ የባለስልጣን መስሪያቤቱም የተቋቋመው በአሜሪካ ድጋፍና ትብብር ነው፡፡

የባለስልጣኑ መስሪያ ቤት በአሜሪካውያኑ የበላይነት ተቋቁሞ ስራውን ሲጀምርም ግንባታው እንደ አገራቸው አምሳያ /ኦፊስ ኦፍ ፐብሊክ ሮድስ/ ሆኖ ተነድፎ ነበር የቀጠለው፡፡በ1953 ዓ.ም የስራ አስኪያጅነቱን ስልጣን ኢትዮጵያውያኑ ቢረከቡም፤የመንገድ ስራ እንቅስቃሴዎች ይከናወኑ የነበሩት ግን በአሜሪካ ስር ከሚገኘው ከዓለም አቀፍ የመልሶ ግንባታና ልማት ባንክ /ኢንተርናሽናል ባንክ ኦፍ ሪኮንስትራክሽን ኤንድ ዴቬሎፐመንት/ በተገኘ ብድር ነበር፡፡ በዚህ ምክንያት ባንኩ በባለስልጣኑ ተግባራት ላይ ከፍተኛ የቁጥጥር ኃይል ነበረው፡፡

ቴሌን ለረጅም ጊዜ ይዘው የቆዩት ሲውዲኖች የነበሩ ቢሆንም፤ እንደገና በዘመናዊ መልክ ለማደራጀት የአሜሪካ እጅ ነበረበት፡፡ ከአፄ ምኒልክ ጀምሮም በየጊዜው እየተስፋፋ መሄዱ ይታወቃል፡፡

ከባንክ ጋር በተያያዘ እንግሊዞች ሰፊ ተሳትፎ ነበራቸው፡፡ በወረራው ጊዜ ቀደም ሲል ከነበረው ባንክ ውጪ ባንኮ ዲሮማና ባንኮ ዲናፖሊ የሚባሉ የኢጣሊያ ባንክ ቅርንጫፎች ተቋቁመው ነበር፡፡ ጣሊያኖች ከወጡ በኋላ በ1934 የተቋቋመው የኢትዮጵያ መንግስት ባንክ እንደ ንግድ ባንክም፣ እንደ ብሔራዊ ባንክም ሲያገለግል ከቆዬ በኋላ፤ በ1955 ዓ.ም ተግባራቸው በአዋጅ የተለየ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክና ብሐራዊ ባንክ ተቋቋሙ፡፡ ከዚያ በኋላም እየተስፋፋ ሄደ፡፡

በትምህርቱም እንግሊዝና ፈረንሣይ የማይናቅ ተሳትፎ.የነበራቸው መሆኑ እንዳለ ሆኖ፤ አሜሪካ የአንበሳውን ድርሻ ትይዛለች፡፡ በርካታ ኢትዮጵያውያን ለትምህርት የሚላኩት አሜሪካ ነበር፡፡ በጥቅሉ በአገር ግንባታው ዘርፍ ሰፊ አስተዋፅኦ ያበረከተችው አገር አሜሪካ ነበረች፡፡ ሂደቱ በዚህ ቀጥሎ በስተመጨረሻ ግን የንጉሡን አፍቃሬ ካፒታሊዝምነት እየተቃወሙ የመጡትና የኢትዮጵያን መንግስት ፊውዳል እያሉ የሚጠሩት ምሁራን /ተማሪዎች/ ይሄ የኢምፔሪያሊዝም ነፀብራቅ ነው እያሉ መንቀፍ ጀመሩ፡፡ የሚገርመው ልክ በዚያው ዘመን የሶሻሊስት ርዕዮት ይከተል የነበረውና ለአስዋን ግድብ ከሶቭየት እርዳታ ይጠይቅ የነበረው፣ ሲውዝ ካናልን ከእንግሊዝና ከፈረንሣይ ሊወርስ የተነሳው ጋማል አብደል ናስር ሞቶ አንዋር ሳዳት የግብፅ መሪ ሲሆን፤ ሶቭየትን ትቶ አሜሪካን ወዳጅ አደረገ፡፡ የቃኘው ጦር ሠፈር አስፈላጊነትም አከተመ፡፡ አሜሪካም የመካከለኛው ምስራቅ ስጋቷ ተወገደ፡፡ በዚያ ላይ ዘመን ተራቆ

በሳተላይት መረጃን መሰብሰብ ተችሎ ነበርና የስለላ እምብርቱ ዋጋ ቢስ ሆነ፡፡ ተማሪዎችም አሜሪካን፣ አሜሪካም ተማሪዎችን ተገላገሉ፡፡

አፄ ኃይለስላሴ ተደጋግሞ እንደተገለፀው ኢትዮጵያን ዘመናዊ አገር ለማድረግ የውጭ እርዳታ የግድ አስፈላጊ መሆኑን በማመን በዲፕሎማሲው መስክ ልዩ ጥረት አድርገዋል፡፡

ከአፍሪካ መሪዎችም ተወዳዳሪ ያልተገኘላቸው አገር ጎብኝ በመሆን /የዓለም አገራትን በመጎብኘት/ የአንደኝነቱን ስፍራ ይይዛሉ፡፡ ይህም ለመዝናናት ሳይሆን እርዳታ ፍለጋ ነው፡፡ ከግንቦት 1946 እስከ ታህሳስ 1947 ዓ.ም ድረስ ባሉት 8 ወራት ውስጥ ከፍተኛ ባለስልጣኖቻቸውን አስከትለው አሜሪካን፣ ካናዳን፣ ሜክሲኮን፣ ዩጎዝላቪያን፣ ግሪክን፣ ፈረንሣይን፣ ሆላንድን፣ ምዕራብ ጀርመንን፣ ሲውዲንን፣ ኖርዌይን፣ ዴንማርክን፣ ኦስትሪያን የጎበኙ ሲሆን፤ በህዳር 1949 ደግሞ ህንድንና ጃፓንን እንዲሁም ሌሎችን ጎብኝተዋል፡፡

ዋና አላማቸውም የኢኮኖሚና የቴክኒክ እርዳታ ለማግኘት ነበር፡፡ ለምሳሌ በህዳር 1949 ጃፓንን በጎበኙ ጊዜ በቶኪዮ ከተማ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ባደረጉት ንግግር "የአገራችንን የተፈጥሮ ሐብት በስራ ለማዋልና የህዝባችንን የኑሮ ደረጃ ከፍ ለማድረግ በያዝነው ተግባር አፈፃፀም የጃፓን ገንዘብና የቴክኒክ እውቀት ተካፋይ እንዲሆን በደስታ የምንቀበለው መሆኑን ለክቡርነትዎ ለማረጋገጥ እንፈልጋለን" ብለዋል፡፡በሌሎች አገራትም ተመሣሣይ ተማፅኖቻቸውን እንደቀጠሉ ግልፅ ነው፡፡ አገራቱም ኢትዮጵያን በማዘመን ረገድ የየድርሻቸውን ተወጥተዋል፡፡

እነዚህን የመሳሰሉ የስልጡን ባዕድ አገራት አስተዋፅኦ ስናይም እንዲሁ በችሮታና በርህራሄ ለኢትዮጵያ አዝነው እንዳደረጉት መወሰድ የለበትም፡፡ አገራቱ የየራሳቸውን ጥቅም፣ ክብርና ተወዳዳሪነትን በማሳየት ፖለቲካዊ ትርፍ ለመሸመትና በርዕዮትም በኩል ቀዳሚነትን ለማወጅ ሲሉ የሚራመዱበት መንገድ ነው፡፡

ሐሮልድ ማርክስ "The Politics of empire Ethiopia Great Britain and the United Sates 1941 - 1974" በሚል መፃህፋቸው፤ "ይህ አይነቱ ቀዳማዊ ኃይለስላሴ የወሰዱት ዲፕሎማሲያዊ እርምጃ በቀዝቃዛው ጦርነት ኢትዮጵያ ወደ ምስራቁ ርዕዮት ልታዘነብል ትችላለች የሚል ፍርሃት አሜሪካን ክፉኛ አንቀጥቅጧት ነበር" በማለት ገልፀውታል፡፡ ስለዚህም "አሜሪካ የኢትዮጵያን ጉዳይ ከልቧ እንድታስብበትና ሙሉ ትኩረት ለኢትዮጵያ ፀጥታ እንድትሰራ የሚጋብዝ ነበር" ሲሉ ያክሉበታል፡፡



## ጃንሆይና ትምህርት

ጃንሆይና ትምህርት አብረው የተወለዱ እስኪመስል ድረስ አስገራሚ ፍቅር ነበራቸው፡፡ጃንሆይን ለመተቸት ብዕራቸውን የሚቀስሩ ምሁራን ጃንሆይ ያስተማሯቸው ናቸው፡፡በራሳቸው ገንዘብ ከፍለው ባያስተምሯቸውም፤ዜጎች በአገራቸው ላይ የመማር መብት ቢኖራቸውም፣ መንግስት ትምህርትን የማስፋፋት ግዴታ ቢኖርበትም፣ብዙ ብዙ ነገር ቢባልም፤የዛሬ አገር መሪዎችን በጊዜ እንዲሰለጥኑ አድርገዋልና ቢያንስ በትምህርቱ ዘርፍ በእጅጉ ሊመሰገኑበት የሚገባ ስራ ሰርተዋል፡፡

የትምህርት ፖሊሲው ልክ አልነበረም፣ የምዕራባውያን ምንትስ ነው፣ የመኳንንቱ ልጆች ናቸው የሚማሩበት፣ ትምህርቱ የመንግስት ሃብት ነው፣ የቅበላ አቅሙ አነስተኛ ነው… ወዘተ… እየተባለ ይወራል፡፡ ይሄን ሁሉ ወሬ ለማውራት የሚያስችል እውቀት፣ ስድብን ወደ ወረቀት ገልብጦ መፃፍ የሚያስችል ግንዛቤ፣ መፈክር ካርቶን ላይ በቀለም መፃፍን ሳይቀር ያለማመደ ዘመን ግን የጃንሆይ ዘመን ነው፡፡

ስለዚህ አንዱን መንግስት አግንኖ ሌላውን መንግስት ለማጣጣል ሲባል የሚካሄድ የትችት ዘመቻ፤ ምንም እንኳ "ጨቋኝ" የሚባል ስርዓት ነበረው ቢባልም፣ በመልካም መታወስ የሚችልበትን ታሪክ አብሮ ማንቋሸሽ ተገቢ አይሆንም፡፡ የውጭ አገር ጠላት ይመስል ይህንን ስራቸውን ሳይቀር ሊያዳፍኑ የሚሞክሩ ጥቂት አይደሉም፡፡ ይሄ አካሄድ የቀጣዩን መንግስት መነሳሳት ሊያዳክመው ይችላል፡፡ የምናወራው ስለ ኢትዮጵያ ነው፡፡ እናም ስለ ጃንሆይ የትምህርት አጀማመርና የሚደነቅ የማስፋፋት ስራቸው፡፡

አንድ የነበረችውን የምኒልክ ትምህርት ቤት እሱዋም በፈረንሳይኛና በእንግሊዝኛ ቋንቋ የተወሰነ ትምህርት የሚሰጥባትን ተቋም ከአልጋ ወራሽነት ዘመናቸው ጀምሮ በጥረታቸው በእርዳታም ይሁን በብድር በአገሪቱ ሃብትም ይሁን በምን መልካም ፈቃዳቸው ሆኖ አስፋፍተው ብዙ ምሁራንን ለኢትዮጵያ አስረክበዋል፡፡የጃንሆይ በትምህርት ማመን ቀደም ብሎ የታወቀ ነው፡፡ የንግስና መንገዳቸውን ይጠርጉ በነበረበት ጊዜ የወደፊቷ ኢትዮጵያ በምሁራን አሰራር ትገነባ ዘንድ ዘር ሳይመርጡ ብዙዎችን ወደሰለጠነው ዓለም ለትምህርት ልከዋል፡፡ አፄ ምኒልክ በጣሉት መሠረት ላይ ተንጠላጥለው ጃንሆይ ከአልጋወራሽነት ዘመናቸው ጀምሮ ልዩ ትኩረት የሰጡት ጉዳይ ነው፤ ምሁራንን ማብዛት፡፡

ከኢጣሊያ ወረራ በፊት 250 ምሁራን ውጭ አገር ተምረው መጥተው የመንግስት ባለሥልጣን ሆነው ይሰሩ ነበር፡፡ በወረራው ዘመን የኢጣሊያ ባለስልጣኖች ምሁራኑን እያደኑ ገደሏቸው፡፡ በዚህም ከፊሉ አለቁ፡፡ የተረፉት ከነፃነት በኋላ አገራቸውን እንዲያገለግሉ ተደረገ፡፡

ከጦርነቱ በኋላ ባሉት ተከታታይ 10 ዓመታት ምሁራንን የማበርከቱ ስራ ቀጥሎ ጃንሆይ ብዙዎችን ወደ ውጭ አገር ልከዋል፡፡በ1934 ዓ.ም የትምህርት ሚኒስቴር ተቋቁሞ የትምህርት ሚኒስትርነት ስልጣኑን ንጉሱ ራሳቸው ደርበው ይዘው እስከ 1958 ዓ.ም ድረስ ቆይተዋል፡፡ ይጠነቀቁለትም ነበር፡፡



ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ተማሪዎችን ሲጎበኙ

ከዚያ ጊዜ ጀምሮ 2ሺ ከ1ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ትምህርት የሚሰጥባቸው ትምህርት ቤቶች፣ 14 ዩኒቨርሲቲና ኮሌጆች፣ እንዲሁም 4 ለዩኒቨርሲቲ ዝግጅት የሚያበቁ የተሻለ ውጤት ያመጡ ተማሪዎች የሚማሩባቸው ከፍተኛ ትምህርት ቤቶችን አቋቁመዋል፡፡ በ1960ዎቹ የመጀመሪያ አመታት አጠቃላይ የተማሪው ብዛት 700,000 ደርሶ ነበር፡፡

ለትምህርት ቤቶች መስሪያነት የንጉሱ የግል ርስቶች ነበሩ የሚውሉት፡፡ በየትምህርት ቤቱ እየዞሩ፣ ድንገት እየደረሱ የትምህርት አሰጣጡን ይፈትሻሉ፡፡ ጥሩ ውጤት ላመጡ ተማሪዎች (ከ1 እስከ 3 ለወጡ) በየአመቱ ሽልማት ይሰጣሉ፡፡ የገና በዓልን ዘወትር የሚያከብሩት ከሁሉም የአዲስ አበባ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች ጋር ሆነው በልደት አዳራሽ ነው፡፡ ልዩ ልዩ ስጦታዎችን እየሰጡም ያበረታታሉ፡፡ለከፍተኛ ትምህርት ወደ ውጭ አገር የሚሄዱትንም ሆነ ተምረው የሚመለሱትን አሸኛኘትና አቀባበላቸው የተለየና ዛሬ ለአንድ ዲፕሎማት እንደሚደረገው መሽቆጥቆጥ ያህል ነበር፡፡ መቋቋሚያ ከመስጠት ጀምሮ ወጪያቸው ይሸፈናል፡፡

ጃንሆይ ቤተ-መንግስታቸውን ለትምህርት ቤትነት የሰጡ፣ትምህርትን የሚያከብሩ ንጉሰ ነገስት ናቸው፡፡ጥቂቶችን ለመጠቃቀስ ያህል የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ በ1943 ዓ.ም ከመከፈቱ በፊትና በኋላ በድህረ ነፃነት የኮተቤ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ የጄኔራል ዊንጌት 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የአዳሪ ትምህርት ቤቶች



ሆነው ተቋቁመዋል፡፡ የኮተቤው በ1935 ተቋቁሞ የምግብ ማብሰያ ቤት እስኪሰራለት ድረስ የተማሪዎች ምግብ ከቤተመንግስት ነበር የሚሄደው፡፡ የ1938ቱ ዊንጌት ደግሞ በትምህርት ሚኒስትርና በብሪቲሽ ካውንስል ተራድኦ ትብብር የተገነባ እንጂ እንግሊዞች ሰርተው ያበረከቱት አይደለም፡፡ የትምህርት ስርዓቱ የእንግሊዝን ስርዓት የተከተለ ሲሆን፤ ኢትዮጵያዊ ምሁራን እንዳሉ ሆነው የበላይ ዳይሬክተሮቹ ካናዳውያን ነበሩ፡፡

የአርትና የሳይንስ ፋክልቲዎችን ያቀፈው ዋናው የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ከተቋቋመ በኋላ በነበሩት ተከታታይ 5 አመታትም በአዲስ አበባ "የመሐንዲስ ኮሌጅና የህንፃ ኮሌጅ" በአለማያ "የእርሻ ኮሌጅ"፣ በጐንደር "የጤና ጥበቃ ኮሌጅ"... ተከፈቱ፡፡ በ1953 ዓ.ም እነዚህን የተለያዩ ኮሌጆችና ፋክልቲዎች ጠቅልሎ እንዲያስተዳድር የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (በድሮ አጠራሩ የቀዳማዊ ሃይለስላሴ ዩኒቨርሲቲ) ተመሰረተ፡፡ ከዩኒቨርሲቲው ምስረታ በኋላ የህግ፣ የህክምና፣ የንግድ፣ የአስተዳደር... ወዘተ ዲፓርትመንቶች ተከፈቱ፡፡በ1942 ሰባ አንድ የነበረው የተማሪ ቁጥር (በኮሌጅ ደረጃ) እየቀጠለ ሄዶ በ1965 ዓ.ም የማታ ተማሪዎችን ጨምሮ 10ሺ ደረሰ፡፡

ለድህረ ምረቃ ትምህርት ግን ወደ ውጭ አገር በተለይ ወደ አሜሪካ መሄድ የግድ ነበር፡፡ በ1962 ዓ.ም በአሜሪካ የድህረ ምረቃ ትምህርት የሚከታተሉ ኢትዮጵያውያን ቁጥር 700 የሚደርስ ነበር፡፡

በቅኝ አገዛዝ ይማቅቁ ለነበሩት አፍሪካውያንም ኢትዮጵያ ነፃ የትምህርት እድል መስጠት የጀመረችው በጃንሆይ ጊዜ ነው፡፡ ኢትዮጵያን ዘመናዊ አገር ለማድረግ ለጀመሩት ፕሮግራም ጃንሆይ ትምህርት ወሳኝ ግብአት መሆኑን ስላመኑበት ለዘርፉ ልዩ ትኩረት መስጠታቸው ግልፅ ነው፡፡ ሆኖም በከፊል ምሁራን የሚደነቅ ተብሎ ሲገለፅ፤ በተቃራኒውም የትምህርቱን ስርዓት ከፉኛ የሚተቹት ምሁራን ቀላል ቁጥር የላቸውም፡፡ምንም እንኳ ኢትዮጵያውያን ተማሪዎች የአስተሳሰብ አድማሳቸው እየሰፋ በሄደ ቁጥር የጃንሆይን አገዛዝ ፊውዳላዊነት የተላበሰ መሆኑን ወደመረዳት እያመሩ ለአመፅ ቢነሳሱም ጃንሆይ ይህ ይሆናል ብለው አስበው አያውቁም ነበር፡፡ ይህን ጉዳይ በተመለከተ፡-

ዶ/ር ፍቅሬ ቶሎሣ "Alienation፡ A Result of The impact of western education of Ethiopian intellectuals" በሚል ርዕስ ባቀረቡት ፅሁፍ "አፄ ምኒልክና ቀዳማዊ ኃይለስላሴ የምዕራባውያንን ትምህርት ሲያስተዋውቁ የኢትዮጵያ ልጆችን ከመሰረታቸው እንደሚነጥላቸው አላጤኑትም ነበር" በማለት ይገልፃሉ፡፡ የጃንሆይን የትምህርት ስርዓት የሚተቹ ምሁራን የትችታቸው መንስኤ ምን እንደሆነ ስናይም የብዙዎቹ የምዕራባውያን የእጅ አዙር ቅኝ ነበር ወደማለት ያዘነብላሉ፡፡

ፕ/ር መሣይ ከበደ "The Roots and Fallouts of Hilesilassie's Educational Policy" በተሰኘ ጥናታዊ ፅሁፋቸው ይሄንኑ የጃንሆይን ዘመን የትምህርት ጉዳይ ሲገልፁት "በወታደራዊ መንገድ ተሞክሮ ሣይሳካ የቀረው የቅኝ ግዛት ሙከራ በምዕራባውያን ትምህርት ምክንያት ውጤታማ ሆነ" ብለው ይገነትሉታል፡፡

በዚያ ዘመኑ የኢትዮጵያ ትምህርት ዙሪያ መጠነኛ ጥናት ያደረጉት የእየሩሳሌም ዩኒቨርሲቲው ምሁር ሞርደካይ አብርሃም "Education and natural Unity in Ethiopia" በተሰኘ ፅሁፋቸው "ጃንሆይ ለትምህርት የሰጡት ልዩ ትኩረትና ጥብቅ ክትትል እንዲሁም እስከ ዩኒቨርሲቲ ድረስ በነፃ ያውም የኪስ ገንዘብ ጭምር እየታከለበት የተተገበረውን ትምህርት አጥብቀው በማይመረምሩ ሰዎች ዘንድ ብቻ የሚያስደንቅ፣ ነገር ግን ትኩረት ያልተሰጠው ጉዳይ ነበር" ይሉታል፡፡ እንደሞርደካይ አተያይ "በጃንሆይ ዘመን የነበረው የትምህርት ሁኔታ ከሌሎች የአፍሪካ አገሮች ጋር እንኳ ሲነፃፀር አነስተኛ መጠን ያለው በጀት የተበጀተለት፣ ለትምህርት የሚያስፈልጉ ግብዓቶች በአግባቡ ያልተሟሉለትና፣ ተደራሽነቱም በሁሉም የአገሪቱ ክልሎች ያልተመጣጠነ ነበር፡፡ መምህራኑም በችግር ውስጥ የሚኖሩና ለማስተማር እንዲነሳሱ የሚያደርግ በቂ ጥቅማጥቅም የማያገኙ፣ የሞራል ድጋፍ ያልተሰጣቸው ነበሩ" የሚል ነው፡፡ ምሁሩ ጅምር መሆኑን የዘነጉት ይመስላል፡፡ በተጨማሪም ዛሬስ? ብሎ መጠየቅ ተገቢ ይሆናል፡፡

በወቅቱ ግን ጃንሆይ ሌላ ምን ምርጫ ነበራቸው? የትምህርት ስርዓቱ የምዕራባውያን ከሚሆን ይልቅ ከነአካቴው መቅረት ነበረበት? ወይስ የምስራቃውያን የትምህርት ስርዓት ተመራጭ ነበር? የትምህርት ስርዓቱ ወደ ምስራቁ ሆኖ ቢሆንስ ጃንሆይን ሳያስተች ይቀር ነበር? በዚያ ወቅት ኢትዮጵያ የራሷ የትምህርት ስርዓት አልነበራትምና የራሷ ይሻላት ነበር አይባል ነገር፡፡ ጅምር መሆኑስ እንዴት ይዘነጋል? ጃንሆይስ "ዜጎቼ በትምህርት ሰልጥነው ንጉሣዊ አገዛዜን ሊቃወሙት ይችላሉና መሐይም ሆነው መቅረት አለባቸው" ብለው ማሠብ ነበረባቸው? ለመሆኑስ ኢትዮጵያ ዛሬ ድረስ የራሷ የሆነ የትምህርት ስርዓት አላት? የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ካሪኩለም ተቀርፆ ያለውም ሆነ እየተቀረፀ ያለው በማን ነው? የሚሉ ጥያቄዎችን ስናነሳ የእነ ሞርዶካይ አይነቱ "አጥብቆ የመመርመሩ" ጉዳይ የተለየ ድምዳሜ ላይ ሊያደርሰን እንደማይችል እንረዳለን፡፡

የጃንሆይ የትምህርት ስርዓት የተሟሟተ ከነበረ፣ የዚያ ዘመን ስህተት እንዳይደገም መጠንቀቅ ይሻላል? ወይስ ያን ወቅት በመርገም ብቻ ይቀጠል? በሚለው ላይ ማተኩሩ የተሻለ ነው፡፡ ለማንኛውም ጃንሆይ በትምህርቱ ዘርፍ ያከናወኑት ተግባር ተተችቶ የሚቀር ብቻ ሳይሆን፣



ይበል የሚያሰኝ ጅምር መሆኑን በማየት ብቻ ሊመሰገን የሚገባው ነው፡፡ እንዳለመታደል ይህም ዘርፍ ለውድቀታቸው አንዱ ግብዓት ነበር፡፡

**ጃንሆይ እና ጤና**

በጃንሆይ ጊዜ በጤናው ረገድ "ጥሩ" የሚሰኝ ስራ ተሰርቷል፡፡ በኢትዮጵያ ታሪክ ዘመናዊ ሃኪም አንድ ፍሬ የነበረውና በሸዋ ነገስታት ዘመን ጊዜ ቀደም ሲል ያየነው ፖርቹጋላዊ (ሠላይና) ሃኪም ሁለት ያህል ነገስታትን አክሞ ነበር፡፡

ከ400 አመታት በኋላ በምኒልክ ጊዜ የአድዋ ዘማች ቁስለኞችን የፈረንሳይና የሩሲያ በጎ አድራጊ የህክምና ባለሙያዎች በዘመናዊ መንገድ ህክምና ያደርጉላቸው ነበር፡፡ በተረፈ ንጉሡን ከሚያክሙ ግለሰብ ሃኪሞች ውጪ ምንም የለም፡፡ የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ሃኪም ወርቅነህ እሸቴና ኢትዮጵያ ብቻቸውን ነበሩ፡፡ በምኒልክ ጊዜ ከአንዲት ሆስፒታል ጋር፡፡ አንዳንዶች ጣሊያን ብዙ ሆስፒታሎች እንደገነባ አድርገው ይፅፋሉ፡፡ ይሄ ፍፁም ሃሰት ነው፡፡ በ1901 ዓ.ም በቀበና ወንዝ አካባቢ የሩሲያ ቀይ መስቀል ሆስፒታል መገንባቱ እንዳለ ሆኖ ሌላው የጃንሆይ ዘመን ውጤት ሲሆን፤ ጣሊያን በ5 አመት ቆይታው ለራሱ ሠራዊት የህክምና አገልግሎት የሚጠቀምበት አንድ ሆስፒታል ሰርቷል፡፡ በተረፈ በተንቀሳቃሽ የህክምና አገልግሎት ነበር የራሱን ሠራዊት የሚንከባከበው፡፡

የሚገርመው ግን ከኢትዮጵያ ምሁራን ውስጥ ጥቂቶች "ጣሊያን 14 ሆስፒታል ገንብቷል" ብለው መፃፋቸው ነው፡፡ 14 ሆስፒታል እስከ ነፃነት ዘመን ማለትም እስከ 1933 ድረስ አልነበረም፡፡ እንዲያውም መንግስት ዘግይቶ ነበር ትኩረት የሰጠው፡፡ ከወረራው በፊት በአገሪቱ ውስጥ 10 ሆስፒታሎች፣ አንድ የስጋደዌ ሆስፒታል፣ አንድ ክሊኒክ፣ አንድ የህክምና ላብራቶሪ ብቻ ይገኙ ነበር፡፡

ከነፃነት በኋላ የተሰሩትን እናዘግያቸውና የኢጣሊያን መሠሪነት እናስቀድም፡፡ ፕሮፌሰር ሪቻርድ ፓንክረስት "The Beginning of modem medicine in Ethiopia" በተሰኘ ጥናታቸው ከላይ የሰፈሩ እውነታዎችን ያረጋግጣሉ፡፡

ጣሊያን ኢትዮጵያን መውረርና መዝረፍ ሳያንሰው ታሪክንም ዘርፎ ሊሄድ ሞክሯል፡፡ በኢትዮጵያ መንግስት ከወረራ በፊት የተሰሩት ስራዎችን ስም እየለወጠ የራሱን ቋንቋ መጠሪያ እያላበሰ ነው የኖረው፡፡ ለምሳሌ በኢትዮጵያ የመጀመሪያው ሆስፒታል የሆነውን የዳግማዊ ምኒልክ ሆስፒታልን የቀበናውን ማለት ነው "ዲሊ አከሙዚ ኮሌኒያል ሆስፒታል" ብሎ ሠይሟል፡፡ የቀድሞውን ቤተሣይዳ ሆስፒታልን የቪክቶር አማኑኤል ሆስፒታል ብሎ ሠይሟል፣ ራስ ደስታ ሆስፒታልን "ፕሪንቺ ፒላ ዲ.ፒ ሞንት ሆስፒታል"... እያለ ሠይሟል፡፡ ከፊሉ ተሣክቶለታል፡፡ በተቋም ደረጃ በአዲስ አበባ፣ በሃረር፣ በጅጅጋ፣ በነቀምትና በደሴ አንዳንድ

ሆስፒታሎች ተገንብተው አገልግሎት ይሰጡ ነበር፡፡ ጣሊያን ኢትዮጵያን ሲወር በደብረማርቆስ አንድ ሆስፒታል እየተገነባ ነበር፡፡ በተረፈ ይሄ የንጉሡን ስራ ለማኮሰስ እየተባለ የሚደሰኮረው ሁሉ ከእውነት የራቀ ነው፡፡ ቀለም መቀባትና መስራት ይለያያል፡፡

ባጠቃላይ ሌሎች የኢጣሊያ ጅምሮች መኖራቸውን ሳንዘነጋ፤ በጤናው ዘርፍ ጣሊያን አንድም ስራ አልሰራም፡፡ ጣሊያን የኢትዮጵያ ህዝብ እንዲያልቅ የበሽታ ፋብሪካ ቢያቋቁም ይመርጥ ነበር፡፡ ለማንኛውም ከወረራው በፊት የነበረው ጅምር ከነፃነት በኋላ በ1934 በጤና ዘርፍ ብቻ የሚያተኩር ተቋም ሆኖ፤ ነገር ግን በአገር ግዛት ሚኒስቴር ስር የሚተዳደር "የህዝብ ጤና ጥበቃ ደሬክሲዮን" ተቋቋመና ቀደም ሲል የተጀመሩ ስራዎችን እንዲቀጥል ሆነ፡፡
እየቆየ የታካሚው ቁጥር ማለትም ከባህላዊው ወደ ዘመናዊው የህክምና ተቋም የሚጎርፈው ሰው ስለበዛ፣በ1939 የጤና ጥበቃ ሚኒስቴርን ለማቋቋም የሚያስችል ረቂቅ ህግ ተዘጋጅቶ በ1940 ሚኒስትር መስሪያ ቤቱ በአዋጅ ተመሰረተ፡፡

ከዚያ ጊዜ ጀምሮ በሁሉም ግዛቶች የጤና አገልግሎት ሽፋኑን ሙሉ ለሙሉም ባይሆን በተቻለ መጠን ለማዳረስ ተሞክሯል፡፡ኢትዮጵያ የአለም የጤና ጥበቃ ድርጅት አባል የሆነችውም ከዚያ በኋላ ነበር፡፡እስከ 1966 ዓ.ም ድረስ ከወረራው በፊት 10 የነበሩ ሆስፒታሎች በአጭር ጊዜ ውስጥ 66 ሆስፒታል፣ 679 ክሊኒኮች፣93 ጤና ጣቢያዎች ሊቋቋሙ ችለዋል፡፡የጤና ጥበቃ ሚኒስትር ከ1950 እስከ 1966 ድረስ በነበሩት አመታት ብቻ 9,167 የሆስፒታል አልጋዎች እንዲኖር አድርጓል፡፡

የሐኪሞች ቁጥር 375፣ የነርሶች ቁጥር 934፣ ጤና መኮንኖች 376፣ ነርሶች 286፣ እንዲሁም 270 የጤና ተቆጣጣሪዎች እንደነበሩ የአሁኑም የድሮውም ሚኒስቴር መስሪያቤቶች መረጃ በግልፅ ያሳያል፡፡

እንግዲህ እስካሁን በተናጠል ባጭር ባጭሩ ያየናቸው ፍንጮች ከነፃነት በፊትና በኋላ ተጀምረው እስከ አብዮቱ ዋዜማ በሂደት እያደጉ የደረሱበትን ሁኔታ ነው፡፡ የቀረውን ከራሳቸው ከጃንሆይ እንስማ፡፡

### የጃንሆይ ልማታዊ ንግግር

ይህ ሐተታ ጃንሆይ ስልጣን በያዙ በ30ኛ ዓመታቸው ያደረጉት ንግግር ነው፡፡ የጃንሆይ ልማታዊ ንግግር ብየ የሰየምኩትም በመግቢያው ዘርዘር ያሉ ልማታዊ ትንታኔዎች ስላሉበት ነው እንጂ ርዕሱ "ግርማዊ ንጉሠ ነገስት ቀዳማዊ ኃይለስላሴ ሚያዚያ 6 ቀን 1953 ዓ.ም በገነተ ልዑል ቤተመንግስት ለክቡራን ሚኒስትሮችና ለመንግስት ባለስልጣኖች ያደረጉት ንግግር" የሚል ነው፡፡ በተለይ ለወደፊት እንግዳ አንባብያን የጃንሆይን ንግግር እንደወረደ ማንበብ ጥቅም ይኖረዋል፡፡ የዚያን ወቅት አጠቃላይ ሁኔታንም ያስቃኛል፡፡ በደንብ እንድንስላቸው የሚያግዝም



ነው፡፡ እናም ከጉዳያችን ጋር ተያያዥነት ያለውን እየመረጥኩ አጭሯን "ፓምፍሌት" አሳጥሬ አቀርባለሁ፡፡ በዚህም የጃንሆይን የመናገር መብት ከመጣስ እንቆጠባለን፡፡ በተጨማሪም ሳናውቀው የመጣነው ነገር ካለ በማሳወቅ ያግዙናል፡፡ በመረጃ ሰነድነትም ያገለግሉናል፡፡ ይቀጥሉ ጃንሆይ....

"ከዛሬ ሠላሳ አመት በፊት በእግዚአብሔር ፈቃድ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገስትነትን በመቀባት ዘውድ ጭነን የተወደደችው አገራችን ባህሏንና ልማዷን እያዋሃደች በዘመናዊው የስልጣኔ ጎዳና እንድትራመድ ለመምራት የተመረጥንበትን ተግባር ስንጀምር ኢትዮጵያ እምን ደረጃ እንደነበረች ታውቁታላችሁ፡፡"

ከዚህ ከፊታችን የተሰባሰባችሁ የመንግስታችን ሚንስትሮችና ባለስልጣኖች እስኪ በዚያን ዘመን የነበረውን ወደ ኋላ መለስ ብሎ በህሊና ሲመለከቱት የነበረውን ልታስታውሱት ትችላላችሁ፡፡

ኢትዮጵያ ስልጣኔዋ ተረስቶ ለቅኝ ግዛት የሚወዳደሩባትና ለዚሁ እንድትሆን በምትመራበት ጐዳና ገብታ ወራዳነት ሊያደርስባት በሚችል በልማድ ሽባነት የምትተዳደር፣ ከሌላው ዓለም በብዙ አኳኋን ተለይታ የምትኖር፣ በጅምር ያለ እንጂ ያልተሟላ፣ በቃል ታሪክ እንጂ በፅሁፍ የተመሰረተ የመንግስት አስተዳደር የሌላት በፊውዳል የምትገዛ፣ ንጉሡና ሹማምንቱ እንዳፈተታቸው የሚያዙበት፣ የታወቀ ቋሚ የውጭ አገር ንግድ የሌላት አገር አልነበረችምን? በዚያን ጊዜ የነበረውን ሁኔታ ከዛሬው ጋር በማመዛዘን ይህ ሁሉ መለዋወጥ እንዴት እንደተደረገ ያለፈውን ጊዜ ስራ በፅሁፍ የሚገኘውን ሁሉ እያያችሁ ስትመረምሩት ስራው ምስክርነቱን ይሰጣል፡፡

ይህ መለዋወጥ ያስከተላቸው ችግሮች ወይም ቁልፍልፍ ስራዎች ምንድን ናቸው? በዛሬው በ1953 ዓ.ም የሚኖሩብንን ችግሮች በምን አኳኋን ምን እርምጃ በመውሰድ ልንወጣቸውና ልናስወግዳቸው እንችላለን?

ለአንድ አገር የሚደረገው የመሻሻል እርምጃ ያገሩን መላ ህይወት የሚመለከተው ክፍል ሁሉ ተባብሮ በአንድነት እንዲከናወን ማድረግ የሚያስፈልግ ነው፡፡ አንድ አገር የኢኮኖሚክ መሻሻል በሚያደርግበት ጊዜ እንደዚሁም የተሻሻለ የማኅበራዊ ኑሮና የፖለቲካም ድርጅት እንዲፈጠር ተመሳሳይ የሆነ መሻሻል ማድረግ አለበት፡፡ በአንደኛው ክፍል ያለውን እርምጃ ወደ ኋላ ለማስቀረት የሚደረገው ሙከራ ሁሉ መላውን የመሻሻል እርምጃ ወደኋላ መጎተቱ የማይቀርና በጠቅላላውም የአገሪቱን መሠረታዊ ድርጀት ከትክክለኝነት መስመሩ የሚያቃውስ ነገር የሚፈጥር ይሆናል፡፡

እኛም በእግዚአብሔር አሠሪነት ተስፋ ሳንቆርጥ ስልጣኔ የሚስፋፋበትን፣ እውቀት የሚገኝበትን፣ ተማሪ ቤት ከነተማሪው በማብዛት

ድንቁርና የሚወገድበትን፣ በስራ ለማሸነፍ ትግል ከጀመርንበት ጊዜ አንስቶ ይህንን መሠረታዊ ሃሳብ በመረዳት የምንፈፅመው ተግባራችን ሁሉ የተመራው በዚሁ መሠረት ነው፡፡ ያገራችን ሙሉ ግዛቷ የሚያድግበት መሠረቱን ገንብተናል፡፡

ኢትዮጵያ በስልጣኔ ከአለም ተለይታ ይህን ያህል ዘመን የኖረች ሆና በተገኘችበት መጠን ነፃነቷን ጠብቃ እንድትኖር በዙሪያዋ የነበረባትን ትግል ችለን፤ በውስጥ ደግሞ ለዘመኑ አስተዳደር መሣሪያ የሚሆኗትን ሰዎች በትምህርት እያነፅን በማዘጋጀትና በስራም እየተቀረፁ እንዲወጡ ማድረግ የደከምንበት አይነተኛ ተግባር ነው፡፡ ሙሉ ህይወታችንን መስዋዕት ያደረግንለትን ይህን ተግባር ስንፈፅም ከጥንቱ ባህል ጋር ተቀራኝተው መኖርን የሚፈቅዱ ወገኖች ጋር ይህንኑ የሚያህል ተጨማሪ ትግል እንደነበረብን የሚሳት አይደለም፡፡

ይህ ከውስጥና ከውጭ የነበረብን ትግል ህይወታችንን እረፍት ለሌለው ስራ መስዋዕት ማድረግ እንዳስገደደን ከማንም ይልቅ ከድካማችን የተገኘውን የስራ ፍሬ የተጠቀመበት ህዝባችን ሊረዳ እንደሚገባ ማሳሰብ የሚያስፈልግ መስሎ አይታየንም፡፡

አንድ መለዋወጥ ሌላ መለዋወጥ እንደሚያስከትልና የሚደረገውም አንድ የወደፊት እርምጃ ሌላ እርምጃ ማስከተሉ እንደማይቀር የታወቀ ነገር ነው፡፡ የታሪክና የስራ ማዕበል አንድ ጊዜ ከተጀመረ የማይወሰንና የማይገታ ሲሆን "እስከዚህ ድረስ እንጂ ከዚህ አልፌ ለመሄድ አይቻለኝም" የሚል ቢኖር በእውነቱ እንደ አላዋቂ ራሱን የሚያታልል ሆኖ የሚቆጠር ነው፡፡ ይህንንም መሠረታዊ ሃሳብ ሁልጊዜም ተገንዝበን ሰርተንበታል፡፡

እንግዲህ ኢትዮጵያ ከ1909 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 1953 ዓ.ም ድረስ ያለውን ረጅም ጎዳና እንደምን አድርጋ ነው የተጓዘችው?

"…. በቀድሞ ጊዜ ትምህርት የሚሰጠው በመንፈሣዊ መሪዎቹ ባለስልጣኖች ነበር፡፡ የትምህርት አሰጣጡ ደረጃ መጠን ከማንበብና ከመፃፍ አያልፍም ነበር፡፡ ነገር ግን የንጉሠ ነገስት መንግስታችን ትምህርት አጥብቆ የሚያስብበት ዋና ተግባር ሆነ፡፡ የዘመናዊ ትምህርት መስፋፋት እየተፋጠነ ሄዶ ፍሬ መስጠት ሲጀምር ኢጣሊያኖች አገሪቷን ወረርዋት፡፡ አገሪቱ በኢጣሊያኖች አገዛዝ ስር በቆየችበት ጊዜ ውስጥ የተማሩትን ኢትዮጵያውያንን አንድ በአንድ እየፈለጉ ከመፍጀታቸውም በላይ በዚያን ጊዜ የነበሩትን ወጣቶች ትምህርትን ተነፍገዋል፡፡ ኢትዮጵያ እንደገና ነፃነቷን ከተቀዳጀች በኋላ የትምህርትና የስነ ጥበብ ሚኒስቴር እንደገና ተቋቁሞ የሚንስትርነቱን ስልጣን በእጃችን ማቆየት አስፈላጊ ሆኖ ተሰምቶናል፡፡

ኢትዮጵያ ነፃነትዋን ከአስመለሰች ወዲህ ትምህርት እጅግ እየተስፋፋ ሄደ፡፡ ከ1951 እስከ 52 የትምህርት አመት በጠቅላላው 213ሺ



703 ተማሪዎች የሚማሩባቸው 893 የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ነበሩ፡፡ ከዚህ በቀር ዛሬ 6ሺ 701 ተማሪዎች የሚገኙባቸው 45 የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ሲኖሩ፤ ደግሞ 29 የሁለተኛ ደረጃ የእጅ ስራና የልዩ ልዩ ሞያ ትምህርት ቤቶች አሉ፡፡ እነሱም 3ሺ 646 ተማሪዎች ይገኙባቸዋል፡፡ ከእነዚህም ትምህርት ቤቶች በቀር የልዩ ልዩ የትምህርት ቅርንጫፎች ዲግሪ ለመስጠት የሚችሉ አምስት ኮሌጅ ትምህርት ቤቶች አሉ፡፡ በትምህርት ረገድ የተደረገው እርምጃ እጅግ የሚደነቅ እንደመሆኑ መጠን የትምህርት በጀት በጣም ከፍ ካሉት ክፍል አንዱ ነው፡፡ ለምሳሌ ያህል ባለፈው የበጀት ጊዜ የትምህርት በጀት 19 ሚሊዬን የኢትዮጵያ ብር የነበረ ሲሆን፤ ዛሬ (በ1952 ማለታቸው ነው) በመጀመሪያዎቹ ዘጠኝ ወሮች የትምህርት ሚኒስቴር ወጪ 26 ሚሊዮን የኢትዮጵያ ብር ደርሶ እንደነበረ ይታወሳል፡፡

"እንዲሁም በህዝብ ጤና ጥበቃና በመገናኛዎቹ ረገድ የተደረጉት እርምጃዎች በቀላሉ የሚገመቱ አይደሉም፡፡… የጤና ጥበቃ አገልግሎት ምንም እንኳ ቀደም ብሎ የተጀመረ ቢሆንም ከ1923 ዓ.ም በፊት በመንግስት የስራ አመራር ውስጥ እምብዛም ግምት ያልተሰጠው ነበር፡፡ ከዚያ ወዲህ በንጉሠ ነገስት መንግስታችን ብርታትና ጥረት በ1927 ዓም በአገሪቱ ውስጥ 10 ሆስፒታሎች አንድ የስጋደዌ /በዚህ ፅሁፍ ነው ስጋደዌ የተባለው/ ሆስፒታል፣ አንድ ክሊኒክና አንድ የህክምና ላብራቶሪ ተቋቁመው ይገኙ ነበር፡፡ ዳሩ ግን በዚህ ረገድ የተጀመረው ተግባር በጠላት ወረራ ምክንያት ለጊዜው እንዲቋረጥ ተገደደ፡፡ የኢትዮጵያ ህዝብ ነፃነት ከተመለሰ በኋላ ይኸው ተግባር በሰፊው እንደገና ቀጠለ፡፡"

ሆስፒታሎችና ክሊኒኮች በየአውራጃዎቹ ሁሉ ማቋቋም አስፈላጊ ሆነ፤ እዚህ ላይ ኢትዮጵያዊ ሐኪሞችን፣ ነርሶችንና አስታማሚዎችን፣ ሌሎች የህክምና ሠራተኞችን የማሰልጠን ተግባር ቅድሚያ ተሰጠው፡፡

ዛሬ 66 ሆስፒታሎች፣ 471 ክሊኒኮች፣ 37 የህዝብ ጤና ጥበቃ ጣቢያዎችና ደግሞ ዋናው የህዝብ ጤና ጥበቃ መመርመሪያ ጣቢያ የሆነው የኢትዮጵያ ፖስተር ኢንስቲቲውት ይገኛሉ፡፡ ባለፈው ዓመት በፀናው ህግ የህዝብ ጤና ጥበቃ ታክሎ በየአውራጃዎች ውስጥ የህዝብ ጤና ጥበቃ ድርጅቶችን ለማስፋፋት ብቻ የሚውል 4,500,000 የኢትዮጵያ ብር ገቢ የሚያስገኝ በመሆኑ መጠን ዛሬ የአገሪቱ የህዝብ ጤና ጥበቃ ፕሮግራም በተፋጠነ እርምጃ እያደገ ይሄዳል ተብሎ ይጠበቃል፡፡

"እንዲሁም ደግሞ በትራንስፖርትና በመገናኛዎች ረገድ የተፋጠነ እርምጃ ተደርገዋል፡፡ በብዛት የሚተላለፉ እየበዙ ሄደዋል፡፡ የአውራ ጎዳናዎች ባለስልጣን የመላው የንጉሠ ነገስት መንግስቱ ግዛት ውስጥ የአውራ ጎዳናዎችን መስራትና መጠገን ኃላፊነት ተሰጥቶታል፡፡ የአውራ ጎዳና ባለስልጣን ከዓለም ባንክ በተሰጡት ብድሮችና በተጨማሪም

ከመንግስት በተመደበለት ወጪ ገንዘብ 6ሺ ኪሎ ሜትር በማናቸውም ወራት የሚያገለግሉ አውራ ጎዳናዎችና እንዲሁም ደግሞ በድርቀት ወራት /በበጋ ማለታቸው ነው/ 2ሺ ኪሎ ሜትር መንገዶች እስከዛሬ ሰርቷል፡፡ ከዚህ በቀር 20ሺ ኪሎ ሜትር ሁለተኛ ደረጃ አውራ ጎዳናዎች በአገልግሎት ላይ ይገኛሉ፡፡ 8ሺ ኪሎ ሜትር አዲስ አውራ ጎዳናዎች ለመክፈት አስፈላጊው የፕላን ቅያሶች ተጠናቅቀዋል፡፡" እነዚህ አዲስ የሚከፈቱ አውራ ጎዳናዎች ከፍ ያሉ የእርሻ ሐብቶችና የኢንዱስትሪ ጥቅሞች ለማስገኘት የሚችሉትን አውራጃዎች አለ ችግር እንዲደርሱ መገናኛዎች ይከፍትላቸዋል፡፡

የአውራ ጎዳናዎች ስራ ፕሮግራም መጀመሪያው ክፍል 200 ሚሊዮን ብር የሚፈጅ ሆኖ ለወደፊት በአራት አመት ውስጥ እንዲጠናቀቅ የታቀደ ሲሆን፣ ለኢትዮጵያ አስፈላጊዋን የአንደኛ ደረጃ የአውራ ጎዳናዎች የሚሰጡት ለወደፊቱ በቅርብ ጊዜ የሚዘጋጀው የ10 ዓመት የአውራ ጎዳናዎች ስራ ፕሮግራም 1ሺ ሚሊዮን /1ቢሊዮን ማለታቸው ነው/ የኢትዮጵያ ብር ይፈጃል ተብሎ ይገመታል፡፡

"በ1945 ዓ.ም በተገለፀው የፌዴረሽን አዋጅ ኢትዮጵያ የቀድሞ ክፍሏ የነበረችውን ኤርትራን በማስመለስ የባህር በር ለማግኘት ችላለች፡፡

ይህ ጥንታዊዋን የኢትዮጵያ አውራጃ ከእናት አገሯ ጋር እንደገና ማዋሃድ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ከተፈፀሙት ታላላቅ ሙያዎች መካከል አንደኛው ነው፡፡

ከዚያን ጊዜ ወዲህ የኢትዮጵያ ንግድ የራሷ ወደቦች በሆኑት በምፅዋና አሰብ በኩል በብዛት መጉረፍ ጀመረ፡፡ የአሰብ ወደብ 26 ሚሊዮን የኢትዮጵያ ብር በፈጀ ወጪ ተስፋፍቶ ተሻሽሎዋል፡፡ በጠቅላላው በዚሁ ዓላማ መሠረት የንግድ መርከቦች ተገዙ፡፡ የወደብ ድርጅቶች ተስፋፍተዋል፡፡ በወደቦቻችንም ላይ ሰፊና የሚደነቁ የንግድ ተግባር እንቅስቃሴዎች ይታያሉ፡፡

"ቴሌግራፍ፣ የቴሌፎንና የራዲዮ መገናኛዎች በበኩላቸው እርምጃ ከመስጠት አልቦዘኑም፡፡ እነዚህ የመገናኛ ዘዴዎች በቅርብ ዓመታት የተፈለሰፉ ቢሆንም እንኳ በአገሪቱ ውስጥ በብዛት ተዘርግተው ጠቃሚነታቸውን አስመስክረዋል፡፡ በዚህ ረገድ የአገር ውስጥና ውጭ የኢንተርናሲዮናል መገናኛ ከፍ ያለ ጥቅምና እርምጃ አሳይቷል፡፡ የዛሬይቱ ኢትዮጵያ በእነዚህ ዘመናዊ መገናኛዎች አማካኝነት የ20ኛውን ክፍለ ዘመን የስልጣኔ እርምጃ በቅርቡ ትከታተላለች፡፡

"እንዲሁም የአየር ትራንስፖርት አገልግሎት ወደ ዘመናዊዋ ኢትዮጵያ ውስጥ ገብቶ አገልግሎቱን ሲሰጥ ይታያል፡፡

የኢትዮጵያ አየር መንገድ የንጉሰ ነገስት መንግስት ግዛት አውራጃዎችን ሁሉ የሚያገናኙ ውስጣዊ የአየር ትራንስፖርት መስመሮች



ያለው ከመሆኑም በላይ አውሮፓንና ምዕራብ አፍሪካን በየእለቱና በየሳምንቱ የሚያገናኙ የአየር መንገድ መስመሮች አሉት፡፡ እንዲሁም በሚመጣው ዓመት መጀመሪያ ላይ ቦኢንግ 720 ቢ የተባሉትን ፈጣን ማመላለሻ ጀት አውሮፕላኖች ስታገኝ ወደ ጀት ዘመን ለመሸጋገር ያስችላታል፡፡

"አያሌ ጠቃሚና ሠፊ የልማት ፕሮዤዎች /ፕሮጀክቶች/ ከአሁን በፊት ተጠናቀዋል፡፡ ባለፈው ዓመት ስራው ያለቀለት የቆቃ ግድብ ለኢንደስትሪዎች ማንቀሳቀሻ የሚያስፈልግ የኤሌክትሪክ ጉልበት በአነስተኛ ወጪ ሊሰጥ ችሎአል፡፡ እንዲሁም በአባይ ሸለቆ፣ በዋቢ ሸበሌና በአዋሽ ወንዝ ላይ ተቀዳሚ የልማት ፕሮዤዎች ጥናት ተደርገዋል፡፡ ፕርዤዎቹ በተባሉት ቀበሌዎች ውስጥ በስራ ላይ በአነስተኛ ወጪ የኤሌክትሪክ ኃይል በማቅረብ ለኢንደስትሪ ልማት ታላቅ እርምጃ የሚውሉ ከመሆናቸውም በላይ፣ ለእርሻ መስኖ አገልግሎት ውሃ በብዛት የሚሰጡ ይሆናሉ፡፡ ከአሁን በፊት ለእርሻ መስኖ አገልግሎት በምፅዋ ቀበሌ ውስጥ የተሰራው የዙላ ግድብ ከዚያን ጊዜ በፊት ፈፅሞ ታርሶ የማያውቀውን እጅግ ሰፊ የሆነ መሬት ለእርሻ አገልግሎት በማዋልና በዚሁም አኳኃን ለብዙ ህዝቦች መተዳደሪያ በማስገኘት ጠቃሚነቱን አሳይቷል፡፡ ...

"... እንግዲህ ኢትዮጵያ ከ1909 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 1953 ዓ.ም ድረስ ያለውን ረጅም ጎዳና እንደምን አድርጋ ነው የተጓዘችው?...

"ለተወደደችው አገራችን ህዝብ የመሻሻል እርምጃ የምናቅድለት ፕሮግራም አፈፃፀም ቅድመ አያቶቻችንና አባቶቻችን ይመሩበት ከነበረው የኑሮና የፖለቲካ አካሄድ ፍፁም የሆነ ልዩ አመራር የሚያስፈልገው መሆኑን በመገንዘብ ብዙዎች ቅርባችን የነበሩት ሁሉ የነበራቸውን እስከደም መፋሰስ የነበረውን ኃይለኛ መቃወም ታግሰን በ1923 ዓ.ም የኢትዮጵያን የመጀመሪያውን ሕገ-መንግስት በራሳችን ሙሉ ፈቃድ ለተወደደው ህዝባችን ሰጠነው፡፡

የኢትዮጵያ መንግስት አስተዳደር ለመጀመሪያ ጊዜ የተወሰነና የተብራራ መልክ እንዲኖረውና ለህዝብ በግልፅ እንዲታወቅ ተደረገ፡፡ ... የተወደደው ህዝባችን የአገሩን የመሻሻል እርምጃና የከፍተኛ ኑሮን ደረጃ ለማስገኘት ከእኛ ጋር አላፊነቱንና ስልጣኑን ተካፍሎ በፓርላማ እንዲሰራበት ያደረግነው ለአንዲቱ ኢትዮጵያ ያለመከፋፈል መሠረት ነው በማለት ነው፡፡ በዚህም አኳኋን ለአንድ አገር የተፋጠነና የማያቋርጥ የመሻሻል እርምጃ አስፈላጊ የሆነው የፖለቲካና የማኅበራዊ ኑሮ እድገት እንዲያገኝ ለማድረግ መሠረቱን ሰጠነው አገኘ፡፡

"ይህ ኀሳባችን በወረራ ምክንያት በድንገት የተቋረጠ ቢሆንም፣ ነፃ እንደወጣን ጅምራችንን ቀጥለን የበለጠ በማስፋፋት ጠላት ባደረገው

ጉዳት ፀፀትና ቁጭት በመላው ህዝባችን አድሮበት እንዲሰራበት አደረግን፡፡ በ1935 ዓ.ም የመንግስታችን ሚኒስትሮችና በልዩ ልዩ ክፍል ያሉት ሹማምንት የሚኖራችሁን ተግባርና ኃላፊነት ልትፈፅሙ የምትችሉበትን ስልጣን የሚወስን ትእዛዝ በአዋጅ አወጣን፡፡ ህዝባችንም ፍትህን ለማግኘት የሚችልበትን እና በሕገ-መንግስቱም የተሰጠውን መብት የሚያስከብርበት ፍርድ ቤት አቋቋምን፡፡ ይህንንም ስናደርግ ራሳችን የወጠንነውን የመሻሻል እርምጃ ሊያስከትል የሚችለውን ሁሉ በመገመትና ህይወት የሚመራበትንም መሠረታዊ ሃሳቦች በመገንዘብ የበለጠ መሻሻል እንዲኖር ለማበረታታትና ስራንም ለማቃለል ባለን በፅኑ ፍላጎትና ምኞት ተመርተን፣ ንጉሠነገስት ለመባል ህዝቡም ወደ በእግዚአብሔር ስንመረጥ ለገባነው ቃል ኪዳን ለህዝባችን ታማኝነት ራሳችን እየሰራንና. እየተቆጣጠርን ለመርዳት በራሳችን ሙሉ ፈቃድ ያደረግነው እንጂ ተጠይቀን አልነበረም፡፡

"የኢትዮጵያን የልማት እድገት ለማስገኘት የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ መብራት ኃይል ባለስልጣንን፣ የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ቦርድን፣ የኢትዮጵያ አየር መንገድን የአውራጎዳና ባለስልጣንና ልዩ ልዩ ኢንዱስትሪ እነዚህን የመሳሰሉትን ራሳቸውን ችለው የሚተዳደሩ ድርጅቶች ስራቸውን በሚመለከታቸው ክፍል ሙሉ ኃላፊነትና ስልጣን ኖሯቸው ራሳቸውን ችለው እንዲሰሩ በልዩ ሕግ አቋቁመን ይሰራባቸዋል፡፡

"… የንጉሠነገስት መንግስት ግዛታችን ስራና የመሻሻል እርምጃ እያደገና እየተስፋፋ በመሄዱ መጠን በ1923 ዓ.ም በራሳችን ሙሉ ፈቃድ የሰጠነው ሕገ-መንግስት ህዝባችን ከደረሰበት ደረጃ ጋር ሲመዛዘን በቂ አለመሆኑን ራሳችን ተገንዝበን የህዝባችንም እውቀት በማደጉ በ1948 ዓ.ም አዲሱን የተሻሻለውን ሕገ-መንግስት አሁንም ሳንጠየቅ ተቃዋሚም ቢኖርም በራሳችን ሙሉ ፈቃድ አውጀን ለህዝባችን ሰጠን፡፡

በዚህም በተሻሻለው አዲሱ ሕገ-መንግስት መሠረት በእኛ ሹሞች ጭምር ሲመረጥለት የነበረውን ህዝባችን በቀጥታ ለአማካሪነት የሚመረጡትን በመምረጥ በመንግስታችን ያስተዳደር ስራ ተካፋይ የሚሆንበት መብት እንዲኖረው አደረግን፡፡

በእኛ፣ በሚኒስትሮቻችንና በፓርላማችንም መካከል ያለው የስልጣን መከፋፈል ተወስኖና ፀንቶ ለሁልጊዜም የሚኖርበትን የድርጅት መልክ አገኘ፡፡ እንደዚሁም ህዝባችን በእለት ኑሮው በሚያጋጥመው ጉደይ ሁሉ እርስ በርስና ከመንግስቱም ጋር በሚያገናኘው ነገር የሚመራበት በትክክልና በዝርዝር ተወስኖ የተመለከተ የፍትሐብሔር፣ የባህር፣ የንግድና የወንጀል ሕጎች ተዘጋጅተው እንዲወጡና የኢትዮጵያም የኢኮኖሚ እድገትና ጠቅላላው የመሻሻል እርምጃ መልክ ባለውና በተባበረ አኳኃን እንዲመራ አሁንም የህዝብ ሐብትና መብት ከፍ የሚልበት፣ ለሰው ልጅ



በተወሰነው ደረጃ የሚደርስበትን የብድር ገንዘብም በብዙ ጥረት አገራችን የመታመን ዋስትና እንዲኖራትና የሚበቃ ዋስትና እንዳላት በማረጋገጥ እያሳየን ስንበደር መክፈልም እንዳለብን ቢታወቅም ያምስት ዓመት ፕላን ተዘጋጅቶ እንዲሰራበት አደረግን፡፡ ፍሬውንም ወደፊት የሚሰጥ ነው ብለን አምነናል፡፡

"ይህንን ሁሉ ስናደርግ ለኢትዮጵያ የመሻሻል እድገቷ እርምጃ አስፈላጊ የሆኑትን እርምጃዎች እንደወሰድን ፈጣሪያችን እንዲያውቅልን በማመን የልማት ፕሮግራማችን በቴክኒክ ረገድም ሆነ በቁጥራቸው እጅግ እየበዙና እየተስፋፉ በመሄዳቸው በ1934 ዓ.ም 11 ሚሊዮን የነበረው ዛሬ በ1953 ዓ.ም 272 ሚሊዮን የደረሰው የመንግስታችን በጀት ከዚሁ ጋር እያደገ በመሄዱ መጠን ዘር የበዛውን ያህል ምርቱንም ሰብስቦ ማሳደግ አስፈላጊ እንደሚሆን ሁሉ በመንግስታችን አመራር ውስጥ በየክፍሉ ያሉት አላፊ ባለስልጣኖቻችን በየደረጃቸው ሊወስኗቸው የሚገባቸው ጉዳዮችን እንዲከፋፈሉ በማድረግ የበለጠ አስፈላጊ እየሆነ መሄዱ የታወቀ ነው፡፡ በተለይ በዛሬው ጊዜ ሁሉንም ጉዳይ ጠንቅቆ ለማወቅ እኔ እበቃለሁ የሚል ማን አለ? የአንድን መንግስት የተስፋፋ ፕሮግራም ለማከናወን አስፈላጊ የሆነውን ውሣኔ ሁሉ በዛሬው ሰዓት ብቻውን ለመወሰን የሚቻለው ማን አለ? እነዚህ ጥያቄዎች መልስ የሚያስፈልጋቸው አይደሉም፡፡

እንግዲህ አንድ እውነተኛ ኃላፊነት ያለው የአስተዳደር ሁናቴ ለመፍጠር ከዚህ የበለጠ የሚያስፈልግ ነገር አለን? ምንስ ይጎድላል? የሚያስፈልግና የሚጎድልም ከዓለም ሰው ፍላጎት እንደማይጠፋ ይሰማናል፡፡

በአዲሱ ሕገ-መንግስት በዚህ አስተዳደር ድርጅት ውስጥ ያለውን እያንዳንዱን ክፍል ትክክለኛ ተግባሩና ኃላፊነቱ ምን እንደሆነና ይህንንም ተግባራችንን ለመፈፀም የሚችልበት መብቱ ተረጋግጧል፡፡

ሚንስትሮቻችንና በቅርብም በሩቅም ያሉት የየክፍሉ ሹማምንቶቻችን ሁሉ በማናቸውም ዓይነት የፖለቲካ አመራር ከሚተዳደሩ ከዓለም አገሮች ያንዳቸውም መንግስት ሚኒስትሮችና ባለስልጣኖች ካላቸው ያላነሰ ለስራችሁ የተመደበ ኃላፊነት ተሰጥቷችኋል፡፡ፓርላማችንም ማናቸውም በፓርላማ ሁናቴ የሚተዳደር አገር ካለው መብት ጋር ተመዛዛኝ የሆነ የሕግ ጎሳብ አቅራቢነት ስልጣን አለው፡፡ነገር ግን ኃላፊነቱን በሙሉ ተቀብለው በታማኝነት የሚሰሩ በቂ ሰዎች እንደሚያስፈልጉን ታውቁታላችሁ፡፡ የራሳችሁን ስራ ወደእኛ ማምጣታችሁ አላቋረጠም፡፡….

የበታችንም ሠራተኛ በማትጋትና በመጎትጎት የሚሰራ ስላልተገኘ ለስራ አፈፃፀም መሰናከል የሆኑ ብዙ ችግሮች ተፈጥረዋል፡፡ በስልጣን

አስታኮ ራስን መጥቀም ሲቆረቁረን መኖሩ ግልፅ ነው፡፡ ይህንንም በመመራመራችን አቅመቢስም ቢሆን ስም አጥፊ እንዳልቆመ እናውቃለን፡፡ መንግስት ዝርዝር በሆኑ ነገሮች ተውጦ ከፍ ያለ ዋናነት ያላቸው ጉዳዮች ውሣኔ ሳያገኙ ዘግይተዋል፡፡ ይህ የምንናገረው ቃል ራሳችሁ የምታስታውሱትና የምትመሰክሩት ነው፡፡

በአሁኑ ጊዜ ልናስጠነቅቃችሁ የምንወደው ለወደፊቱ ይህ አሰራር ሊቀጥል የማይችል መሆኑን ነው፡፡ የመንግስታችን አስተዳደር ደምና ስጋ እንደሌለው አካል ድርጅቱ ብቻ ኖሮ አፈፃፀሙ የተጓደለ መሆን ሳይኖርበት ስልጣን ተሰጥቷችሁ ሳለ ኃላፊነቱን ወደእኛ ማሳለፍ ቀርቶ ተግባራችሁንና ኃላፊነታችሁን በሙሉ ተገንዝባችሁ መስራት አለባችሁ፡፡

በስልጣን ምክንያት ለግል ወገን ከማድላትና የራስን ጥቅም ፈላጊ በመሆን እምነትን ከማጉደል በብርቱ ልትጠነቀቁበት የሚገባችሁና ከእኛና ከህዝብም የተጣለባችሁን ከፍተኛ አደራና እምነት ጠብቃችሁ መገኘት የመጀመሪያ ዋና ተግባራችሁ እንዲሆን በአደራ ጭምር አጥብቀን የምናዘው ነው፡፡

በተሰጣችሁ መምሪያና ኃላፊነት መውሰጃ ዝርዝር ውስጥ ሊታረምና ሊሻሻል የሚያስፈልግ ቢኖር ብታመለክቱን በደስታ እንቀበላለን፡፡ ተቀብለንም እናቃናለን፡፡

"ከዛሬ ጀምሮ እያንዳንዳችሁ በተመደባችሁበት ሚኒስቴር ተቀምጣችሁ የየክፍላችሁን የስራ ፕሮግራም በቀጥታ ማስተዳደርና መፈፀም አለባችሁ፡፡ በየዓመቱ በሕገ-መንግስቱና ለአገራችን እድገት መሻሻልና ብልፅግና ተጠንቶ በተዘጋጀው የአምስት ዓመት ፕላን መሠረት ለሚቀጥለው ዓመት በየክፍላችሁ የምትፈፅሙትን የስራ ፕሮግራም እያዘጋጃችሁ፤ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ተመክሮበት እየቀረበልን ከተፈቀደ በኋላ በዚሁ ፕሮግራም መሠረት ስራችሁን በቀጥታ መምራትና ማከናወን አለባችሁ፡፡ የስራ ፕሮግራማችሁን በሚገባ አዘጋጅታችሁ በመልካም ያከናወናችሁ እንደሆነ ችሎታችሁ የሚታወቅበትና የምትመሰገኑበት ነው፡፡ ነገር ግን ስራችሁን በሚገባ አቅዳችሁ ማከናወን ቢያቅታችሁ ችሎታችሁ የሚነቀፍበትና ከስራችሁም ተሽራችሁ በምትካችሁ ሌላ ችሎታ ያለው የሚደረግበት ነው፡፡ ከፍተኛ ትልቅ ስራና የፖሊሲ፣ የፖለቲካ ጉዳይ በሚያጋጥማችሁ ጊዜ በማናቸውም ሰዓት የምንቀበላችሁ ነን፡፡ ባዘጋጃችኋቸውም የስራ ፕሮግራሞች አፈፃፀም የሚገጥሟችሁን የዘወትር ችግሮች ለማቃናት የሚረዳችሁ ጠቅላይ ሚኒስትራችንን ሾመናል፡፡ የእርሱም ዋና ተግባር የሚንስትሮቻችንን ስራ ማስተባበርና በመንግስቱም የስራ ፕሮግራሞች አፈፃፀም የሚገጥሙትን ችግሮች እንዲቃኑ ማድረግ ነው፡፡ ከፍተኛ የፖሊሲ ጉዳዮች በሚያጋጥሙት ጊዜ ግን እርሱም እንደዚሁ ለእኛ ያቀርብልናል፡፡



አዘጋጅታችሁ የምታቀርቧቸው የስራ ፕሮግራሞችና እነርሱንም የምትፈፅሙበት ሁኔታ ህዝብ እንዲያውቀው ይሆናል፡፡ ዞሮ ዞሮ ጠቅላላው ሹማምንት የሆናችሁ ሁሉ ከትልቅ እስከ ትንሽ ኃላፊነታችሁ ለኢትዮጵያ ህዝብ ስለሆነ በአስተዳዳሪነታችሁና በስራ አስፈፃሚነታችሁ ለምትጠየቁበት መልስ የሚኖርባችሁ መሆኑን እወቁ፡፡ በሕገ-መንግስቱም ለፓርላማውና ለእኛ ኃላፊ ናችሁ ያልነው ስለዚህ ነው፡፡ በህይወታችን ዘመን ሙሉ በራሳችን ላይ የሚደርሰው ጉዳት ሳይሰማን ለተወደደው ህዝባችን፣ለአገራችን ልናደርገው የሚገባን ተግባር ሆኖ የተሰማንን ሁሉ ያለማጓደል የፈፀምን ለመሆናችን ሁሉን አዋቂ የሆነው አምላክ ታዛቢያችን ነው፡፡

እናንተ በመንፈስና በእውቀት በማሰራት በስራ የቀረፅናችሁ ሚንስትሮችና ባለስልጣኖች የተሰጣችሁ ስራ አንድ ጊዜ ከተወሰነ በኋላ ራሳችሁን ችላችሁ ለመፈፀም ከምትበቁበትና እኛም ለኢትዮጵያ ዘለቄታ እድል አስፈላጊዎች በሆኑት ዋናዎች ጉዳዮችና የፖለቲካ አመራር አሳባችንን በሙሉ ለማዋል ከምንችልበት ደረጃ ላይ እንደምንደርስ እምነን ያለማቋረጥ የደከምንበት ስለሆነ ለተሰጣችሁ ግምት የተገባችሁ ሆናችሁ እንድትገኙ ራሳችሁን ለአገራችሁ ለመሰዋት ቆርጣችሁ የጣልንባችሁን አደራ ታላቅ መሆኑን ልታውቁት ይገባል፡፡

ለዚህ አደራ የደረሳችሁ መሆናችሁን የሚመሰክረው እኛ የጣልንባችሁ እምነት ብቻ ሳይሆን፤ እናንተም ራሳችሁ ለህዝቡ አገልግሎትና ለተወደደችው አገራችን እድገት የመሠረትነውን ሁሉ በመፈፀም በዚህ በተቀበላችሁት ስልጣን ወደፊት የምታሳዩት የስራ ፍሬ መሆኑን ልትዘነጉት አይገባም፡፡

ቢሮዋችሁን ቤታችሁ ኦድርጋችሁ እለት በእለት የሚያጋጥማችሁን ጥቃቅን ጉዳይ ሁሉ ፈፅሙ፤ ከሾምናችሁ ውስጥ ባለፈውም ጊዜ እንደዚህ የሰሩ ነበሩ፤ አሉም፡፡ ያለረዳትና የስራ አስተናባሪ አለተውናችሁምና የሰጠናችሁ የቴክኒክ አማካሪዎችና በቢሮ ውስጥ ያሉ ሠራተኞች በወገንነት፣ በዝምድና ብቻ ያልተመረጡ ከሆኑ ትጋት ያገኛሉ፡፡ እየተቆጣጠራችሁም ልታሰሯቸው ትችላላችሁ፡፡ በስህተታችሁ እየተነቀፋችሁና ለወደፊቱም ትምህርት እየሆናችሁ በመልካም ስራችሁ እየተመሰገናችሁ ኃላፊነታችሁን ይዛችሁ መስራት አለባችሁ፡፡

በዘመድና በዝምድና ብቻ ያልተመረጡ ስንል ዘመድ የሌለው ሰው አይገኝም፡፡ በዝምድና እውቀቱ ከመረጠው ዘመዴ ከሆነ ስራ አይግባ ለማለት ምክንያት ሊሆን አይችልም፡፡ (እገሌን ስራ ባስገባው "ዘመዱ ነው ወይም ዘመዱ ስለሆነ ስራ አስገባው እባላለሁ" በሚል ስጋት እውቀት ያለው ሰው እንዳይገለል ሲያስጠነቅቁ ነው፡፡)

በስራ ፕሮግራማችሁ አፈፃፀም ያከናወናችሁትንና የገጠማችሁንም ችግር ልትገልፁልን እንድትችሉ በየሳምንቱ እያንዳንዳችሁን ለተወሰነ ሰዓት ተቀብለን እናነጋግራችኋለን፡፡ ነገር ግን ይህ ሰዓት የስራ ፕሮግራማችሁ ከምን እንደደረሰና የፖለቲካም ችግር ቢኖር ለማወቅ የምንረዳበት ጊዜና የምንረዳችሁ ነው እንጂ ራሳችሁ ልትወስኑት የሚገባችሁን ጉዳይ ከእኛ ውሣኔ የምትጠብቁበት ወይም የምታገኙበት ጊዜ አይደለም፡፡...

"በዘመኑ መንግስታችንም በተከናወነውና በተፈፀመው ስራና ለወደፊት በመሰረትናቸው ሁሉ ፈጣሪያችንን እያመሰገንን ከፍ ያለ ደስታ ይሰማናል፡፡ ለአገራችንና ለህዝባችን በፈፀምነውና ወደፊት በምንፈፅመው ተግባር ባለን አቅማችን ከመስራት አናቋርጥም፡፡ ብዙ ስራ አለ፡፡

በየእለቱ መፈፀም የሚገባው ስራና እያንዳንዱም ቀን የሚያስከትለው አስቸጋሪ ተግባር የቱን ያህል አስቸኳይና አጣዳፊ መሆኑን ሳንዘነጋ የአገራችን ታሪክ የረጅም ዘመን ጉዞ አልፎ እንደመጣ ሁሉ ወደፊታችንም ያለው ይልቁንም የኑክሌርና ሰውም ወዳልታወቀበት ዓለም የሚላክበት ዘመን የሚያስከትለው ወሰን የሌለው ተግባር መኖሩን አጥብቀን መገንዘብ ይኖርብናል፡፡ (ወደ ሌላ ፕላኔት ማለታቸው ነው) በምንፈፅማቸው ስራ ሁሉ ዛሬ ውሣኔ የምንሰጥበት እያንዳንዱ ጉዳይ በወደፊቱ ላይ ሊያስከትል የሚችለውን በመገመትና በመገንዘብ መስራት አለብን፡፡ ይህ ዛሬ የምንነግራችሁ ቃል በወደፊቱ የኢትዮጵያ ትውልድ ላይ ሊያስከትለውና ሊያኖረው የሚችለው ሁኔታ ሊገመትበት ይቻላል፡፡

ዛሬ የተናገርነው ቃላችን የሚያስገኘው ውጤት ከእኛም በኋላ የሚከተሉን ለሁልጊዜም የሚጠቀሙበት እንደሚሆን እናምናለን፡፡ ሰው ሟች ነው፡፡ እዚህ ያለነው እያንዳንዳችን ለሰራነው ሁሉ በፈጣሪያችን ዘንድና በዚህ ዓለም ዋጋችንን እንቀበልበታለን፡፡

ለህዝብ መሪነትና አስተዳዳሪነት ከባዱን ሸክም የተቀበልነውም ሰዎች ይህንን የጣሉብንን ከፍተኛ አደራ በትክክልና በሚገባ ለመፈፀማችን በህዝባችንና በእግዚአብሔር ፊት ያለብን ኃላፊነት እጅግ ከባድ ነው፡፡ ኢትዮጵያ አገራችንና የተወደደውም የኢትዮጵያ ህዝባችን በደስታና በብልፅግና እንዲኖር ይህንን ኃላፊነት በመገንዘብ በሙሉ ልባችንና ኃይላችን በቅንነት እንድንሰራ ኃያሉ እግዚአብሔር ይርዳን" ብለዋል፡፡ አሜን ብለን እንቀጥል፡፡

ይህንን የአፄ ኃይለስላሴን ንግግር አንብበን እንድናዝንላቸው ወይም ደግነታቸውን እንድንረዳላቸው ወይም ለሌላ ተመሳሳይ ውዳሴ በር ልከፍትላቸው አይደለም ያካተትኩት፡፡ ጥቂት መንግስታት ባዶ ፕሮፓጋንዳ መንዛት ቋሚ ስራቸው እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ነገር ግን የጃንሆይ ንግግር አንድም የሚጣል የሌለው ጠጣር እውነት ነው፡፡



ከዚህ በፊት ያየናቸውን አጫጭር ታሪኮች በሙሉ ጃንሆይን በእጅጉ ከሚተቹ ምሁራንና በከፊል ከሚተቹ ምሁራን ነው የቃረምኳቸው ናቸው፡፡ የአቀራረባቸው መለያየት ብቻ እንጂ ስለተሰሩት ስራዎች የጃንሆይ ንግግርም፣ የምሁራኑም የሚጣረስ አይደለም፡፡

ንጉሡ እንዳሉት "የተሰሩት ስራዎች ለትውልድ ቋሚ እንደሚሆኑ እናምናለን" በትክክል እንደዚያ ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ ለመተቸት ያመች ዘንድ የተሰሩትን ስራዎች የጃንሆይ ውጤት እንዳይመስሉ "አሜሪካ፣ ጣሊያን፣ እንግሊዝ፣ ፈረንሣይ፣ ... ወዘተ ናቸው የሰሯቸው" በሚል መነሻ ጃንሆይን ዋጋ ቢስ ለማድረግ ይሞከራል፡፡

አዎ! እንዳየነው እያንዳንዱ ዘመናዊ ስራ የሰለጡን አገሮች አሻራ አለበት፡፡ ታዲያ ከየት ይመጣል? ምሁር የለ ምን የለ! ትምህርት ቤት ተሰርቶ በነጮች የበላይነት ይተዳደር ነበር፡፡ ኢትዮጵያ የራሷ ምሁራን እስኪኖሯት ድረስ፡፡ አየር መንገድ ተመስርቶ በአሜካኖች የበላይነት ተመርቷል፡፡ ኢትዮጵያ የራሷ ባለሙያዎች እስኪኖሯት ድረስ፡፡ አውራጎዳናም እንደዚያው፣ ሌላውም በተመሳሳይ፡፡ አንድ አፍሪካዊ መሪ የነበረው ብቸኛ አማራጭ ይሄው ነበር፡፡ እርዳታውም ያስፈልግ ነበር ለምነዋል፡፡ ብድሩንም እንደዚያው፡፡ እኛን ቢገድሉንም፣ ቢያድኑንም ዛሬ ድረስ ነጮች ናቸው፡፡ ይህችን አገር ሙሉ ለሙሉ በጦር ይዘው አይግዟት እንጂ በምሁርነትና በርእዮተዓለም ሽፋን ሲያሽከረክሯት ኖረዋል፡፡ ይሄ ሁሉ የምን ችግር ነው? ኢትዮጵያ የራሷ ምሁራን ስለሌላት ብቻ፡፡ ጃንሆይ ይሄን ለመቅረፍ ጥረዋል፡፡ ወደፊትም ትምህርት ላይ ካልተተኮረ ይህች አገር ታሪኳን ስትደግም ትኖራለች፡፡ ትምህርት ሲባል ግን ‹‹አለምን በመርከብ የዞረው ማነው፣ አውሮፕላንን የሰሩት ወንድማማቾች ስማቸው ማን ይባላል፣....››እየተባለ የሚደሰኮረውን አይነት ትምህርት አይደለም፡፡ ስለነሱ ለማወቅ ከመማር ያለፈ ት/ት ያስፈልጋል፡፡የሰሪውን ስም ሳይሆን ያሰራሩን ጥበብ እንደማለት፡፡ እናም.... የጃንሆይን ጅምር ልናበረታታው እንጂ ልናጣጥለው ይከብዳል፡፡

ዙፋኑን የገዘገዘው ሙስና

የቀደምቶቹም ሆነ የአሁኑ ዘመን ኢትዮጵያውያን አቶ ብርሃኑ ድንቄን ጠንቅቀው ያውቋቸዋል፡፡ ለማያውቋቸው አንባብያን ለመግለፅ ካስፈለገ "አቶ ብርሃኑ ድንቄ ድንቅ ኢትዮጵያዊ ናቸው" ብዬ በድፍረት እገልፅላቸዋለሁ፡፡

አቶ ብርሃኑ ድንቄ በዚያ ዘመን አገላለፅ ከአፈር ተነስተው በልዩ ልዩ የስራ ዘርፍ አልፈው አምባሳደር መሆን የቻሉት በጃንሆይ መልካም ፈቃድ ነበር፡፡ ነገር ግን በስተመጨረሻ ጃንሆይ ሊያስገድሏቸው ለአመታት ሞክረው ሳይሳካላቸው ቀርቷል፡፡

ከተራ ትኬት ቆራጭነት ጀምረው በአሜሪካ የኢትዮጵያ አምባሳደርና ባለሙሉ ስልጣን እንደራሴ መሆን እስከቻሉበት ጊዜ ድረስ በበርካታ የመንግስት መስሪያ ቤቶች ተመድበው ሲያገለግሉ፤ በተመደቡባቸው መስሪያ ቤቶች ሁሉ ከፍተኛ ምዝበራ ይካሄድ እንደነበር ይነግሩናል፡፡ እዚህ ላይ ቀድሜ ለአንባብያን በአፅንኦት መግለፅ የምፈልገው ጉዳይ አለ፡፡ ይኸውም አንባብያን በአንድ የብርሃኑ ድንቄ ገጠመኝ ብቻ ሳትወሰኑ በየመንግስት መስሪያ ቤቱና በየአገልግሎት ሰጭ ተቋማቱ አቶ ብርሃኑ ያላዩዋቸው ሌሎች ከፍተኛ ምዝበራዎች ምን እንደሚመስሉ በጥምረት ማሰብ ሞክሩ፡፡

ተከታዩን ታሪክ በዚህ መፅሐፍ ለማካተት ያስፈለገኝ ታሪኩ በአንድ መፅሐፍ ብቻ ተካቶና ተወስኖ መቅረቱ ስለከነከነኝ ነው፡፡ ማለትም ከረጅሙ የኢትዮጵያ ታሪክ ጋር ቢካተት ብዙ ነገር ያስገነዝባል ብዬ ስላመንኩ ነው፡፡

ሙሉውን ታሪክ የፈለገ አንባቢ "ቄሣርና አብዮት" በሚል ርዕስ በአንድ በኩል፣ በጀርባዋ ደግሞ "አልበ ዘመድ" በሚል ርዕስ የተጠናቀረች ሆና በሁለቱም በኩል 145 ገጾች ያሏት ትንሽዬ፣ ነገር ግን ግዙፍ የሆነች መፅሐፍ በቀላሉ አግኝቶ ማንበብ ይችላል፡፡ የታተመው በ1987 ዓ.ም ነው፡፡ ያነበባችኋት ካላችሁ ግድየለም፡፡ ሁለት አማራጭ መሆኑ ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያውያን ቢጠቅም እንጂ አይጎዳም፡፡ በጃንሆይ ጊዜ ተደርጎ ያለፈ ብቻ ስላይደለና አሁንም ድረስ በከፍተኛ ሁኔታ ተስፋፍቶ ስለሚገኝም ልዩ ትኩረት መስጠቱ ተገቢ ነው፡፡

"ቄሣርና አብዮት" ውስጥ በመግባት ከዚህ ንዑስ ርዕስ /ሙስና/ ጋር ግንኙነት ያለውን ብቻ እየመረጥኩ አቀርባለሁ፡፡ አቶ ብርሃኑ ድንቄ በአንደኛ መደብ የትረካ አንፃር "እኔ" እያሉ ነው የተረኩት፡፡

እንግዲህ ጃንሆይን በተመለከተ ቀደም ሲል መንግስታዊ አወቃቀራቸውና የሚኒስትሮች የስራ ስምሪት፣የመስሪያ ቤቶች አላማና ተግባር፣ጅምር ስለመሆናቸው እንዲሁም ለባለስልጣናቱ ስለተሰጡት አደራዎች ብዙ ነገር አይተናል፡፡ከዚያስ? የሚለውን ነው የምናየው፡፡ አቶ ብርሃኑ ድንቄ የሚገጥሟቸውን ሙሰኞች ስማቸውን እስከነአባት፣እስከነማዕረጋቸው እንደወረደ ጠቅሰው ፅፈዋቸዋል፡፡በዚህ መፅሐፍ ያባትን ስም ባለመግለፅ ለመራራት ተሞክሯል፡፡መጥፎ ስራ የሰሩትን ለማለት ነው፡፡

ለማንኛውም ክቡር አቶ ብርሃኑ ድንቄ በመፅሐፋቸው መግቢያ ካሰፈሩዋቸው ሐተታዎች ጥቂት አረፍተ ነገሮችን ላስቀድምና ልቀጥል፡፡

"... ቄሣርና አብዮት በሚል ስያሜ ይህችን መፅሐፍ ለማሰናዳት ስሞክር የአፄ ኃይለስላሴን ውድቀትና የአብዮቱን አሸናፊነት እያጋነንሁ



የምተርክ መስሏቸው አንባብያን በውሸት ተስፋ እንዳይጠባበቁ አስቀድሞ ማስጠንቀቅ ይኖርብኛል፡፡

"... አንዳንድ ሰዎች በአሁኑ ጊዜ ስለ አፄ ኃይለስላሴ መናገር ወይም መፃፍ የሚያሳፍር ነገር መስሎ ሊታያቸው ይችላል፡፡ በእኔ አስተያየት ይህ ታላቅ ስህተት ነው፡፡ መጪው ትውልድ ስለኒህ ሰው ውነተኛውን ታሪክ ለማወቅ ያለውን መብት መንፈግ ከቶ አይገባንም፡፡

"ይችን መፅሐፍ ለማሰናዳት ያለኝን ኀሳብ ያካፈልኩት አንድ ኢትዮጵያዊ ወዳጄ በጉዳዩ ተገርሞ የሰጠውን ሐተታና የተለዋወጥነውን ንግግር ሳልጠቅስ አላልፍም፡፡

"አቶ ብርሃኑ ያ ሁሉ ችግር፣ መከራ፣ ስደት፣ የሐብት መወረስ፣ የቤትና የንብረት መፍረስ ከደረሰብዎ በኋላ፣ አሁን ስለ አፄ ኃይለስላሴ መፅሐፍ እጽፋለሁ ብለው ጊዜዎን ለምን በከንቱ እንደሚያጠፉ አይገባኝም፡፡ ... ምናልባት ጠላታችሁን ውደዱ የሚለውን ወርቃማ ሕግ ለመፈፀም ይሆን" ሲሉ አቶ ብርሃኑ እንዲህ ይመልሳሉ፡፡

"ወዳጄ ሆይ ጠላትን መውደድ ምንም እንኳ አስቸጋሪ ነገር ቢሆንም፤ ስለእርሱ የምናውቀውን እውነት መናገር ይህን ያህል የሚያስደንቅ ሞያ ሆኖ አላገኘውም፡፡ በእርግጥ ዛሬ በኢትዮጵያ ያለው ፕሮብሌም ይህ ነው፡፡ አንድ ሰውን የጠላን እንደሆነ የጥላቻችንን ምክንያት በመናገር ፋንታ የሌለውን ነገር ፈጥረን በእርሱ ላይ ስናወራ እንደሰታለን፡፡ ይህ ታላቅ የሞራል ውድቀት ይባላል፡፡ የእኔ ሙከራ ስለአፄ ኃይለስላሴ በምናውቀው መጠን እውነተኛውን የታሪክ ቅርስ ለሚመጣው ትውልድ ለማቆየት ብቻ ነው፡፡" ...

"... አገራችን ኢትዮጵያ የሚጠብቃትን የፖለቲካ ትርምስ አስቀድሞ በመገንዘብ የወደፊቱን ችግር ለማቃለል የሚቻለው አፄ ኃይለስላሴ ስልጣናቸውን በሕገ-መንግስት ወስነው እንደ ምዕራባውያን ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ ህዝብ በመንግስቱ ጉዳይ በቀጥታ ተካፋይ እንዲሆን ሲፈቅዱ ብቻ መሆኑ ስለታየኝ ይህንኑ ደጋግሜ አመልክቻቸው ነበር፡፡ ግን እርሳቸውን በመደለል መጠቀም የለመዱ ሹማምንቶቻቸው ኀሳቡን ሳይደግፉት ስለቀሩ በመጨረሻ ግልፅ ደብዳቤ እንድፅፍላቸው ተገደድሁ፡፡

ይህ የእኔ ግልፅ አቋም አፄ ኃይለስላሴን በብርቱ ስላስቀየማቸውና ስላስቆጣቸው በሚስጥራዊ የፀጥታ ጠባቂዎቻቸው አማካይነት ህይወቴን ለማስጠፋት ዘጠኝ አመታት ያህል ተከታትለውኛል፡፡ ግን በእኔ ላይ ስላመጡብኝ መከራና ጭንቀት ለመበቀል ወይም በልዩ ልዩ ምክንያት ይጠሏቸው የነበሩትን ሰዎች ለማስደሰት ስል በዘመነ መንግስታቸው የተመለከትሁትን ሁሉ አጣምሜ ባቀርብ የታሪክ ቅርስነቱ ስለሚቀር ኃላፊነቱ ይሰማኛል፡፡ ከዚህም በቀር ከመቃብር በታች ድንጋይና አፈር

ተጭነውት አፉን ዘግቶ፣ ትንፋሹ ጠፍቶ ስለሚገኝ ሰው በምንናገርበት ጊዜ የሚከተለውን ማሰብ አለብን፡፡

1ኛ. ሟቹ የራሱን ወገን የመከላከያ ታሪክ ለማቅረብና ምስክርነታችንን ለማስተባበል እድል የለውም፡፡

2ኛ. በምንም ሊዛነፍ የማይችለው መለኮታዊ ሕግ ነገ በእኛም ላይ ተጠቅሶ በፈረድንበት እንዲፈረድብን ሊያደርግ ይችላል፡፡ ስለዚህ ሌላው ቢቀር በወቀሳችን ተቀይሞ ይበቀለናል ወይም በምስጋናችን ተደልሎ ውለታ ይከፍለናል ብለን ስለማንጠብቀውና ወደ ትቢያነት ስለተመለሰው ሰው ያለፈ ህይወት እውነትን ለመናገሪያ ከአሁን የተሻለ ምን ጊዜ አለ?" ብለው ይጠይቃሉ፡፡

"ይህ መፅሐፍ" ይላሉ አቶ ብርሃኑ "ይህ መፅሐፍ የአፄ ኃይለስላሴ የፍትሐት ማሳረጊያ ቡራኬ አለመሆኑን ለመግለጥ የአንባቢን ትኩረት መጥራት እፈቅዳለሁ፡፡ ለምሳሌ ስለመንግስታቸው አቋም፣ ስለ ትምህርት ቤቶች፣ ስለአገር አገዛዝ፣ ስለፍርድ ቤቶች፣ ስለውጪ አገር ፖሊሲ፣ ስለኢኮኖሚ ፕላን... የተናገርሁት ነገር የለም፡፡ በተለይ አንባቢን ለመርዳት ያሰብሁት፣ የመንግስታቸው ክፍል በነበርሁበት ጊዜ የተመለከትኳቸውን የተወሰኑ ድርጊቶች እንደ ዓይን ምስክር ለማቅረብ ነው፡፡ ይህ በማድነቅም፣ በመንቀፍም ሊሆን ይችላል..." እያሉ ይቀጥላሉ፡፡

አቶ ብርሃኑ ድንቄ ለአፄ ኃይለስላሴ በስተመጨረሻ እዚያው አሜሪካ ሆነው የፃፉት ድፍረት የተሞላበት ግልፅ ደብዳቤ አለ፡፡ አቶ ብርሃኑ በዚች መፅሐፋቸው ባያካትቷትም እኔ በቀላሉ ማግኘት ስለቻልኩ ወደበኋላ አስገባታለሁ፡፡ እኒህ "ምሁር" ይችን መፅሐፍ የፃፏት ስለሙስናው ብቻ ማውራት ፈልገው አይደለም፡፡ ከልጅነታቸው ጀምሮ ... ከጃንሆይ ጋር እንዴት እንደተዋወቁ ... ወዘተ ... እየተረኩ በስራው ዓለም የገጠማቸውን ሲያሳዩን የምናገኘው ነው፡፡ ስለዚህ የእኔ ስራ ሙስናውን መልቀምና ይዘቱን ባልለቀቀ አተራረክ ደግሞ ማሳየት ነው፡፡ ይህችን አገር አወዛውዞ አወዛውዞ ከስሯ መንግሎ ሊጥላት የሚችለውና እያወዛወዛትም ያለው ይሄው ጉዳይ ስለሆነ ነው፡፡ ኢትዮጵያ በህይወት እስካለች ድረስ መንግስታት ሊያተኩሩበት የሚገባ ዋነኛ ነጥብ ንቅዘት! ለዚህ የግድ ሰፊ ሽፋን መሰጠት አለበት፡፡ ሌላው ነገር ሁሉ ቢቀር ይሻላል ባይ ሆኛለሁ፡፡

ከነፃነት በኋላ እንደነአቶ ብርሃኑ ድንቄ ላሉ ወይ አርበኛ ወይ ስደተኛ ላልነበሩ ሰዎች ስራ ማግኘት ከባድ ነበር፡፡

ወ/ሮ ሸዋረገድ ገድሌ በወረራው ዘመን በፈፀሙት ስራ ሳቢያ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ተሰሚነት ያላቸው ሆነው ነበር፡፡ ከአቶ ብርሃኑ ድንቄ ጋር ትውውቅ ነበራቸውና ሊጠይቋቸው በሄዱ ጊዜ ወ/ሮዋ "ብርሃኑ



ባለፈው አዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ የፃፍከውን አነበብሁት፤ በጣም ጥሩ ኀሳብ ነው" እየተባባሉ ጥቂት ተጨዋወቱ፡፡

አቶ ብርሃኑ ድንቄ በልጅነታቸው የቤተ-ክህነቱን ትምህርት ቶት አድርገውታል፡፡ "አያሌ ዓመታት ዘግይቼ የፈረንሣይ ቋንቋ ካወቅሁ በኋላ ከስመጥሩው ደራሲ ከቮልቴር የተፃፈ መፅሐፍ ሳነብ የአስተሳሰባቸውን አድማስ ጠባብ አድርገው ለሚኖሩ ሰዎች ማዘን ጀመርኩ" በማለትም በልጅነታቸው ከእንጦጦ በቀር ሌላ አድማስ ያለ አይመስላቸው እንደነበር ይነግሩናል፡፡ ያች የልጅነት ጠባብ አእምሮ በየጊዜው እየሰፋች ሄዳ ነው እንግዲህ ኀሳባቸውን በብዙሃን መገናኛ ወደማሰራጨትና ሌሎችን ወደማስደመም የደረሰችው፡፡

ስራ ያልነበራቸው አቶ ብርሃኑ ድንቄ አንዳንድ ጠቃሚ የሆኑ በኢጣሊያ ቋንቋ የተፃፉ ፅሁፎችን መተርጎም የሚችሉበት ስራ ቢገኝላቸው ይመርጡ ነበር፡፡ ጣሊያንኛ ለምደው ነበርና፡፡ ሆኖም በመጀመሪያ የተገኘው ስራ በተሽከርካሪ መኪና ክፍል ገንዘብ ተቀባይነት የነበረ ሲሆን፤ እሱም በሸዋረገድ ገድሌ ጥረት የተገኘ ነው፡፡

ከባባድ መኪናዎች እቃ ጭነው ከአንድ አውራጃ ወደ ሌላ አውራጃ ለመሄድ ከአገር ግዛት ሚኒስቴር ፈቃድ መጠየቅ ነበረባቸው፡፡ የሚከፍሉት ቀረጥም እንደየርቀቱ ይወሰናል፡፡ ባለቤቶቹም ከመዘጋጃ ቤት የተሰጣቸውን የባለቤትነት ማስረጃ ከማቅረብ ጀምሮ ልዩ ልዩ መመዘኛዎችን ማሟላት ይጠበቅባቸዋል፡፡

የአገር ግዛት ሚኒስቴር ዋና ዳይሬክተር የነበሩት የፊት አውራሪ ደምሴ ወንድም አቶ ኃይሌ ግን መቶ መቶ ብር ጉቦ እየተቀበለ ይሸኛቸዋል እንጂ ብዙዎች መመዘኛውን አሟልተው ማቅረብ የማይችሉ ነበሩ፡፡ አንዳንዱ ካሚዮን ከጣሊያን በዘረፋ የተገኘና በአፈሳ የተወሰደ ነበር፡፡ አቶ ኃይሌ ቀደም ሲል ፀሐፊም፣ ገንዘብ ተቀባይም ሆነው ነበርና የሚሰሩት፤ አቶ ብርሃኑ የገንዘብ ተቀባይነቱን ስራ ሲይዙ ባለመኪኖችን ማስረጃ በሚጠይቁ ጊዜ 50 ብር ለአቶ ብርሃኑ፣ 50ብር ለአቶ ኃይሌ ሊያካፍሉ ሞከሩ፡፡ አቶ ብርሃኑ "አይደረግም!" አሉ፡፡ ኃይሌ ሊያግባባቸው ሲሞክር ተቆጡት፡፡ "በጭራሽ!" ሲሉም አረጋገጡለት፡፡

የአገር ግዛት ሚኒስቴር ዋና ፀሐፊ የነበሩት አቶ ኃይሌ መርሻ የአቶ ብርሃኑን ሁኔታ ሰምተው አድናቆታቸውን ቸሩ፡፡ ኃይሌ ግን ለወንድሙ ለፊት አውራሪ ደምሴ ተናገረ፡፡ አቶ ብርሃኑ እንዲህ ይሉናል፤ "በ5ኛው ቀን ዋናው ዳይሬክተር ይጠሩሃል ተብዬ ተነገረኝ፡፡ እኔ ደግሞ ስለእምነቴ ማን ነግሯቸው ይሆን? ምስጋና ሊሰጡኝ ይሆናል እያልኩ አስብ ነበር፡፡ ... ከቢሮዋቸው እንደገባሁ እጅ ነስቼ ከፊታቸው ቆምሁ፡፡ ... ግንባራቸውን ቋጥር አድርገውታል፡፡ በቁጣ መልክ ትክ ብለው እኔን እያዩ፤

"ማን ትባላለህ?" አሉኝ፡፡

"ስሜ ብርሃኑ ድንቄ ነው" ብዬ መለስኩላቸው፡፡

"ማነው ይሄን ስራ የሰጠህ?"

"ዋናው ፀሐፊ አቶ ኃይሌ መርሻ ናቸው፡፡"

ወደ ፐርሶኔሉ ሹም ፊታቸውን ዘወር አደረጉና ... "በል አሁን በእጁ ያለውን ማናቸውንም ገንዘብና ማስረጃ ሁሉ ተረከበው" ብለው ከቢሮዋቸው አስወጡኝ፡፡ ምስኪን ብርሃኑ! ምን ማድረግ ይቻላል? ጠመንጃ ይዞ እያስፈራራ የሚቀማ ወንበዴ በድንገት ሳልጠነቀቅ እንዳነቀኝ እንጂ ከአንድ የመንግስት ባለስልጣን ፊት እንደቆምሁ ለማሰብ በፍፁም አልቻልኩም፡፡ ልሳኔ ተሳሰሮ፣ አፌ በፍርሐት አመድ ቅሞ፣ ፊቴ በቁጣ ደም ለብሶ፣ ሰውነቴ እየተንዘፈዘፈ በእጄ ያለውን ማናቸውንም ገንዘብና ማስረጃዎች ወዲያው አስረክቤ ከአገር ሚኒስቴር አዲሱ ስራዬ በአንድ ሳምንት ውስጥ ተሰናበትሁ፡፡ እንግዲህ ይሄን ለማን ያዋዩታል? ያ ነፃነት የሚባለው ትርጓሜው ምንድነው? እያልኩ ብቻዬን ማልጎምጎም ብቻ ሆነ!..." አንድ በሉ እንግዲህ፡፡...

"የቤተ-ክህነት ሰው እንደመሆኔ መጠን ህይወቴ ሰላምና ፀጥታ ማግኘት የሚችለው በማስተማር ላይ መሆን አለበት ብዬ አስብ ነበር፡፡ ግን አንዳንድ ጊዜ ደግሞ የደራሲነት ፍላጎት ይመጣብኛል፡፡ በህይወት ላይ የሚያሳዝን ወይም የሚያስደስት ነገር ስመለከት በፅሁፍ ለመግለጥ እሞክራለሁ፡፡ ግን የመንግስት ሹም እሆናለሁ ብዬ ከቶ አስቤ አላውቅም ነበር፡፡

"የኑሮ ፍላጎት አስገድዶኝ በአገር ግዛት ሚኒስቴር ከያዝኩት ስራ ፊትአውራሪ ደምሴ በግፍ ባባረሩኝ ጊዜ የደረሰብኝ የመንፈስ ቁስል በቶሎ ሊድን አልቻለም፡፡ አገር፣ ነፃነት፣ ትክክልነት፣ ወንድማማችነት፣ ፍትህ ... የሚባሉት እንደኔ ያሉትን ተራ ሰዎች ለመደለያና ለማጭበርበሪያ የተፈጠሩ ቃላት እንጂ ከእውነተኛ ህይወት ጋር ምንም የተያያዘ ነገር እንደሌላቸው ለመመልከት ስላጋጠመኝ ሁሉንም በኑፋቄ ዓይን ማየት ጀመርሁ፡፡ ይሄን ግብዝነት እንዴት ነው የማጋልጠው? እያለኩ በብርቱ አስብ ነበር፡፡ ስለዚህ አልፎ አልፎ በውስጠ ወይራ አማርኛ ምሬቴን የሚገልጥ የጋዜጣ አንቀፅ እየፃፍኩ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ማሳተም ጀመርሁ፡፡..." ይሉናል፡፡

አቶብርሃኑ ድንቄ የሚፅፉትን ጽሁፍ ውስጠ ወይራው የገባቸው "ብርሃኑ የምትለው ገብቶናል" እያሉ የጥቅሻ ምልክት ያሳዩዋቸው እንደነበርም ፅፈዋል፡፡

"በህዳር 21 ቀን በየዓመቱ የፅዮን በዓል በአባቴ ቤተ-ክርስቲያን በወጨጫ ማርያም ስለሚከበር አባቴ እጣነ ሞገር ቅኔ እንድቀኝ



ጠየቁኝ፡፡..." የተቀኙትን ከግዕዝ ወደ አማርኛ ተርጉመው እንዲህ አስፍረውታል፡፡

"በኢትዮጵያ የብዙ ሰዎችን ደም የጠጣው ጦርነት አለቀ፡፡
ግን ረቂቅና ብርቱ የሆነ የሠላም ጊዜ ጦርነት ተከቷል፡፡
በመሪያችን በኃይለስላሴ እናምናለን፡፡
አድሎአዊነትንና ጉቦኝነትን በሕግ ተቆጣጥሮ
ድል አድራጊነቱን አሁንም እንዲያረጋግጥ፡፡"

ይህ ቅኔ በአዲስ ዘመን ታትሞ ወጣ፡፡ ብርሃኑ ድንቄ ተደነቁበት፡፡ ጃንሆይ ጋዜጣ ሲያነቡ አዩትና ከ15 ቀን በኋላ አቶ ብርሃኑን ቤተ-መንግስት አስጠሯቸው፡፡ ኮሎኔል አብይ /በኋላ ጄኔራል/ ይዘው ወደ ጃንሆይ ቢሮ ማስገባት፡፡ አቶ ብርሃኑ በድንጋጤ በግንባራቸው ተደፍተው እጅ መንሳት፡፡

"ብርሃኑ ድንቄ አንተ ነህ?"

"አዎን ጃንሆይ"

ጠረጴዛው ላይ ያለውን ጋዜጣ አንስተው የግዕዙን ቅኔ ደግመው አነበቡት፡፡ "በአነባበባቸው እንደተመለከትኩት ግዕዝ ስለማይችሉ ብዙ ስህተት አድርገዋል" ይሉናል አቶ ብርሃኑ፡፡

"ቅኔ ማነው ያስተማረህ?"

"አባቴ ሊቀ ጠበብት ድንቄ የቅኔ መምህር ናቸው፡፡"

"ድንቄ የራጉኤሉ? ሰላባትህ ህሩይ ይነግረን ነበር፤ ህሩይን ታውቀዋለህ?"

"አዎ ጃንሆይ፤ ያባቴ ጓደኛ ነበሩ፡፡"

"በጣሊያን ጊዜ ምን ትሰራ ነበር?"

"አስተርጓሚ ነበርሁ ጃንሆይ፡፡"

"የኢጣሊያ ቋንቋ የት ተማርህ?"

"ከትምህርት ቤት አልሄድሁም፤ በራሴ ነው የተማርኩት፡፡"

"ከኢጣሊያ ወደ አማርኛ መፅሐፍ መተርጎም ትችላለህ?"

"አዎ ጃንሆይ፡፡"

"ይገርማል! አሁን ምን ትሰራለህ?"

"ስራ የለኝም ጃንሆይ፡፡"

በዚህ ጊዜ ጃንሆይ "አብይ ማስታወሻ ያዝ" ሲሉ አቶ ብርሃኑ እጅ ነስተው ይሰናበታሉ፡፡ "ሰዓቱ ትልቅ ትዝታ ነው ትቶልኝ ያለፈው ..." ይሉታል ይህንኑ ክስተት፡፡

ከቀናት በኋላ ከኮሎኔል አቢይ አበበ ቢሮ ተጠርተው ወደ ጽህፈት ሚኒስቴር የተፃፈ ደብዳቤ ተሰጣቸው፤ እንዲህ ይላል፤

"አቶ ብርሃኑ ድንቄ በግርማዊነታቸው መልካም ፈቃድ የወላሞ አውራጃ ግዛት ዋና ፀሐፊ ሆነው መሾማቸውን እንዳስታውቅዎ ስለታዘዝሁ ይህንኑ ለአገር ግዛት እንዲያስተላልፉላቸው በማክበር አሳስባለሁ፡፡"

በወቅቱ የሲዳሞና የወላሞ /በአሁኑ አጠራር የወላይታ/ ጠቅላይ ገዥ ሆነው የተሾሙት ራስ አበበ የነበሩ ሲሆን "አሳሽ" የሚባሉ ሹማምንት በስራቸው ሆነው የአካባቢውን ግዛቶች ያስሱ ነበር፡፡ "አሳሽ" በቀድሞው ልምድ የዋናው ሹም ወኪል ነው፡፡ ዋናው አዛዥ እስኪመጣ ያዛል፣ ያስገብራል፣ ያሥራል፣ ይፈታል፣ ይቀጣል...፡፡

በአዲሱ የአገር ግዛት ደንብ ግን ቀርቷል፡፡ ስለዚህ ራስ አበበ ከሕግ ውጪ "አሳሽ" ሾመዋል፡፡ የራስ አበበ የወላይታ አሣሽ ፊትአውራሪ ተሰማ ይባላሉ፡፡

አቶ ብርሃኑ ድንቄ ጉድ አዩ! ዘረፋ፣ ግድያ ... ግፍ ይፈፀማል ከሕግ ውጪ፡፡ እንደ አቶ ብርሃኑ አገላለፅ "በየቀኑ ሦስት ሰው ሳይሞት አይውልም" "የሚዘረፈውን ሐብት ለመገመት ያስቸግራል" ሲሉም ይነግሩናል፡፡

የአረመኔው የፊት አውራሪ ተሰማ ስም ሲጠራ የማይበረግግ የለም፡፡ አቶ ብርሃኑ የአውራጃ ግዛት ዋና ፀሐፊ ሲሆኑ፤ የወላይታ ገዥ ደግሞ /ጠቅላይ ገዥ አይደለም/ ፊትአውራሪ ግርማ ነበሩና "ይህን ሁሉ እየተመለከትኩ ዝም ብዬ መኖር አልችልም" ይሏቸዋል ለፊትአውራሪ ግርማ፡፡ "ታዲያ ምን ማድረግ ትችላለህ?"

"አንድ ረዥም ሪፖርት ለግርማዊነታቸው ልፃፍና ፈርመውበት ወደ አዲስ አበባ ይላክ፡፡"

"ብርሃኑ፤ እኔ አዋቂ ሰው መስለኸኝ ነበር፡፡ ለካ ልጅ ኖረሃል" ብለው ሳቁባቸው፡፡

አቶ ብርሃኑ ለወላይታ ባላባቶች ለፊታውራሪ ደስታ ጦና እና ለፊትአውራሪ ገብረስላሴ ጦና ወደ አዲስ አበባ የሚላክ ሰው እንዲያዘጋጁ በሚስጥር ነግረው ተከታዩን ደብዳቤ ላኩ፡፡

"ግርማዊነትዎ ከማይታወቅ ስፍራ ፈልገው ይህን ሹመት ስለሰጡኝ የማመሰግንበት ቃል ያጥረኛል፡፡ ግን ሹመት የተሰጠኝ ደመወዜን እየተቀበልሁ በምቾት ለመኖር ብቻ እንዳይደለ አውቃለሁ፡፡ ከፍ ያለ ኃላፊነት አለብኝ፡፡ እዚህ እወላሞ ከደረስሁ 30 የሚያህሉ ሰላማውያን ሰዎች በአርበኞች ተገደሉ፡፡ ዘረፋው በየቀኑ ይቀጥላል፡፡ አንድ መቶ ባላገሮችና ባላባቶች ፊት አውራሪ ተሠማ በተባለው በራስ አበበ አሳሽ እጅ ታስረው ይማቅቃሉ፡፡ የወላሞ ህዝብ የወተት ላሙን ሳይቀር ይገብራል፡፡ ያ አዲስ ዘመንና ነፃነት የምንለው ትርጓሜ የሌለው ባዶ ቃል ሆኗል፡፡ የግርማዊነትዎ ሹም መሆኔ ቀርቶ ተራ ሰው ብሆንም ይህን አሰቃቂ ግፍ ዝም ብል የኢትዮጵያ አምላክ ይፈርድብኛል፡፡ በዚህ



ጉዳይ ከአገረ ገዥው ከፊት አውራሪ ግርማ ጋር አልተስማማንም፡፡ ግን እኔ ህሊናዬ የሚያዘኝን አድርጌያለሁ፡፡ ይኸውም ለግርማዊነትዎ ማመልከት ነው፡፡ ግርማዊነትዎ ከማናችንም ይልቅ ታላቅ ኃላፊነት ስለተሰጠዎ ይህን ግፍ ከወላሞ ህዝብ እንዲያስወግዱለት ዝቅ ብዬ እለምናለሁ፡፡"

አቶ ብርሃኑ ይህን ጽፈው ከግንብ ጋር እንደመላተም ቢቆጥሩትም፤ አንድ ነገር በውስጣቸው ያውጠነጥኑ ነበር፡፡ "ጃንሆይ እንደ ሌሎች ሹሞቻቸው ስለ ፍትህ ስሜት የሌላቸው ሆነው ከተገኙ የመንግስት ስራ ለእኔ አይደለም!"....

መልሱ መጣ፡፡

"አቶ ብርሃኑ ድንቄ፤

ለግርማዊነታቸው የፃፉት ራፖር ደርሶ ተመልክተውታል፡፡ ጉዳዩን በጥንቃቄ ተከታትለው በማመልከትዎ ግርማዊነታቸው እንደተደሰቱ እገልፅልዎት ዘንድ አዘውኛል፡፡ ፊት አውራሪ ተሠማ በቶሎ ወደዚህ እንዲላክ ለራስ አበበ ትዕዛዝ ተላልፏል፡፡

ከሠላምታ ጋር፡፡"

የወላይታ ባላባቶች እነፊታውራሪ ደስታ ጦና የደብዳቤውን መልስ ሰምተው ኖሮ ወደ አቶ ብርሃኑ ሄደው "እንኳን ደስ ያለን!" ሲሉ "ምን ተገኘ ደግሞ" አቶ ብርሃኑ፡፡

"መቼም እናንተ አማራዎች ሁሉን ሚስጥር ማድረግ ትወዳላችሁ" በደስታ ተቃቀፉ፣ ተሳሳቁ፡፡ የወላይታ ህዝብ የወተት ላሙን መገበር ቀርቶ ቅንጣት ችግር እንድትደርስበት አይፈለግም፡፡ ነገር ግን ማን አለብኝ ባዮች ከሕግ ውጪ ይዘርፋሉ ይገድላሉ፡፡ ፊትአውራሪ ተሠማ ደነገጠ አሉ፡፡ ራስ አበበ ንዴታቸውን በውስጣቸው ይዘው ከይርጋለም ወደ ወላይታ ሰደ መጡ፡፡ ችሎት ሰይመው አቶ ብርሃኑን ጠሩ፡፡

"አሁን የጠራንህ በቅርብ ጊዜ እዚህ አገር ስለሞቱት ሰዎችና ስለተዘረፈው ንብረት አላፊው ፊትአውራሪ ተሠማ ነው ብለህ ለጃንሆይ ስለፃፍህ ሁለት ጥያቄዎች ልንጠይቅህ ነው፡፡

1ኛ. ምን ማስረጃ አለህ?

2ኛ. መጀመሪያ ለእኛ ሳታመለክት ለጃንሆይ የፃፍክበት ምክንያት ምንድነው?"

አቶ ብርሃኑ ይቀጥላሉ፤ "ክቡር ሆይ በዚህ ጉዳይ እኔ ከሳሽ ወይም ተከሳሽ አይደለሁም፡፡ ደረጃዬ ዝቅ ቢልም የመንግስት ሹም ነኝ፡፡ ስለዚህ ለግርማዊነታቸው በፃፍኩት ራፖር ምክንያት በችሎት ቆሜ መልስ እንድሰጥ የተጠየቅሁት ያለአግባብ ነው፡፡ በፅህፈት ቤት በኩል ነገሩን ክቡርነትዎ ለመረዳት ቢፈቅድ ለማብራራት ፈቃደኛ ነኝ፡፡"

"ሰው እየከሰሱ መልስ አልሰጥም ማለት የት አለ!"

"ክቡር ሆይ እኔ ማንንም አልከሰስሁም፡፡ እኔ የግል ዘመድ አልተገደለብኝም፡፡ እኔ የግል ሐብት አልተዘረፈብኝም፡፡ ሀብታቸውን የተቀሙት፣ ዘመዶቻቸው የተገደሉባቸው ሰዎች ዳኝነት በተሰጣቸው ጊዜ ክሳቸውን እንደሚያቀርቡ አልጠራጠርም፡፡ እኔ በሹመተ ኃላፊነቴ የፃፍኩት ሪፖርት እውነት ቢመስልዎ ተቀበሉት፡፡ እውነት ባይመስልዎ ሊተውት ይችላሉ፡፡"

"ቆይ የሚሆነውን እናስታውቅሃለን፡፡" ብለው ከችሎት ተነሱ፡፡ ፊት አውራሪ ተሠማ ወደ አዲስ አበባ መጥቶ ፍርድ ቤት ቀርቦ ታሠረ፡፡ ፍፃሜውም እዚያው ሆነ፡፡ የወላይታ ህዝብ "እፎይ" አለ፡፡ ራስ አበበ ፊትአውራሪ ተሠማን ለማዳን ያደረጉት ጥረት ሁሉ አልተሳካም፡፡ አቶ ብርሃኑ እንዲህ ይሉናል፤ "... እነራስ አበበን የመሳሰሉ ሹማምንቶቻቸውን ይቀየማሉ ሳይሉ አፄ ኃይለስላሴ ያሳዩት የፍትህ ሚዛንነት የወላሞን ህዝብ ፍርሃትና ስጋት ከሞላበት አኗኗር ነፃ አድርጎ ሰላምን ስለሰጠው በንጉሠነገስቱ ላይ ያለኝ እምነት ጠንካራ ሆነ፡፡ ..."

አቶ ብርሃኑ የወላይታ ተጠባባቂ ገዥ ከሆኑ በኋላ ወደ አዲስ አበባ የመመላለስ እድል ነበራቸውና ጃንሆይን ለማመስገን በሄዱ ጊዜ እንዲህ እንዳሏቸው ይነግሩናል፤ "እኛን አምነህ በቅንነት ከሰራህ ምንም ችግር አያገኝህም፡፡"

ከዚህም በላይ በተለያዩ የአስተዳደር ጉዳዮች ላይ አቶ ብርሃኑ ያቀረቧቸውን ምክሮች ጃንሆይ ተቀብለው ተግባራዊ ማድረጋቸውን ይገልፁልናል፡፡ ከአዲስ አበባ ወደ ወላይታ ሲመለሱ ሲሰናበቱ በቅርብ ጊዜ ለሌላ ስራ ወደ አዲስ አበባ እንደሚመለሱ ተነግሯቸው ነበርና የሄዱት፤ ወዲያው የወሊሶው ጀግና አርበኛ ደጃዝማች ገረሡ ዱኪ ተሾመው መጡ፡፡ አቶ ብርሃኑ ጥቂት አለማምደው ወደ አዲስ አበባ መጡ፡፡ ብላታ መርስኤ ሐዘን ወልደቂርቆስና አቶ ብርሃኑ ድንቄ "የታሪክና የቤተ-መንግስት ዜና ማሰናጃ" የሚባል መስሪያቤት እንዲያቋቁሙ ታዘዙ፡፡ ብላታ መርስኤ ሐዘን ዋና ዳይሬክተር፣ አቶ ብርሃኑ ዋና ፀሐፊ ሆነው ተሾሙ፡፡

ስራቸው የተቃና ይሆን ዘንድም የብርሐንና ሠላም ማተሚያ ቤት በእነሱ ስር እንዲተዳደር ሆነ፡፡ መስሪያ ቤቱ /የዱክ ቤት/ ቤተ-መንግስቱ ጊቢ ውስጥ ነበር፡፡

"... መስሪያ ቤቱ ጊቢ ውስጥ ስለሆነ ለጃንሆይ በማናቸውም የቅርብ አገልጋዮች አደረገን፡፡ እለት እለት ጃንሆይ የሚፈፅሟቸውን ዋና ዋና ታሪካዊ ጉዳዮች ከመከታተል በቀር አንዳንድ ጊዜ ደግሞ በአስተዳደር ወይም በፍርድ ያለአግባብ ተወሰኑ ስለሚባሉት ነገሮች አጥንተን ኀሳብ እንድናቀርብ እንታዘዝ ነበር" ይሉናል፡፡ "ብላታ መርስኤ ሐዘን በአገራችን ባህል ረገድ የተሟላ ድርጅት ያላቸው ሰው ናቸው..." ሲሉም ያደንቋቸዋል፡፡



በታሪክና ዜና ማሰናጃ ጽ/ቤት ሁለት ዓመት ከሰሩ በኋላ ጃንሆይ አቶ ብርሃኑን የጤና ጥበቃ ሚኒስትር ዋና ዳይሬክተር አድርገው ሾሟቸው፡፡ ብዙዎች ተገረሙ፡፡ ወይ ጤና! ጤና!

ጃንሆይ የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታልን አሰርተው ለስራ ማስኬጃ ገንዘብ ያጥራል፡፡ በዚህ ጊዜ ከመንግስት ንብረት ውስጥ ጥሩ ገቢ ያለውን ለሆስፒታሉ መርጃ መስጠት አስፈላጊ ሆኖ ተገኘ፡፡ ከጠላት የተወረሰው መካኒሳ የአልኮልና የአረቄ ፋብሪካ ለሆስፒታሉ እንዲተላለፍ አዘዙ፡፡ ነገር ግን የግል ተጠቃሚ /ባለአክሲዮን/ ከሌለ ስራው ሊቀዘቅዝ ስለሚችል በሚል 30 በመቶ ክፍያ ለቀድሞ አስተዳዳሪዎቹ ለፊትአውራሪ አስፋው፣ ለቀኝአዝማች ገ/ህን፣ ለአቶ በቀለ እንዲሰጥና የቀረው 70 በመቶ ለቅዱስ ጳውሎስ መተዳደሪያ እንዲሆን ተወስኖ ነበር፡፡ እነ አጅሬ ግን 4 ዓመት ሙሉ ቤሳቤስቲኒ ሳያቀምሱ እንደቆዩ የሚያረጋግጥ ሪፖርት ለአቶ ብርሃኑ ደረሳቸው፡፡ በዚህ ሚስጥራዊ ሪፖርት መነሻነት አቶ ብርሃኑ ያደረጉትን ከራሳቸው እንስማ፡፡ "... ከፋብሪካው መስሪያ ቤት ራሴ ሂጄ መዝገቦቹ የሚገኙበትን ክፍል አሳሸግሁት፡፡ እንዲሁም የየቀኑን የአልኮል "ፕሮዳክት" የሚቆጣጠሩ ኤንስፔክተሮች ሾምኩ፡፡ የሰጡት ሪፖርት እንደሚያመለክተው ሦስቱ ሰዎች የተጣራ 350,000.00 ብር ለግላቸው ተከፋፍለው ተገኙ፡፡... በዚህ ጊዜ እኔ በሦስቱ ሰዎች ላይ፤

1ኛ. የተካፈሉትን ገንዘብ ከነወለዱ እንዲከፍሉ፣

2ኛ. ከአስተዳዳሪነት ስራቸው እንዲወገዱ፣

3ኛ. እምነታቸውን አጉድለው ስለተገኙ በወንጀል እንዲቀጡ ስል ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ክስ አቀረብሁ፡፡..."

ወሬው ተነዛ፡፡ የጃንሆይ ታላላቅ ሹማምንት'ኮ ናቸው፡፡ ታማኝ፡፡ እናማ... ብዙ ዛቱ፣ ለህይወታቸው ፈርተው ጉዳዩን እንዲተውት አስፈራሩ ... ወዘተ፡፡ አልሆነም፡፡ በመጨረሻ ፊትአውራሪ አስፋው ለጃንሆይ ጉዳዩ በፍርድ ቤት ከሚታይ በኮሚሲዮን /በኮሚሽን ወይም በኮሚቴ/ እንዲታይ ጠየቀ፡፡

አቶ ብርሃኑ ተጠርተው ወደ ጃንሆይ ሄዱ፡፡ ፊትአውራሪ አስፋው ከጃንሆይ ጋር ነው፡፡ ጃንሆይ "ብርሃኑ ይሄውልህ በል ተናገር!" አሉት፡፡

"ጃንሆይ የመካኒሣ ፋብሪካ በትክክል እንዲሰራ ለማድረግ የቱን ያህል ችግር እንዳጋጠመን ብርሃኑ አያውቀውም፡፡ ... አሁን በድንገት ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ጃንሆይ ስራ ቢሉት የራሱን ስራ ሳያስተካክል የሚያደርገው ሁሉ የእኛን ስራ መበጥበጥ ብቻ ሆነ፡፡ ነገሩ ረዥም ስለሆነ ሁኔታውን በአጭር ጊዜ ለማስረዳት አልችልም፡፡ ስለዚህ ጃንሆይ በኮሚሲዮን እዛው እንዲመረመርና እርሱ ከፍርድ ቤት የጀመረው ክስ

እንዲቆም ያድርጉልን፡፡" ሲል፤ ሐቀኛው ተናጋሪ፤ "ጃንሆይ ሦስቱ የመካኒሣ ፋብሪካ አስተዳዳሪዎች እምነታቸውን በማጉደል ለቅዱስ ጳውሎስ የተሰጠውን ንብረት 4 ዓመት ሙሉ አንድ ቤሳ ሳያካፍሉ ለግላቸው ተጠቅመውበታል፡፡ ነገሩ ከፍርድ ቤት እንዳይቀርብና በኮሚሲዮን እንዲታይ የሚጠይቁት ለመጎተት እንዲመቻቸው ብቻ ነው፡፡ ጉዳዩን በትክክል አጣርቶ ለመወሰን ከፍርድ ቤት የተሻለ ሌላ አይገኝም፡፡"

በዚህ ጊዜ ጃንሆይ ፊታቸውን ወደ ፊትአውራሪ አስፋው ቀና አድርገው "200 ሺ ብር አሁን በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ስም እባንክ የምትከፍሉ ከሆነ ስለቀረው ሂሳብ ኮሚሲዮኑ እንዲያጣራ እናዛለን" አሉ፡፡

አስፋው ግን "ከየት አምጥተን ነው የምንከፍለው? እርስዎ ይከፍሉልናል?" ብሎ ጠየቀ፡፡ ሙልቅቅ ማለቱ ገረመኝ ይሉናል አቶ ብርሃኑ፡፡ ለካ... ስደት ላይ እያሉ ብዙዎች እየከዷቸው አስፍሽ ታማኝ ሆኖ አገልግሏቸው ስለነበር ነው የሚሞላቀቀው፡፡ ጉዳዩ ረጅም ጊዜ ቆዩና በመጨረሻ ፊታውራሪ አስፋው ንብረቱ በከፊል ተሽጦ እዳው ተከፍሎ፤ እሱም ከቤተ-መንግስት አስተዳዳሪነቱ ተገልሎ ወደ ግዞት፣ በቀለና ገ/ህን ደግሞ ረጅም ጊዜ በእስራት ካሳለፉ በኋላ ንብረታቸው ተሽጦ እዳው ተከፈለ፡፡

እንግዲህ የዚያን ጊዜ 350 ሺ ብር ያሁን 35 ሚሊዮን ሊባል ይችላል፡፡ እነበቄ ህዝብ ቢያልቅ ባያልቅ፣ ጤናው ቢጠበቅ ባይጠበቅ ምን አገባቸው?

"የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር አስተዳደር ንቅዘት /Corruption/" በሚል ንዑስ ርዕስ ስር ካሰፈሩት ታሪክ ውስጥ የሚከተለውን ጭብጥ እናገኛለን፡፡

"ኡንራ" የተባለ ኢንተርናሽናል ድርጅት ለጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ከ500 ሺ ብር በላይ ግምት ያላቸው ልዩ ልዩ እቃዎችና መድሐኒቶች ሰጥቶ ነበር፡፡ እነዚህ እቃዎችና መድሐኒቶች አንድ ትልቅ መጋዘን ውስጥ ታጉረው ቀኛዝማች ገ/ህን በተባለ ሰው ሲጠበቁ፣ ዝርዝር ለማሰናዳት ያሰበበት ሰው የለም፡፡ ቀኝአዝማች ገ/ህን የጤና ጥበቃ ሚኒስትር የነበረ የአቶ አበበ ዘመድ ነው፡፡ ይህንን ምክንያት በማድረግ እቃዎቹን አንድ በአንድ እያወጣ ሲሸጥ ስጋት አልነበረውም፡፡" ... ይሉናል አቶ ብርሃኑ ድንቄ፡፡

የዚህ ጉድ ሰፋ ያለ ነው፡፡ አንድ የአቶ ብርሀኑ ድንቄ ወዳጅ መንገድ ላይ ያገኛቸውና እንዲህ ይላቸዋል፤ "እንዲያው አደራህን የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ከሚሸጣቸው እቃዎች ለመግዛት ስለምፈልግ ለእቃ ሻጩ አደራ በልልኝ" ሕጋዊ መስሏቸው ነው፡፡ እንግዲህ አስቡት፤ ከተማው ሁሉ መግዛት ይፈልጋል፡፡ ርካሽ ነበር ማለት ነው?



አቶ ብርሃኑ "የእቃዎቹን አይነትና የሻጩን ማንነት እንደቀልድ አጣሩ፡፡ እንግዳ ናቸዋ፡፡ ለመስሪያቤቱም ለንግዱም እንግዳ ነበሩ፡፡ እና ... ሻጩ ቀኝአዝማች ነው፡፡ አቶ ብርሃኑ እንዲህ ይሉናል፤

"... በማግስቱ የ"ኡንራ"ን እቃ ቤት ለመጎብኘት እፈልጋለሁ ብዬ ቀኝአዝማች ገ/ህን ከስፍራው እንዲጠብቀኝ አዘዝሁ፡፡ መቸም እቃዎቹ በያሉበት ተበታትነው ያዩ ሰው ሁሉ እንደተጣሉ እንጂ ዋጋ እንዳለው ነገር ተጠብቀው ተቀምጠዋል ብሎ ለማመን አይችልም፡፡" ከጉብኝት መልስ አንድ ለየት ያለ እቃ አይተው መጡና አንድ ሰው ጠርተው የእቃውን አይነትና ሁኔታ ነግረው "ያንኑ እቃ የተጠየቀውን ዋጋ ከፍለህ ገዝተህ አምጣልኝ" ብለው ይልኩታል፡፡ ያው... የተለያየ እቃ ስለሆነ መድሐኒትም አለ፣ ሳሃንም አለ ... ወዘተ፡፡ መልዕክተኛው አይነቱ የተለየውን ሳህን በ5 ብር ገዝቶ መጣ፡፡ ከዚህ በላይ ማስረጃ ስለሌለ አቶ ብርሃኑ ምን እንዳደረጉ ከራሳቸው እንስማ፡፡ "... ወዲያው ከስራው አግዶ የመጋዘኑን ቁልፍ እንዲያስረክብ አዘዝሁት፡፡ እርሱ ግን አሻፈረኝ አለ፡፡"

አጣርቼ አልጨረስኩም ማለቱ ነው፡፡ ገና ብዙ እቃ አለ ያልተሸጠ፡፡ ወይም ዋናውን አልያዘም፡፡ የግሉ ይመስል መጋዘኔን አላስነካም! መሆኑ ነው፡፡ እሺ ከዚያስ ...?

"ነገሩን ወደ ፍርድ ቤት ለማቅረብ እየተዘጋጀሁ ሳለሁ ቀኝአዝማች ያርበኝነት ሽጉጡን ጠራርጎ ከቢሮዬ መጥቶ "ከዋናው ዳይሬክተር ጋር መነጋገር እፈልጋለሁ አገናኙኝ" ሲል ለልዩ ፀሐፊዬ ነገረው፡፡ ልዩ ፀሐፊዬ ግን ቀኝአዝማች ሽጉጥ መያዙን አረጋግጦ ስላስጠነቀቀኝ ቢሮዬ እርሱን ከመቀበሌ በፊት ለፖሊስ ስልክ ደወልሁ፡፡..."

ሲቪል ልብስ የለበሰ ፖሊስ መጥቶ ተዘጋጀ፡፡ ቀኝአዝማች ገባ፡፡ "እጆቹ ሲንቀጠቀጡ እመለከት ነበር፡፡ ጉሮሮውን "እህ" ብሎ በመጠራረግ "እኔ የመጣሁት... እኔ የመጣሁት..." እያለ ሽጉጡን ከኪሱ ለማውጣት ሲሞክር የፖሊስ መኮንኑ ከወደኋላው እጁን ከነሽጉጡ ለቀም አድርጎ መሣሪያውን ነጠቀው፡፡ ሽጉጡ ጎርሶ ተቀባብሎ ነበር፡፡ ግርማዊነታቸው በህይወቴ ላይ አደጋ ለማድረግ የሆነውን ዱለታ ሰምተው "እንኳን እግዚአብሔር ጠበቀህ!" ብለው አነጋገሩኝ፡፡ ነገሩም በጥንቃቄ እንዲመረመር አዘዙ፡፡" ይላሉ፡፡

ሁኔታው የጃንሆይን ማንነት በግልፅ ያሳያል፡፡ የዘመኑን ሕግም ጭምር፡፡ አንዳንድ ምሁራን እንደሚነግሩን በዚያ ዘመን ፍርድ ቤቱ የውሸት፣ የሚያዙበት ራሳቸው፣ ሁሉንም ነገር የሚቆርጡ የሚፈልጡ ጃንሆይ እንደነበሩ አድርገን እንድንስለው ይጋብዙናል፡፡ አሁን እያየን ካለነው ነገር ጋር ግን ይጣረሳል ልበል? በጥምረት ብዙ ነገር እያየን እንቀጥላለን፡፡

“በዚያው ሰሞን ብላታ ዘውዴ ከስራ ሚኒስትር ወደ ጤና ጥበቃ ሚኒስትር ተዛወሩ፡፡ የስራ ሚኒስትር በነበሩ ጊዜ ልዩ ልዩ ክስ ቀርቦባቸው ነበር፡፡ የተዛወሩበትም ምክንያት በዚሁ ነው፡፡ የስራ ሚኒስትር ለጉቦ በጣም ያመች ነበር፡፡ አንዳንድ የስራ ተቋራጮች ከትርፋቸው 30 በመቶ ወይም 40 በመቶ ጉቦ ለመስጠት አያመነቱም፡፡ ከዚህም የተነሳ ወደ ጤና ጥበቃ በመዛወራቸው አዝነዋል፡፡ ይልቁንም የስራ ተቋራጮችን እርዳታ በመተማመን አንድ ትልቅ ቤት ለመስራት ጀምረው ለመፈፀሚያ ገንዘብ ስለጎደላቸው የሚያደርጉትን አጥተው ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የገንዘብ ቤት ሹም ጋራ በመመሳጠርና በብድር 60ሺ ብር መውሰድ ግድ ሆኖባቸው ኖሯል፡፡ ይህን ገንዘብ የተበደሩበትን ፊርማ በምስጢር አግኝቼ ግምጃ ቤቱን ካሸግሁ በኋላ ገንዘቡ እንዲቆጠር አዘዝሁ፡፡”

ብላታ አበዱ፡፡ ጨሱ፡፡ ቤታቸው ሳያልቅ? ከስንቱ ተቋራጭ ስንት ነገር እንዳልቆረጡ ዛሬ የእሳቸው ቤት ተቋርጦ እንዴት ይቀራል? “አይደረግም!” አሉና ሄደው እሽጉን ቀደዱት፡፡ እሽ አቶ ብርሃኑ ምን አደረጉ በዚያ ሰዓት? “... ስለዚህ የሚከተለውን ፃፍሁላቸው፡፡”

“ክቡር ሆይ፤

በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ግምጃ ቤት የገንዘብ መጉደል መድረሱን ሰምቸ ሳጥኑን ራሴ አሽጌ፣ ዋናው ኢንስፔክተር፣ የፐርሶኔል ሹሙና የሆስፒታሎች አስተዳደር መሪ ሹም ባሉበት ገንዘብ እንዲቆጠር አዝዤ ነበር፡፡ ነገር ግን የገንዘቡ ቤት ሹም እሽጉን ክቡርነትዎ እንደቀደዱትና ወደፊትም ያለእርስዎ ፈቃድ እንዳይታሸግ መከልከልዎን ነገረኝ፡፡ ማመን ያስቸግረኛል፡፡ ስለዚህ ነገሩን በግልጥ ለመከታተል እንድችል በጉዳዩ አንድ መግለጫ ይሰጡኝ ዘንድ በማክበር እለምናለሁ”

ብላታ ተከታዩን ምላሽ ፃፉ፡፡

“ደብዳቤህ ደርሶኛል፡፡ ይህን የመሰለ ደብዳቤ ወደፊት ብትፅፍልኝ ከፍ ያለ የዲሲፒሊን ጉድለት ስለሆነ ቅጣት እንደሚያስከትል እግልፅልሃለሁ፡፡” አያችሁ! ዲሲፒሊን! ይሄን አይነት ዲሲፒሊን ነው ዛሬ ድረስ በጉያችን ሸጉጠን የምናቀነቅነው፡፡ አይ ሚኒስትር! አይ ኢትዮጵያ! የዋህ ቀኝአዝማች አትል፣ ፊትአውራሪ አትል፣ ሚኒስቴር አትል፣ ብላታ አትል፣ ዘበኛ አትል ... በቃ!

አቶ ብርሃኑ ይቀጥሉ፡፡ “ይህ እጅግ ጥሬ የሆነ የማናለብኝ አፃፃፋቸው እንደሚያስደነግጠኝና ራሴን ዝቅ አድርጌ በመለማመጥ እንደምተዳደር ብላታ ዘውዴ ጠብቀው ነበር፡፡ ደብዳቤያቸውን ሲፈርሙ “እምቢ ካለ እናሳየዋለን!” ብለው እንደተናገሩ ከዚያ የነበረ ሰው ነገረኝ፡፡ ግን ይህ ሊያስደነግጠኝ ቀርቶ የታጋይነት መንፈሴን ስለቀሰቀሰው የሚከተለውን ፃፍሁ፡፡

“ክቡር ሆይ



ደብዳቤ አትፃፍ የሚል ትዕዛዝ ሲደርሰኝ ይህ ለመጀመሪያ ጊዜ ነው፡፡ ጉዳዩ በጠቅላላ የሰውነትን ነፃነት የሚነካ ስለሆነ የመናገርና የመፃፍ መብቴን በቀላሉ ለማስረከብ ያስቸግረኛል፡፡ ስለዚህ ባለፈው ላቀረብሁት ጥያቄ መልስ እንዲሰጠኝ እንደገና ስጠይቅ በትዕግስትዎ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡”

ብላታ “አትፃፍልኝ ብዬ ካስጠነቀቅሁህ በኋላ ስለፃፍክልኝ 50 ብር ቀጥቼሃለሁ”

አቶ ብርሃኑ፤ “ቅጣቱን አልተቀበልሁትም፤ አሁንም ለመጀመሪያው ጥያቄዬ መልስ በመጠበቅ ላይ ነኝ”

“አትፃፍልኝ ብዬ ስለፃፍክ ቅጣቱን 100 ብር አድርጌዋለሁ”

“አትፃፍ” “እፅፋለሁ” ሲባባሉ ቅጣቱ 1 ሺ ብር ደረሰ፡፡ የወሩ መጨረሻ ሲደርስ አቶ ብርሃኑ የሚከፍላቸው ሹም ሲቀር ራሳቸው ሄደው ቆጥረው ወስደው ፈረሙ፡፡ “ሚኒስትሩ ለዋናው ዳይሬክተር ደሞዝ አትክፈሉ ብለውናል” ሙግት ሆነ፡፡ አቶ ብርሃኑ አልሰሟቸውም ይዘው ሄዱ፡፡ ብላታ አበዱ እንደገና፡፡ ስለዚህ “ከስራ አግጄሃለሁ!” ብለው ፃፉ፡፡ አቶ ብርሃኑም “የርስዎ ቅጥር ሠራተኛ አይደለሁም” የሚል መልስ ሰጥተው ስራቸውን ቀጠሉ፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ ሚኒስትሩ ብላታ 25 የጤና ጥበቃ የጥገና ክፍል ሠራተኞች በጥገና ክፍል ኃላፊው እየተመሩ የተጀመረውን ቤታቸውን እየሰሩላቸው መሆኑ ተደረሰበት፡፡ ደመወዝ የሚከፍላቸው ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ነው፡፡ እነሱ ግን የብላታን ቤት እየሰሩ ነው፡፡ ስራውን ትተውታል፡፡ እዚያኛው መስሪያ ቤት ...!

“.... እንደገና አቤቱታ ፃፍኩላቸው፡፡ በዚህ አኳኋን ነገሩ እየተካረረ ስለሄደ ሁኔታውን በሰፊ ጽሁፍ ለግርማዊነታቸው ማመልከት ግድ ሆነብኝ፡፡ ብላታም እንዲሁ አመልክተው ኖሮ ቢትወደድ መኮንን እንዳልካቸው፤ ራስ አበበ አረጋይ፣ ፀሐፌ ትዕዛዝ ወልደጊዮርጊስ ባሉበት ሁለታችንም ተጠርተን ከጃንሆይ ፊት ቀረብን፡፡” ይላሉ አቶ ብርሃኑ ድንቄ፡፡

ጃንሆይ፤ “ሁለታችሁም የፃፋችሁትን አቤቱታ ተመልክተናል፡፡ ዘውዴ ብርሃኑን ከስራው አግጄዋለሁ ያልከው አግባብ አይደለም፡፡ በእኛ የተሾመ ስለሆነ ጥፋቱ ሲረጋገጥ በእኛ ይሻራል፡፡ ለሁሉም በመኮንን ሰብሳቢነት ነገራችሁን እነሱ መርምረው እንዲያቀርቡልን አዘናል” ሁሉም ተሰናብተው ወጡ፡፡

ራስ ቢትወደድ መኮንን ጠቅላይ ሚኒስትር ናቸው፡፡ ፀሐፌ ትዕዛዝ ወልደጊዮርጊስ የጽህፈት ሚኒስትር ናቸው፡፡ ራስ አበበም የጦር ሚኒስትር መሆን የቻሉ ናቸው፡፡ በነገራችን ላይ በታሪክም በስፋት እንደሚታወቀው እነዚህ ሦስቱ ባለስልጣናት የወሰኑትን ውሣኔ ጃንሆይ ፈፅሞ “ውድቅ” አድርገውት አያውቁም፡፡ ኮሚሲዮኑ መቸም በአቶ ብርሃኑ ላይ ምን

እንደሚወስን ግልፅ ነው፡፡ በዚያን ጊዜ አቶ ብርሃኑ እንዲህ ሲሉ ይብሰለሰሉ ጀመር፡፡

"…. ብላታ ከጤና ጥበቃ ግምጃ ቤት 60 ሺ ብር ለመውሰዳቸው ፊርማቸው በእጄ አለ፡፡ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የዋናን ክፍል ሠራተኞች ቤታቸውን እንደሰሩ ግልፅ ነው፡፡ የግምጃ ቤቱን አሽጌ ለመቅደዳቸው አይከዱም፤ እንግዲህ ምን ብለው ሊፈርዱላቸው ይችላሉ?..."

የኮሚስዮኑ ውሣኔ ግልባጭ ለሁለቱ ተቃራኒ ወገኖች ይሰጥ ነበር፡፡ ነገር ግን አቶ ብርሃኑ አልደረሳቸውም፡፡ 7 ወራት አለፉ፡፡ ስለዚህ አቶ ብርሃኑ ለጃንሆይ ማመልከቻ አቀረቡ፡፡ ጃንሆይ ግራ ገብቷቸዋል፡፡ በመጨረሻ አቶ ብርሃኑ ተጠርተው ወደ ጃንሆይ ቀረቡ፡፡

"ጃንሆይ የኔ ማመልከቻ እንደደረሳቸው ጠርተው በስድብ ተለቀቁብኝ" ይሉናል፡፡ "ግድርድር! የማትረባ! እውነተኛ መስለሽን!..." እያሉ ሲናገሩ ፊታቸው በቁጣ ደም ለብሶ ይታይ ነበር፡፡ እንደዚህ ያለ የሚያስፈራራ ፊት ከዚህ ቀደም አላየሁም፡፡ "ምን አደረግሁ? ጥፋቴ ይነገረኝ! እያልኩ ብወተውት ማን ሰምቶኝ! ካባቸውን እያስተካከሉ በቁጣ ወደእኔ አፍጠው ስደባቸውን እንደመዓት ማውረድ ቀጠሉ፡፡ ራሴን መቆጣጠር አልቻልኩም፤ እንባዬ በዓይኖቸ ግጥም ብሎ በትክክል ለማየት ከለከለኝ፡፡ በተሰባበረ ቃል፤ "ጃንሆይ! ጃንሆይ ይስሙኝ፤ … ሹማምንቶችዎ የፍትህ ፀሮች መሆናቸውን የማያውቅ የለም፡፡ ግን ጃንሆይ ይህ ዘመዴ ነው፤ ይህ ጠላቴ ነው ሳይሉ ለህዝባቸው ትክክለኛ ፈታሂ ናቸው የሚል እምነትና ተስፋ ነበረኝ፡፡ ይህ እምነቴ ይኸው አሁን ተንኮታኮተ፡፡ ጃንሆይ እኔ የደሃ ልጅ ነኝ፡፡ በመቀማጠል አላደግሁም፡፡ ያለጫማ መሄድ ያለ አልጋ መተኛት እችላለሁ፡፡ ሹመት ቢቀርብኝ የሚጎድልብኝ ነገር የለም፡፡ ግን የሚያሳዝነኝ የጃንሆይ መንግስት ነው..." ብዬ ንግግሬን ከመጨረሴ በፊት እልህ ጉሮሮዬን እያነቀ ስላስቸገረኝ አቋርጬ ጥያቸው ከቢሮዋቸው ወጣሁ፡፡ ከዚያም በቀጥታ ወደቤቴ ሄጄ ልብሴን ከለዋወጥሁ በኋላ ወደ ወጨጫ መሬቴ ሄድሁ፡፡

ወደኋላ ተመልሼ ሳስበው በዚያን ጊዜ ጃንሆይ እኔን ለመቆጣት ምንም እንኳ በቂ ምክንያት ባይኖራቸውም ንግግሬን አቋርጬ ጥያቸው ስሄድ ያሳዩት ትዕግስት ያስደንቀኛል፡፡ ከቶ ልረሳው አልችልም" ይሉናል፡፡

በ5ኛው ቀን ተጠሩና ወደ ጃንሆይ ቀረቡ፡፡ እታሰር ይሆን? እያሉ በስጋት ቀረቡ፡፡

"ጃንሆይ ፈገግ ብለው ተቀበሉኝ፡፡ "ብርሃኑ" አሉኝ ጃንሆይ… "ያንተን ነገር ደህና አድርገን ነው ያጠናነው፡፡ ባደረግኸው ሁሉ ተደስተናል፡፡ ኮሚሲዮኑ በአንተ ላይ የወሰነው ያሳዝናል፡፡ ገልብጠነዋል!" አሉ ጃንሆይ፡፡ ይሄ ሁሉ ሲሆን አቶ ብርሃኑ ኮሚሲዮኑ ምን እንደወሰነ



በዝርዝር የሚያውቁት ጉዳይ አልነበረም፡፡ የኮሚሲዮኑ ውሣኔ ምን ቢሆን ጥሩ ነው?

"… ብርሃኑ ወደፊት በመንግስት መስሪያ ቤት እንዳይቀጠር" የሚል ነው፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትሩ አንዱ ነው፡፡ ተውን እንጂ እንዝረፍበት መሆኑ ነው፡፡ ከውሳኔው ጋር አብረው የተዘረዘሩ ክሶች "አለቃ አያከብርም፤ ዘላፊ ነው..." አይነት ጭብጥ ያላቸው ናቸው፡፡ ይሄን ወደእኛ ጨዋታ ስናመጣው ምን ማለት ነው? አትዝረፉ ይላል፤ የመንግስት ሠራተኞች የሚኒስትሮችን ህንፃ አይገንቡ ይላል፤ የእርዳታ እቃ አትሽጡ እያለ አስቸግሯል፤ ሐቀኛ ልሁን እያለ እያስቸገረ ነው … ማለት ነው፡፡

ወይ ብላታ! ንጉስ ቢሆኑማ በቃ…!

ቀደም ሲል በጃንሆይ "ልማታዊ ንግግር" ላይ እንዳየነው "የሚከብዳችሁ ነገር ካለ ጠቅላይ ሚኒስትር ሾመንላችኋል፡፡ እርሱም የሚከብደው ነገር ካለ ወደእኛ ያመጣዋል" ማለታቸው የሚታወስ ነው፡፡ ኧረ እሱ እቴ! ምንም የሚከብደው ነገር የለም፡፡ "አለመዝረፍ" ብቻ ነው የከበደው፡፡

አቶ ብርሃኑ ድንቁ በምዕራፍ 8 እንዲህ ሲሉ ይጠይቁናል፡፡ "… በዚያ ጊዜ ውስጥ በአገራችን የፖለቲካ ተመራማሪ ሰው እንዳለ ባውቅ ኖሮ አያሌ የማቀርብለት ጥያቄ ነበረኝ፡፡ እኔ ኃይለስላሴ እንደ ሹሞቻቸው ንቅዝ ናቸውን? ንቅዝ ካልሆኑ ለምን ንቅዝ የሆኑ ሹማምንቶች በዙሪያቸው ያስቀምጣሉ? በሌላው በኩል ደግሞ እነርሱን ቢያስወግዱ ንቅዝ ያልሆኑ ሹማምንቶች ከወዴት ይገኛሉ? ችግሩ ወጣት ወይም ሽማግሌ፤ የተማረ ወይም ያልተማረ አላለም፡፡ ሁሉም ያው ሆነው ተገኝተዋል..." የሚል ነው የጥያቄያቸው መነሻ፡፡

ለማንኛውም "አብሮ መስራትና አለቃን ማክበር የማያውቅ" በሚል ውሣኔ አቶ ብርሃኑን ውሣኔ አሳልፈውባቸው ነበር፡፡ ጃንሆይ ግን ባልተለመደ ሁኔታ ገለበጡት፡፡ በዚያ ዘመን አብሮ መስራት መገለጫው አብሮ መዝረፍ ነበር ማለት ነው፡፡ ዛሬስ? የሚለውን እያብሰለሰልን ወደ ሌላኛው "ጉድ" እናልፋለን፡፡

በነገራችን ላይ ብላታ ከዚያ በኋላ ከጤና ጥበቃ ሚኒስትርነታቸው ተነስተው ወደፓርላማ ተከተቱ፡፡ በዚህ መሰሉ ሂደት "የኢትዮጵያ ፓርላማ የግዞት ቤት ይባል ነበር" ይሉናል፡፡

አቶ ብርሃኑ ከዚያ በኋላ የአዲስ አበባ መዘጋጃ ቤት ዋና ዳይሬክተር ሆነው ተሾሙ፡፡ "የመዘጋጃ ቤት አስተዳደር የነቀዙ ከሚባሉት የመንግስት መስሪያቤቶች የመጀመሪያውን ደረጃ መያዝ ይችላል" ይላሉ አቶ ብርሃኑ፡፡

ፊትአውራሪ ደምሴ ወንድማቸውን የታክስ ክፍል ምክትል ዳይሬክተር አድርገው ከአዲስ አበባ ከተማ ነጋዴዎች ጉቧቸውን እየሰበሰቡ ነው፡፡

"በሕጉ መሠረት በአዲስ አበባ ከተማ ንግድ የሚያቋቁም ሰው ፈቃድ የሚሰጠው ለዚህ ስራ የተመረጡ ሁለት የመዘጋጃ ቤት ምክር ቤት አባሎች ከታክስ ክፍል ዳይሬክተር ጋር ሆነው ስለነጋዴው ችሎታና ስለንግዱ ስፋት ምርመራ ካደረጉና የዓመቱን ታክስ ከወሰኑ በኋላ ነው፡፡ የፊታውራሪ ደምሴ ወንድም ግን ጉቦ ተቀብሎ ማናቸውም ነጋዴ ታክስ ሳይከፍል እንዲሰራ ማድረግ ይችላል፡፡ ጉቦ ያልሰጡትን ነጋዴዎች ደግሞ ፈቃድ ቢኖራቸውም ምክንያት ፈልጎ ሱቃቸውን ይዘጋል፡፡" አቶ ገብረመስቀል ኦዳ የተባሉ ሐቀኛ ይህን ጉዳይ ተቃውመው "እሪ" ሲሉ ስለነበር ዋናው ፊታውራሪ ደምሴ ምክንያት እየፈለጉ መቀጫ እየጣሉባቸው የወር ደሞዝ ለዘመናት ወስደው አያውቁም፡፡

አቶ ብርሃኑና አቶ ገብረመስቀለ ኦዳ መተባበር ጀመሩ፡፡ እናም በአቶ ገብረመስቀልና በጉቦኛው በፊትአውራሪ ወንድም መካከል ለዘመናት የቆየውን ጭቅጭቅ ለማርገብ ኮሚሲዮን ተቋቋመ፡፡

ሰብሳቢ ራሳቸው ፊታውራሪ ሆነው ቁጭ አሉና የወንድማቸውንና የአቶ ገብረመስቀልን ውዝግብ ለመዳኘት ተዘጋጁ፡፡ (ፊትአውራሪ ከንቲባ ናቸው፡፡ ተጠባባቂ ወይም ምክትል) "እርስዎ ዳኛ ሆነው የወንድምዎን ነገር ለመፍረድ እንዴት ይችላሉ? ለምንስ ሌላ ኮሚሲዮን አይመረጥም?" አቶ ገብረመስቀል ኦዳ ናቸው ይሄን ያሉት፡፡ ፊትአውራሪ እንዲህ አሉ "አንተ ከሹመቴ ልትሽረኝ ነው? ይሄን ትተህ ነገርህን አመልክት!" አሉት በቁጣ፡፡ ሌላው የመዘጋጃ ቤት ሹማምንት በዝምታ ያዳምጣል፡፡ አቶ ብርሃኑ ቀጠሉ፤ "እኔ የአቶ ገብረመስቀልን አቤቱታ እደግፋለሁ፡፡ ... እርሰዎ ነገሩን ለማየት ከቆረጡ እ የኮሚሲዮኑ አባል ሆኜ ለመቀመጥ አልፈቅድም፡፡" አሉ፡፡

"በኮሚሲዮኑ መቀመጥ ካልፈለግህ መሄድ ትችላለህ፡፡" ሲሉ ፊታውራሪ አቶ ብርሃኑ ወጡ፡፡ አቶ ገብረመስቀልም ተከተሏቸውና ወጡ፡፡ ወዲያው ፊትአውራሪ የፈፀሟቸውን ሕገወጥ ስራዎች ሁለቱ ሐቀኞች በትብብር ሰበሰቡና ከመዘጋጃ ቤት አውጥተው ሌላ ቦታ አስቀመጡ፡፡

አቶ ብርሃኑ 10 ገጽ ደብዳቤ ለፊትአውራሪ ፃፉላቸው፡፡ "ደብዳቤው ፊትአውራሪ ሹመታቸውን ከለላ አድርገው የፈፀሟቸውን 12 ወንጀሎች ገልጦ ከነማስረጃዎቹ ይዘረዝራል፡፡ በመጨረሻው እንዲህ ሲል ይዘጋል፡፡

"እነዚህ ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን ወንጀሎች መስራትዎን ለማስረዳት ዝግጁ ነኝ፡፡ ይህንን እያደረጉ በዚህ የመንግስት ከፍተኛ ኃላፊነት እንዲቀጥሉ የሚገባ አይመስለኝም፡፡ በበኩሌ የማሳስብዎ ሳይዘገዩ



የስራ መሰናበቻዎን ለግርማዊነትዎ እንዲያቀርቡ ብቻ ነው፡፡ ነገር ግን ይህን ለማድረግ የማይፈቅዱ ከሆነ፤ የእኔን ደብዳቤ መቅረብ በ15ኛው ቀን ውስጥ ካላረጋገጡልኝ እኔ በቀጥታ ለግርማዊነታቸው ለማቅረብ እሞክራለሁ፡፡" ብለዋቸው እርፍ፡፡ ልብ አድርጉ፤ የእስካሁኖቹ ሁሉ ለበላይ አለቃ የሚፃፉ ናቸው፡፡ ቀጣዩን ሂደት እንደወረደ እንስማ፡፡

"ፊትአውራሪ ደምሴ ነገሩን ሲያጠኑና ሲያስጠኑ ከቆዩ በኋላ ሌላ መንገድ ስላላገኙለት ደብዳቤዩን ለግርማዊነታቸው ማቅረባቸውን ፃፉልኝ፡፡ የእርሳቸው ደብዳቤ በደረሠኝ በማግስቱ ከቤተ-መንግስት ተጠርቼ ከጃንሆይ ስገናኝ "ምንድነው ይህ የምታደርገው ነገር?" ብለው ጠየቁኝ፡፡ አደራረጉ በጣም እንግዳ ስለሆነባቸው ጃንሆይ ላቃቸውን አፍነው ተቆጣጥረው እንደያዙት ከከንፈሮቻቸው ላይ ይታይ ነበር፡፡ እኔም የሚከተለውን መልስ ሰጠሁ፡፡

"ጃንሆይ ይህን ደብዳቤ ጽፌ ለፊትአውራሪ ደምሴ የሰጠሁት ለፌዝ አይደለም፡፡ በጣም ተጨንቄ በቁም ነገር ካሰብሁበት በኋላ የወሰንሁት ነው፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ የግርማዊነትዎ "ሞዴል" ሆኖ መታየት ነበረባት፡፡ ግን የሚታየው ሁሉ ጉቦ፣ ማጭበርበርና ግፍ ነው፡፡ ይህንን ለማስወገድ ግርማዊነትዎን መርዳት ያለብኝ መስሎ ታይቶኛል፡፡"

"ታዲያ ወንጀሉን ለራሱ ጽፈህ ነው የምትሰጠው?" አሉ ጃንሆይ፡፡

"ጃንሆይ ፊታውራሪ በስተጀርባዬ ወጋኝ እንዲሉ አልፈልግም" አልኳቸው፡፡ ከዚህ በኋላ ጃንሆይ ነገሩን የሚመረምሩ ዳኞች እንሾማለን ብለው አሰናበቱኝ፡፡" ከጊዜ በኋላ ፊትአውራሪ ከሹመታቸው ተሻሩ፡፡ ባላምባራስ ማሕተመ ስላሴ ተጠባባቂ ከንቲባ ሆነው ጥቂት እንደሰሩ በመጨረሻ ደጃዝማች ከበደ ከንቲባ ሆነው ተሾሙ፡፡ አቶ ብርሃኑም ከዋና ዳይሬክተርነት ወደ ምክትል ከንቲባነት ተሸጋገሩ፡፡ እኛም የሙስናን ጉዳይ በጨረታ በኩል ወደማየት እንሻገራለን፡፡

ደጃዝማች ከበደ ለጃንሆይ ከአልጋወራሽነታቸው ጀምሮ ታማኝ ሆነው ያገለገሏቸው ወዳጅ ናቸው፡፡

አቶ ብርሃኑ ድንቄ ታመው ለቀናት እቤት ተኙ፡፡ በዚህ ጊዜ ስለ ገፈርሳ ውሃ ግድብና የቧንቧ ዝርጋታ ጨረታ ወጣ፡፡ በጨረታው የፈረንሣይ፣ የጣሊያን፣ የጀርመን፣ የእንግሊዝ ኩባንያዎች ተሳታፊ ናቸው፡፡ ስራው 1,000,000 ብር የሚገመት ነው፡፡

"ዴግሬሞን" የተባለው የፈረንሣይ ኩባንያ ማሸነፍ ነበረበት፡፡ 100 ሺ ብር ቅናሽ ነበረው፡፡ ደጃዝማች ግን "ጣልያንዬ!" አሉ፡፡ ምክንያታቸውም ዴግሬሞን የተባለው የፈረንሣይ ኩባንያ ያቀረበው የቧንቧ አይነት አሰራሩ WELDED ስለሆነ "ቮልካኒክ" በሆነ መሬት ላይ ለመዘርጋት አያስተማምንም፡፡ ነገር ግን የኢጣሊያው ኩባንያ ያቀረበው ምንም እንኳ ዋጋው ከፍተኛ ቢሆን፤ አሰራሩ SEAMLESS በመሆኑ ለእኛ

አገር መሬት ተስማሚ ነው፡፡ ስለዚህ የእርሱን ጨረታ ተቀብለናል” የሚል ነው፡፡

ጨረታው ተዘጋጅቶ አቶ ብርሃኑ እንዲፈርሙበት ወደቤታቸው ተላከ፡፡ ግራ የሚያጋባ ልዩነት ስላዩ ከመፈረማቸው በፊት የዧንዧዎቹን ልዩነት ለማጣራት ፈለጉ፡፡ እነደጃዝማች ቸኩለዋል፡፡ የኢጣሊያ ኩባንያ ኮንትራቱን ሲያገኝ ደጃዝማች ከቤ 60 ሺ ብር፣ ለመዘጋጃ ቤት ሹማመንቶችና መሐነዲሶች 20 ሺ ብር፣ ሌላውን ለግብዣ አቅደው ጨርሰዋል፡፡

ደጃዝማች ከቤ ደወሉ ወደ አቶ ብርሃኑ “ቶሎ ፈርመህ ላክ እንጂ!”

“ቆይ የማጣራው ነገር አለ፡፡”

“አንተ መቼም ቄንጥ ማውጣት ትወዳለህ፡፡ ለመፈረም ያልፈለግህ እንደሆነ ላክልኝና እኔ እፈርመዋለሁ” አሉ፡፡

“ደጃዝማች ይህ የቄንጥ ነገር አይደለም የዋጋ ልዩነት ነገር ነው፡፡ ይህ ከመጣራቱ በፊት እርስዎም ቢሆኑ እንዲፈርሙበት አልመክርዎም፡፡”

ደጃዝማች በቁጣ “አንተ ታዘኛለህ? ይልቁንስ ቶሎ ወረቀቶችን ላክልኝ” አሉና ስልኩን ጠረቀሙት፡፡ ወዲያው ወረቀቶችን ለመውሰድ አቶ ተፈራ የተባለውን ልዩ ፀሐፊያቸውን ላኩ፡፡ የዚህን ታሪክ ሙሉውን እንደወረደ እንየው፡፡

“እርሱ ወረቀቶቹን ይዞ ከቤቴ ወጣ ሲለ ወደ ቤተ-መንግስት ስልክ ደውዬ አድማሱ ረታን “ለሚያስቸኩል ጉዳይ ከጃንሆይ በስልክ መነጋገር እፈልጋለሁ” አልሁት፡፡ በአንድ ደቂቃ ውስጥ ጃንሆይ ከስልክ ስለቀረቡ የሚከተለውን አመለከትሁ፡፡

“ጃንሆይ በድፍረቴ ይቅርታ ይደረግልኝ፡፡ እኔ በጤና ጉድለት ከቤቴ ተኝቻለሁ፡፡ ስለገፈርሳ ውሃ ግድብ ደጀዝማች ከበደ አሁን ኮንትራት ሊፈርሙ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት የመዘጋጃ ቤት ብዙ ገንዘብ ይከስራል፡፡ እኔ ምክር ብሰጣቸው ደ ዝማች መስማት አልፈለጉም፡፡ ነገ እኔ ራሴ ቀርቤ በሰፊው እስካስረዳ ድ ስ ኮንትራቱ እንዳይፈረም ጃንሆይ ያዙልኝ ዘንድ እለምናለሁ፡፡”

ጃንሆይ፤ “መልካም ነገ መጥተህ እሱ ባለበት አስረዳ፡፡” ካሉኝ በኋላ ለደጃዝማች ወዲያው ስልክ ተደውሎ ኮንትራቱን እንዳይፈርሙ ተከለከሉ፡፡ ሁኔታው አምስት ደቂቃ በማይሞላ ጊዜ ውስጥ ስለተፈፀመ በዚያን ጊዜ ደጃዝማችን ያዩ ሰው እንደነገረኝ፤ ከነጭ ሰማይ ላይ በድንገት ሳይጠብቁት ነጎድጓድ እንደወረደባቸው ሁሉ ክው ብለው ነበር፡፡ እየደጋገሙ የተናገሩት ቃል “ምን ያለ ሰይጣን ነው! ምን ያለ ሠይጣን ነው! የሚል ብቻ ነበር፡፡ ኮንትራቱን ለመፈራረም መጥተው የነበሩት የኢጣሊያ ኩባንያ ወኪሎችና የማዘጋጃ ቤት መሐንዲሶች ከቢሮዋቸው



እንዳሉ ምክንያቱን ሳይገልፁላቸው ትተዋቸው በችኮላ ወደ ቤተ-መንግስት ሄዱ፡፡

ይህን አሳፋሪ ሁኔታ ለማስወገድ ኮንትራቱ እንዲፈረም ይፈቅዱ ዘንድ ጃንሆይን ለማግባባት በብርቱ ተጣጥረው ነበር፡፡ ጃንሆይ ግን “ብርሃኑ ቀርቦ የተቃወመበት ሳይሰማ ኮንትራቱ አይፈረምም፡፡” ብለው በውሣኔያቸው ፀኑ፡፡ ደጃዝማች ቤተ-መንግስት እንዳሉ ለፀሐፊያቸው ደውለው ባለጉዳዮቹ የኢጣሊያ ኩባንያ ወኪሎችና ለሴሪሞኒ የተሰበሰቡት ሰዎች፤ ፎቶግራፍ አንሺዎች ሳይቀሩ እንዲሰናበቱ አደረጉ፡፡ ምክንያቱን ግን አልገለፁም፡፡ በጣም የሚያሳፍር ሆኖ አገኙት፡፡

በማግስቱ ደጃዝማች ከበደ እና እኔ ከጃንሆይ ፊት ቀርበን የተደራጀው ኮንትራት፤

ሀ. የጨረታውን ስርዓት ስላልተከተለ፣

ለ. ማዘጋጃ ቤትን ብዙ ሺ ብር ስለሚያከስር፣

ሐ. የኢጣሊያ መሐንዲሶች የአገራቸውን ኩባንያ ለመደገፍ ስለዧንዧ አሰራር የሰጡት ኀሳብ ትክክል ስላይደለ መጣራት አለበት ስል መቃወሚያዬን በዝርዝር አቀርባለሁ፡፡

ደጃዝማች በበኩላቸው “ኮንትራቱን ከመፈረም የሚያዘገይ በቂ ምክንያት የለም” ሲሉ የኔን ኀሳብ አስተባበሉ፡፡ ጃንሆይ የሁለታችንም አቋም ከሰሙ በኋላ፤

1. ደጃዝማች ከበደ /ሰብሳቢ/
2. ባላምባራስ ማሕተመ ስላሴ
3. ደጃዝማች ክፍሌ
4. አቶ ምናሴ
5. አቶ ብርሃኑ ድንቄ
6. Mr. Clark /አሜሪካዊ የኢትዮጵያ ባንክ አዛዥ/
7. Mr Pery /ካናዳዊ የገንዘብ ሚኒስትር አማካሪ/
8. ባላምባራስ እማኙ
9. Dr Naudeha /የአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት አማካሪ/

በኮሚሲዮን አይተውና ነገሩን አብራርተው እንዲያቀርቡላቸው አዘዙ፡፡ ይህ ትዕዛዝ በተሰጠበት እለት የተባሉት ሰዎች ተሰብስበው አንድ ሰዓት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ተነጋግረው ቃላቸውን ሰጡ፡፡ ሚስተር ፔሪ እና እኔ ብቻ በኀሳብ ስንለይ የቀሩት በሙሉ ደጃዝማችን ደገፉ፡፡ በዚያን ጊዜ በእያንዳንዱ የኮሚሲዮን አባል አእምሮ የሚመላለሰው አሳብ፤ “ብርሃኑ ማነው? ምንስ ማድረግ ይችላል?” የሚል እንጂ የገፈርሣ ውሃ ጉዳይ አልነበረም፡፡ Mr Pery የሰጠው አስተያየት በጣም ያስደንቃል፡፡ ይህ ሰው ካናዳዊ ነው፡፡ ኢኮኖሚስት በመሆኑ የገንዘብ ሚኒስትር በአማካሪነት ቀጥሮት ለረጅም ጊዜ ሰርቷል፡፡ ሰውየው በጣም ትሁት ነው፡፡ ግን

በአማካሪነት ስለሚሰጠው አስተያየት "ኀሳቤን እገሌ ይወደዋል፣ ወይም እገሌ ይጠላዋል" ብሎ የሰውን ዓይን የማይመለከት፣ በኢትዮጵያ ካሉ የውጭ አገር አማካሪዎች እርሱ ብቻ ነበር ይባላል፡፡ በዚህ ጉዳይ የሰጠው አስተያየት በአጭሩ እንደሚከተለው ነው፡፡

"እኔ የአቶ ብርሃኑ ድንቄን ኀሳብ በሙሉ እደግፋለሁ፡፡ እዚህ አሁን የተሰበሰብነው ሁሉ አድሚኒስትሬተሮች እንደመሆናችን መጠን ገንዘብ እንዲቆጠብና በማይበቃ ምክንያት እንዳይጠፋ መጠንቀቅ ተግባራችን ነው፡፡ በሁለቱ የቧንቧ አይነቶች ዋጋ መካከለ በሺ የሚቆጠር የገንዘብ ልዩነት አለ፡፡ አንዱ የቧንቧ አይነት ከሌላው በማናቸውም እንደሚበልጥ እርግጠኛ ማስረጃ ሳይጨበጥ ከፍተኛ ዋጋ እንዲከፈል አይገባም፡፡" መቼም በድምፅ ብልጫ ደጃዝማች ከበደ አሸንፈዋል፡፡ ግን ክርክሩን እንዲሁ በቀላሉ ለመተው አልተዘጋጀሁም ነበር፡፡

ስለዚህ ቃለ-ጉባኤ ተዘጋጅቶ ለፊርማ ሲቀርብ "አቶ ብርሃኑ ድንቄና ሚስተር ፔሪ አልተስማሙም" ከሚል በቀር፣ ያልተስማማንበትን ምክንያት አለመገለጡን ተመልክቼ እንደገና ተብራርቶ እንዲፃፍ ጠየቅሁ፡፡ ደጃዝማች ግን "ባይፈርም ይተወው!" ብለው አስቀድመው ያዘጋጁትን ቃለ-ጉባኤ እኔ ሳልፈርምበት ለጃንሆይ አቀረቡ፡፡

መቼም በማሸነፋቸው የተሰማቸው ደስታ ሊዘረዘር አይቻልም፡፡ አያሌ ወዳጆቻቸውን እየጨበጡ እያቀፉ የደስታቸው ተካፋይ መሆናቸውን ገለጡላቸው፡፡ ማታውን የኢጣሊያ ኩባንያ እንደራሴ በራስ ሆቴል ምርጥ ለሆኑ ሰዎች ራት ጋበዘ፡፡

በዚህ ጊዜ እኔ ደጃዝማች ከበደን በግል ከስሼ ለጃንሆይ አቤቱታ ፃፍሁ፡፡

አቤቱታዬ፣ "ደጃዝማች ከበደ የአዲስ አበባ መዘጋጃ ቤት ከንቲባ መሆናቸውን ረስተው የኢጣሊያ ኩባንያ እንደራሴ የሆኑ ይመስላል፡፡" የሚል ብርቱ ክስ የያዘ ስለሆነ እንደገና ጃንሆይ ሁለታችንንም አቀረቡን፡፡ በዚህ ጊዜ ደግሞ በተጋነነ ቃል የከንቲባው ስራ የሚያጠራጥር ነው ብዬ ተናገርሁ፡፡ በቃለ-ጉባኤውም ውስጥ የእኔና የሚስተር ፔሪ አስተያየት ተብራርቶ ያልተፃፈበትን ምክንያት ጠየቅሁ፡፡ ደጃዝማች ለማልቀስ የተዘጋጀ ፊት ነበራቸው፡፡ እንደሚገባም ራሳቸውን ለመከላከል አልቻሉም፡፡

በዚያ ሰዓት ጃንሆይ ወደእኔ ፊታቸውን ቀና አድርገው፣ "አሁን ምን ይሁን ነው የምትለው?" አሉኝ፡፡ እኔም፣

"ጃንሆይ በለንደን "ስኩል ኦፍ ቴክኖሎጂ" የተባለ አንድ ትምህርት ቤት አለ፡፡ ይህም ትምህርት ቤት የንግድ ጥቅም የለውም፡፡ ግን ስለአንዳንድ እቃዎች አሰራር በቴክኖሎጂ ረገድ ኢንፎርሜሽን ሲጠየቅ የተጣራ መልስ ይሰጣል፡፡ አሁን እኔ የማሳስበው ለዚህ ትምህርት ቤት



ቴሌግራም አድርገን SEAMLESS እና WELDED በሆነ የቧንቧ አሰራር ልዩነት እንዳለው ጠይቀን ከዚህ ትምህርት ቤት በምናገኘው መልስ መሠረት ነገሩን እንድንወስን ብቻ ነው፡፡"

ጃንሆይ፣ "መልካም ነው!" ብለው የውጪ ጉዳይ ሚኒስትሩ አቶ አክሊሉ ሐብተወልድ ቴሌግራሙን እንዲያስተላልፉ አዘዙ፡፡ ከሁለት ቀን በኋላ የቴሌግራሙ መልስ መጣ፡፡"

እነ አቶ ብርሃኑ እንዳሉት WELDED "በማናቸውም የመሬት አይነት ያለአንዳች ስጋት ሊዘረጋ ይችላል" የሚል መልስ ሲሆን፣ ከSEAMLESS እንደሚበልጥም ተረጋገጠ፡፡

"ግርማዊነታቸው ቁጣና ሐዘን በተቀላቀለበት መልክ ደጃዝማች ከበደን ገላምጠው "ይገርማል እኮ!" አሉ፡፡ ከዚህ ሌላ አንድ ቃል ሳይጨምሩ የልፍኝ አስከልካዩ ከግርማዊነታቸው ጽ/ቤት እንድንወጣ የእጅ ምልክት አሳየን፡፡ በዚያን ጊዜ ደጃዝማች ከበደ የተከናነቡት ሐፍረት እንደ ሐምሌ ጥቁር ደመና በፊታቸው አካባቢ ተንጠልጥሎ ይታይ ነበር፡፡ ስለዚህ የገፈርሳ ውሃ ግድብና የቧንቧ ስራ እርሳቸው እንደተመኙት ሳይሆን፣ በጨረታ ላሸነፈው ለፈረንሣይ ኩባንያ ለዴግሬሞን ተሰጠ፡፡ ማዘጋጃ ቤትም ብዙ ሺ ብር አዳነ፡፡ ቀጥሎም ከጥቂት ጊዜ በኋላ ራሳቸው ደጃዝማች ከመዘጋጃ ቤት ስራቸው ኃላፊነት ተራገፉ..."

አቶ ብርሃኑ ድንቄ በምዕራፍ 9 እንዲህ ይሉናል፡፡

"አንዳንድ ሹማምንቶች በንቅዘት ምክንያት ከስራ ሲወገዱ፣ ወይም ከሹመት ደረጃቸው ዝቅ ሲሉ የሚያስደስተኝ የነርሱ ሐዘን ወይም እኔ ከእነርሱ ጋር ታግዬ ማሸነፌ አይደለም፡፡ ነገር ግን፣

ሀ. የእነርሱን እድል በመመልከት ሌሎች ይታረማሉ፣

ለ. በእነርሱ ምክንያት የተበደሉ ወይም የተገፉ ሰዎች ነፃነት ይሰማቸዋል፣

ሐ. የፍትህ መተካከል ቀስ በቀስ እያለ በንጉሠነገስቱ መንግስት አስተዳደር ይዛመታል የሚል ጠንካራ ተስፋ ነበረኝ፡፡

የሆነ ሆኖ የግል ጠላቶች ከማብዛቴ በቀር ይህን ተስፋዬን የሚደግፍ አንዳች ምልክት አይታየኝም ነበር፡፡ ..." በማለት በተሻሩት ደጃዝማች ምትክ ቀደም ሲል ያየናቸው የጤና ጥበቃው ሚኒስትር ብላታ በመተካታቸው ማዘናቸውን ይገልፁልናል፡፡ (የጃንሆይ ትልቁ ጥፋትም ይሄ ነበር) ስለዚህም ወደ ጃንሆይ ሄደው አለመደሰታቸውን ተናገሩ፡፡ በዚህ ጊዜ ጃንሆይ አቶ ብርሃኑ ስላደረጉት ብርቱ ትግል አመስግነው እንዲህ አሉ፡፡

"ብርሃኑ አንድ ህዝብን ማስተዳደር የበጎች መንጋ እንደመጠበቅ ቀላል ነገር አይደለም፡፡ እግዚአብሔር ሲያስችለን ብቻ የሚቻለውን እናደርጋለን፡፡" አሏቸው፡፡ የመልሶ መሾሙ ሁኔታ አንድ ራሱን የቻለ

ፖለቲካዊ ዱለታ በውስጡ ስለነበረው ይህን ከመፅሐፉ ማግኘት ትችላላችሁ፡፡ ብቻ ጃንሆይ አጣብቂኝ ውስጥ ነበሩ፡፡

አቶ ብርሃኑና ብላታ ደግሞ በአንድ ክፍል አብረው መስራት የማይታሰብ ነበር፡፡ በስምንተኛው ቀን ጃንሆይ አቶ ብርሃኑን ጠርተው፤ "እውጭ አገር ብንልክህ ትወዳለህ?" ብለው ጠየቁ፡፡ አቶ ብርሃኑ ፈቃደኝነታቸውን ገልፀው የመጀመሪያውን የዲፕሎማትነት ስራ ለሦስት ዓመት ያህል በዋሽንግተንና በሳዑዲ /ጅዳ/ አገልግለው ከ3 ዓመት በኋላ ወደ አዲስ አበባ እንዲመለሱ ተደረገ፡፡ በየጊዜውም ወደ አዲስ አበባ እየመጡ ከጃንሆይ ጋር ይገናኙ ነበር፡፡

መጥተውም የፖስታ፣ የቴሌግራፍና ቴሌፎን /ቴ.ቴ/ ምክትል ሚኒስትር ሆነው ተሾሙ፡፡ በወቅቱ ዋናው ሚኒስትር ቢትወደድ መንገሻ ነበሩ፡፡ እኝህ ሰው "ቤተ-መንግስቱ የእኛ ነው" የሚሉ አባታቸው የዘውዲቱ ባል የነበሩ የተኮፈሱ ሰው እንደነበሩ ይነግሩናል፡፡ ቢትወደድ መንገሻ አንዳንዴ ያማቸው ስለነበር ቤት ነው የሚውሉት፡፡ እንደ ሚኒስትር ሆኖ የሚሰራውና የማያዘው ልዩ ፀሐፊያቸው አቶ ታደሰ ነው፡፡ እየሰማችሁ ነው? ሚኒስትሩ ሌላ ሚኒስትር ቀጥረዋል፡፡ እሳቸው እርፍ ብለው በወኪል እያሰሩ ነው፡፡ አቶ ብርሃኑ እንዲህ ይሉናል፤ "... ስለዚህ ከደንበኛ ደመወዙ በቀር ልዩ አበል ተመድቦለታል፡፡ ነፃ የቴሌፎን አገልግሎት ከቤቱ ገብቶለታል፡፡ ለተመደበለት መኪና ትርፍ ቤንዚል ይሰጠዋል፡፡ ይህ ትክክል መስሎ ስላልታየኝ ቢትወደድ ከመስሪያ ቤት ባልነበሩበት ጊዜ እንዲሰረዝ ትዕዛዝ ፈርሜ አስተላለፍሁ፡፡ ቢትወደድ ግን ለእረፍት ከሄዱበት በፍጥነት ተመልሰው እኔ የሰጠሁትን ትእዛዝ የሚያፈርስ ደብዳቤ ብቻ ፈርመው ወደ እረፍታቸው ተመለሱ፡፡"

እሺ ከዚያስ? "... ስለዚህ የሚከተለውን ልፅፍላቸው ግድ ሆነብኝ" ይሉናል አቶ ብርሃኑ፡፡ እኛም ምን ብለው ፃፉላቸው? ብለን እንጠይቃለን በጋራ፡፡ ይሄው፡፡

"ክቡር ሆይ

ይህን መስሪያ ቤት ክቡርነትዎ እንዲያስተዳድሩ ኃላፊነት ሲሰጥዎ በነጋሪት ጋዜጣ ስለሚንስትሮች ስልጣን የወጣውን ሕግ እንደሚያከብሩ በመተማመን መሆኑን አልጠራጠርም፡፡ የፖስታ ቴ.ቴ ሚኒስትር የመንግስት መስሪያ ቤት እንጂ የክቡርነትዎ ማዕድ ቤት እንዳልሆነ ማስገንዘብ ያስፈልገኝ አይመስለኝም፡፡ ልዩ ፀሐፊዎ ከተወሰነለት ደመወዝ በቀር ልዩ አበልና ነፃ የቴሌፎን አገልግሎት እንዲሰጠው የበጀት ስርዓቱ አይፈቅድም፡፡ ልዩ ፀሐፊዎ እርስዎ በሌሉበት ሚኒስትር እንዲሆን ሕግ አይፈቅድለትም፡፡ እርስዎ በሌሉ ጊዜ ምክትል ሚኒስትሩ አለ፡፡ ምክትል ሚኒስትሩ በሌሉ ጊዜ ዋና ዳይሬክተር አለ፡፡ ይህን ሁሉ አልፈው ልዩ ፀሐፊውን የሚወክሉበት ምክንያት አይገባኝም፡፡



የንጉሠነገስቱ መንግስት አስተዳደር አልተስማማዎት እንደሆነ የተሻለ መንገድ ስለሌለ ቢሰናበቱ መልካም ይመስለኛል"

"ከዚህ በላይ የተፃፈው ደብዳቤ ጠንካራ እንደሆነ ይሰማኛል፡፡ ግን የቢትወደድ አደራረግ ለእኔ ጠንካራ ሆኖ ነው ያገኘሁት፡፡ ከሁሉ አስቀድሞ አሰራራቸው ከሕግ ውጪ እንደነበረ ሳያውቁት አይቀርም፡፡ ቀጥሎም የእኔን ትዕዛዝ ከመሻራቸው በፊት ጠርተው እንኳ ሊጠይቁኝ አልፈቀዱም፡፡ ስለዚህ ለዘብ ያለ አቤቱታ እንደማይበግራቸው ተረድቼ ሆነ ብዬ ነው ያጠነከርኩት፡፡" ይላሉ አቶ ብርሃኑ፡፡ እኛም "ኸረ እንኳን አጠነከሩት!" እንላቸዋለን በጋራ፡፡

ቢትወደድ ደብዳቤው ሲደርሳቸው በንዴት ጨሱ! አይገልፀውም፡፡ በቀጥታ ወደቤተ-መንግስት ሄደው ለጃንሆይ "ጃንሆይ፤ ምን በደልኩዎና ነው ይህን ሰው ልከው የሚያዋርዱኝ?!" በማለት ደብዳቤውን አሳዩዋቸው፡፡ ጃንሆይ አነበቡትና ወዲያው፤ "ታዲያ አንተ ሕጉን እየጣስህ ስትሰራ ምን ያድርግህ? ውሸት ነው ትላለህ ብርሃኑ በደብዳቤው የፃፈው?" ሲሉ ቢትወደድ መልስ አልነበራቸውም፡፡ ስለዚህ በስምንተኛው ቀን ከስራቸው ተነሱ፡፡

አቶ ብርሃኑ እንዲህ ይላሉ፤ "በዚህ አደራረግ ከቢትወደድና ከተከታዮቻቸው ይልቅ የደነገጥሁ እኔ ነኝ፡፡ ጃንሆይ እንደዚህ ፍጡን የሆነ እርምጃ ይወስዳሉ ብዬ በፍፁም አልጠበቅሁም ነበር"

"በፖስታ ቴ.ቴ ሚኒስቴር በተጠባባቂነት /በምክትልነት/ ስሰራ የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ቦርድ ሊቀመንበር ሆኜ ቦርዱን መሰብሰብ ጀመርኩ፡፡ በዚያን ጊዜ የቴሌኮሙኒኬሽን መስሪያቤት ስራውን ለማሻሻል ከዓለም ባንክ ከፍ ያለ ብድር ጠይቆ ነበር፡፡ ነገር ግን ብድሩ ከመፈቀዱ በፊት የዓመቱን ገቢና ወጪ ሂሳብ፣ አገልግሎት ተሰጥቷቸው ያልከፈሉ ሰዎች እንዳሉ የእዳቸውን መጠን የሚያሳይ ጠቅላላ ሪፖርት የቴሌኮሙኒኬሽን መስሪያቤት ለባንኩ እንዲልክ ማስታወሻ ደርሶት ስለነበር የሲውዲን ተወላጅ የሆነው ዋና አስተዳዳሪው ሚስተር ሊንድ ኮስት ባዘጋጀው መልስ እንደተመለከትሁት ብዙ ሺ ብር ያልተከፈለ እዳ ተገኘ፡፡ ምክንያቱን ብጠይቀው አብዛኛው ገንዘብ የቴሌኮሙኒኬሽን ስለሰጠው የቴሌፎን አገልግሎት ንጉሣዊ ቤተሰቦችና መኳንንቶች ያልከፈሉት እዳ መሆኑን ገለጠልኝ፡፡ ካቀረበው ዝርዝር ውስጥ የሚከተሉትን ሰዎች ስም ተመለከትሁ፤

- ልዑል አልጋወራሽ አስፋወሰን ኃይለስላሴ፣
- ልዑል ሣህለስላሴ፣
- ራስ ቢትወደድ መኮንን እንዳልካቸው፣
- ራስ አበበ አረጋይ፣
- ራስ ቢትወደድ አንዳርጌ መሣይ፣

- አቶ መኮንን ሐብተወልድ ... ሌሎችም ብዙ አሉ፡፡

"ሚስተር ሊንድ ኮስት ለ8 ወይም ለ9 ዓመት ከእነዚህ ሰዎች ላይ አንድ ቤሳ እንኳ አልተቀበለም፡፡ ምክንያቱን ብጠይቀው "አንከፍልም ሲሉ ጊዜ ምን ማድረግ እችላለሁ?" አለኝ፡፡ "ሌሎቹ አንከፍልም ሲሉ ስልካቸውን ትቆርጣለህ፡፡ ለምን የእነዚህን ሰዎች በዚሁ መሠረት አላስገደድሃቸውም?" ብዬ ስጠይቀው "የንጉሣዊ ቤተሰቦችን ስልክ ቁረጥ ነው የምትለኝ?" ብሎ ሣቀ፡፡ በጣም ገረመኝ፡፡ ሚስተር ሊንድኮስት የወር ደመወዙ 5 ሺ ብር ነው፡፡ ለቤት ኪራይ 900 ብር በወር ይከፈለዋል፡፡ ሜርሴዴስ መኪና ከነሾፌሩ፣ ከነነዳጁ ተሰጥቶታል፡፡ ግን የቴሌፎን ኪራይ እንኳ ለመሰብሰብ አልቻለም፡፡

በስራው ከታላላቆቹ ኢትዮጵያውያን ሹማምንቶች ለመወዳጀት እንጂ ኃላፊነቱን ለመወጣት አልሞከረም፡፡ ከዚህም በቀር ከአገሩ ከሲውዲን ስለ ቴሌኮሙኒኬሽን ስራ ምንም እውቀት የሌላቸውን ሰዎች በከፍተኛ ደመወዝ እየቀጠረ ሲያስመጣ ማንም ተቆጣጣሪ አልነበረውም፡፡ ስለዚህ የቴሌኮሙኒኬሽን መስሪያቤት "በኢትዮጵያ የሲውዲን ኮሎኒ" ይባል ነበር፡፡ በዚያ ለሚሰሩ የስውዲን ቤተሰቦች ከግል መኪና በቀር ልጆቻቸውን ከትምህርት ቤት የሚያመላልስና "ፒክኒክ" ወይም ሽርሽር የሚወስድ ትላቅ "ስቴሽን ዋገን" መኪና በቴሌኮሙኒኬሽን ገንዘብ ተገዝቶ ከነሾፌሩ ተሰጥቷል፡፡ ይህ ሁሉ መቼም ያለአግባብ መሆኑን የማያውቅ የለም፡፡ ግን ማን ቢናገር! ኢትዮጵያውያን ሠራተኞች ሚስተር ሊንድኮስትን ያለልክ ይፈሩታል፡፡ በክፍሉ ለመጉዳት እንደ ኮሎኒያል ገዥ ፍፁም ስልጣን ነበረው፡፡

ይህን ሁሉ ጉድለት መርምሮ ውሣኔ የሚሰጥ ኮሚሲዮን እንዲሾሙ ጃንሆይን ለመጠየቅ አንድ ማመልከቻ አሰናድቼ ነበር፡፡ ግን ለእንደዚያ ያለ ነገር የሚመርጧቸው ሕግ ተምረናል እያሉ የሚያጭበረብሩትን እንደነ ተሾመ ... ያሉትን እንደሆነ ተገነዘብሁ፡፡ መቼም እነ ተሾመ ቢመረጡ ሚስተር ሊንድኮሰትን እንደሚደግፉ አያጠራጥርም ነበር፡፡ ስለዚህ ለጃንሆይ ያዘጋጀሁትን ማመልከቻ ቀድጄ ከእሳት ውስጥ ጨመርሁና በቀጥታ ኃላፊነቴ አንድ ነገር ማድረግ አለብኝ ብዬ ቆረጥሁ፡፡ ቀጥሎም ለቦርዱ አባሎች ኀሳቤን ካካፈልኳቸውና የእነሱን ድጋፍ ካገኘሁ በኋላ ለሚስተር ሊንድኮስት የሚከተለውን ደብዳቤ ፃፍኩ፤

"የተወደዱ ሚስተር ሊንድኮስት

በተቀጠሩበት ኮንትራት የተመለከቱትን ግዴታዎች ብማፍረስ የቴሌኮሙኒኬሽን መስሪያ ቤትን ጥቅም የሚያበላሹ አድራጎቶች መፈፀምዎን ካረጋገጥሁ በኋላ አገልግሎትዎ ዛሬ ማለቁን ላስታውቅዎ እወዳለሁ፡፡"



እንደጠበቅሁት በዚህ ምክንያት የተነሳው ጩኸት ከአዲስ አበባ እስከዋሽንግተን ማስተጋባት ጀመረ፡፡ አቶ ይልማ ደሬሳ ስልክ ደውለው፤ "ከዓለም ባንክ ጋር ስምምነት ስላለን ዋናውን አስተዳዳሪ አንተ ልታሰናብተው አትችልም" አሉኝ፡፡ አዲስ አበባ ያለው የዓለም ባንክ እንደራሴ "ሚስተር ሊንድኮስትን ካሰናበትህ ባንክ ብድር አይሰጣችሁም" ብሎ አስፈራራኝ፡፡ ያም ሆነ ይህ እኔ በውሳኔዬ ላይ ለመፅናትና ሕጋዊነቱን ለማስረዳት ተደራጅቻለሁ፡፡ ከዚህ ቀጥሎ ወዲያው የቴሌፎናቸውን ኪራይ ወዳልከፈሉት መሣፍንትና መኳንንት ተመልሼ እስከ 15 ቀን ድረስ ባይከፍሉ አገልግሎቱ እንደሚቋረጥ የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ ፃፍሁ፡፡ ግን የልዑል አልጋወራሽ እንደራሴ ብቻ በተወሰነው ጊዜ እዳውን ሲከፍል የቀሩት ማስጠንቀቂያውን ከምንም አልቆጠሩትም ነበር፡፡

የተወሰነው ጊዜ ካለፈ በኋላ ቴሌፎናቸው እንዲቆረጥ አዘዝሁ፡፡ በዚያ ቀን የፖስታ ሚኒስቴርና የቴሌኮሙኒኬሽንን መስሪያ ቤት የጩኸት ማዕበል አነቃነቃቸው፡፡ በመጀመሪያ ጥሪ የደረሰኝ ከራስ ቢትወደድ መኮንን እንዳልካቸው ነው፡፡

"በቶሎ ከቢሮዬ ድረስ እንድትመጣ!" አሉኝ፡፡ በዚያን ጊዜ ጠቅላይ ሚኒስትርነታቸውን ለቅቀው የሴኔቱ ፕሬዝዳንት ሆነው ነበር፡፡ ከቢሮዋቸው ስገባ ሠላም እንኳ አላሉኝም፡፡ አፋቸውን የከፈቱት እኔን ለመስደብ ብቻ ነበር፡፡መቼም እየደጋገሙ ሊያስገነዝቡኝ የፈለጉት እርሣቸው ክብር የዘራቸው የሆነ የመኳንንት ተወላጅ፣እኔ የመጣሁበት የማይታወቅ የደሃ ልጅ መሆኔን ነው፡፡

"ከአመድ ላይ ይነሱና ሰው ነን ይላሉ!" የሚል ነበር ንግግራቸው፡፡ ፊታቸው አመድ፣ ዓይናቸው ደም ለብሶ የእብድ መልክ ነበራቸው፡፡የቁን ያህል እንደሚጠሉኝ አይቼ ገረመኝ፡፡ በበኩሌ ስድባቸውን ዝም ብዬ ለመስማት ራሴን ከመቆጣጠሬ በቀር መልስ ልሰጣቸው አልሞከርሁም፡፡ስድባቸውን እንደመዓት አወረዱብኝና ሲበቃቸው "በል አሁን በቶሎ ሂደህ ስልኩን ቀጥል!" ብለው አሰናበቱኝ፡፡ይህ መቼም የሚቻል አልነበረም፡፡ ከራስ ቢትወደድ መኮንን ዘንድ ስመለስ ከፀሐፊዬ መልዕክት ተቀበልሁ፡፡የመጣው ከልዑል ሳህለስላሴ ዘንድ ነበር፡፡እርሳቸው በፍጥነት ከቤታቸው ሊያዩኝ ይፈልጋሉ፡፡ መቼም እምቢ ማለት አልችልም፡፡ ግን የተቀበሉኝ በሠላምና በአክብሮት ነበር፡፡ቢሆንም በጣም አዝነው እንደነበረ በገፃቸው ይነበባል፡፡ በቴሌፎናቸው መቋረጥ ምክንያት የደረሰባቸውን ችግር እየነገሩኝ ሳለ በድንገት እንባ አነቃቸውና ያለቅሱ ጀመር፡፡ ያለ ልክ ደነገጥሁ፡፡ በምን እንደምተረጉመውም አስቸገረኝ፡፡

በመጨረሻው እንባቸውን ጠራርገው በድርጎ /በስጦታ/ የሚኖሩ መሆናቸውንና እዳቸውን የሚከፍሉበት ራሳቸው የሚያዙበት ገንዘብ አለመኖሩን ገልፀው፤ ይህንን ለጃንሆይ እንዳመለክትላቸው ስለጠየቁኝ፤

ነገር ተዘበራረቀብኝ፡፡ በአንድ በኩል አነጋገራቸው ያለጥርጥር ልቤን ነክቶታል፡፡ በሌላው በኩል ደግሞ ለልዑል ሣህለስላሴ አማላጅ ሆኜ ለመቅረብ እኔ ማነኝ? ብዬ ራሴን ጠየቅሁ፡፡ በማናቸውም አኳኋን ከዚያ ስፍራ ለመሸሽ እንጂ ለመቆየት ስላልፈቀድሁ ልዑልነታቸው የጠየቁትን ሁሉ እሺ ብዬ ተሰናበትሁ፡፡

ከልዑልነታቸው ቤት ስመለስ ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ከአቶ አክሊሉ ሐብተወልድ ስልክ ተደወለልኝ፡፡ በጉዳዩ አቤቱታ ደርሷቸው ኖሯል፡፡ ስለቴሌኮሙኒኬሽን ስራ አካሄድ በጠቅላላው አቋሜን እንዳሻሽል ምክር የሚመስል ትእዛዝ ከሰጡኝ በኋላ ነገሩን በሰፊው ለመመርመር ጊዜ እስካገኙ ድረስ፣ የማስታወቂያ ምክትል ሚኒስቴር የነበሩትን የአቶ አምደሚካኤልን.... ስልክ በቶሎ እንድቀጥል አዘዙኝ፡፡ እኔ ግን ትዕዛዙን ሰምቼ ዝም አልኳቸው፡፡ ከሁሉ አስቀድሞ የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት በተለዩ ቻርተር የተቋቋመ ነፃ መስሪያቤት ስለሆነ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከዝርዝር ጉዳይ እየገቡ ለማዘዝ ሕጋዊ መብት እንደሌላቸው ተገንዝቤያለሁ፡፡ ስለዚህ አቶ አምደሚካኤል ከቢሮዬ መጥቶ በጉዳዩ ላይ እንደገና ባነጋገረኝ ጊዜ እዳውን ሳይከፍል ምንም ላደርግለት እንደማልችል አረጋገጥኩለት፡፡

አቶ አክሊሉ የእኔን እምቢታ ሲሰሙ ያለልክ ተቆጡና በቴሌኮሙኒኬሽን የደረሰውን ሁኔታ በማጣመም ለጃንሆይ አቅርበው ከስራዬ እንድወገድ ጠየቁ፡፡ መቼም በዚህ የሚደግፋቸው ብዙ ሰው ነበር፡፡

በማግስቱ ከቤተ-መንግስት ማልጄ እንድገኝ በግርማዊነታቸው የዕልፍኝ አስከልካይ አማካይነት ተነገረኝ፡፡ ወዳጆቼ ሁሉ አዝነው ነበር፡፡ በጠቅላላው ሰው ሁሉ ገምቶት እንደነበረው በመንግስት ስራ ለመቆየት ያለኝ ጊዜ አንድ ቀን ብቻ ነበር፡፡ ተወቅሼ ወይም ተቀጥቼ የምሰናበትበትን የመጨረሻውን ሰዓት ለመመልከት ከቤተ-መንግስቱ ቅጥር ግቢ ብዙ ሰዎች ተሰብስበዋል፡፡ የተሰማቸው ደስታ መቼም ግልፅ ነበረ፡፡ በመካከላቸው አልፌ ወደ ቤተ-መንግስቱ ስገባ አንዳንዶቹ እየተጠቃቀሱ ይሳሳቁ እንደነበረ በአጋጣሚ ተመልክቻለሁ፡፡ ከጃንሆይ ዘንድ እንደቀረብሁ፤ አቶ አክሊሉ ቀደም ብለው በእኔ ላይ አቅርበውት የነበረውን ክስ ደግመው ተናገሩ፡፡ እንደ እርሳቸው አነጋገር የቴሌኮሙኒኬሽንን ዋና ዳይሬክተር ከስራው ለማገድ በቂ ምክንያት የለኝም፤ በመስሪያ ቤቱ ትርምስ ፈጥሬያለሁ፣ የቴሌፎን አገልግሎት የሚያስፈልጋቸውን ሹማምንቶች ያለአግባብ ከልክያቸዋለሁ፡፡ እንደ እርሳቸው አስተሳሰብ፤ ስራው ስነ-ስርዓት ለማግኘት የሚችለው እኔ ከዚያ ስነሳ ብቻ ነው፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ይህን ሁሉ ምክንያት በማድረግ እኔን ከዚያ ለማስነሳት ጃንሆይን ጠየቁ፡፡



የመከላከያ ጊዜ ሲሰጠኝ፤ "የቴሌኮሙኒኬሽን መስሪያ ቤት "የሲውዲን ኮሎኒ እየተባለ የኢትዮጵያን ህዝብ ሐብት ለግል ተጠቃሚዎች ይባክን በነበረበት ጊዜ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለማስመርመርና አስፈላጊው እርማት እንዲደረግ አንድ ቀን እንኳ አስበውበት አያውቁም" ስል ንግግሬን ጀመርሁ፡፡ "የኢትዮጵያ መሳፍንቶችና የመንግስቱ ታላላቅ ሹማምንቶች በነፃ የቴሌፎን አገልግሎት ሲጠቀሙ፤ "በምን ምክንያት?" ብለው ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሊጠይቁ አልፈቀዱም፡፡ ስለቴሌኮሙኒኬሽን ስራ አንዳች የቴክኒክ እውቀት የሌላቸው ሰዎች ከሲውዲን አገር በከፍተኛ ደመወዝ እየተቀጠሩ ሲመጡ "በምን ምክንያት?" ብለው ጠቅላይ ሚኒስትሩ ጠይቀው አያውቁም፡፡ እርሳቸውን ያሳሰባቸው የኮንትራት ግዴታውን በማፍረስ ከስራው የተወገደው የዋናው ዳይሬክተር ጉዳይ ነው፡፡ እርሳቸውን ያሳሰባቸው ከ8 እስከ 9 ዓመት የአገልግሎት ዋጋ ባለመክፈላቸው ቴሌፎናቸው የተቆረጠባቸው ሹማምንቶች ችግር ነው!" ስል በበኩሌ የፈፀምሁት ሁሉ ሕጋዊና ትክክለኛ መሆኑን የሚያሳዩ ልዩ ልዩ ማስረጃዎች አቀረብሁ፡፡ በዚህ ጊዜ ጃንሆይ ወደ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ዞወር ብለው፤ "ብርሃኑን የምትወቅስበት የሚበቃ ምክንያት አናይም፡፡ ይልቁንስ የእርሱን ጥረት መደገፍ ነበረብህ፡፡" ብለው አሰናበቱን፡፡

በዚያን ጊዜ አቶ ወርቁ ሐብተወልድ የተባለው የቴሌኮሙኒኬሽን ቦርድ አባል የተናገረው በፍፁም አይረሳኝም፡፡ "ብርሃኑ በመንግሰት ስራ ላይ ያለው ጊዜ ዛሬ ያበቃል" እየተባለ በከተማ ውስጥ የተወራውን ሰምቶ ለእኔ በማዘን፤ ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ጋር ያለኝን የክርክር ውጤት ለመስማት እንደ ሌሎቹ ሰዎች ሁሉ በቤተ-መንግስቱ ቅጥር ጊቢ ውስጥ ይጠባበቅ ነበር፡፡ ከጃንሆይ ጽ/ቤት እየሳቅሁ ስወጣ አንገቴን አቅፎ ከሳመኝ በኋላ፤ ወደ ጆሮዬ ተጠግቶ "የአፄ ኃይለስላሴ ጥፋት በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ መንገሳቸው ነው... ቀጣፊ ህዝብ!" ብሎ ሹክ አለኝ፡፡ ..." ይሉናል፡፡ እዚህ ላይ ያብቃን፡፡

መቼም የአቶ ብርሃኑ ድንቄን "ቄሣርና አብዮት" የሚለውን መጽሐፍ "ቆርጬ" ሳይሆን "ገምድዬ" ነው ያካተትኩት፡፡ ምን ላድርግ? ይሄን የመሰለ የተጣራ ታሪክ ለጃንሆይ ዙፋን መነቃነቅ አስተዋፅኦ እንደነበረው ለመግለፅ ከዚህ የተሻለ መረጃ የለም፡፡

የጃንሆይ የውድቀት መንስኤ ፊውዳላዊ አገዛዛቸው ነው ይባላል፡፡ እነዚህን የመሰሉ ንቅዝ ባለስልጣናት እስካሉ ድረስ አገዛዙ ምንስ ቢሆን ምን ለውጥ ያመጣል? በእርግጥ ግን በዚያ ወቅት ኢትዮጵያ ምን አይነት ልጆች ነው የነበሯት? አሁንስ ምን አይነት ልጆች ነው ያሏት? ስንት ብርሃኑ ድንቄዎች አሉ? ባለስልጣን ማለት እኛ አገር ምን ማለት ነው? ከዚህ በላይስ ምን የሚያሳዝን ነገር አለ? ህዝቡን ለአመፅ ለማነሳሳት የባለሥልጣናቱ ንቅዘት ብቻውን በቂ አይሆንም ወይ? ይህን አይነት ዘረፋ

የሚፈፀምባት አገር ላይ ረሃብና ድርቅ ካልተከሰተ የት ይከሰት? እያልን ስንቀጥል ነው የአገሪቱ ባለችበት የመርገጥ ጉዳይ ምንጩ የሚገባን፡፡ ይህ የታሪክ መጽሐፍ ነው፡፡ ከላይ ያየነው እውነትም ታሪክ ነው፡፡ ዛሬም ድረስ ያለ ህያው ታሪክ! መንግስትና ህዝብ ሊማርበት የሚችል፣ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ግለሰብ ራሱን ሊፈትሽበት የሚችልና የሚገባ ድንቅ ታሪክ!

ታሪኩ እውነት ለመሆኑ የሚጠራጠር አንባቢ ካለ ኢትዮጵያን የማያውቅ ብቻ ነው፡፡ ይሄ ስም ለማጥፋት ተብሎ የተፃፈ ታሪክ ነው ብሎ የሚከራከር ካለ ከእውነት አብልጦ ራሱን የሚወድ ብቻ ነው፡፡ ግልፅ ነዋ! አገር ያወቀው ሐቅ፡፡ ከታሪክ መማር ካለብን በአንደኝነት ይህንኑ ነው ብዬ አምናለሁ፡፡ አሁን አሁን በዚህ ሰዓት የእነ ብላታ፣ የነደጅአዝማች፣ የእነ እገሌ ተግባር እየተፈፀመ እንዳለ ወይስ እንደሌለ ነው የሚሰማን? ኢትዮጵያን በድህነት እርቃኗን ያስቀራት የዝናብ እጥረት አይደለም፡፡ የመሬት ጥበት፣ የረጂዎቻችን ማነስ አይደለም፣ የርዕዮተ ዓለም ትክክል መሆን ያለመሆን አይደለም፡፡ ብዙ ነገር አይደለም፡፡ ሙስና ነው፡፡

"ባላባት፣ መሣፍንት፣ ሹማምንት ..." ይባላል፡፡ ያ ስም እና ዘርን ብቻ ነው የሚያመለክተው፡፡ "የመንግስት ባለስልጣን" አበቃ፡፡ በጃንሆይ ዘመን የነበረውን ሙስና በአንድ ብርሃኑ ድንቄ ነጣላ ገጠመኝ ስንረዳ ለውድቀታቸው አንዱ መንስኤ ሊሆን እንደሚችል እናስባለን፡፡

በዘመናቸው የነበረው ብልሹ አሰራር ህዝቡን ምን ያህል ሊጎዳና ሊያማርር እንደሚችልም ግልፅ ነው፡፡ ፍትህ የለም፣ ሕግ ይጣሳል፣ የህዝቡ ጉርምርምታ በታላላቅ ሹማምንቱ ተውጦ የሚቀር እንጂ ወደጃንሆይ ጆሮ የሚደርስ አይደለም፡፡ ትልልቅ ባለሥልጣናቱ አገር ሲበዘብዙ አብሮ መተባበር እንጂ አፈንግጦ ለጃንሆይ ማመልከት አይችልም፡፡ ቢችል ምን እንደሚገጥመው በግልፅ ያየነው ነው፡፡

የተለመደው የተማሪ አመፅ፣ የገበሬ አመፅ፣ ረሃብ፣ የወታደር አመፅ የሚሉትንና ብዙዎች ለለውጥ ሲሉ ያደረጉትን ትግልም ሆነ የከፈሉትን መስዋዕትነት ቆየት ብለን እንደ ሌሎች ታሪኮች ሁሉ በአጭሩ እናያቸዋለን፡፡ ከዚያ በፊት ግን እያየናቸው የመጣነውን ብልሹ አካሄዶች መሠረት አድርገን ጥቂት ነጥቦችን ብናነሳ አመፅ እንዴት እንደሚረገዝ ግልፅ ይሆንልናልና እሱኑ እናስቀድም፡፡

ለምሳሌ ቀኝአዝማች እገሌ በእርዳታ የመጣውን መድሐኒት ብቻ ሳይሆን ሰሃን ሳይቀር በሞኖፖል ይዘው መጋዘኑ ላይ ቆመው "ማነው ወንድ ይህችን መጋዘን የሚያሸግ!" እያሉ እየፎከሩ እንደ ነጋዴ በችርቻሮም በጅምላም ሲቸበችቡት አይተናል፡፡ በሽተኛ አቅም ስለሌለው ሊያምፅ አይችልም እንጂ በዚህ ድርጊት "የበሽተኞች እመፅ" ሊኖር ይችል ነበር ብንል ማጋነን አይሆንም፡፡



ወታደሩ "ደመወዝ ይጨመርን፣ ስንቃችን የተበላሸ ነው፣ የምንጠጣው ውሃ ቆሻሻ ነው ..." በሚል ለአመፅ ተነሳሳ፡፡ ብላታ እገሌ ቤት ያሰሩበት ገንዘብ በዚያ ዘመን ለአራቱም ክፍለ ጦር ሠራዊቶች ለረጅም ጊዜ እጥፍ የደመወዝ ጭማሪ ይሆናቸው ነበር፡፡ የወታደር ደመወዝ 15 ብር ነበራ! ቆሻሻ ውሃን በተመለከተ ጉዳዩ የሚመለከተው ደጃዝማችን ነው፡፡ እንኳን ነገሌ ቦረና ለአዲስ አበባው የገፈርሣ ውሃ ግድ አልነበራቸውም፡፡ እሳቸው እዚህ ጨረታውን ጣሊያን ይውሰድ፣ የፈረንሣዩ ለጉቦ አይተርፍም፣ ራስ ሆቴል ድግስ አለብኝ እያሉ እንዴት ነው ንፁህ ውሃ ነገሌ ቦረና የሚደርሰው? የወታደር አመፅ፡፡

ወደ ገበሬ አመፅ ስንመጣ፣ ገበሬው ያመፀው ምርር ብሎት እንደሆነ ጥርጥር የለውም፡፡ የመሬት ግብር ግን አልነበረም ያማረረው፡፡ ሕገ-ወጥ ግብር ነው ያማረረው፡፡ አንድ መንግስት ያለ ግብር ምንም ሊፈጥር አይችልም፡፡ ስለዚህ ግብር ተጥሎበታል፡፡ ቀደም ሲል እንዳየነው ፍትሐዊ ያልሆነ የግብር አጣጣል ነበረ፡፡ ያ ግን ተጋኖ የሚወራ አልነበረም፡፡ ችግሩን የፈጠረው ሕገ-ወጥ አሳሽ ነው፡፡

ፊታውራሪ እገሌ የወላይታን ሕዝብ የውተት ላሙን ሲያስገብሩት ለምን አያምፅ? ጃንሆይ ይሄን አላዘዙም፡፡ ሰው ግደሉ፣ ዝረፉ አላሉም፡፡ አሉ የተባሉ ሹማምንት ግን እላፊ ያስገብራሉ፣ ይገድላሉ፣ ይዘርፋሉ፣ ከሕግ ውጪ ያስራሉ ... ወዘተ፡፡ ስለዚህ ገበሬው አመፀ፡፡ የሚስተር ሉንድኮሰት አለአግባብ የሆነ ጥቅማ ጥቅምና የባእዳን መንፈላሰሻ የነበረው ገንዘብ በቀጥታ የወሎን የአንድ ዙር ድርቅ ለመቆጣጠር ይችል ነበር፡፡

ጃንሆይ ለህዝባቸው የማያስቡ ባይሆን ኖሮ በስማቸው ተመዝግቦ የነበረውን ከጠላት የተወረሰውን የመካኒሳ ፋብሪካ በፈቃዳቸው ላሰሩት ቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል መተዳደሪያ ሙሉ ለሙሉ ባልሰጡት ነበር፡፡

በዚህ መሠረት በዘመናቸው ይከሰቱ የነበሩትን ረሃቦችም ሆኑ ድርቆች ለመቋቋም ጥረት ሊያደርጉ ይችሉ እንደነበር ስንረዳ፣ ነገር ግን የመንግስታቸው ገቢ በየሚኒስትር መስሪያ ቤቱ ተውጦ ስለሚቀር ይህን ለማድረግ የሚያስችል አቅም አይኖራቸውም፡፡ ለ4 ዓመታት ያህል 70 በመቶ ለሆስፒታሉ መስጠት እየነበረባቸው ምንም ሳይከፍሉ ቆዩ ማለት ምን ማለት ነው? 350 ሺ ብር! ሦስት ሰዎች የወሰዱት፡፡ ለሆስፒታል ስራ ማስኬጃ የሚሆን፡፡ ስንት ሰው ያድናል? ግማሹ እንኳ ቢዘረፍ ሌላው ለሰፊ የመስኖ ልማት ሊውል ይችል ነበር፡፡ በዚህ ብቻ የአንድን ዘመን ረሃብ እንደምንም ማሳለፍ ይቻል ነበር፡፡ አልሆነም፡፡ (የዚያን ዘመን የገንዘብ ሁኔታ ለመረዳት ኢጣሊያ በወልወሉ ግጭት ለ80 ዜጎቿ ሞት የጠየቀችው 200 ሺ ብር መሆኑን ማሰብ ይበቃል፡፡)

የተማሪ አመፅ ግልፅ ነው፡፡አዲስ አበባ ሆነው ባያምፁ ነው የሚገርመው፡፡ማገናዘብ የሚችል ጭንቅላት አላቸው፣ጭቆናው ይገባቸዋል፣ቢሮክራሲውን ያውቁታል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ጉቦ የማይቀበል ባለስልጣንን እውቅና አይሰጡም ነበር፡፡ ያስወግዱታል! (መሬት ላራሹ፣ ጭሰኛ፣ ገባር፣ ፊውዳላዊ አገዛዝ ... ወዘተ ሁሉም በዚህ ስር ነው) ነገር ግን ተማሪው ብዙ መነሻ ሊያገኝ የሚችልበት አጋጣሚ ሰፊ እንደነበር ከወዲሁ ተረድተን እንለፍ፡፡ ተማሪው የባላባቱን ንቅዘት በግልፅ ስለሚያውቀው ለማለት ነው፡፡ ነጋዴም ያው ፊታውራሪ ከወንድማቸው ጋር ያሸጉበት ስለነበር ሊያምፅ ይችላል፡፡

ሠራተኛውማ ምን ጥርጥር አለው? የመንግስት ሠራተኛ በዚያ ዘመን ካላመፀ መቼ ሊየምፅ ኖሯል? የመንግስት መስሪያ ቤት ተቀጥሮ የግል ቤት እንዲሰራ እየታዘዘ! እንዲያ ነበር...ዛሬም እንዲህ ነው.....

የጃንሆይን ጥፋትና የአቶ ብርሃኑን ደብዳቤ ወደማየት እንለፍ፡፡

ጃንሆይና ጥፋታቸው

የጃንሆይ ትልቁ ጥፋት ስልጣን አፍቃሪነታቸው ነው፡፡ይሄን ሁሉ ሙስና እያዩ አንዳንዶችን መልሰው ትልቅ ቦታ ላይ ይሾሟቸዋል፡፡ጠንካራና ዘላቂ እርምጃ ቢወስዱ ስልጣናቸው አደጋ ይደርስበታል፡፡ስለዚህ ለሥልጣናቸው ሲሉ ብቻ ሕገ-መንግስቱም ሆነ ማናቸውም አይነት ሕግ ሲጣስ እያወቁ በቸልታ ያልፉ እንደነበር ግልፅ ነው፡፡

ዋና ትኩረታቸው ዙፋናቸው ላይ ሆነና ኢትዮጵያን ረሷት፡፡ ወይም "በስልጣኔ አትምጡብኝ እንጂ እንዳሻችሁ" ያሉ ይመስላል፡፡ ስለዚህ የየዘርፉ ሹማምንት በነፃነት መበዝበዛቸውን ቀጠሉ፡፡ የአቶ ብርሃኑን ገጠመኞች በጥቂት መስሪያቤቶች ብቻ ያየናቸው ናቸው እንጂ በሁሉም መሰል የመንግስት መስሪያቤት፣ ተቋማትና ድርጅት ይፈፀሙ እንደነበር አይሰወርብንም፡፡

ጃንሆይ በተለይ ከ1950 ጀምሮ ባሉት ጊዜያቶች ፍፁም አምባገነን እየሆኑ እንደሄዱ የብዙዎች ስምምነት ነው፡፡ በተለይ በ1951 - 52 ዓ.ም በጃፓኖች የረቀቀ ምክርና የቴክኖሎጂ ድጋፍ በመመርኮዝ ስልጣናቸውን ለማጥበቅ የወሰዷቸው እርምጃዎች ወይም በተግባር የተረጎሟቸው አሰራሮች ለዚህ እውነታ ማስረጃ ናቸው፡፡

ሙስናን ለማስወገድ ቆርጠው ተነሱ ማለት በሹማምንቱ ሁሉ ተቃውሞ ይመጣል ማለት ነው፡፡ ሁሉም ሹማምንት ተቃወመ ማለት ዙፋኑን ለቀቁ ማለት ይሆናል፡፡ ለዚህም ይመስላል አቶ ብርሃኑን የመሰሉ ጽኑ አጋላጭ ከሁሉም ጋር እንዳያጋጪቸው ሰግተው ራቅ ያደረጓቸው፡፡



"በአሜሪካ የኢትዮጵያ አምባሳደርና ባለሙሉ ስልጣን እንደራሴ" ብለው ሾመው ላኳቸው አቶ ብርሃኑን፡፡

ይህ ምን ያሳያል? "አጉል ትግል እያዋጣኝምና ተዋቸው ይዝረፉ፡፡ አምላክ ልቦና ይስጣቸው እንጂ ሌላ ምን ይባላል፤ እነሱን ማን ተቆጣጥሮ ይችላል?" የማለት ያህል ነው፡፡ አቶ ብርሃኑ ድንቄ ግን ሁሉንም ነገር አውቀው ለህሊናቸው ያደሩ ሰው ነበሩና ከአሜሪካ ወደ ጃንሆይ በመጨረሻ በ1952 ዓ.ም የሚከተለውን ደብዳቤ ፃፉላቸው፡፡

"ለግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለስላሴ ንጉሠ ነገስት ዘኢትዮጵያ"

<u>አዲስ አበባ</u>

ግርማዊ ሆይ፤ በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ማኅበራዊ ህይወት የሚታየውን ምሬትና ግፍ በፍትህም መጓደል ምክንያት የሚደርሰውን የአስተዳደር በደል ስመለከት ወደአገሬ ለመግባት ያለኝን ኀሳብ ማቆየት ግድ እንደሆነብኝ ለግርማዊነትዎ መግለጥ አስፈላጊ መስሎ ታይቶኛል፡፡ ይህ ሁኔታ የሚታረምበትን በኅብረት ለመስራት ባንሞክር ታላቅ ብጥብጥ እንደሚያስከትልብን ከታሪክ መማር ካልቻልን ከተከታዩ መቅሰፍት የምናመልጥበትና የምንከለልበት ሰው ሰራሽ ዘዴ ይገኝለታል ብሎ ራስን መደለል በህልም ዓለም ውስጥ ለመኖር እንደመሞከር ይቆጠራል፡፡

ከዚህም በቀር ለተተኪው ትውልድ አቋም ይሆናሉ ብለን ተንከባክበን ልናሳድጋቸው ኃላፊነት ያለብንን ህፃናትና ውለታ ትተው ለማለፍ የተዘጋጁትን ሽማግሎቻችንንም ደህና እረፍት እንዲያገኙ ከአገሪቱ በተፈጥሮ ያገኙትን ዕድል መንፈግ ያሰኛል፡፡በዚህም ምክንያት በፈፀምነው ስህተት ታሪክ ምህረት ሊያደርግልን በፍፁም አይችልም፡፡ይህን የመሳሰለው ሁኔታ በብርቱ የሚያሳስበን መሆኑን ስንገልጥ ምንም እንኳ አንዳንድ ሰዎች "አንተ ምን አገባህ" በማለት በጉዳዩ ባለቤትነት ክፍያ ድርሻችንን ለማሳነስ ቢሞክሩም፤በኢትዮጵያዊነት ትክክለኛ መብት ላይ አጥብበው ያሰመሩትን የወሰን ክልል አሜን ብሎ ለመቀበል ከቶ ስለሚያስቸግር እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ኃላፊነቱን የማስወረድ ተግባር እንዳለበት አይካድም፡፡

እኔም ይህን ምክንያት አድርጌ በአሁኑ የመንግስት አስተዳደር የደረሰውን ሕገ-ወጥ አፈፃፀም ሁሉ ለማረምና ፍትህን ለማደላደል የሚቻልበትን ኀሳብ በነፃ ለመግለጥ ስል ከውጭ አገር መቆየትን መረጥሁ፡፡

በአሁኑ እያያዝ እንዲቀጥል የተተወ እንደሆነ በኢትዮጵያ የወገን መለያየትና የደም መፋሰስ እንደሚያስጋ የመላው ኢትዮጵያውያን ግምት የወደቀበት ነው፡፡ ዋናው ዓላማ ይህ እልቂት የሚወገድበት መድሐኒቱ ምንድነው? ለተባለው ጥያቄ ለመመለስ እንደሆነ ጥርጥር የለውም፡፡ መቼም እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ በሚመስለውና በሚያምንበት ረገድ

መልሱን ለመስጠት ሞክሯል፡፡ አሁን የጎደለ መስሎ የሚታየው ከዙፋኑ በኩል የሚጠበቀው ይሁንታ ብቻ ነው፡፡ ነገሩን በመጠኑ ለማብራራት ያህል በሚከተሉት መስመሮች አስተያየቴን ለመግለፅ እሰነዝራለሁ፡፡

የኢትዮጵያ ህዝብ ለዙፋኑ የሰጠው ልባዊ አክብሮት ዘላቂ ሆኖ በታሪካዊ ቅርስነት እንዲጠበቅ በቤተ-መንግስቱ በኩል አልታሰበበትም ለማለት ያስደፍራል፡፡ ባለፈው "መለኮታዊ መብት" የተባለው የዘውድ "ቲዎሪ" የተሳሳተ መሆኑን ቢረዳውም ህዝቡ ዘውዱን ታሪካዊ ሲምቦል ወይም ምሳሌ አድርጎ በክብር ሊያኖረው ሲፈቅድ ወደ መለኮታዊ መብት አስተያየት እንደገና እንዲመለስና ጣኦታዊ ስግደት እንዲያደርግ ማስገደድ በእክል ዘውዱን ለማስረገጥ ካልሆነ በቀር ለሌላ አያገለግልም፡፡

ጃንሆይ ባለዘውድ፣ አስተዳዳሪ፣ ሕግ አውጪ፣ ዳኛ፣ ምስለኔ፣ ፖሊስ፣ ጭቃሹም ሆኘ ልስራ ሲሉ በሃያኛው ክፍለ ዘመን የሚገኝ ህዝብ ይህን መብት አጠቃሎ በፈቃዱ ለዘውዱ ብቻ ይለቃል ማለት የማይታመን ነው፡፡ መቼም እየተደጋገመ የሚሰጠው ምክንያት "ህዝቡ ኃላፊነትን ለመቀበል አልደረሰም" የሚል መሆኑን በየጊዜው ሰምተናል፡፡ በእውነቱ ከአፍሪካና ከኤሽያ ህዝብ መካከል አልደረሰም ተብሎ በኢትዮጵያ ህዝብ መፍረድ ይገባልን? ደግሞስ ያለመድረስ ትርጓሜው ምንድነው? ምናልባት የማሰብ፣ የመምረጥ፣ የማመዛዘን፣ የመፍረድ ሴንስ አልተፈጠረበትም ማለት ነው? እንደዚህማ ከሆነ በ3000 ዘመን ውስጥ ለዚህ ህዝብ ጭንቅላት ሆኖ ያሰበለት፣ ዓይን ሆኖ ያዬለት፣ ጆሮ ሆኖ የሰማለት የዛሬው ዘውድ ነው ማለት ነዋ! የሚፈተነው ይህን የመሰለ አስተያየት ለማቅረብ እንደሆነ ምህረት የሌለው በደል ነው፡፡ ይልቁንስ ጃንሆይ የሕግ ጠባቂነትን ልብስ ተጎናፅፈው በዚህ መንፈስ ፍትህን ከሚያጓድሉ ስልጣኑን ለህዝብዎ ሰጥተው እርሱ ቢጨነቅበት እንደሚሻል ጥርጥር የለውም፡፡ ያለዚያ ከዚህ ማስታወሻዬ ውስጥ ለስማቸው እንኳ ስፍራ ለመስጠት ዋጋ የሌላቸውና ህሊና ቢሶች የሚያቀርቡልዎትን "ደህና ታይቷል" እያሉ ፍትህን ለግል ስሜት መወጫ ማድረግ የቱን ያህል ለትውልድ መተዛዘቢያ ሆኖ እንደሚኖር የተሰወረ ሊሆን አይችልም፡፡

ይህን ተስፋ አስቆራጭ ሁኔታ ለማሻሻል የሚቻለው ጃንሆይ ዘውዱን ለራስዎ አስቀርተው አስተዳደሩን ለህዝብ በመስጠትና የዴሞክራሲን መንፈስ በማስገባት ነው፡፡ ነገር ግን ይህ አስተያየት ለግርማዊነትዎ ሰውነት "አለርጂ" ሆኖ ቢያስቸግርዎ እንኳ ሌላ ማማረጫ ይኖራል፡፡

ይኸውም ዘውዱን ለልዑል አልጋወራሽ ማስተላለፍና "አብዲኬት" ማድረግ ነው፡፡ እርሳቸው ሕገ-መንግስትን ጠብቀው ለመኖር ፈቃደኛ እንደሆኑ እያሌ ሰዎች ሲመሰክሩላቸው ሰምቻለሁ፡፡ ያለዚያ ተከታዩ ትርምስና ደም መፋሰስ እንደሚሆን ጥርጥር የለውም፡፡



ይህ አቤቱታ ከእኔ ብቻ የቀረበ አይደለም፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ በፍርሐት ታፍኖ ነጋም መሸም የሚያጉተመትመው ይህንኑ ነው፡፡ ድምፁን ከፍ ለማድረግ ግን አካባቢው አልፈቀደለትም፡፡ እኔም ከእርሱ የተለየሁ መስዬ ታይቼ እንደሆነ ያጋጣሚ ነገር ብቻ ነው፡፡ አዲስ አበባ በሹሞችዎ የታፈንኩትን ያህል እዚህ ከተነፈስኩ በኋላ ወደ አገሬ እንድመለስ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ ምናልባት ይህን አቤቱታ በመፃፌ እወነጀል ይሆናል፡፡ ግድ የለም፡፡ የሆነው ሆኖ በትዕዛዝ ሳይሆን በነፃ የሚፈርድና በግልፅ የሚያስችል ፍርድ ቤት ተቋቁሞ ራሴን በሕጋዊ ጠበቃ አማካይነት ለመከላከል ጃንሆይ የሚፈቅዱሉኝ ከሆነ በአገሬ ውስጥ ለመተንፈስ እድል ተሰጠኝ ማለት ነው፡፡

ከዚህም ሁሉ ጋራ ላስታውስ የምፈቅደው ይህን ማስታወሻ በመፃፌ ተቀይመው የእኔን ህይወት ለማስጠፋት በሺ የሚቆጠር ገንዘብ እንደሚወጣ ጥርጥር የለውም፡፡ አዝናለሁ፣ እኔ ለሞት የተዘጋጀሁ ስለሆነ ገንዘቡ ባይባክንና ለነፍስ ገዳይ በመስጠት ፋንታ ለጦም አዳሪ ችግረኛ ቢውል የበለጠ እንደሚጠቅም ጥርጥር የለውም፡፡

በበኩሌ በአገራችን "ሪቮሉሽን" እንዲነሳና የማንም ደም እንዲፈስ አልፈቅድም፡፡ በዚህ በአቤቱታዬ የምወተውተውም ሠላማዊ ለውጥ እንዲሆንና የምንፈራው ደም መፋሰስ እንዳይኖር ስለሆነ ጃንሆይ አንድ ቀን "ለካ ብርሃኑ እውነቱን ኖሯል" ሳይሉ አይቀርም፡፡

እንኳን ዘውድ የጫነ ሰውነትንና ማናቸውንም ሰው የማክበር ልምድ ስላለኝ ይህ አቀራረቤ ክብርን ለመድፈር እንደማያስቆጥርብኝ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡እውነት ሁልጊዜ መራራ ናት፡፡የመድሐኒት ፈውሱ እንጂ ምሬቱ አይታሰብም እንደተባለው፣ ይህ በቅን ልቦና የቀረበው እውነተኛ አቤቱታዬ የግርማዊነትዎን ልብ አራርቶ ለኢትዮጵያ ማኅበራዊ ህይወት አንድ ፈውስ እንዲያመጣለት ተስፋ አደርጋለሁ፡፡

ጃንሆይ! በኢትዮጵያ ወጣቱ፣ ሽማግሌው፣ ሴቱ፣ ወንዱ የአኗኗሩ ዘዴ ውሉ ተዘባርቆበታል፡፡ አምላካችን፣ፈጣሪያችን እያለ ቢደልልዎት አይመኑት፡፡ ጨንቆት ነው፡፡ ከልብ የሚመርቅዎት ግን ራስክን አስተዳድር ብለው አርነት ሲያወጡትና ወደ ዴሞክራሲ ሲመሩት ነው፡፡ይህንንም ስል ህዝብ በራሱ ሲተዳደር ችግር አይገጥመውም ማለቴ አይደለም፡፡እስከዚህ አልሳሳትም፡፡ነገር ግን ሌላው ገፍቶ ከሚጥለውና ላንሳህ ከሚለው ራሱ ወድቆ በራሱ መነሳትን ይመርጣል፡፡ይኸውም ከስህተት መማር ይባላል፡፡

ስለዚህ ጃንሆይን ተሳሳቱ እያለ ከሚከስዎት እርሱ በስህተቱ እንዲፀፀትና እንዲማር ቢያደርጉት ከትልቅ ውለታ ይቆጠራል፡፡ የዛሬው ሕገ-መንግስት ዴሞክራሲን ለማስገባት የሚረዳ ካለመሆኑም በላይ ያንኑም ቅሉ አክብሮ ለመጠበቅ በአንቀፅ 21 እንደተመለከተው ከንጉሠ ነገስቱ

በመሐላ የተሰጠው ቃል ፈርሷል እያሉ አያሌ ኢትዮጵያውያን እንደሚያማርሩ ግርማዊነትዎ ሳይሰማው አይቀርም፡፡ መቼም ሕገ-መንግስቱን ለመጣስ አንድ የጽህፈት ሚኒስቴር ደብዳቤ ይበቃል፡፡ እንግዲህ ህዝቡ ወይም ሹማምንቱ ለንጉሠ ነገስቱ ታማኝ ነኝ እያሉ ቢምሉም፤ ንጉሠ ነገስቱ በበኩሉ መሐላውን የሚጠብቅ ካልሆነ በመሐላቸው ታስረው እንደማይኖሩ በልጅ እያሡ ጊዜ የደረሠው ሁኔታ ምሳሌ ሊሆን ይችል ይመስለኛል፡፡

ዋሽንግተን፤ ግንቦት 25፤52

ከታላቅ አክብሮታዊ ፍርሐት ጋራ

ብርሃኑ ድንቄ፡፡" ይላል ደብዳቤው፡፡

ጃንሆይ ግን ዛሬም ድረስ በአፍሪካ መሪዎች ዘንድ የማይሞከረውን ዙፋን መልቀቅን በሚመለከት መልሳቸው አንድ ነው፡፡ "ሞት ይንቀለኝ" አበቃ፡፡

አፍሪካ ውስጥ መፈንቅለ መንግሰት ያላስተናገደ አገር የለም፡፡ በፈቃደኝነት ስልጣን መልቀቅ? አይታሰብም፡፡ እንኳን በዚያን ጊዜ ሕገ-መንግስቱ እንደማይለቁ አረጋግጠላቸው፤ንጉሰነገስት ሆነው፣ ዛሬ እንኳን ፓርቲ፣ ምርጫ ባለበት ዘመን ማንም አይለቅም፡፡ ሶስት ያህል አፍሪካዊ አገሮች ብቻ ታይተዋል፡፡ ስልጣንን በምርጫ /በሰላማዊ/ ያስተላለፉ፡፡ በነገራችን ላይ ከነፃነት በኋላ በአፍሪካ መፈንቅለ መንግስት አንደኛ ደረጃ ላይ የምትገኘው ሱዳን ስትሆን 25 ጊዜ የተሳካና ያልተሳካ መፈንቅለ መንግሰት ተካሂዶባታል፡፡ ኢትዮጵያ ዝቅተኛውን ደረጃ ይዛለች 6 ጊዜ በቻ ስለሆነ፡፡ ሌላውም በአስራዎቹ ይተመናል፡፡ ችግሩ ግን ይሄ ብቻ አይደለም፡፡ ስልጣንን ለማጥበቅ የሚሰሩ ስራዎች ብዙ በመሆናቸው፤በዚህም ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊና በተለይም ኢኮኖሚያዊ ብክነት ይከሰታል፡፡ ታማኝ ሹማምንት ሲዘርፉ እንዲኖሩ መፍቀድንም ያካትታል፡፡ የ"አባልን" "አበል" ጨምሮ ብዙ ገንዘብ በስልጣን ላይ ኢንቨስት ይደረጋል፡፡ የጃንሆይ ጥፋት በዚህ ክብ ውስጥ የሚሽከረከር ነው፡፡ እናም ከክቡ ውጪ ያለውን ህዝብ ዘነጉት፡፡

ጃንሆይ የከተማውን ንቅዝ ሹማምንት እያወቁ ትተውታል፡፡ይህም ህዝቡን በንቅዝ ሹማምንት የጭቆና ቀንበር ስር እንዲኖር መፍቀድ ማለት ሲሆን፤ከህዝቤ ስልጣኔ ይበልጣል የሚል እንድምታ ያለው ግዙፍ ጥፋት ተደርጎ ሊወሰድ የሚችል ነው፡፡

ከዚህም ባለፈ ጃንሆይ በወቅቱ የነበረውን ዓለም አቀፍ የአስተዳደር ስርዓትና የኢትዮጵያ ህዝብም የግንዛቤ አድማሱ መስፋቱንም ሆነ ለውጥ መፈለጉን ማሰብ አልፈለጉም፡፡ ሌላው ቀርቶ ብዙ የአፍሪካ አገሮች ከቅኝ ገዥዎቻቸው ነፃ ለመውጣት የተንቀሳቀሱበትና ነፃ ከሆኑ በኋላም የይስሙላም ቢሆን ዴሞክራሲያዊ ምርጫ እያካሄዱ በነበረበት



ሁኔታ የኢትዮጵያ ሕገ-መንግስት ግን ንጉሠነገስቱን "ኃይሉ የማይደፈር፣ የማይገሰስ" በሚል የእድሜ ልክ ሕግ ሆኖ ይቀጥላል ብለው መታተራቸው አንዱና ዋናው ጥፋታቸው ሲሆን፤ ዘውዱ እንደተከበረ ሆኖ ከዘውዱ በታች እንኳ ዴሞክራሲያዊ መንግስት ለመመስረት የሚቻልበትን አማራጭ አልተጠቀሙበትም፡፡ የጳጳሡን ግዝትም ሆነ "በእግዚአብሔር የተሾሙ" የሚለውን ቃል እንደጥንቱ ህዝብ ምሁሩም ጠብቆትና አክብሮት ይቀጥላል ብለው ማሰባቸውም በዘመናቸው ያሳዩት የመጀመሪያው "የዋህነታቸው" ሆኖ የሚመዘገብ ነው፡፡ እነዚህን የመሰሉ የለውጥ አስተሳሰቦች በተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ዘንድ ሊብላላ እንደሚችል ቢያስቡም፤ ጥቂቶች ሊጠቁሟቸው ቢሞክሩም "የኢትዮጵያ ህዝብ ለዚያ አይነቱ አስተዳደር ልምድ የለውም፤ ኃላፊነቱን ለመሸከም ገና አልደረሰም" የሚል ምላሽ እየሰጡ፤ ነገር ግን በጎን የሁኔታውን አስጊነት ተመልክተው ወደመፍትሔው ከማምራት ይልቅ የመረጡት መንገድ ሥልጣናቸው ከዚህ መሰሉ አደጋ ተጠብቆ የሚቀጥልበትን ሁኔታ ማመቻቸት ሆነ፡፡ ከዚሁም ጋር ተያይዞ የአስተዳደር ክሽፈት ተፈጠረና አልደረሰም ያሉት ህዝብ ደርሶ ጠበቃቸው፡፡ ከዚህ አንፃር የጃንሆይ ጥፋት በአፍቃሬ ስልጣንነታቸው ስር ተጠቃሎ የሚገለፅ ሆነ፡፡

በጃንሆይ ላይ የተነሱ አመጾች

ጃንሆይ ለአመፅ ብርቅ አይደሉም፡፡ ከስደት ከተመለሱ በኋላ በሰጡት ሹመትና ሽልማት "ፍትሐዊ አይደለም" በሚል ተገቢ መነሻ በርካቶች ባይሆኑም አምፀዋል፡፡ ለምሳሌ ጀግናው የጎጃም አርበኛ በላይ ዘለቀ የንጉሡን ሹመት አሰጣጥ ተቃውሟል፡፡ በጎጃም የጠላትን ጦር ሲያንቀጠቅጥ የነበረ የተዋጣለት ጀግና ነው በላይ ዘለቀ፡፡ ከእርሱም ጋር ልጅ ኃይሉ በለው፣ ደጃዝማች መንገሻ ጀንበሬና ደጃዝማች ነጋሽ በዛብህ በድፍን ጎጃም በአርበኝነት ይታገሉ ነበር፡፡ ከበላይ ዘለቀ በስተቀር ሦስቱ የነገስታት ዘር ናቸው፡፡ ከነፃነት በኋላ በ1934 ዓ.ም ጃንሆይ ከጎጃሙ ንጉስ ተክለሐይማኖት ለሚወለዱት ለልጅ ኃይሉ በለው ከራስ ማዕረግ ጋር የጎጃም ጠቅላይ ገዥነት፣ ለደጃዝማች መንገሻ ከቢትወደድ ማዕረግ ጋር የጎጃም ምክትል ጠቅላይ ገዥነት፣ ለደጃዝማች ነጋሽ ከቢትወደድ ማዕረግ ጋር የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት ፕሬዝዳንትነትን ሲሰጡ ለልጅ በላይ ዘለቀ ደግሞ ከደጃዝማች ማዕረግ ጋር በጎጃም የቢቸና አውራጃ ገዥነትን ሾሙት፡፡

በአርበኝነቱ ዘመን መሪ የነበረውና በጀግንነት ማንም ያልደረሰበትን ሰው ከእነርሱ ያነሰ ሹመት ሲሰጡት ቅር ተሰኘ፡፡ የንጉሡን ትዕዛዝና ሹመት ውድቅ በማድረግ ከተከታዮቹ ጋር የጎጃሙን የሶማ ኮረብታን ይዞ አልገዛም አለ፡፡

ሚያዚያ 16 ቀን 1935 ዓ.ም የመንግስት ጦር ዘምቶበት የተኩስ ልውውጥ ተደርጎ 38 ሰዎች ሞተው 92 ቆሰሉ፡፡ከሦስት ወር በኋላ ከ19 ተከታዮቹ ጋር ተማርኮ ወደ አዲስ አበባ መጣ፡፡የእስራት ቅጣት ተፈረደበትና ወሊሶ ሄዶ ታሰረ፡፡ ከወሊሶ ሲያመልጥ በድጋሚ ተያዘና ወንድሙን እጅጉ ዘለቀን ጨምሮ ከሌሎች እስረኛ ከሆኑ ባንዳዎች ጋር በአዲስ አበባ ታሰረ፡፡ታህሳስ 19 ቀን 1937 ዓ.ም ከ5 እስረኞች ጋር ከእስር ቤት አምልጠው ወደ ጎጃም ለመገስገስ ጉዞ ሲጀምሩ በ3ኛው ቀን ሱሉልታ ላይ ተይዘው እንደገና ወደ አዲስ አበባ አመጧቸው፡፡ የጦር ፍርድ ቤት የወሰነው የሞት ቅጣት በጥር 5 ቀን 1937 ዓ.ም ተግባራዊ ሆነና በአደባባይ በስቅላት ተቀጣ፡፡

ሌላው አደገኛ አመፀኛ ደጃዝማች ታከለ ወልደሐዋርያት ናቸው፡፡ንጉሡ ስደትን ከመረጡ ጊዜ ጀምሮ ለ30 ዓመታት ያህል መንግስታቸውን ለመፈንቀል ሲጣጣሩ ነው የኖሩት፡፡እኚህ ሰው ሲታሰሩ፣ሲፈቱ፣ሲሾሙ፣ሲሻሩ፣ሲያሴሩ ነው ያሳለፉት፡፡

በመጀመሪያ አርበኞችን አስተባብረው አሳድመዋል ተብለው ታሰሩ፡፡ እንደገና ተፈትተው በ1938 ዓ.ም ምክትል አፈ-ንጉስ ሆነው ተሾሙ፡፡ አመት ሳይቆዩ ሌላ ተመሳሳይ ሴራ ሲጠነስሱ ተደረሰባቸውና ታስረው 7 ዓመታትን አሳለፉ፡፡ ተፈቱና የአገር ግዛት ምክትል ሚኒስትርና የአፈ-ንጉሥነቱ ስልጣን ተመለሰላቸው፡፡ ይሄ ሁሉ ሲሆን ጃንሆይ ከአሁን አሁን ይበርድላቸዋል ብለው በመገመትና ጀግንነታቸውንም በደንብ ስለሚያውቁት ነበር የሚታገሷቸው፡፡ በመጨረሻ በ1962 ዓ.ም ጃንሆይ የሜታ አቦ ቢራ ፋብሪካን ለመጎብኘት ሲሄዱ ሰበታ አካባቢ ፈንጅ አጥምደው ንጉሡን ከነመኪናቸው ድምጥማጣቸውን ሊያጠፉ ተዘጋጁ፡፡ ሁኔታው ቀድሞ በጥቆማ ተደረሰበትና ከሸፈ፡፡ ደጃዝማች ታከለ ቤታቸው መሽገው ነበርና በወታደር ተከቦ ተኩስ ተከፈተ፡፡ እጅ አልሰጥም ብለው ሲዋጉ ቆይተው ሊያዙ ሲሉ ራሳቸውን ገደሉ፡፡

የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት ፕሬዝዳንት ሆነው የተሾሙት ቢትወደድ ነጋሽ በዛብህም እንዲሁ በንጉሡ ላይ አምፀው ነበር፡፡ ወታደራዊ መኮንኖችን አስተባብረው ንጉሡን በመግደል የሪፐብሊክ መንግስት ለመመስረት እንደነበር ይነገራል፡፡ ይህም ልክ እንደ ደጃዝማች ታከለ አይነት መሆኑ ነው፡፡ በመጨረሻ ግን በ1943 ዓ.ም ይሄው ሴራ ተደርሶበት በእስራት ተቀጡ፡፡ የእነዚህን አድመኞች እንቅስቃሴ ሁሉ በቁጥጥር ስር ያውል የነበረውና ለፍርድ ያቀርብ የነበረው ኮሎኔል መንግስቱ ንዋይ ነበር፡፡ የ1943ቱን አመፅ በቁጥጥር ስር ካዋለ በኋላ ደግሞ በ10 ዓመቱ ብርጋዴር ጄኔራል መንግስቱ ንዋይ ራሱ ከወንድሙ



ከገርማሜ ንዋይ ጋር ሆኖ የታህሳስ 5 ቀን 1953 ዓ.ምቱን መፈንቅለ መንግስት ሞከረ፡፡

ይህ ሙከራ ከላይ እንዳየናቸው በግል ኩርፊያና በመሳሰሉት ሳይሆን፣ምሁራዊ አስተሳሰብ የታከለበትና ፖለቲካዊ፣ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ መሠረት የነበረው ስርነቀል ለውጥን የሚሻ እንደነበር ከአነሳሱ ያስታውቅ ነበር፡፡ አነሳሱም ነው ለዘላቂ ለውጥ ፍለጋ ብዙዎችን እንዲነቃቁ በር የከፈተው እንጂ ከዚህ ጊዜ በፊት ምሁሩም፣ጦሩም፣ሠራተኛውም ሆነ ሌላው ምን አይነት ለውጥ እንደሚፈልግ ለይቶ አያውቀውም ነበር ለማለት ይቻላል፡፡ቢያውቅም እንዴት መነሳት እንዳለበት አያውቅም ወይም አይደፍርም፡፡በአጠቃላይ የንጉሡ ዙፋን እንደሚነቃነቅ የተደረሰበት ዘመንና ሁኔታ የተከሰተው በመንግስቱ ንዋይ ሙከራ ነው፡፡

ገርማሜ ንዋይ በአገር ውስጥም በአሜሪካም በዘመናዊ ትምህርት ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሰ የዚያ ዘመን ምሁር ነበር፡፡ ብርጋዴር ጄኔራል መንግስቱ ነዋይም ከወረራው በፊት ተጀምሮ በነበረው ዘመናዊ የጦር ትምህርት ቤት መሰልጠን ጀምሮ የነበረና ከጥቁር አንበሳ አባላት ውስጥ አንዱ የነበረ አርበኛ ነው፡፡ ከነፃነት በኋላም በወታደራዊ ማዕረጎች በየጊዜው እያደገ የንጉሡ ታማኝ ሆኖ ጄኔራልነት ደርሷል፡፡ በዚህም የክቡር ዘበኛ ክፍለ ጦር አዛዥ ሆኗል፡፡

የጎሳቡ አፍላቂ ገርማሜ እንደሆነ የሚነገርለት ይህ መፈንቅለ መንግስት የኮሎኔል ወርቅነህ ገበየሁ /የፀጥታ ኃላፊው/ና የመንግስቱ ንዋይ የጦር ትብብርን አግኝቶ ጥቂት ተራምዶ ነበር፡፡ በሬዲዮም በአልጋወራሽ አስፋወሰን ኃይለስላሴ ንባብ አዋጅ አሰምተው ነበር፡፡

"የኢትዮጵያን ማኅበራዊና ብሔራዊ የእድገት እርምጃ ጥቂት ራስ ወዳድ ግለሰቦች ወደኋላ አስቀርተውታል፤ በቅርቡ የተነሱ የአፍሪካ አገሮች በስልጣኔና በእድገት ጥለውን ሄደዋል፣ አጠቃላይ አገዛዙ ሁሉንም የኅብረተሰብ ክፍል እየጎዳ ነው፤ የህዝቡ ቁጭት ለዚህ ተግባር አነሳስቶናል፣ ፋብሪካዎችን እናበዛለን፣ ትምህርት ቤቶች ይስፋፋሉ፣ የወታደር ደመወዝ ይጨመራል፣ ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን ሁሉ እናከብራለን..." የሚል ማኑፌስቷቸውን ታህሳስ 5 በሬዲዮ አሰራጩ፡፡ ብዙ ባለሥልጣናትንም አሰሩ፡፡ ሆኖም የክቡር ዘበኛና የፖሊስ ሠራዊት ብቻውን በቂ አልነበረም፡፡



ብርጋዴር ጄነራል መንግስቱ ነዋይ እና ገርማሜ ነዋይ

ጃንሆይ በዚህ ጊዜ ለጉብኝት ከሄዱበት ከላቲን አሜሪካ ወዲያው ተመለሱ፡፡ ጳጳሱም ገዘቱ፡፡ በጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኤታማዦር ሹም የተመራው ጦር ከሁለት ቀን የተኩስ ልውውጥ በኋላ አመፁን ተቆጣጠረው፡፡ ንጉሡም ከከሸፈ በኋላ ነበር ኢትዮጵያ የደረሱት፡፡እነመንግስቱም መክሸፉን ሲያውቁ በገነተ ልዑል ቤተ-መንግስት አስረዋቸው የነበሩትን ሹማምንት ገድለው ለማምለጥ ሞከሩ፡፡ ኮሎኔል ወርቅነህ ገበየሁ ራሱን ገደለ፡፡ገርማሜ ዝቋላ ደርሶ ከሚያድኑት ጋር ተታኩሶ ሞተ፡፡መንግስቱ ቆስሎ ተይዞ ከመጣ በኋላ ለፍርድ ቀርቦ በስቅላት ተቀጣ፡፡ ትግሉ ግን ቀጠለ፡፡

እነ መንግስቱ ንዋይ በሬዲዮ ባስተላለፉት ቃል በየትኛው ዘርፍ የትኛው ባለሥልጣን እንደሚሾም ሳይቀር ለመግለፅ ሞክረው ነበር፡፡ የሚገርመው ግን አድመኞችን ደግፎ ሰልፍ የወጣው ህዝብ ጃንሆይ ሲመጡ በእልልታ መቀበሉ ነው፡፡ እናም ጃንሆይ በደስታ ወደዙፋናቸው ተመለሱ፡፡ ሴረኞች ያሏቸውን እያስለቀሙ ቀጡ፡፡ ታማኝ ሆነው ያከሸፉትን ሾሙ ሸለሙ፡፡ እነ ገርማሜ ንዋይ ለሠራዊቱ ገብተውት የነበረውን የ"ደሞዝ ይጨመራል" ቃል መሠረት በማድረግ ወታደሩ እንዲፈፀምለት ደጋግሞ መጠየቁን የቀጠለው ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ነው፡፡ ከረጅም ጊዜ በኋላ ለወታደሩም ለመኮንኖችም ደሞዝ ተጨመረ፡፡ ወቴ "አሁንም ጨምሩ" እያለ አላስቀምጥ አለ፡፡ ቀጠለ ሂደቱ…፡፡

በአጠቃላይ የ1953ቱ ሙከራ የንጉሡን ልዩ ካቢኔ ዋጋቢስነት ከማሳየት ባለፈ፣ የሁሉንም የአገዛዙን ተቃዋሚዎች ያለልክ አነሳስቶ ያለፈ ሆነ፡፡ ጃንሆይም አመፁን ያስነሱትን የግለሰቦችን ከሃዲነት እንጂ ጥያቄዎቻቸውን ለመመርመር አልሞከሩም፡፡ አገዛዛቸውን እርምት ሳያደርጉበት ቀጠሉ፡፡



ከ1934 ዓ.ም ጀምሮ በተለያዩ ግዛቶች በተለይ ከመሬት ጋር በተያያዘ አመጾች ይነሱ ነበር፡፡ አንዳንዱ በትክክለኛ ብሶት ያምፃል፡፡ ሌላው ኢጣሊያ ጥሎት የሸሸውን መሣሪያ ወድቆ ስላገኘ ብቻ ያምፃል፡፡ አንዳንዱ በግብር ሲያኮርፍ የቀረው በሹመት አነሰኝ ያኮርፍና አስተባብሮ ያሳምፃል፡፡ በተለያዩ ግዛቶች ከተነሱ የገበሬ አመጾች ውስጥ የባሌ፣ የጌዲኦ፣ የራያና አዘቦ፣ የየጁ፣ የጎጃምና የትግራይ አመጾች ይጠቀሳሉ፡፡ ሌሎቹ ሁሉ ስር ከመስደዳቸው በፊት በፍጥነት ሲረግቡ፤ የባሌው አመፅ ግን ለረጅም ጊዜ የቆየና መንግስትን የተፈታተነ ነበር፡፡

የባሌ አመፅ በገበሬው ላይ የሚደርሰውን ግፍ መነሻ ያደረገና የባላባቱን ሕገወጥ ምዝበራና ዝርፊያ፣ እንዲሁም የመሬት ግፊት መሠረት ያደረገ ነው፡፡ የመሬት ቀላድ ሲጣል ብዙዎች ለጭሰኝነት ተዳርገዋል፡፡ በየጊዜው እያደገ የሄደውን ግብር ለመክፈል የሚያስችል በቂ መሬትም ሆነ ምርት አልነበራቸውም፡፡

በባሌም ብቻ ሳይሆን በአጎራባች ግዛቶች ብዙ የመንግስት ሹማምንት ርስት ተሰጥቷቸው ስለሰፈሩ የአካባቢውን ነባር ህዝብ በብዝበዛ ተጫኑት፡፡ ከአቅማቸው በላይ ሲሆን መሬታቸውን እንዲያስረክቡ ሹማምንቱ ያስገድዷቸዋል፡፡ የሹማምንቱ የፖለቲካና የኢኮኖሚ የበላይነት በመሬት ላይ ብቻ ሳይሆን በሃይማኖትና በባህል ላይም ተከሰተ፡፡ ይህም ለረጅም ጊዜ የቆዩ ተቃውሞ ያስነሳ ቢሆንም በቀላሉ ሲረግብ ነበር፡፡ በ1952 ዓ.ም ባሌ ከሐረርጌ ተቆርጦ ራሱን የቻለ ግዛት ወይም ክፍለ አገር በሆነ ጊዜ የዶሎ፣ የመንደዩ፣ የዋቤ፣ የገናሌ፣ እና የኤልከሬ በሚል በ5 አውራጃዎች ተከፈለ፡፡ ኤልከሬ ሙሉ በሙሉ የሶማሌ ዘላን ማኅበረሰብ ክልል ነበር፡፡ ሌሎች 4ቱ ደግሞ የኦሮሞ ብሔረሰብ ክልሎች ናቸው፡፡ እነዚህ ህዝቦች የመንግስትን ሹማምንት ጫና አሜን ብለው የሚቀበሉ አልሆኑም፡፡ ቀደም ካለው ጊዜ ጀምሮ የተጨቆኑት አርሶአደሮችና አርብቶ አደሮች በ1955 ዓ.ም ወደተደራጀ አመፅ አመሩ፡፡ አመፁንም በአውራጃና በክፍለ አገር ደረጃ እያዋቀሩና ከጎረቤታቸው ከሱማሊያ መንግስት እርዳታ እየተደረገላቸው ራሳቸውን ሻለቃ፣ ኮሎኔል፣ ጄኔራል እያሉ እየሾሙ የደፈጣ ውጊያውን አጧጧፉት፡፡

ከእነዚህም ውስጥ የዶሎው /ከባሌ ክፍለ አገር የአንዱ አውራጃ/ ተወላጅ "ጄኔራል" ዋቆ ጉቶ በዋናነት ሲጠቀስ፤ የኤልከሬው "ኮሎኔል" ካህን አብዲ፣ የዋቤው "ኮሎኔል" ሁሴን ቡኒ፣ የገናሌው "ኮሎኔል" ኡማር ከቤሎ ዋና መሪዎች ሆነው የአካባቢው ማኅበረሰብ የዓላማቸው ተባባሪ ሆኖ ከጎናቸው በመሰለፍ በመንግስት ሹሞች ላይ ለ7 ዓመት ያህል ጥቃት ሲያደርሱ ቆይተዋል፡፡

የሱማሊያ መንግስትም አጋጣሚውን ተጠቅሞ "የሶማሌ ነፃነት እንቅስቃሴ" ሆኖ እንዲቀጥል ለማድረግ ሞክሮ ነበር፡፡ እንደ ፕሮፌሰር

ላጺሶ አገላለፅ፣ "በ1956 ዓ.ም ንጉሡ በስራ ጉብኝት እስከ ባሌ ክፍለአገር በመሄድ 1ኛ. በሌላ ደቡብ ክፍላተ አገር ድሮ እንደተደረገው ሁሉ አሁን ለባሌም ባላባቶች ከመሬት የባላባት ሲሶ እንደሚሰጣቸው ቃል ገቡ:: 2ኛ. ከ1945 - 1954 ዓ.ም የግብር ውዝፍ ምክንያት "ግብረ ጠል" ተብሎ በመንግስት የተወረሰው መሬት (ለዓመታት ግብር ያልተከፈለበት ሆኖ ሲገኝ ይወረስ ስለነበር) ለህዝብ እንደሚመለስለት ተናገሩ:: 3ኛ. ለብዙ የክፍለአገሩ ተወላጆች ሹመትና ማዕረግ ሰጡ:: 4ኛ. የሼክ ሁሴንን መስጊድ ጎብኝተው ወደአዲስ አበባ ተመለሱ::

ይሁን እንጂ በአመፅ መንፈስና ተግባር አንዴ ከተቀሰቀሰ በኋላ ለረጅም ዘመን በጉልተኞችና ባለሥልጣኖች ጭቆና በኃይል የተመረረው የባሌ ህዝብ በንጉሡ ጉብኝትና መልካም ቃላት ከአመፅ እርምጃው አልተገታም:: በአጭሩ ከ1956 - 1959 ዓ.ም የክፍለ አገሩ እንደራሴ በፊትአውራሪ ወርቁ እንቁስላሴ መሪነት የባሌ ክፍለአገር ጉልተኞችና ባለሥልጣኖች ከፖሊስና ከብሔራዊ ጦር ጋር የህዝቡን አመፅ መቆጣጠርና ማቆም ፈፅሞ አቃታቸው:: በመሆኑም እንደራሴው እንዲነሳ ተደርጎ በታህሳስ 1959 ዓ.ም የባሌ አራቱ የኤልከሬ፣ የዶሎ፣የገናሌና የዋቤ የአመፅ አውራጃዎች ከአጎራባቹ የቦረና አውራጃ ጋር በወታደር ስር እንዲሆኑ ተወሰነ::" በ4ኛ ክፍለ ጦር ስር መሆኑ ነው::

እናም በክፍለ ጦሩ አዛዥ በጄኔራል ጃገማ ኬሎ አመራር ስር ከሆኑ ጊዜ ጀምሮ ልዩ ዲፕሎማሲያዊ ጥረት ተደርጎ በ1962 ዓ.ም ጄኔራል ዋቆ ጉቶ ለመንግስት እጁን ሲሰጥ የባሌና የአጎራባቾች አመፅ ተገታ::

በአብዮቱ መዳረሻ ከአገሪቱ ገበሬዎች ውስጥ ከአጠቃላዩ ሲሶ ያህሉ ጭሰኛ ነበሩ:: "ጭሰኛ" ማለት የራሱ መሬት የሌለውና በሌሎች መሬት ላይ በጉልበቱ እያገለገለ የሚኖር፣ በማንኛውም ሰዓት ባለቤቱ ሊያፈናቅለው የሚችል አገልጋይ ማለት ነው:: "ተቀጣሪ" ማለት ነው::

"ገባር" ሲባል ደግሞ በጃንሆይ ጊዜ "ግብር ከፋይ" ማለት ነው::

"ፊውዳል" ማለት ደግሞ መሬትን በሞኖፖል ይዞ እንዳሻው የሚያደርግ አገዛዝ ማለት ነው:: ጥቂት ምሁራን የጃንሆይን አገዛዝ "ፊውዶ ቡርዧ" ብለው ወፈር አድርገው ይጠሩታል:: ከፊል ካፒታሊዝም ማለት ነው::

ወዝአደር፣ ላብአደር፣ ሠርቶአደር የሚባሉ የዚያ ዘመን ስያሜዎችም ግልፅ ናቸው:: በጃንሆይ ጊዜ ባላባቱና ባለሐብቱ የያዙት ሰፋፊ መሬት እንዳለ ሆኖ፣ ተራ ገበሬዎች ደግሞ 1 ሔክታር ማሳ ነበራቸው:: ከአሁኑ ጋር ሲነፃፀር ባለፀጋ የሚያሰኝ ይዞታ ነበር:: ለማንኛውም በዚያ ጊዜ ገበሬው ሁሉ ከየአቅጣጫው ጭቆናው በዝቶበት ስለነበር አመፀ::



በየካቲት ወር 2002 ዓ.ም ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ /የቀድሞው የኢህፌዲሪ ፕሬዝዳንት/ በአንድ ስብሰባ ላይ ለስራ ተገኝቼ ነበርና እንዲህ ሲሉ አደመጥኩ "ከ1950ዎቹ ጀምሮ መሬት ላራሹን ሳቀነቅን ኖሬያለሁ፣ አሁንም ማሰብ እስካቆም ድረስ ይሄንኑ አቋሜን አልለቅም"

በጃንሆይ ላይ ከተነሳው ዘርፈ ብዙና ከየአቅጣጫው የተቀጣጠለው አመፅ ይሄን ያህል ፈታኝ አልነበረም:: በከፍተኛ ሁኔታ ስርዓቱን የተፈታተነው ተማሪው ነው:: የተማሪው ተቃውሞ ከ1953 ዓ.ም ጀምሮ ውስጥ ውስጡን ሲብላላ ቆይቶ፣ ከ1957 ዓ.ም በኋላ ወደ አደባባይ በመውጣት የተቃውሞ ሰልፍ ማድረግ ተለመደ:: በድርድር የማይከሽፍና ስር ነቀል ለውጥ የሚፈልግ ሆኖ የተነሳው ምሁር እስከመጨረሻው የሚያቆመው ኃይል ጠፍቶ አብዮቱን አሳብጧል::

በዩኒቨርሲቲው ውስጥ የተለያዩ ማኅበራት በተማሪው እየተመሰረቱ፣ የክርክር መድረኮች እየተዘጋጁ፣ ለከፍተኛ ትምህርት ወደሌላው ዓለም የተላኩ ምሁራንም ተመሳሳይ ማኅበር እየመሠረቱ ስርዓቱን በእጅጉ በመተቸት ተግባር ላይ ተጠመዱ::በተማሪው ልሳን በሆኑ መጽሔቶች የተለያዩ ፖለቲካዊ ትንታኔዎች ይቀርቡ ጀመር::ርዕዮተ ዓለማዊ መፈክሮችና መግለጫዎች በየጊዜው ይሰራጫሉ::

እንዲህ እንዲያ እያሉ በ1957 "መሬት ለአራሹ" ብለው ሰልፍ ወጡ:: ከመንግስት የፀጥታ ኃይሎች ጋር ፊት ለፊት መጋተር የተጀመረውም በዚሁ ዘመን ነበር:: በየጊዜው የሚያነሱት አጀንዳ የተለያዩ እየሆነ ቀጠለና በ1961 ዓ.ም "የትምህርት ፖሊሲው ይሻሻል" የሚል ጥያቄ ሲያነሱ ይህ ጉዳይ ከዩኒቨርሲቲው ማኅበረሰብ አልፎ በ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችም ድጋፍ ያለው ጥያቄ ሆነ:: በ1962 ዓ.ም በደንብ ያላብላሉትን ጥያቄ ይዘው የወጡት ወገኖች ነበር መንግስትን ቁጡ ያደረገው:: ይህም በግርግር መሃል ድንገት የተሰነዘረና "ብሔር ብሔረሰቦች የራሳቸውን እድል በራሳቸው መወሰን አለባቸው" የሚል ነው:: የጃንሆይ መንግስት ከተራ ድብደባና ግርፋት አልፎ ጠንከር ያለውን እርምጃ ወሰደ:: በታህሳስ 19 ቀን 1962 ዓ.ም ስመጥር የሆነው የተማሪዎች መሪ ጥላሁን ግዛው በአደባባይ ተመታ::(የጥላሁንን መመታት በሚመለከት ሁለት ነጥቦች ይነሳሉ::አንዱ ከመንግስት ታጣቂዎች በተተኮሰ ጥይት የሚል ሲሆን፤ሌላውና ሰፊ ተቀባይነት አግኝቶ ያለው ገለጻ ደግሞ ወደፊት ስውር አሰራራቸውን በስፋት በምናይላቸው የአመጽ አነሳሽ በነበሩ የኤርትራ ድርጅት አባላት አማካኝነት በግርግሩ መሀል በረቀቀ ዘዴ እንደተመታ ነው)በዚህ ጊዜ ተማሪው "የጀግናችን ሬሣ እንቀብራለን" በሚል ወደ የካቲት 12 ሆስፒታል ሆ ብሎ ሲነጉድ ጥላሁን አርፏል::አመፁ ተቀጣጥሎ ቀጠለ:: የፀጥታ ጥበቃ አባላቱ ተኩስ ከፍተው

ጥቂቶች ሲገደሉ ብዙዎች ቆሰሉ፡፡ ዓለም አቀፉ ተቃውሞም እጅግ እየበረታ ሄደ፡፡



የጸጥታ ጠባቂዎች እና የተማሪዎች ግብግብ

ገሚሱ አገር ውስጥ ሆኖ ሲፋለም የቀረው በየውጭ አገሩ እየፈለሰ ማኅበራቱን ተቀላቀለ፡፡ አመፁ የአውሮፕላን ጠለፋንም ያካተተ ነበር፡፡ ህዳር 29 ቀን 1965 ዓ.ም እነዋለልኝ መኮንን እና ማርታ መብራቱን የመሣሠሉ አደራጅና አስተባባሪዎች ወደ ኤርፖርት አምርተው ፕሌን ውስጥ ከገቡ በኋላ ጠለፋውን ከመተግበራቸው በፊት መንግስት ባዘጋጃቸው የጠለፋ አክሻፊ ኃይሎች እዚያው በጥይት ተደብድበው ሞቱ፡፡

የኢትዮጵያውያን የፖለቲካ ልዩነት፣ የፓርቲ ምስረታ፣ የርዕዮት መለያየት፣ በቡድን መደራጀትና ፖለቲካዊ አጀንዳ አንስቶ መንግስትን የመሞገት ተግባር ምንጭም ሆነ አፈሳሰሱ የሚነሳው ከዚሁ ከዩኒቨርሲቲው ማኅበረሰብ ሆነ፡፡ በኢትዮጵያ ታሪክም ለመጀመሪያ ጊዜ ያልታጠቀ ኅብረተሰብ መንግስትን ተቃውሞ ድምፁን ያሰማበት ዘመን ተከሰተ፡፡ የመጀመሪያዎቹ ኢትዮጵያዊ ምሁራን ምንም እንኳ የተቀረፁት በምዕራባውያን ትምህርት የነበረ ቢሆንም፤ የምዕራባውያንን የቡርዣ አገዛዝ አንሸከምም አሉ፡፡

ሐሮልድ ማርክስ "THE ULTIMATE IRONY" ብለው እንደገለፁት ጃንሆይ በስኬታቸው የመውደቃቸው ጉዳይ ግልፅ እየሆነ ሄደ፡፡ በወቅቱ የጃንሆይ መንግስት በተማሪዎች ላይ ጨከን ያለ እርምጃ ወሰዷል፡፡

ተማሪውም በተጨከነበት ቁጥር የታጋይነት መንፈሱ እያደገ የማይገሠሠውን ማዕረግ ገሶ፣የማይደፈረውን ክብር ደፍሮ፣ የጃንሆይን ዙፋን ገዝግዞ አብዮቱን አሳበጠ፡፡ ነገር ግን ሳይፈነዳ ጥቂት ጊዜ ይቆይ ዘንድ የአገዛዙ (የዘውዱ) ጠበቃ መስለው የራሳቸውን የዘረፉ ጊዜ



ለማራዘም የሚሹ ባለስልጣናት መፍትሔው ኃይል እንደሆነ ገልፀው እሱኑ ተገበሩት፡፡

ጃንሆይ እና ኪነ-ጥበብ

በጃንሆይ ጊዜ ዘመናዊ ማተሚያ ቤቶች ተከፍተዋል፡፡ የቴአትርና የስነ-ጥበብ ትምህርቶች እንዲሁም የስነ-ጽሁፍ ዲፓርትመንቶች ተከፍተው ትምህርቱ በአገር ውስጥ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት መሰጠት ጀምሯል፡፡ ይህ ከመሆኑ በፊትም በጋዜጠኝነትና በሌሎች ዘርፎች ወደ ውጪ አገር ሄደው እንዲማሩ የጃንሆይ መልካም ፈቃድ ሆኖ ተምረው የተመለሱ ኢትዮጵያውያን ነበሩ፡፡ ከዚሁም ጋር ተያይዞ ጋዜጦች፣ መፅሔቶች፣ የልብወለድና የኢ-ልብወለድ መጽሐፍቶች፣ የታሪክ መጽሐፍትና የግጥም መድብሎች እየታተሙ ለአንባብያን ይደርሱ ነበር፡፡ ቴአትር ቤቶችም ተከፍተው በየመድረኩ ተውኔቶች ይቀርቡ ነበር፡፡

ምንም እንኳ እንደዛሬዎቹ አፍሪካውያን መሪዎች አገዛዛቸውን በብዕር የሚያወግዙ ደራሲያንና ፀሐፊ ተውኔቶች በገዥው አካል የተለመደው ኃይለኛ በትር በጃንሆይ ጊዜም መኖሩ ባይዘነጋ፣ በተጠቀሰው ዘርፍ በርካታ ስራዎች የተሰሩት በጃንሆይ ዘመን ነው፡፡በዘርፉ የጃንሆይን አገዛዝ በጥልቀት የሚተቹ የኪነ-ጥበብ ውጤቶች ይታገዱ እንደነበር የመታወቁን ያህልም፤ለዘብተኛ ትችት የያዙት ሳይታገዱ መቀጠላቸው አይካድም፡፡ጃንሆይንና አገዛዛቸውን የሚያሞካሹት በርክተው የመገኘታቸውን ያህልም፤የሚያጣጥሉዋቸውም በጥቂቱ እንደነበሩ ግልፅ ነው፡፡

ገጣሚያን፣ደራሲያንና ፀሐፊ ተውኔቶች በስራቸው የመታሰር የመንገላታታቸውን ያህልም በይቅርታ የታለፉ በርካታ የአገዛዙ ተቺ የሆኑ ባለሙያዎች ነበሩ፡፡ በዚህ መሰሉ እንግልት ሞራላቸው የተነካ የኪነ-ጥበብ ሰዎች እንደነበሩ ሁሉም፤ በዘርፉ ባበረከቱት አስተዋፅኦ የማበረታቻ ሽልማት ከጃንሆይ እጅ የተቀበሉ ሞልተዋል፡፡ ለአብነትም የ1952ቱ የብላቴን ጌታ ፀጋዬ ገብረመድህን ሽልማትን መጥቀስ ይቻላል፡፡ምንም ቢባል ግን በኢትዮጵያ ታሪክ ለዚህ ዘርፍ የጃንሆይን ያህል ትኩረት ሰጥቶ የተንቀሳቀሰ መንግስት ኖሮ አያውቅም፡፡ ቴአትር ቤቶችን ብቻ ነጥለን ብናይ በጃንሆይ ጊዜ የተመሠረቱት ናቸው ዛሬም ድረስ አገልግሎት እየሰጡ ያሉት፡፡

ከጃንሆይ በኋላ በተነሱ የኢትዮጵያ መንግስታት አንድም ቴአትር ቤት ተገንብቶ አልተጨመረም፡፡(በቅርቡ በእቅድ ደረጃ ሊገነባ የታሰበው የብሔራዊ ቴአትር አዲስ ተጨማሪ ህንፃ ምናልባት ተግባራዊ ከሆነ ብቻ የጃንሆይ ውጤት ያልሆነ ቴአትር ቤት ሆኖ ይመዘገባል) በተረፈ ያሉት ሁሉ የጃንሆይ ዘመን ውጤቶች ናቸው፡፡

በዘመነ ዛግዌ ብልጭ እንዳለ የሚነገርለትና በጎንደሩ ንጉስ በአፄ ዳዊት ዘመን በቤተ-መንግስት ደረጃ በኢትዮጵያ እየተለመደ የሄደው ቴአትር፤በዳግማዊ ምኒልክ ጊዜ ዘመናዊ ቅርፅ ይዞ በትምህርት ቤቶች አካባቢ ቀጥሎ ነበር፡፡

ከትምህርት ቤቶች አልፎ ቴአትር (ድራማ) ወደ መድረክ የወጣው ግን በጃንሆይ ዘመን በ1927 ዓም በተቋቋመው በአገር ፍቅር ማኅበር አማካኝነት ነው፡፡ በወቅቱ ኢጣሊያ ኢትዮጵያን ከመውረሯ አንድ ዓመት ቀደም ብሎ የስነልቦና ጦርነት ተጀምሮ ነበር፡፡ ይህም በተለያዩ የሐሰት ፕሮፓጋንዳዎች የኢትዮጵያን ህዝብ የትግል መንፈስ አዳክሞና አንድነቱን ሸርሽሮ፣ ወረራው በሚጀመርበት ወቅት ህዝቡ ከመንግስት ጎን ቢቆም ከሞት በቀር የሚያተርፈው አንዳች ነገር እንደማይኖር የሚገልፅ ሆኖ በኢጣሊያ መንግሰት እየተዘጋጀ የሚቀርብ ነበር፡፡ ከዚያ ይልቅ የኢትዮጵያ ህዝብ ሊያሰለጥነው ከሚመጣ ቅኝ ገዥ አገር ጋር ቢወዳጅ ትርፋማ እንደሚሆን ለማስገንዘብ የሚጠቀሙበት የፕሮፓጋንዳ ስልት ነበር፡፡

የኢጣሊያ የፕሮፓጋንዳ ስራ በህዝቡ ዘንድ የሚያሳድረው ተፅዕኖ ከባድ መሆኑን በመገንዘብም ፕሮፓጋንዳን በፕሮፓጋንዳ የማክሸፉን ስራ ኢትዮጵያውያኑ ጀመሩት፡፡ በ1927 ዓ.ም "የኢትዮጵያ ሀገር ፍቅር ማኅበር" ተቋቋመና በየሳምንቱ እሁድ ስብሰባ እየተደረገ፤ ለህዝቡ ኪነ-ጥበባዊ ለዛ ባለው አቀራረብ የአገርን ፍቅር የሚያስታውሱ፣ የጀግንነት መንፈስን የሚቀሰቅሱ ንግግሮች፣ ግጥሞች፣ መጣጥፎችና መዝሙሮች ይቀርቡ ጀመር፡፡በተጠቀሰው ጊዜ የኢጣሊያን ወራሪ ጦር በኦጋዴን ድንበር መክተው የመለሱት የእነደጃዝማች ኡመር ሰመተር ጀግንነት ሲሰማም፤ የአገር ፍቅር ማኅበር ከነበረበት የበለጠ ተሻሽሎ ብዙ ታዳሚዎችንም እያፈራ ተግባሩን በመቀጠል ወኔ ቀስቃሽ ንግግሮች መቅረብ ጀመሩ፡፡በወቅቱ ታዋቂ ከነበሩ ተናጋሪዎች ውስጥ አቶ ዮፍታሔ ንጉሴ (በኋላ ብላታ)፣ አቶ ደምሴ ወልደአማኑኤል (ደጃዝማች)፣ አቶ ክፍለ እግዚአ ይህደጎ (ብላታ)፣ አቶ ተመስገን ገብሬ፣ አቶ ኃይለገብርኤል ነገሮ፣ አቶ መንገሻ ከፈለ ይገኙበታል፡፡ እነዚህን የመሣሠሉ የአገር ፍቅር አባላት በንጉሡ ፊት ቀርበው የጠላትን ፕሮፓጋንዳ በመቃወምና የህዝቡን ወኔ በማነሳሳት የተጫወቱት ሚና በቀላሉ የሚታይ አልነበረም፡፡ በዚህ መልኩ የተጀመረው የመጀመሪያው ቴአትር ቤት አገር ፍቅር ሆነና፤ ቀጥሎ በ1948 ዓ.ም የዛሬው ብሔራዊ ቴአትር ቤት ተከፍቶ ስራውን ቀጠለ፡፡ ከዚያም የመዘጋጃ ቤት ቴአትር፣ቀጥሎም የቀድሞው የራስ ኃይሉ ሲኒማ ቤት የቴአትር መድረክ ተዘጋጅቶለት በመከፈቱ የቴአትር ቤቶችን ቁጥር ወደ 4 ከፍ ማድረግ ተቻለ፡፡ በተጨማሪም የድሮው "ሰይጣን ቤት" ይባል የነበረው ተሐድሶ ተደርጎለት "እምዬ ቴአትር" በሚል ስያሜው



ስራውን ቀጠለ፡፡ ከእነዚህ የጃንሆይ ዘመን ውጤቶች ውጪ ባለፉት 50 ዓመታት ውስጥ ምንም አይነት አዲስ ቴአትር ቤቶች አልተሰሩም፤ አልተጨመሩም፡፡



አርቲስት ዘነበች ታደሰ(ጭራ ቀረሽ)በወጣትነቷ ለጃንሆይ በበዓል ጊዜ እቅፍ አበባ ስታበረክት፡፡

ጥቅምት 25 ቀን 1952 ዓ.ም በቀድሞው ቀዳማዊ ኃይለስላሴ ቴአትር ቤት የሩሲያ አርቲስቶች መጥተው ጃንሆይና እቴጌ መነን በተገኙበት የኪነጥበብ ውጤታቸውን አሳይተው ነበር፡፡ ከትእይንቱ በኋላ ጃንሆይ ለኢትዮጵያውያን የኪነ-ጥበብ ባለሙያዎች ተከታዩን መልዕክት አስተላልፈዋል፤

"ትምህርት ለሁሉ የሚሰጥ ነገር ነው፡፡እንደባህሪው ለመምረጥ ግን የእያንዳንዱ መንፈስና አካል የሚይዘው ነገር ነው፡፡

አሁን እዚህ ያየነው ሁሉ እድላችሁ ለዚሁ የመራችሁ መሆኑን ይገልፃል፡፡ መጀመር ብቻ ጠቃሚ ነገር አይደለም፡፡እስከፍፃሜው ግብ ማድረስ የበለጠ ነገር ነው፡፡ በዓለም ላይ ያሉ የታወቁ ሰዓሊዎች ስመ ጥሩ ሆነው፤ እነሱ ቢሞቱ አሁን እንዳልሞቱ ሆነው የሚቆጠሩት በእጃቸው ስራና በአእምሮአቸው ፈተናውን አልፈው ስለደረሱ ነው፡፡አሁን ከመካከላችሁ አዲስ የጀመራችሁም የቆያችሁም ትገኛላችሁ፡፡ ስለዚህ የጀመራችሁትን ወደ ጫፍ ብታደርሱ የራሳችሁን ስም ታስከብራላችሁ፡፡ ለእናንተም የዘላለም መታሰቢያ ይሆንላችኋል፡፡ለዚህ ነገር ከብዙ ጊዜ ጀምሮ ያሰብንበት ለመሆኑ እነ አፈወርቅ ተክሌ ሄደው እንዲማሩ ያደረግነው ይህን የመሰለ ፍሬ እንዲገኝ በማመን ነው፡፡በየአይነቱም ዘመናዊውንም የጥንቱንም ስዕል ታዩታላችሁ፡፡ አሁን በሰራችሁት ስራ

ሁሉ ደስ እንዳሰኛችሁን እንደዚሁም ወደፊት ለአገራችሁ ስም ለምናስብለትም የትምህርት እድገት ምስክር እንድትሆኑ ጠንክራችሁ መስራት ነው፡፡"/ፍሬ ከናፍር 1952ዓ.ም/

ጃንሆይ እና ስፖርት

ኢጣሊያ ኢትዮጵያን ከመውረሩዋ በፊትና በኋላ በአዲስ አበባና በአስመራ ጥቂት የእግር ኳስ ቡድኖች ነበሩ፡፡

በ1928 ዓ.ም የቅዱስ ጊዮርጊስ ቡድን አዲስ አበባ፣ በ1929 ዓ.ም የሐማሴን ቡድን አስመራ፣ በ1938 ዓ.ም የጦር ሠራዊት ጠቅል ቡድን አዲስ አበባ፣ እንዲሁም የተፈሪ ቡድን ከድሬዳዋ ተመስርተው የእግር ኳስ ውድድር ያደርጉ ነበር፡፡ በብዙ የውጭ ጨዋታዎችም ኢትዮጵያ ተካፋይ ነበረች፡፡ የኢትዮጵያ ሻምፒዮና በ1937 ዓ.ም ሲጀመርም፣ በጥሩ ድርጅት ባይሆንም በመካከለኛ ዝግጅት የተቋቋሙት 5 ያህል ቡድኖች በኢትዮጵያ ሻምፒዮና ተካፋይ ነበሩ፡፡

ጃንሆይ ለስፖርቱ ምን ያህል ትኩረትና ዋጋ ይሰጡ እንደነበር ከአንደኛው እስከ ስድስተኛው የአፍሪካ ዋንጫ የብሔራዊ ቡድኑ ቋሚ ተሰላፊ የነበሩት አቶ አዋድ መሐመድ ለአዲስ ነገር ጋዜጣ በሰጡት ቃል አስታውሰዋል፡፡

"ኢትዮጵያ አገራዊ ውድድር ስታደርግ ቀዳማዊ ኃይለሰላሴ አሉ ማለት ነበር፡፡ በወቅቱ መንግስት ለእግር ኳሱ ምን ያህል ትኩረት እንደሚያደርግ ብዙ መጠየቅ ሳያስፈልግ ዛሬም የምንጫወተው ያኔ በተገነባው ስቴዲየም መሆኑን ማሰብ ብቻ ይበቃል" ባይ ናቸው፡፡

በእንጨት ታጥሮ የነበረውና በሚስማር ተራ በኩል ባለው የጎል ጀርባ ወንዝ የሚያልፍበት የዛሬው የአዲስ አበባ ስታዲየም የቀድሞው የቀዳማዊ ኃይለስላሴ ስታዲየም ከመሰራቱ በፊት ጨዋታዎች በጃንሆይ (ጃን) ሜዳ ላይ ነበር የሚካሄዱት፡፡ ጃን ሜዳ 30 ሺ ተመልካች የመያዝ አቅም ነበረው፡፡ ከ50 ዓመታት በላይም አገልግሏል፡፡





ይድነቃቸው ከቀ.ኃ.ሥ ዋንጫ ሲቀበል

ከአዲስ አበባ ቀጥሎ በአስመራ የንግስተ ሣባ ስታዲዩም፣ በድሬዳዋ-አሰፋወሰን ስታዲየም እንዲሁም በሐረር፣ በባህርዳርና በሌሎች አስር የአገሪቱ ጠቅላይ ግዛቶች የተገነቡት ስታዲየሞች የጃንሆይ ዘመን ውጤቶች ናቸው፡፡

ኢትዮጵያ የአፍሪካ ዋንጫን የማዘጋጀት እድል ያገኘችውም የአስመራውና የአዲስ አበባው ስታዲየሞች በተገነቡ ጊዜ ነው፡፡ ኢትዮጵያ፣ ግብፅና ሱዳን የጀመሩት የአፍሪካ ዋንጫ መካሄድ ከመጀመሩ በፊትም ታህሳስ 28 ቀን 1940 ዓ.ም ጃን ሜዳ ላይ ኢትዮጵያ ጅቡቲን 6 ለ 0 በማሸነፍ ነበር አገራዊ ውድድር የጀመረችው፡፡

ኢትዮጵያ በ1954 ዓ.ም ሦስተኛውን፣ በ1960 ዓ.ም ስድስተኛውን የአፍሪካ ዋንጫ አስተናግዳለች፡፡ በዚያ ዘመን ለብሔራዊ ቡድኑ ከክለቦች ብቻ ሳይሆን ከየትምህርት ቤቱም ተጫዋቾች ይመለመሉ ነበር፡፡ ተጫዋቾችም ለጥቅማ ጥቅም የታደሉ አልነበሩም፡፡ ለእግር ኳስ ያላቸውን ፍቅር ብቻ መሠረት አድርገው ይጫወቱ የነበሩ ናቸው፡፡

በባዶ እግር መጫወት በዓለም አቀፍ ደረጃ ሲከለከልና ታኬታ ብቻ ለኳስ ጨዋታ ሲፈቀድም ትጥቆቹ የሚመረቱት በውጭ አገር ስለሆነ መንግስት ወጪውን በማገናዘብ የስፖርት ትጥቆች ከቀረጥ ነፃ እንዲሆኑ

አድርጓል፡፡ ከትኬት ሽያጭ ላይም መንግስት ቀረጥ እንደማይወስድ በሕግ ተደነገገ፡፡

ሁኔታዎች እስኪመቻቹ ተጫዋቾች በትጥቅ አለመሟላት ምክንያት የደረሰባቸውን ችግር ለአብነት ስናነሳ፣ በ1951 ዓ.ም በግብፅ ካይሮ የተካሄደውን 2ኛውን የአፍሪካ ዋንጫ ያስታውሰናል፡፡ ግንቦት 14 ቀን በኢትዮጵያና በግብፅ መካከል የተደረገው ጨዋታ ግብፅ 4 ለ 0 ያሸነፈችበት ነበር፡፡ ለዚህ ሽንፈት የኢትዮጵያ ቡድን የሰጠው ምክንያት በሜዳ ውስጥ እንዳሉ የተጫዋቾቹ ታኬታዎች የመርገጫ ጡቶች እየወላለቁ በመበተናቸው ሳይጫወቱ ቀርተው ለመሸነፍ እንደተገደዱ ነው የገለፁት፡፡

ኢትዮጵያ በጃንሆይ ዘመን በተከታታይ በአፍሪካ ዋንጫ መካፈሏ በወቅቱ የዘርፉ ትልቅ ስኬት ሲሆን፣ ለተለያዩ የወዳጅነትና የአቋም ማጠንከሪያ ጨዋታዎች ከአውሮፓ ቡድኖች ጋርም ታደርግ ነበር፡፡ ከጎረቤት አገሮች ጀምሮ እስከ ሜክሲኮ ድረስ በመጓዝ ብሔራዊ ቡድኑ ተጫውቷል፡፡

ከእነዚህም ውስጥ መስከረም 19 ቀን 1961 ዓ.ም ሜክሲኮ እና ኢትዮጵያ በሜክሲኮ ሊአን ስታዲየም ተጫውተው ሜክሲኮ ኢትዮጵያን 3 ለ 0 አሸንፋለች፡፡ ጥር 14 ቀን 1959 ዓ.ም በአዲስ አበባ ኢትዮጵያና ሮማንያ ተጋጥመው ኢትዮጵያ ሮማንያን 2 ለ 1 አሸንፋለች፡፡ በአዲስ አበባ ታህሳስ 10 ቀን 1955 ዓ.ም ኢትዮጵያና ቱርክ ተጫውተው 0 ለ 0 በሆነ ውጤት ተለያይተዋል፡፡

በተጨማሪም ቺሊ ላይ ይካሄድ ለነበረው የዓለም ዋንጫ ኢትዮጵያ የማጣሪያ ጨዋታ የምታደርገው ከእስራኤል ጋር ነበር፡፡ (ያኔ የማጣሪያ ጨዋታ በአህጉር አይወሰንም ነበር) እናም የደርሶ መልስ ጨዋታ ግድ ነበርና የአዲስ አበባው ስታዲየም የተሟላ ስላልነበር ኢትዮጵያ ሁለቱንም ጨዋታዎች በቴላቪቭ ከተማ ማድረግ ነበረባት፡፡ የእስራኤል ቡድን በለመደው አየርና በደጋፊዎቹ ድጋፍ 3 ለ 2 እና 1 ለ 0 ኢትዮጵያን ማሸነፍ በመቻሉ የዚያ ወቅት የብሔራዊ ቡድን አባላትን በእጅጉ የሚከነክን ትውስታ ሆኖ አልፏል፡፡

በጃንሆይ ዘመን የነበረውን የእግር ኳስ ፌዴሬሽን ለመምራት የሚመረጡት በጊዜው ከነበሩ ባለሥልጣናትና ሚኒስትሮች እንደሆነ የሚገልፁት አቶ አዋድ መሀመድ "እግር ኳሱ ህይወት የነበረው የተከበሩ ሰዎች ይመሩት ስለነበር ብቻ ሳይሆን፣ ስፖርቱን ከልባቸው ይወዱት ስለነበረም ነው" በማለት "እንደ አቶ ይድነቃቸው ተሠማ ያሉ ስፖርቱ ደማቸው ውስጥ የተዋሃደባቸው ሰዎች እግር ኳሱ ስላገኘ" የላቀ ደረጃ ላይ ሊደርስ መቻሉን ይነግሩናል፡፡ ሚኒስትሮችና ከንቲባዎችም ለፌዴሬሽኑ ልዩ ትኩረት ሰጥተው እየተከታተሉና ያለአንዳች ጥቅማ ጥቅም



ኃላፊነታቸውን በአግባቡ እየተወጡ በጃንሆይ ጊዜ የነበረውን ስፖርት ውጤታማ እንዲሆን አድርገውታል፡፡

ጃንሆይ ፌዴሬሽኑ 25ኛ ዓመቱን ሲያከብር ያደረጉት ንግግር እንዲህ የሚል ነበር፣ "የኢትዮጵያ ፉትቦል ፌዴሬሽን ሃያ አምስተኛውን ዓመት ሲያከበር በማየታችን በጣም ተደስተናል፡፡ የዛሬ ሃያ አምስት ዓመት ድርጅቱ ገና ለመቋቋም በሚራመድበት ጊዜ ከዚያም በጥርጊያ ሜዳ ላይ ጃንሜዳ ከጅቡቲ ቡድን ጋር ሲጋጠም በድንኳን ውስጥ ተቀምጠን የተመለከትንበትን ጊዜ እናስታውሳለን፡፡

ይህ ስፖርት በኢትዮጵያ እንዲስፋፋ ያደረግነው ጥረትና እርዳታ ዛሬ በአዲስ አበባ በድሬዳዋ፣ እንደዚሁም በልዩ ልዩ ጠቅላይ ግዛቶች በተሰሩት ስታዲየሞችና በውድድሩ ኃይል ድምቀት በማያቋርጠው ኢንተርናሽናል ግንኙነትና በየሳምንቱ ጊዜውን ስፖርት በመመልከት በሚያሳልፈውና ወደስታዲየም በሚጎርፈው ህዝብ ብዛት ፍሬ ያገኘ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

የእኛን ምክርና እርዳታ በመልካም ዘዴ ላይ በማዋል ሃያአምስት ዓመት ሙሉ በመከታተል ፌዴሬሽኑን የጠቅላይ ግዛት መምሪያዎችና ክለቦችን በጉልበት፣ በእውቀት፣ በገንዘብ አገልግሎታቸውን የሰጡትን አባሎች ስናመሰግን፣ ከጥንት ጀምሮ ለዚህ ስፖርት መመስረትና መስፋፋት ምክንያት የሆኑትን፣ ሰውነታቸውንና ጊዜያቸውን ለዚህ ስፖርት አገልግሎት ያዋሉትን ሁሉ በተለይም ይድነቃቸው ተሰማን ልናመሰግን እንወዳለን፡፡"

ጃንሆይ በወቅቱ ቁንጮ ተጫዋች የነበሩትን አዋድ መሐመድ ሎሜማቸውን የመስቀላቸውን ወሬ ጋዜጠኛ ሰለሞን ተሰማ በዜና ማሰራጨቱን በሰሙ ጊዜ አዋድ መሐመድን፣ መንግስቱ ወርቁንና ሉቺያኖ ቫሳሎን ወደ ቤተ-መንግስት ጠርተው ለማነጋገር ተገደዱ፡፡ በወቅቱ ኢትዮጵያ በአዲስ አበባ ስታዲየም ሊቢያን አሸንፋ ስለነበርም በቤተ መንግስቱ ግብዣ ተደርጎ ነበር የተጠሩት፡፡ ጃንሆይ የሁለቱን ተጫዋቾች እድሜ ሲጠይቁ ሠላሳ ዓመት እንደሞላቸው ተናገሩ፡፡ "አንተስ?" አሉት አዋድን "30 ዓመት ሞላኝ" መለሰ አዋድ፡፡ "ታዲያ በ30 ዓመት ማርጀት አለ ወይ? በል ተጫወት! ገብታችሁ ተጫወቱ፣ በርቱ" ብለው አበረታተው ሸኟቸው፡፡/አዲስ ነገር 2001ዓ.ም/ ጃንሆይና ስፖርት ከዚህም በላይ ነበሩ፡፡

ለአትሌቲክሱም ቢሆን ጃንሆይ ትኩረታቸው ተመሳሳይ የነበረ ሲሆን፣ በዘመናቸውም እንደነ አበበ ቢቂላ ባሉ ጀግኖች ኢትዮጵያ የተወደሰችበት ዘመን እንደነበር በደንብ የሚታወቅ ነው፡፡ በተለይ የእግር ኳሱን ጉዳይ ዛሬስ? ብሎ ጠይቆ ለማለፍ በቂ ነው፡፡

*ጃንሆይ እና አፍሪካ*

ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በፊት አፍሪካውያን ለብሔራዊ ነፃነት ያደረጓቸው ትግሎች ሁሉ አልተሳኩም ነበር፡፡ ከጦርነቱ ፍፃሜ በኋላ ግን የፓን አፍሪካን እንቅስቃሴ በመከተል በአውሮፓና በአሜሪካ የተማሩ አፍሪካውያን ወደየአገራቸው በመመለስ የነፃነት ትግሉን በማቀጣጠል መላው አፍሪካን ከቅኝ ገዥዎች ነፃ ማድረግ ችለዋል፡፡

የቅኝ ገዥዎች እስራት፣አፈና፣ግድያና ስቃይ ሳይበግራቸው በዲፕሎማሲ እና በጦር ግንባሮች እየተፋለሙ ህዝባቸውን ብሔራዊ ነፃነት አጎናፅፈዋል፡፡ክዋሜ ንክሩማ ጋናን፣ ሴኮ ቱሬ ጊኒን፣ጆሞ ኬንያታ ኬንያን፣ኒሬሬ ታንዛንያን፣ኬኔት ካውንዳ ዛምቢያን፣መሐመድ 5ኛ ሞሮኮን፣ሐቢብ ቡርጊባ ቱኒዚያን፣ቤንቤላ አልጀሪያን፣ኔልሰን ማንዴላ (ከአፓርታይድ አገዛዝ) ደቡብ አፍሪካን ነፃ አውጥተዋል፡፡

እነዚህ የነፃነት አባቶች ኅብረታቸውን በማጠንከር የፓን አፍሪካ ፅንሰ ኀሳብን በተግባር በመተርጎም ለአፍሪካውያን ትልቅ ኩራት የሆነውን የአፍሪካ አንድነት ድርጅትን እ.ኤ.አ በ1963 ዓ.ም ለጥቁር ህዝብ የነፃነት ምሳሌ በሆነችው በኢትዮጵያ መዲና በአዲስ አበባ ለማቋቋም ችለዋል፡፡ ለውጤት ከመብቃታቸው በፊት የነበረው ሂደትም ፈታኝና እልህ አስጨራሽ የነበረ ሲሆን፤ የኢትዮጵያና የጃንሆይ እገዛ ለአፍሪካውያን ህልም እውን መሆን ወሳኝ አስተዋፅኦ ነበረው፡፡

ያኔ ፋሽስት ኢጣሊያ ኢትዮጵያን በወረረበት ዘመን ጃንሆይ ለመንግስታቱ ማኅበር አቤቱታቸውን ለማቅረብ በ1929 ዓ.ም በሲውዘርላንድ ጄኔቭ በአዳራሹ መድረክ ላይ ቆመው ንግግር ለማድረግ ሲዘጋጁ የነበረው ሁከት አሳዛኝ ነበር፡፡ የተቃውሞ ጩኸት፣ የዘለፋ ቃል፣ የእስከብሪቶ ክዳኖችና የመሳሰሉ ጥቃቅን ነገሮች ወደንግግር ማድረጊያው መድረክ የተወረወረበት ሁኔታ ተስተውሏል፡፡ ኢትዮጵያ አባል የሆነችበት ያ ማኅበር የየአገራቱ ተወካይ የሆኑ ታላላቅ ምሁራንና ባለሥልጣናት የተሰበሰቡበት አዳራሽ አልመሰለም፡፡ ከወሮበሎች ቡድን የማይጠበቅ ክንውን ነበር በአዳራሹ የነበረው፡፡

ጃንሆይ ዙሪያ ገባውን እየተዟዟሩ በዓይኖቻቸው ፀጥታ እንዲከበር ቢማፀኑም ፀጥታ ሊያስከብር የደፈረ ባለስልጣን አልነበረም፡፡በወቅቱ በኢትዮጵያ ምድር የመርዝ ጋዝ በአውሮፕላን እየተረጨ ዜጎች ያለቁበት ሁኔታ ነበር፡፡ጃንሆይና ቤተሰቦቻቸው ስደት ላይ ናቸው፡፡ፍፁመ ብቸኝነት ተሰምቷቸዋል፡፡ተስፋ የጣሉበት ማኅበርና ዓለም አቀፍ ሕግ በዚያ ሁኔታ ይጠብቀኛል ብለው አላሰቡም፡፡ በጃንሆይ ዘመን የተቀረፁ ምስሎች እና ፎቶግራፎችን ሁሉ ያየ ሰው የዚያችን እለት የጃንሆይን የፊት ገፅታ በማየት ብቻ በዘመናቸው ክፉኛ የተናደዱበት እለት መሆኗን በቀላሉ ይረዳል፡፡እንባ እየተናነቃቸው፣ የንዴት ላባቸው ፊታቸው ላይ ቸፍ ብሎ



ይታያል፡፡ነገር ግን የመጡበት ነውና ካባቸውን ገለጥ አድርገው ከኪሳቸው አቤቱታ የያዘውን ወረቀታቸውን አውጥተው በሲቃ ድምፅ በጩኸቱ መካከል አነበቡት፡፡ያ ታሪካዊና “ነብይ” ያስባላቸው ንግግራቸው ለሁከት በተሰበሰቡት ባለሥልጣናት ልብ ውስጥ እየጠለቀ ሲሄድ፤ ብዙዎች መበጥበጣቸውን ትተው በጥሞና ማዳመጥ ጀመሩ፡፡ቢሆንም ኃያላኑ ለኢጣሊያ እውቅና ከመስጠት አልታገዱም፡፡

ያ አስጨናቂ ወቅት ካለፈ በኋላ ጃንሆይ ዓለም አቀፍ ሕግ ለጥቁሮች እንደማይሰራ በውል ተረድተዋል፡፡ ይህ ከሆነ ከእሩብ ምዕተ ዓመት በኋላ ጃንሆይና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ክቡር አቶ ከተማ ይፍሩ “የጄኔቩ አይነት የመንፈስ ስብራት ዳግም ቢደርስብን ከጎናችን የሚቆመው ማነው?” በሚል መነሻ አጭር ውይይት አድርገው የደረሱበት ድምዳሜ “ኢትዮጵያ መወዳጀትም ሆነ መደጋገፍ ያለባት ከመሰሎቿ ከአፍሪካውያን ጋር እንጂ ከሌላ ከማንም ጋር ሊሆን አይችልም” የሚል ነው፡፡ በመሆኑም ከ1950 ዓ.ም ጀምሮ ኢትዮጵያ አፍሪካውያንን በመደገፍ፣ በማስተባበርና በልዩ ልዩ መንገዶች መርዳት ዋና ስራዋ አድርጋ ያዘችው፡፡

በዓለም አቀፍ የጥናት ውጤት ይፋ እንደተደረገው ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በፊትና በኋላ በነበሩት ጊዜያቶች ከዓለም ህዝብ ውስጥ 66 በመቶ የሚሆነው ቅኝ ተገዥ ህዝብ የነበረ ሲሆን፤ ከአጠቃላዩ የዚህች ምድር ስፋት ውስጥ 63 በመቶው የብስና ባህር በተለይ በእስያና በአፍሪካ አህጉር የሚገኘው በቅኝ ገዥዎች የበላይነት የተያዘ ነበር፡፡አፍሪካ ውስጥ ደግሞ ከኢትዮጵያ በስተቀር ሁሉም አገር በአውሮፓውያኑ ቅኝ ገዥዎች ስር የተያዘ ነው፡፡ብዙ ጊዜ “ኢትዮጵያና ላይቤሪያ” ተብሎ ይገለፃል፡፡ነገር ግን ላይቤሪያ በካርታ አቀማመጧ ማዕከላዊነት ሳቢያ ቅኝ ገዥዎች በአፍሪካ ላይ በሚሰሩት ስራና ሴራ የሚገለገሉባቸውን እቃዎች የሚያወርዱ የሚያወጡባት፣የሚያሰራጩ የሚያራግፉባት፣አንዳንዴም ጥቁሮችን የሚያጉሩባት መጋዘን አድርገው ስለተጠቀሙባት ነው፡፡ከዚህ አንፃር ብቸኛ ነፃ አፍሪካዊት አገር ኢትዮጵያ በመሆኗ አፍሪካን ባላት አቅም ለመርዳት የምትችል ሲሆን፤የአፍሪካ ህዝቦችና የነፃነት ታጋዮችም የኢትዮጵያ እርዳታ በእጅጉ ያስፈልጋቸው ነበር፡፡

የጀርመን ፋሽዝም በአውሮፓ፣የጃፓን ሚሊታሪዝም በእስያ ድል ከሆኑበት ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ፍፃሜ በኋላ የተፈጠረው ሁኔታ የቅኝ ተገዥ አገራት ህዝቦችን የነፃነት ጥያቄና ትግል ተጠናክሮ እንዲቀጥል አድርጓል፡፡

ድል ባደረጉት በተባበሩት አገራት ጦር ሠራዊት ውስጥም የአፍሪካውያን ወታደሮች ተሳታፊ ሆነው ለድሉ ሰፊ አስተዋፅኦ አበርክተዋል፡፡በዚያ

ጦርነት አንድ ሚሊዮን አፍሪካውያን ወታደሮች በተባበሩት ጦር ኃይሎች ውስጥ ተሰልፈው ተዋግተዋል፡፡

ለምሳሌ ፓሪስ ነፃ ከመውጣቷ በፊት የጀርመንን ፋሽዝም ለመደምሰስ በተካሄደው ውጊያ ከፈረንሣይ ጎን የተሰለፉት አፍሪካውያን ወታደሮች በቁጥር ከፈረንሣውያን ወታደሮች ይበልጡ ነበር፡፡ አልጀሪያውያን ወታደሮች ብቻ ሦስት መቶ ሺ ይደርሱ ነበር፡፡ በተመሳሳይም የእስያ ህዝቦች የጃፓንን ሚሊታሪዝም በመደምሰስ በኩል ከፍተኛ ተሳትፎ አድርገዋል፡፡

የፋሽስት ኢጣሊያን ጦር ከአፍሪካ ለመደምሰስም አፍሪካውያን ወታደሮች ትልቁን ሚና ተወጥተዋል፡፡ 50 ሚሊዮን ህዝብ ያለቀበት ሁለተኛው የዓለም ጦርነት የተጀመረው ኢትዮጵያ ላይ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ምንም እንኳ "የዓለም ጦርነት" የሚለው ስያሜና አገላለፅ በይፋ የታወቀው ጀርመን ፖላንድን በወረረች ጊዜ ይሁን እንጂ፣ ጀማሪዋ ጣሊያን፣ ተጀማሪዋ ኢትዮጵያ ነበረች፡፡

ጦርነቱ ተጀምሮ እስኪጨረስም ኢትዮጵያ አርበኞቿን ጨምሮ አንድ ሚሊዮን ዜጎቿን አጥታለች፡፡ የኢጣሊያን ጦር ከአፍሪካ ለማስወጣት በተካሄደው ውጊያ የኢትዮጵያ ወታደሮች አገራቸውን ነፃ ከማውጣት አልፈው ከእንግሊዝ ጦር ጋር ወደ ሊቢያ ዘምተዋል፡፡

በሂደቱ አፍሪካውያን በጥይትና በቦምብ ካለቁት ውጪ በርካታ ምሁራን በየእስር ቤቱ ታጉረው እድሜያቸውን አባክነዋል፡፡ የአፍሪካ ህዝቦች በቅኝ ገዥ አገራቱ እየተመለመሉ በጦርነቱ ገዥ አገራቸውን ለመርዳት ሲሰለፉም የተገባላቸውን ቃል መሠረት አድርገው ነው፡፡

በተለይ እንግሊዝና ፈረንሣይ ለረጅም ዓመታት የገዟቸውን የአፍሪካ ዜጎች በዚያ አጣብቂኝ ላይ በነበሩበት ጊዜ የአፍሪካውያኑ ትብብር ያስፈለጋቸው ነበርና "ለነፃነታችሁ መዋጋት አለባችሁ" ከማለት አልፈው "ከድል በኋላ ነፃነታችሁን መልሰን እንሰጣችኋለን" በሚል ቃል ገቡላቸው፡፡

ለጥቁር ህዝቦች ማንም ያሸንፍ ማን እዚህ ግባ የሚሉት ለውጥ አይኖርም፡፡ "ከማያውቁት መላዕክ የሚያውቁት ሠይጣን"ን ካልተረቱት በቀር ከሁለት አውሮፓዊ ገዥ አንዱን የመምረጥ ያህል ነበር፡፡ኢምፔሪያሊዝምም ፋሺዝምም ተገዥ ለሆነ አገር ልዩነቱ ያዘለና ያቀፈ መሆኑን ስለተረዱም ነው "ነፃነታችሁን እንመልሳለን" ወደማለት ያመሩት፡፡በዚህ መሠረት አፍሪካውያን በጦርነቱ ሊሳተፉ ችለዋል፡፡ ቅኝ ገዥ አገራቱ ከድል በኋላ ቃላቸውን ሙሉ በሙሉ ለመጠበቅ ባይችሉም፣ ለአፍሪካውያኑ ግን ከጦርነቱ ፍፃሜ በኋላ የገዥዎቻቸውን ቀንበር ከላያቸው ላይ ለማውረድ የራሳቸውን ትግል ብቻ እንጂ በገዥዎች ችሮታ እንደማይገኝ አስገንዝቧቸዋል፡፡



ከዚህም በላይ የጦርነቱ ፍፃሜ በራሱ ለብሔራዊ ነፃ አውጪና ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄዎች መስፋፋት ከፍተኛ ግፊት ፈጥሯል፡፡ የነበሩት የነፃነት ትግሎች ተጠናክረው፣ ያልነበሩት በአዲስ መልክ ብቅ ብቅ እያሉ የቀጠሉት ከድል በኋላ ምንም ያተረፉት ነገር ባለመኖሩ ነው፡፡

ለፋሽዝም መሸነፍ ትልቅ አስተዋፅኦ ያበረከቱት፣ በጦርነቱም ቀዳሚ ተዋጊ እየተደረጉ ከፍተኛ መስዋዕትነት የከፈሉትና መራራ ስቃይ የተቀበሉት አፍሪካውያን የተገባላቸው ቃል በመታጠፉም ብቻ ሳይሆን፣ በጦርነቱ ወቅት የተለያዩ አገራት ዜግነት ካላቸው ወታደሮች ጋር ተሰባጥረው ስለተዋጉ አመለካከትና ግንዛቤያቸው ዳብሮ ነበርና ግዳጃቸውን ተወጥተው ወደሰላማዊ ኑሮዋቸው እንዲመለሱ በተደረገ ጊዜ በቅኝ አገዛዝና በፖለቲካዊ፣ በኢኮኖሚያዊ፣ በአይዲዮሎጂያዊ መሠረቶች ላይ በመነሳት ቀደም ብለው በተጀመሩት በነፃነት ትግሎች ላይ ንቁ ተሳትፎ ማድረግ ጀመሩ፡፡

አፍሪካውያን ሚሊቴሪዎች በአገራቸው ውስጥ ሆነው ለነፃነታቸው መታገላቸውን በቀጠሉበት ሁኔታም፣ በውጭ አገር ትምህርታቸውን የተከታተሉ የየአገራቱ ምሁራንና ፖለቲከኛ የሆኑ ሲቪል ዜጎችም በዲፕሎማሲና በተለያዩ የትግል ስልቶች የነፃነቱን ንቅናቄ የሚያጎለብት ስራ ይሰሩ ነበር፡፡

በመሆኑም ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ፍፃሜ በኋላ አፍሪካውያን የፓንአፍሪካኒዝም ንቅናቄያቸውን አጧጧፉት፡፡ በአህጉሪቱ ውስጥም ብዙ የፖለቲካ ፓርቲዎችና ድርጅቶች ፈለቁ፡፡ የፓን አፍሪካ ጉባኤዎችም በየጊዜው መካሄድ ጀመሩ፡፡ ኢትዮጵያም ምንም ነፃ አገር ብትሆን የፓን አፍሪካኒዝም ንቅናቄ ደጋፊ መሆኗን ገለፀች፡፡ ጃንሆይ "በማናቸውም ረገድ ቢሆን አፍሪካውያን ወንድሞቻችንን ለነፃነት የሚያደርጉትን ትግል ደግፈን የሚቻለንን ሁሉ እንረዳለን" አሉ፡፡

አፍሪካውያኑ በውስጣቸው ያለውን ምሬት ይፋ ያወጡትና ጠንካራ ውሣኔ የወሰኑት ጦርነቱ በአውሮፓ ሙሉ በሙሉ ሊጠናቀቅ የጥቂት ወራት እድሜ በቀረበት በጥቅምት ወር እ.ኤ.አ 1945 ላይ በእንግሊዝ ማንችስተር ከተማ ውስጥ በተደረገው በ5ኛው የፓን አፍሪካ ጉባኤ ላይ ነው፡፡ በዚያ ጉባኤ በአህጉሪቱ የፈለቁ የፖለቲካ ፓርቲዎችና ድርጅቶች አባላት የተካፈሉ ሲሆን፣ ከእነርሱ ውስጥ የጋናው ክዋሜ ኑክሩማ እና የኬንያው ጆሞ ኬንያታ ይገኙበታል፡፡ እነርሱና መሰል እውቅ የብሔራዊ ነፃ አውጪ ንቅናቄ መሪዎች በጉባኤያቸው ለአፍሪካ ህዝቦች ያቀረቡት ማሳሰቢያና የወሰዱት አቋም እንዲህ የሚል ነበር፡፡

"ሁሉም ህዝቦች ራሳቸውን ለመምራት መብት እንዳላቸው እናምናለን፡፡ ሁሉም ቅኝ ግዛቶች ከባእዳን የፖለቲካና የኢኮኖሚ ቁጥጥር ነፃ መሆን አለባቸው፡፡ የቅኝ ግዛት ህዝቦችም ባእዳን ኃይላት ከሚጥሉት

ማንኛውም ገደብ ነፃ ሆነው የየራሳቸውን መንግስታት የመምረጥ መብት ሊኖራቸው ይገባል" ሲሉ አስገነዘቡ፡፡

ይህን የውሣኔ አቋም ኢምፔሪያሊስቶች ለማፈን ጥረት አደረጉ፡፡ አፍሪካውያኑ ግን የነፃ አውጪ ንቅናቄ መሪዎችን መልዕክት ተቀብለው በተግባር ወደመተርጎም አመሩ፡፡

ጦርነቱ በአውሮፓ ባበቃበት ግንቦት 8 ቀን 1945 እ.ኤ.አ የፈረንሣይ ቅኝ ገዥዎች በግዛታቸው በአልጀሪያ ውስጥ የተነሳውን የነፃነት አመፅ ለማዳፈን ከፍተኛ ወረራ አካሂደው 45 ሺ አልጀሪያውያንን ገደሉ፡፡ በ1947 ማዳጋስካር ውስጥ ለነፃነቱ ለመዋጋት በተነሳውና ምንም ባልታጠቀው የማላጋሲ ህዝብ ላይ የፈረንሣይ ወታደሮች በዘመናዊ መሣሪያ ታግዘው በከፈቱት ተኩስ 100 ሺ የደሴቲቱን ተወላጆች ፈጁቸው፡፡

የነፃ አውጪ ንቅናቄ መሪዎች የትግል ስልት አይነቱ ይለያይ እንጂ በአህጉሪቱ በሚካሄዱ ትግሎች ምክንያት ተመሳሳይ የኢምፔሪያሊስቱ የጭካኔ እርምጃ ለዓመታት በየአገሩ ሲፈፀም ቆይቷል፡፡ በሰሜን አፍሪካ የሚገኙ አገራት ውስጥ ኮሚኒስት ፓርቲዎች እንደመበርከታቸው መጠንም በኃያሏ ሶቭየት እርዳታ ምክንያት የትግላቸው ጊዜ አጭር እንዲሆን አግዟቸዋል፡፡

ነፃነቷን በመቀዳጀት ረገድ የመጀመሪያዋ የአፍሪካ አገር ሊቢያ ናት፡፡ ከቀድሞ ገዥዋ ከኢጣሊያ ነፃ ከሆነች በኋላ በእንግሊዝና በፈረንሣይ ወታደሮች ተይዛ የቆየችው ሊቢያ፣ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ውሣኔ መሠረት መንግስታዊ ሉዓላዊነት ያገኘችው ታህሳስ 24 ቀን 1951 እ.ኤ.አ ነው፡፡ ሆኖም ባዕዳኑ አገሪቱን ሙሉ ለሙሉ ለቀው የወጡት እ.ኤ.አ በ1970 ነበር፡፡ጋዳፊ ስልጣን እንደያዙ ጠራርገው አባረሯቸው፡፡

በሐምሌ ወር 1952 እ.ኤ.አ ግብፅ በጋማል አብድል ናስር መሪነት ፀረ-ኢምፔሪያሊስት አብዮት ተከናውኖ የአብዮታዊ መምሪያ ምክር ቤት ከተቋቋመ በኋላ የአርበኞች ድርጅት አባሎችን የያዘ ቡድን ስልጣኑን ይዞ በጋማል አብድል ናስር ሲመራ ቆይቶ፣በግብፅ አብዮታዊ መንግስት ጥያቄ መሠረት ከረጅም ጊዜ ግብግብ በኋላ እንግሊዝ ወታደሮቿን ሙሉ በሙሉ በሰኔ ወር 1956 እ.ኤ.አ ከአገሪቱ አስወጣች፡፡በአገሪቱ የኢምፔሪያሊስት መንግስትን መልሶ ለማቋቋም የሚፈልጉ ኃይሎች ቢኖሩም ሶሻሊስቱ ቦታውን ሳይለቅ ቆዬ፡፡እንግሊዝና ፈረንሣይ የስዊዝ ካናል ኩባንያን ለግብፅ ማስረከብ እንዳለባቸው የተጠየቁትን ጥያቄ መሠረት አድርገው እስራኤልንም ከጎናቸው አሰልፈው በግብፅ ላይ ጦርነት ቢከፍቱም የግብፅ ህዝብ በጀግንነት ተዋግቶ መከተ፡፡ለዚህም የሶሻሊስት አገሮች በተለይ ሶቭየትና ቼኮዝላቫኪያ ለግብፅ የሰጡት የመሣሪያ እርዳታ ለድሉ ከፍተኛ



አስተዋፅኦ ነበረው፡፡ሦስቱ አገሮች ግብፅን መልሰው ለማጥቃት ሲዘጋጁም ሶቭየት በሦስቱ አገሮች ላይ ጦርነት እንደምትከፍት ስላስጠነቀቀች ወራሪዎቹ ተኩስ አቁመው ከግብፅ ወጡ፡፡የግብፅ ድል ለሰሜን አፍሪካና ለዓረቡ ዓለም የነፃነት እንቅስቃሴ ወኔን የሚቀሰቅስ ሆኖ ሲገኝ፣ናስርም የዓለም ነፃ አውጪ ንቅናቄ እውቅ መሪ ተሰኘበት፡፡በመሆኑም ጥር 1 ቀን 1956 እ.ኤ.አ በእንግሊዝ ስር የነበረችው ሱዳን ነፃ ሪፐብሊክ ሆነች፡፡ፈረንሣይ በበኩሏ መጋቢት 2 ቀን 1956 የሞሮኮን፣መጋቢት 20 ቀን የቱኒዚያን ነፃነት እውቅና ለመስጠት ተገደደች፡፡ የግብፅ ተፅዕኖ ለተጠቀሱት የአፍሪካ ዓረብ አገራት ነፃነት የራሱ የሆነ አስተዋፅኦ ነበረው፡፡እ.ኤ.አ መጋቢት 6 ቀን 1957 ጋና ነፃነቷን መጎናፀፏ ታወጀ፡፡እ.ኤ.አ በ1958 ጊኒ ነፃ ወጣች፡፡በዚያ ጊዜ (በእኛ አቆጣጠር 1950 ዓ.ም) "ነፃ የአፍሪካ መንግስት ጉባዔ" ተመሠረተና በጋና አክራ ከተማ የመጀመሪያው ውይይት ተካሄደ፡፡ እለቱንም "የአፍሪካ ቀን" በማለት በአህጉር ደረጃ ሰየሙት፡፡የነፃ መንግስታቱ ድርጅት ጉባዔ በፖለቲካና በኢኮኖሚ ጉዳዮች እየተወያዩ ሌሎች አገራት በአጭር ጊዜ ውስጥ ለነፃነት የሚበቁበትን መንገድ ማመቻቸትና መርዳት እንዲሁም ግፊት ማድረግ ነበረበት፡፡ለዚህም ምቹ ሁኔታ መፍጠር የምትችለው ኢትዮጵያ ነበረችና ተከታታይ ጉባኤዎች በኢትዮጵያ መካሄድ ጀመሩ፡፡ የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽንም በኢትዮጵያ ተመሠረተ፡፡ነፃ የአፍሪካ አገሮች ኅብረት ፈጥረው ያደረጉት ግፊትም ፍሬ መስጠቱን ቀጠለ፡፡



ጃንሆይ ከአፍሪካውያን መሪዎች ጋር

በኛ አቆጣጠር ሚያዚያ 7 ቀን 1952 ዓ.ም ጃንሆይ የአፍሪካን ጉዳይ በሚመለከት በሬዲዮ የተናገሩት ንግግር በአጭሩ እንዲህ ይነበባል፣

"የአፍሪካ ቀን ክብረ በዓል የተመሠረተበት ሁለተኛው ዓመት በሚውልበት በዛሬው እለት ከልብ የሆነውን የራሳችንን ሠላምታና የምንወደው ህዝባችን ለአፍሪካውያን ወንድሞቹ የሚልከውን የወንድማማችነት በጎ ምኞት ለመላው አፍሪካ ህዝቦች እንገልፃለን፡፡

ስለዚህ ታላቅ ስለሆነው ክፍለ ዓለም ህዝቦች ነፃነትና የወደፊት እርምጃ በሚያደርገው ትግል ባለፈው ዓመት ውስጥ የአፍሪካ አገሮች ያሳዩት መተባበር ደስ የሚያሰኝና የሚያበረታታ ነው፡፡

ካሜሮን ነፃ እንደወጣች እንዲሁም ኮንጎ፣ ናይጀሪያ፣ ሶማሊያና ቶጎ ላንድ በዚህ ዓመት ውስጥ ነፃነታቸውን የሚያገኙ በመሆናቸው አፍሪካውያን ወንድሞቻቸው በሙሉ ይደሰቱበታል፡፡ የእነዚህ አገሮች ነፃ መውጣት የአገሬውን ህዝብ በተለይ የሚያስደስተው ብቻ ሳይሆን ይህንኑ መልካም ውጤት ለማስገኘት ሳይሰለቹ ለደከሙት እህትማማች አገሮች ህዝብ ጭምር ብርታትን የሚሰጣቸው ነው፡፡ በዚህም አኳኋን ከአስር ዓመት በማያንስ ጊዜ ውስጥ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት አባል የሆኑት የአፍሪካ አገሮች ቁጥር በዝቶ ከሦስት እስከ አራት መድረሱ ስለአፍሪካ ነፃነት የሚደረገውን እንቅስቃሴ በበለጠ የሚያጠነክረው ስለሆነ ሌሎችም በአፍሪካ ውስጥ የሚገኙ ግዛቶች በአጭር ጊዜ ውስጥ ነፃነታቸውን እየተጎናፀፉ ከአፍሪካውያን ወንድሞቻቸው ጎን ተገቢ የክብር ስፍራቸውን እንደሚይዙ አያጠራጥርም፡፡

አሁንም እንኳ ቢሆን በማናቸውም አገር የሚገኙ ህዝቦች ሁሉ በዘር ምክንያት ልዩነት እንዳይደረግባቸውና የእድል እኩልነት እንዳይነፈጋቸው ለማድረግ በተባበሩት መንግስታት ሸንጎ በሚደረገው ትልቅ የአፍሪካ መንግስታት ኀሳብና ዓላማ አንድ መሆንና በሰፊው መተባበራቸው ከብዛታቸው ጋር ሆኖ በተባበሩት መንግስታት ሸንጎ የሚናገሩዋቸውን ቃላት በተለይ ተደማጭ አድርጎታል፡፡

ይህ ኅብረትና መረዳዳት በመጠኑ ከታሪካቸው ቅርስ የተገኘ እንዲሁም የጋራ ተጋድሏቸውን ባለመዘንጋት ላይ የተመሠረተ ሆኖ ሲገኝ፤ስለኢኮኖሚና ስለፖለቲካ ጉዳዮች መመካከሪያ እንዲሆን የተቋቋመው ድርጅት መሠረታዊ ስለሆኑት የኀሳብ አንድነት ተባብሮ በጥንካሬ ስለመስራት መርዳት ደስ የሚያሰኘን ነው፡፡

በዚህ ዓመት ከአራት ወራት በማይበልጥ ጊዜ ውስጥ የአፍሪካ አገሮች በቱኒዝ፣ በአክራና በኮናክሪ ሦስት ጊዜ ስብሰባ ያደረጉ ሲሆን፤ በሚመጡት ወራት ውስጥ ደግሞ በመናገሻ ከተማችን ሁለት ጊዜ እንዲሰበሰቡ መታቀዱን እኛን አፍሪካውያንን የሚያኮራን ነው፡፡

…. በዚህ በዛሬው የአፍሪካ ቀን ለወንድሞቻችን ነፃነት፣ ደህንነትና መሻሻል እንቅፋት የሆኑትን ነገሮች ሁሉ ለማስወገድ ያለንን ከፍተኛ



ዓላማ በበለጠ እንድናከናውን ኀሳባችንንና ቆራጥነታችንን እንደገና እናድስ፡፡" *(ፍሬ ከናፍር 1952 ዓ.ም)*

በዚሁ የአፍሪካ ቀን በተከበረበት እለት እ.ኤ.አ 1960 ዓ.ም 17 የአፍሪካ አገሮች ነፃነታቸውን ተቀዳጁ፡፡ በተጠቀሰው ዓመት የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ጠቅላላ ጉባዔ ለቅኝ ግዛት አገሮችና ህዝቦች ነፃነት ስለመስጠት ጉዳይ የቀረበውን ውሣኔ አፀደቀ፡፡

የካፒታሊስት አገራት ተወካዮች ረቂቁን ውድቅ ለማድረግ አልሞከሩም፡፡ ነገር ግን ቅኝ አገዛዙ በተሻሻለ ሁኔታ የሚቀጥልበትን መንገድ ለማመቻቸት ጥረው ነበር፡፡ ሆኖም የገለልተኛ አገራትና የሶሻሊስት አገራት በተለይ የሶቭየት ኅብረት ተወካዮች ካፒታሊስቶችን ተቃውመው ጥረታቸውን አከሸፉት፡፡

43 የእስያና የአፍሪካ አገሮች ያረቀቁትን መግለጫ ጠቅላላ ጉባኤው በከፍተኛ የድምፅ ብልጫ ሲያፀድቀውም "ቅኝ አገዛዝ ከተባበሩት መንግስታት ድርጅት መርሆዎች ጋር የማይጣጣም" መሆኑን በመግለፅና፤ ህዝቦች የራሳቸውን እድል በራሳቸው የመወሰንና በነፃነት የመኖር መብት እንዳላቸው በማረጋገጥ ነው፡፡ ከውሣኔው መፅደቅ በኋላ ለብሔራዊ ነፃነት የሚካሄደው ትግልና የሚከተለው እልቂት ሙሉ ለሙሉም ባይሆን በመጠኑ ጋብ አለ፡፡

ለ7 ዓመታት ያህል ደም ያፋሰሰው የአልጀሪያና የፈረንሣይ ጦርነትም ተገታ፡፡ ሐምሌ 1 ቀን 1962 እ.ኤ.አ አልጀሪያ ነፃ አገር ሆነች፡፡ ከዚህ በኋላ ባሉት ተከታታይ ዓመታት የቅኝ ግዛት ስርዓት በመላው ዓለም እየፈራረሰ ሄደ፡፡

አፍሪካውያን ቀስ በቀስ ነፃነታቸውን እየተጎናፀፉ ለመሄድ ካስቻሏቸው መንገዶች ውስጥ አንዱ ኅብረታቸው እንዳለ ሆኖ፤ በኢኮኖሚ በኩል ሊረዳዱ የሚችሉበት "የአፍሪካ ኢኮኖሚ ኮሚሽን" በተባበሩት መንግስታት አማካኝነት ማቋቋም በመቻሉ ነው፡፡

በእኛ አቆጣጠር 1951 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ የአፍሪካ ኢኮኖሚ ኮሚሽን የመጀመሪያ ጉባዔ ተመርቆ ከተከፈተ ከአንድ ዓመት በኋላ ጃንሆይ በሁለተኛው የአፍሪካ ነፃ መንግስታት ኮንፈረንስን ሲከፍቱ ባደረጉት ንግግር ውስጥ ያካተቱት ገለፃም ይህንኑ የሚያረጋግጥ ነው፡፡

"… የአፍሪካ ኢኮኖሚ ኮሚሲዮን የመጀመሪያው ጉባዔ በተደረገበት ጊዜ የአፍሪካ ህዝብ ያደረገውን የተፋጠነ የፖለቲካ እድገት በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ከተፈፀሙት እጅግ አስገራሚና አስደናቂ ሆነው ከሚታዩት የስልጣኔ እርምጃዎች አንዱ መሆኑን ገልጠናል፡፡ ከዚያም ወዲህ በተከተሉት ወራት ውስጥ የቀጠለው ትግል በአጭር ጊዜ ውስጥ ብዙ አዳዲስ መንግስታት በማስገኘቱና የቅኝ ግዛት ሰዎች ወደነፃነት

ግባቸው የሚያደርጉትን እርምጃ በማፋጠኑ መጠን ከታሰበው በላይ የሆነ መልካም ውጤት አስገኝቷል፡፡

በዚህ ከእግዚአብሔር በተመረጠው እድል ጊዜና ቀን መመስረትና መስራት የሚገባን መሆኑን አውቀን እድል ህልም ሆኖ እንዳይቀር የአንድነትን መሠረት መጣል ስራችን እናድርግ፡፡

ኮንጎ፣ ካሜሩን፣ ቶጎላንድ፣ ናይጄሪያና ሶማሊያ ዛሬ ከመካከላችን ተገኝተው በዚህ ጉባዔ ስራ ሙሉ ተካፋይ ለመሆን በመቻላቸው ሁላችንም ደስ ይለናል፡፡ ከአሁን በፊት እንደተናገርነው የአፍሪካ ህዝቦች የፖለቲካ እድገት ወደመጨረሻው ግቡ ሳይደርስ የማያቋርጥ መሆኑን በጥብቅ እናምንበታለን፡፡ከዚሁም ግብ የሚደርሰው መላው የአፍሪካ ህዝብ ነፃነቱንና ሠብዓዊ መብቱን በሙሉ ሲያገኝ ነው...፡፡"

በዚያ ወቅት ኢትዮጵያ ለአፍሪካውያን ነፃነትና የወደፊት ዕጣ ሲባል ያደረገችው ድጋፍ ዘርፈ ብዙና ሁሉን አቀፍ መሆኑን ለመገንዘብ የሚያስችለን ጃንሆይ በእኛ አቆጣጠር ሰኔ 7 ቀን 1952 ዓ.ም ሁለተኛውን የአፍሪካ ነፃ መንግስታት ኮንፈረንስ በከፈቱ ጊዜ ከተናገሩት ውስጥ ተካቶ እናገኛለን፡፡

"... በደቡብ አፍሪካ የሚደረገውን የዘር ልዩነትና ግፍ ተባብረን ለህዝቡ ጠበቃ ለመሆን በስራ መግለጥ አለብን፡፡ አባቶቻቸው በግፍ ለሞቱባቸው የደቡብ አፍሪካ ወጣቶች እስኮላርሽፕና የገንዘብ እርዳታ የሰጠነው በዚሁ በመቆርቆር ነው፡፡" ብለዋል፡፡

በእለቱ ከወቅቱ ኢትዮጵያዊ ምሁራን ውስጥ አንዱ የነበሩት ክቡር አቶ ይልማ ደሬሳ (የታዋቂው የኢኮኖሚ ሊቅ የብላታ ደሬሳ አመንቴ ልጅ) በስብሰባው ከተናገሩት ንግግር ውስጥ ጥቂት ሐተታዎችን ስናይም የኢትዮጵያ ሚና እምን ድረስ እንደሆነ በአጭሩ እንገነዘባለን፡፡

"ክቡራን መልዕክተኞች፤

ወይዛዝርትና መኳንንት፡፡

ይህ የአፍሪካ ነፃ መንግስታት ሁለተኛ ጉባዔ ሊቀመንበር እንድሆን በመመረጤ ከፍ ያለ ክብር ይሰማኛል፡፡

ይህ ምርጫ የእኔ መሆኑ ስለአገሬ ክብርና በተለይም ታላቁ መሪ ገናናው ገኘርዬና ንጉሠነገስቴ ስለአፍሪካ ህዝብ ነፃነት ህዝባዊ መብትና በመሻሻል ወደፊት መራመድ በዚህ ክፍለ ዘመን ያደረጉትን ተጋድሎ ከማወቅ የተነሳ እንደተደረገ እቆጥረዋለሁ፡፡ ...

.... የአፍሪካ ህዝብ እንደራሴዎች አከታትለው ባደረጓቸው ስብሰባዎች የአክራ ጉባዔ የመጀመሪያ እንደነበረ በደስታ የምናስታውሰው ነው፡፡ ይኸውም ጉባዔ ከተደረገ በኋላ ከአንድ ዓመት በሚያንስ ጊዜ ውስጥ የአፍሪካ ኤኮኖሚ ኮሚሲዮን የመጀመሪያው ጉባዔ የድርጅቱ ዋና መስሪያ ቤት በተቋቋመበት ከተማ እዚሁ አዲስ አበባ ላይ ተደረገ፡፡ ከጥቂት



ወራት በኋላ ደግሞ አሁን ስራው ለማለቅ በተቃረበው በአዲሱ የአፍሪካ አዳራሽ የዚሁ ድርጅት ሦስተኛ ጉባኤ እንዲሰበሰብ ተወስኗል፡፡

ስለዚህ ለኢኮኖሚ ጉዳዮች መመካከሪያ የሚሆን ድርጅት እንዲቋቋም የአክራ ጉባኤ ያሳሰበውም አሟልቶ ከስራ በማዋል ረገድ በጣም የተጋፋበት መሆኑን በአጭር ጊዜ ውስጥ ልናውቀው ችለናል፡፡

እንደዚሁም ሁለት መቶ አፍሪካውያን ተማሪዎች በኢትዮጵያ ከፍተኛ ት/ቤቶች ትምህርታቸውን እንደሚከታተሉ ገናናው ገኘርዬ ያቋቋሙት እስኮላር ሽፕ፤ ስለካልቸር ጉዳዮች የተደረገው ውሣኔ በሥራ ላይ ማዋሉን በጉልህ የሚያስረዳ ነው ..." ጉባኤው የሚመክርባቸውን ጉዳዮች በአጭሩ አጠቃለው ሲገልፁም፤

".... ዛሬም ቢሆን ዋናው ችግራችን በአጀንዳችን ተራ ቁጥር 11 የተመለከተውና የቅኝ ግዛትን ከአፍሪካ ጨርሶ ስለማስወገድ፤

ሀ. ነፃ ያልሆኑት አፍሪካውያን አገሮች ነፃነታቸውን እንዲያገኙ ስለሚወሰደው እርምጃ፤

ለ. አዳዲሱ አይነት ኮሎኒያሊዝም ወደ አፍሪካ እንዳይገባ ስለመከላከል" በሚለው እርእስት ተጠቃሎ የሚገኘው ጉዳይ ነው፡፡ ..."

የላይቤሪያ የልዑካን መሪ ሆነው የመጡት ክቡር ሚስተር ሩዶልፍ በእለቱ ከመግቢያ ንግግራቸው አስከትለው የተናገሩት ንግግርም ጃንሆይ ለአፍሪካ ነፃነትና ሠላም ሲሉ በሰሯቸው ስራዎች በአፍሪካውያን መሪዎች ዘንድ ልዩ አክብሮት እንዳሰጣቸው ከማስረዳት ባለፈ፣ የኢትዮጵያን የአፍሪካ ተምሳሌትነት የሚያረጋግጥ ነው፡፡

"... ግርማዊ ሆይ፤

የውቢቷ አገርዎ ታሪክ የመላው አፍሪካ ህዝብ መመኪያ ሆኖ ይታያል፡፡ ግርማዊነትዎም በአፍሪካ ብቻ ሳይሆን በመላው ዓለምም ጭምር ጥንካሬ ከብሩህነት ጋር የተመላበት መሪ ምልክት ሆነው ይታያሉ፡፡ ግርማዊነትዎ በታላቅ መከራና ችግር ዘመን ለነፃነቱ እየታገለ ለመዋጋት ለቆረጠው ህዝብ ምልክት ነው፡፡

ግርማዊነትዎ ፋሽዝም ለዘለዓለም አይኖርም፤ ይደመሰሳል ብሎ ያምን ለነበረው በሚሊዮን ለተቆጠረው ህዝብ ምሳሌ ነው፡፡ ኢትዮጵያ የብዙ ሺ ዘመናት የነፃነት ጣዕም የቀመሰች አገር በመሆኗ ነፃነትን ለሚፈልጉ በሚሊዮን ለሚቆጠሩ ህዝቦች መፅናኛና መነቃቂያ፣ መበረታቻም ሆና ትታያለች፡፡

ግርማዊነትዎ የእኩልነት መብት በሰው ልጅ እንዲኖር በሚጥሩ መካከል ታላቅ ምሳሌ ሆነዋል፡፡..." ካሉ በኋላ "በሁለኛው የነፃ አፍሪካ አገሮች ጉባዔ ስም ሆኜ ዳግም ምስጋናዬን በማቅረብ ለግርማዊነትዎና ለቤተሰቦችዎ ጤናና ረጅም እድሜ፣ ለኢትዮጵያና ለህዝቧም ብልፅግና እመኛለሁ" በማለት ነበር ንግግራቸውን የደመደሙት፡፡

አፍሪካን በሚመለከት ጃንሆይ የነበራቸውን አቋምና ታሪካዊ ንግግራቸውን እውቁ የሬጌ ሙዚቃ አቀንቃኝ ቦብ ማርሌ ሳይቀር "War" በሚለው ዜማ አካቶት እናገኛለን፡፡

"... በደቡብ አፍሪካ፣ በአንጎላ፣ በሞዛምቢክ የሚገኙት ወንድሞቻችን ካሉበት የባርነት ቀንበር ነፃ እስኪወጡ ድረስ መላው አፍሪካውያንና እስያውያን በዓለም ሸንጎ በእኩልነት ደረጃ ድምፃቸው እስኪደመጥ ድረስ የአፍሪካና የእስያ ክፍለ ዓለም ሙሉ ሠላም አላቸው ለማለት አስቸጋሪ ይሆናል፡፡ .... የዘር ልዩነትና ጭቆና የቅኝ አገዛዝ መሠረቱ ኢኮኖሚ ነው፡፡

እነዚህም አሰቃቂ ተግባሮች የሚወገዱት በኢኮኖሚክ መሣሪያ ነው፡፡ በአዲስ አበባው የመሪዎች ጉባዔ የአፍሪካ አገሮች በቅኝ አገዛዝ ስር የሚገኙት አፍሪካውያን ካሉበት የባርነት ቀንበር ነፃ ለመውጣት በሚያደርጉት ትግል እንዲረዱቸው በማለት በገዥዎቻቸው ላይና ሙሉ የኢኮኖሚ አክሲዮን እንዲደረግ ወስነው በስራ ላይ አውለውታል፡፡..." እያሉ በማተት "በመጨረሻም መልካም መጥፎን ድል እንደሚነሳና እኛም እንደምናሸንፍ ጥርጥር የለውም" ባሉት መሠረት የአፍሪካውያን ጥረት ለመጨረሻው ድል በቅቶ በ1970ዎቹ አጋማሽ አመታት የአንጎላ፣ የሞዛምቢክና የጊኒ ቢሳው ህዝቦች ነፃነታቸውን ተቀዳጁ፡፡ እነዚህ የፖርቹጋል ይዞታዎች ነፃነታቸውን ካወጁ በኋላም እ.ኤ.አ በ1989 የመጨረሻዋ አፍሪካዊት አገር ናሚቢያ ለህዝቦቿ በተሰጠው የመምረጥ እድል አማካኝነት ነፃ አገር በቀል መንግስት መመስረት ቻለች፡፡

የደቡብ አፍሪካ የአፓርታይድ አገዛዝም በሕግ ተሽሮ ከዘር ነፃ የሆነ ምርጫ ተካሂዶ በምርጫው /A.N.C./ ኤ. ኤን. ሲን ወክለው የተወዳደሩት ኔልሠን ማንዴላ እ.ኤ.አ በ1994 ዓ.ም በከፍተኛ ድምፅ አሸንፈው በደቡብ አፍሪካ ሪፐብሊክ የመጀመሪያው ጥቁር ፕሬዝደንት ለመሆን ቻሉ፡፡

ባየነው መልኩ የቅኝ አገዛዝ ስርዓት ቢያከትምም የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዙ ዛሬም ድረስ እንደቀጠለ መገኘቱ አይዘነጋም፡፡ ጃንሆይ "የቅኝ አገዛዝ መሠረቱ ኢኮኖሚ ነው፣ ማስወገጃውም ኢኮኖሚ ነው" እንዳሉት የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዙም በኢኮኖሚ ድክመት በኩል የሚተገበር መሆኑን እያየን ነው፡፡

በእነዚያ ዘመናት ከኢትዮጵያ በስተቀር መላው አፍሪካና ህዝቦቿ ለነፃነታቸው ሲፍጨረጨሩ ኢትዮጵያ ነፃ የትምህርት እድል ለአፍሪካውያን ከመስጠት ባለፈ፤ ራሱን የቻለ በባለሙያ የተሞላ የውጭ ግንኙነት የነበራትና ቢሮክራሲዋም ዓለም አቀፍ ይዘት የነበረው አገር ነበረች፡፡



ልክ በዚሁ መጠንም ጃንሆይ አፍሪካ ውስጥ ራሱን የቻለ መንግስት ባልተመሰረተበት አህጉር ከታዋቂ መሪዎች ተርታ የተሰለፉ፣ ዓለም አቀፍ እውቅናቸው የዳበረና የተከበሩ ተሰሚነት የነበራቸው መሪ ነበሩ፡፡

ለውጭ ግንኙነት ምቹ የሆነ የአየር መንገድ ስለነበረም አፍሪካውያን የነፃነት ታጋዮች ባሻቸው ጊዜ በነፃነት ወደ ኢትዮጵያ እየመጡ በአህጉሪቱ ቀጣይ ዕጣ ፋንታ የመወያየት እድል ነበራቸው፡፡ በእኛ አቆጣጠር በ1953 ዓ.ም ግንባታው የተጠናቀቀውን የኢ. ሲ. ኤን /E.C.A/ አዳራሽ የመሰሉ ምቹ መሰብሰቢያዎችን ጃንሆይ በራሳቸው ገንዘብ አስገንብተው የፓን አፍሪካኒዝም ውልድ ለሆነው ለአፍሪካ አንድነት ድርጅት አበርክተዋል፡፡ የድርጅቱ ቋሚ መቀመጫ ኢትዮጵያ እንድትሆን የተደረገውም የጃንሆይ መንግስት ለአህጉሪቷ ነፃነት ያበረከተው አስተዋፅኦ ከፍተኛ በመሆኑ ምክንያት ነው፡፡

ጃንሆይ "የአፍሪካ አባት" ነበሩና ዛሬም ድረስ በዚሁ ስም ይጠራሉ፡፡ ኢትዮጵያ "የአፍሪካ እናት" የተሰኘችውም በቅኝ ግዛት ያልተያዘች ብቸኛ አፍሪካዊት አገር በመሆኗ ብቻ ሳይሆን ለአፍሪካ ነፃነት ተምሳሌት በመሆኗ ነው፡፡ ከአፍሪካም ባለፈ በቆየው የአድዋ ድል ለመላው ተገዥ ህዝቦች የፅናት ተምሳሌት ሆና የተጠቀሰች ብቸኛ አገር ናት፡፡

ይህን መነሻ በማድረግም በርካታ የአፍሪካ አገሮች ከነፃነታቸው በኋላ የየራሳቸውን ሠንደቅ ዓላማ ሲያዘጋጁ የቀለም ምርጫቸው የኢትዮጵያን ሠንደቅ ዓላማ መሠረት ያደረገ ሆኖ ቀርቷል፡፡

-ይህን ንዑስ ርዕስ ከማጠቃለላችን በፊት አንድ ከአፍሪካ ጉዳይ ውጪ የሆነ የጃንሆይን ተግባር እንይ፡፡ በእኛ አቆጣጠር በ1952 ዓ.ም በፈረንሣይ አገር የተፈጥሮ አደጋ ደርሶ ነበር፡፡ በዚያን ጊዜ ጃንሆይ የሐዘን መግለጫቸውን ከላኩ ከጥቂት ቀናት በኋላ የገንዘብ እርዳታ ለፈረንሣይ ሰጥተዋል:: በዚያ አፍሪካውያን ልዩ እርዳታ በሚያስፈልጋቸው ወቅት ጃንሆይ ከአፍሪካ አልፈው ለፈረንሣይ ያደረጉት እርዳታ ቀደም ሲል ያየናቸው ሐተታዎች ከወጡበት ከ1952ቱ "ፍሬ ከናፍር" ከተሰኘው መጽሐፍ ተካቶ የሚገኝ ሲሆን፤ የፈረንሣዩ መሪ ቻርለስ ደጎል እና ጃንሆይ የተለዋወጧቸው ቴሌግራሞች የሚከተሉትን ይመስላሉ፤

"ለክቡር ፕሬዝዳንት ደጎል
ኤሊዜ ቤተ-መንግስት
ፓሪስ፡፡

የፍሬዡስ ከተማ በደረሰባት አሰቃቂ አደጋ ምክንያት ጉዳቷን ለማቃለል ይረዳ ዘንድ በፓሪስ ኢንዶሺን ባንክ በኩል አምስት ሚሊዮን ፍራንክ ልከንልዎታል፡፡ ይህ የተላከው እርዳታ በዚህ መቅሰፍት ለተጎዳው ህዝብ በመሰለዎ አይነት ለእርዳታ ይውል ዘንድ ክቡርነትዎን እንጠይቃለን፡፡"

ከኘሬዝዳንት ቻርልስ ደጎል የተሰጠ መልስ፤

"የኢትዮጵያ ንጉሠነገስት ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለስላሴ

አዲስ አበባ፡፡

በፍሬዥስ ከተማ ላይ በወደቀበት አሰቃቂ መቅሰፍት ምክንያት ጉዳት ለደረሰበት ህዝብ ማቃለያ ይሆን ዘንድ ግርማዊነትዎ ርህራሄ በተመላ ቸርነቱ ስላደረገው ከፍ ያለ ስጦታ በሙሉ ልቤ ሳመሰግን፤ እንዲሁም በእኔና ይህ ጉዳት በወደቀበት ህዝብ ስም ሆኜ ጥልቅ የሆነ ባለውለታ መሆኔን እገልፃለሁ፡፡

ቻርልስ ደጎል፡፡"

ጃንሆይና ራስ ተፈሪያውያን

የጃንሆይ ንጉሠነገስትነት ለእኛ ነው፡፡ ለሌሎች ደግሞ አምላክ የሆኑበት ሁኔታ አለ፡፡ ይህን ታሪካቸውን ላለመዘለል ያህል ጥቂት ማለት ተገቢ ይመስላል፡፡ ኢትዮጵያን የዓለም ህዝቦች ዓይን ማረፊያ ካደረጓት ነገሮች ውስጥ አንዱ ነፃነቷን ሳታስደፍር መቆየቷና ብቸኛዋ ነፃ አፍሪካዊት አገር መሆኗ ነው፡፡ አውሮፓውያን በአፍሪካ ምድር ቅኝ ግዛታቸውን አንሰራፍተው ከዚችው አህጉር ጥቁር ህዝቦችን በባርነት እያጋዙ በየአገሮቻቸው የጥጥ፣ የትምባሆ እና የሌሎች ሰፋፊ የግብርና መስኮች ስራ ላይ እያሰማሩ በአሰቃቂ ሁኔታ ጉልበታቸውን በሚበዘብዙበት ጊዜ የጥቁር ህዝቦች ብቸኛ ተስፋና አርአያ የነበረችው ኢትዮጵያ ብቻ ነበረች፡፡

በተለይም የየካቲት 23/ 1888ቱ የዓድዋ ድል የበርካታ ጥቁሮችን ስሜት ያነሳሳና የነፃነት እንቅስቃሴያቸውን ያቀጣጠለ ክስተት ሆኖላቸዋል፡፡ ከተለያዩ ቅኝ ተገዥ አገራት የሚጋዙ ጥቁር ህዝቦችም በጉዞ ላይ ሳሉ በሚደርስባቸው ስቃይ ሳቢያ ሲታመሙ፣ ሲቆስሉና ጉዳት ሲደርስባቸው እስኪያገግሙ ይቆዩ የነበረበት ቦታ ጃማይካ ነበረች፡፡

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የነበረው ፍልሰት ቀጥሎ ብዙሃኑ ለረጅም ዓመታት በአውሮፓ ምድር ሲሰቃዩ ኖረው ከነፃነት በኋላም ዛሬም ድረስ ያልተመለሱ ኑሮዋቸው እዚያው የሆነ ጥቁር ህዝቦች ሞልተዋል፡፡

"ነብይ በአገሩ አይከበርም" እንዲሉ ራስ ተፈሪ በእኛ እይታ ከንጉሠነገስትነት ያለፈ ሚና ባይኖራቸውም፤ በጃማይካውያን ዘንድም ሆነ በዘመናቸው በነበሩ ጥቁር ህዝቦች ዘንድ የአምላክነት ወይም የነብይነት ስፍራ የተሰጣቸው ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡

በተለይም ለማርክስ ጋርቬይ እና ለመሰሎቹ ወደ አፍሪካ የመመለስ እንቅስቃሴ ጽኑ መሠረት ለመሆን ችለዋል፡፡ አሜሪካ በኢኮኖሚ ቀውስ በምትናወጥበት በ1920ዎቹ የመጀመሪያ አመታት ከነበረው የጭቆና አገዛዝ ጋር ተዳምሮ የጥቁር ህዝቦችን ጭቆና የመረረ አደረገው፡፡ ከ1887 እስከ 1940 ዓ.ም ድረስ ምድር ላይ የነበረው



ጃማይካዊ ማርክስ ጋርቬይ "Back to African Movement" ወደ አፍሪካ የመመለስ ንቅናቄ መስራችና አስተባባሪ በመሆን ታሪካዊውን የአድዋ ድል መነሻ በማድረግ ንቅናቄውን አጠናከረው፡፡

ከ1920ዎቹ ጀምሮ ብዙዎች ወደ አፍሪካ ምድራቸው ሲመለሱ ጥቂቶች ወደ ኢትዮጵያ መጥተዋል፡፡ይህ በእንዲህ እንዳለ ራስ ተፈሪ ንጉሠነገስት ሆነው ማስተዳደር ከጀመሩ በኋላ ፋሽስትም ዳግም ወረራ ባደረገበት ጊዜ ንጉሡ በስደት ለንደን ሆነው አቤቱታቸውን በሚያቀርቡበት ወቅት ጥቂት ጃማይካውያን ጥቁሮች ከንጉሠነገስቱ ጋር በመገናኘት በፌዴሬሽን ከኢትዮጵያ ጋር የመተሳሰር ሀሳባቸውን አቀረቡላቸው፡፡ጃንሆይም ሀሳባቸውን ተቀብለው ፈቃዳቸውንም ገልፀው አሰናበቷቸው፡፡

በዚያን ጊዜ "W.F.R. (World Federation of Rasta)" በሚል ለመጀመሪያ ጊዜ የዓለም የራስ ተፈሪያውያን ፌዴሬሽን ተመሠረተ፡፡ ከዚህ ጊዜ በፊትም እ.ኤ.አ በ1920 ዓ.ም ኃይለስላሴ ከመንገሳቸው በፊት (ራስ ተፈሪ እያሉ) ማርክስ ጋርቬይ አውሮፓውያን ለአውሮፓ እንደሆኑት ሁሉ አፍሪካውያንም ለአፍሪካ ሆነው ባርነትን ትተው ወደ ምድራቸው መመለስ እንዳለባቸው፤ ባለመብት በሆኑበት በአፍሪካ ውስጥም በነፃነት ራሳቸውን በማደራጀትና በማስተባበር ታላቅ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ለውጥ መፍጠር መቻል አለባቸው የሚለውን አቋሙን በአሜሪካ ማስተማር ጀምሮ ነበር፡፡ ማርክስ ጋርቬይ አውሮፓና አሜሪካ የማስተማር ቆይታውን ጨርሶ በ1927 እ.ኤ.አ ወደ ጃማይካ ተመለሰ፡፡

ለህዝቦቹም ትምህርቱን ከፖለቲካዊ ዓላማው እየተነተነ በደንብ አስረዳቸው፡፡ "የአፍሪካ ቀን እየመጣ ነው፡፡ ቀኑ መቼ እንደሆነ የሚያውቅ የለም፣ ነገር ግን ይመጣል" በማለት ሲያስተምር ቆየ፡፡

በትምህርቱ ውስጥም ለጥቁሮች ችግር መፍትሔ አፍሪካ መሆኗን፤ ጥቁር ህዝቦች የአምላክ አምሳያ መሆናቸውን፤ በቅርቡ የሚነሳ ጥቁር ንጉስ የዚህ ትምህርት ትንቢት ፍፃሜ አመላካች መሆኑን" ደጋግሞ ገለፀ፡፡

የጋርቬይ ትምህርት በጃማይካ ጥቁር ህዝቦች ዘንድ ከሰረፀ ከጥቂት አመታት በኋላ ራስ ተፈሪ ንጉሠነገስት ሆኑ፡፡ ይህ ክስተት ጃማይካውያንን ጋርቬይ በመሠረተው ድርጅት እንዲያምኑና እንዲቀላቀሉ አስገደዳቸው፡፡ በሁኔታዎችና በሚዲያ በሚሰጡ መግለጫዎች የበለጠ አላማው እየታወቀለት ትንቢቱ መስመሩ ተቀባይነት እያገኘለት ይሄድ ጀመር፡፡

ከዚያም ታሪኩ መፅሐፍ ቅዱሳዊ ይዘት እንዳለው ሆነና በአውሮፓና በአሜሪካ የደም ላባቸውን የሚያፈሱና በባርነት ቀንበር ስር የአውሮፓን ህንፃ የሚገነቡ፣ ግብርናውን የሚያቀላጥፉና ኢንደስትሪውን የሚያንቀሳቅሱ ባሮች በአጠቃላይ በነጭ ስር የሆኑ ጥቁር ህዝቦች ራሳቸውን እንደ እስራኤላውያን ተገዥዎች መቁጠር ሲጀምሩ፤

ገዥዎቻቸው የሆኑ ነጮችን እንደ ግብፅ ፈርኦኖችና ህዝቦች መቁጠር ጀመሩ፡፡ ጋርቬይም ይህንኑ መፅሐፍ ቅዱሳዊ ቃል ምሳሌ እያደረገ ማስተማሩን ቀጠለ፡፡

እናም አፍሪካውያን ጥቁር ህዝቦች በባርነት የሚኖሩበት አገር "ባቢሎን" ሲባል፤ የሚመለሱባት የተስፋይቱ ምድር "ከነዓን" እንደሆነች እሷም ኢትዮጵያ መሆኗን አምነው ተቀበሉ፡፡

ኢትዮጵያ ከባርነት አገር ተነስተው የሚመጡባት የተስፋ ምድር ከነዓን የመሆኗን ሚስጥርም የማርከስ ጋርቬይ /የነብያቸው/ ትምህርት የፈጠረው መሆኑ ነው፡፡ ጋርቬይ ቀደም ሲል በጀመረው የመመለስ እንቅስቃሴ ይህ ነው የሚባል ተጨባጨ ለውጥ ያልመጣ ቢሆንም፤ ራስ ተፈሪ ከነገሱ በኋላ ግን ትንቢቱ ተፈፀመለትና ራስ ተፈሪያኒዝም ራሱን የቻለ ሃይማኖት /እምነት/ እየሆነ ሄደ፡፡

በዚህም በርካቶች ወደተስፋይቱ ምድር የመመለስን ጥያቄ በውስጣቸው ማንሰላሰል ያዙ፡፡ ቀስ በቀስም በመላዋ ጃማይካ ተከታዮቹ በረከቱ፡፡ ቀደም ሲል ይዝናኑበትና ይታወቁበት የነበረው የ"ብሉዝ" የዜማ ስልት በ"ሬጌ" ስልት ተለወጠና እነ ኒስታ ቦብ ማርሌይ ለራስ ተፈሪያኒዝም ተከታዮች ዓላማቸውን የማስራጫ መንገድ አደረጉት፡፡ ቦብ ማርሌ (ኤክሲደስ) "ዘፀዓት" ሲል አዜመ፡፡ ተቀብለው አቀነቀኑ፡፡ በዘፈናቸው ተደጋግሞ የሚደመጠው "ባቢሎን" የሚለው ቃልም ካየነው ታሪክ በመነሳት ሳይጠቀስ የማይታለፍ ሆነ፡፡

የጃንሆይ የንግስና ስማቸው ኃይለስላሴ ስለሆነም በስላሴ ትምህርት መሠረታቸውን በማድረግ እንደ አምላክ እንዲቀበሏቸው ማረጋገጫ ሆነላቸው፡፡ በዚህ ጊዜ ማርከስ ጋርቬይ ነብይ፤ ራስ ተፈሪ አምላክ ሆነው ታመኑ፡፡

ንጉሡ ጃማይካን በጎበኙ ጊዜ "እኔ አምላክ አይደለሁም" ብለው ቢያስተባብሉም መላው የጃማይካ ህዝብ ግን የንጉሡን ንግግር እንደ ትህትና ቆጥረው "አምላካችንን አየናቸው" አሉ እንጂ ማስተባበያውን አልተቀበሉትም፡፡

እ.ኤ.አ በ1966 ዓ.ም አፄ ኃይለስላሴ ጃማይካን በጎበኙበት ጊዜ በመላው ጃማይካዊ ራስ ተፈሪያኒዝም ዘንድ ታላቅ ታዓምራት የታየበት እለት ተባለ፡፡ የጃንሆይን የጃማይካ ጉብኝት በተመለከተ በአዲስ ውበት መፅሔት በ1997 ዓ.ም ቃለ-ምልልስ ያደረገው የራስ ተፈሪያን ተከታይ የሆነው ዳኒ በወቅቱ ቦታው ላይ ነበርና ሁኔታውን እንዲህ ይገልፀዋል፡፡

"ንጉሡ ከአውሮፕላን በወረዱ ጊዜ አለቀሱ፡፡የማልቀሳቸውም ምስጢር ያንን ከቦ የሚጮህ ህዝብ ማየታቸው ነው፡፡የህዝቡ ፍቅር፣ደስታ፣መሪና አምላክ መፈለግ ልባቸውን ነካው፡፡ደግሞም የሚያዩት ህዝብ ከኢትዮጵያውያን ጋር የሚመሳሰል ነው፡፡ንጉሡም"በእርግጥ የማየው



ህዝብ በትክክል ከኢትዮጵያውያን ጋር የሚመሳሰል ነው" ማለታቸውን" ይገልፃል፡፡ "በወቅቱ ጃማይካ ለ7 ወራት ያህል ዝናብ አጥታ ድርቅ ሆኖ ነበር፡፡ንጉሡ ግን ዝናብ ዘንቦ ካባራ በኋላ ነበር የደረሱት፡፡

ቀኑ በጣም ጨለማና ጨፍጋጋ ሆኖ ውሎ ልክ ንጉሡ ከአውሮፕላን በወረዱ ጊዜ ገፈፈ፡፡ ብርሃንም ሆነ፡፡ እናም እውነት ነው፡፡ ህዝቡም ዝናቡንም ሆነ ብርሃኑን ያመጡልን ንጉሡ ናቸው በማለት የዓይን እማኝነቱን አረጋግጧል" የሚል ቃሉን የሰጠው በየካቲት ወር 1997 ዓ.ም የቦብ ማርሌ 60ኛ ዓመት በአዲስ አበባ ሲከበር በተደረገለት ቃለ ምልልስ ነበር፡፡

ይህን መሰሉ ታሪካዊ ግጥምጥሞሽ ለራስ ተፈሪያኒዝም ግን እውነት ነውና አፄ ኃይለስላሴ ለአንዳንዶቹ አምላክ፤ ለሌሎቹ ነብይ ሆነው ዛሬም ድረስ ይመለካሉ፡፡ ኢትዮጵያም የተስፋይቱ ምድር መሆኗ ቀጥሏል፡፡

ራስ ተፈሪያኒዝም አንድ ራሱን የቻለ እምነት /ሃይማኖት/ ይሁን እንጂ ተከታዮቹ ግን አንድ የሚያምኑት ነገር አለ፡፡ ይኸውም በውስጡ ፖለቲካዊ የነፃነት ትግል የያዘ መሆኑን ነው፡፡
ራሳቸውን ሲጠሩ ራስታ፣እምነታቸውን ደግሞ ራስተፈሪያኒዝም በማለት አፄ ኃይለስላሴን አምላካችን ናቸው ብለው ማመናቸው እንዳለ ሆኖ፤የነፃነት ትግል በውስጡ መያዙን አይክዱም፡፡ጠቅለል ተደርጎ ሲታይ ራስ ተፈሪያኒዝም ተብለው ቢጠቃለሉም በስሩ ግን በርካታ ልዩነቶችን እናያለን፡፡የተለያዩ ቡድኖችም በስሩ ይገኛሉ፡፡ ለምሳሌ፤"ቦቦ ድሬድ /BOBO -DRED TWELVE/ አንድ የአማኞች ቡድን ሲሆን (በሻሸመኔ የሚገኝ ቡድን ነው)መሪያቸው ፕሪንስ ኢማኑኤል ነው፡፡እንደ ቦቦ እምነት ማንኛውም የእምነቱ ተከታይ ወንድ እንደ ነብይ ይቆጠራል፡፡ሲል እንደ ሌሎቹ ራስ ተፈሪያን ሁሉ የጥቁሮች ደህንነት ከባቢሎን ወደ ኢትዮጵያ መመለስ ነው፡፡

ሌላው ቦብ ማርሌይ እና ቤተሰቦቹ የሚገኙበት የእምነት ቡድን ሲሆን፤ በራስ ተፈሪያን ስር ሆኖ የ12ቱ የእስራኤል ነገዶች /TWELVE TRIBES OF ISRAEL/ የሚባል ነው፡፡ በዶክተር ቬርኖን መሪነት ይተዳደር ነበር፡፡ የአፄ ኃይለስላሴን የልጅ ልጅ ወደዙፋን የመመለስ ህልምም ነበራቸው፡፡ ዛሬም የልጅ ልጅ ልጅ የሆነውን እንዲመለስ ይናፍቃሉ፡፡ መሠረታቸው አርቶዶክስ ሆኖ፤ ከእምነቱ መመሪያ ውስጥ በየቀኑ አንድ ምዕራፍ ከመፅሐፍ ቅዱስ ማንበብ የሚል ጥብቅ መመሪያ አላቸው፡፡

ሌላው ቡድን "ኒያቢንጊ" ማለትም "ሞት ለነጮች" የሚል ትርጉም ያለውና "ጥቁር ያልሆነ ወይም ነጭ የሆነ ሰው የራስ ተፈሪያን ተከታይ

መሆን አይችልም የሚል አቋም ያለውና በራስታ ክበሮ ራስ ተፈሪን በማሞገስና በማመስገን በባህላዊ ዘዴ ያመልካሉ፡፡

ሌላው የኢትዮጵያ የዓለም ራስታዎች ፌዴሬሽን ወይም በምህፃረ ቃል E.W.F.R በመባል የሚታወቀው ነው፡፡ የዚህ ቡድን ምስረታ ራቅ ያለና ቀደም ሲል እንዳየነው በፌዴሬሽን ከኢትዮጵያ ጋር የመቀላቀል ኀሳብ ያቀረበው ነው፡፡ በራስ ተፈሪ አምላክነት የፀና እምነት ያለውና አክራሪ ራስተፈሪያን የታጨቁበት ነው፡፡ ክርስቶስ ማለት ኃይለስላሴ፣ ኃይለስላሴ ማለት ክርስቶስ ራሱ እንደሆነ ማመን የአንድነታቸው መገለጫ ነው ...”

ከአራቱ ቡድኖች የአምልኮ ቀናቸውን ሦስቱ ቅዳሜን ሲያደርጉ፤ የቦብ ማርሌይ ቤተሰቦች ቡድን ግን እሁድን መርጧል፡፡ በአጠቃላይ እምነቱ (ወዝገብገብ ያለ ነገር እንዳለው ሆኖ) ኃይለስላሴ የክርስቶስ ቅጥያ ሆኖ ነው ነፃ ያወጣን፣ ክርስቶስ ኃይለስላሴን ተመስሎ ነው የሚል ይዘት አለው፡፡

ትስስሩ እየተጠናከረ የሄደው በተለያዩ ታሪካዊ አጋጣሚዎች ነበር፡፡ በይበልጥ ግን በእምነቱ ውስጥ ጠንካራ መሠረት የተጣለው በዳግም የኢጣሊያ ወረራ ወቅት ንጉሡ ለንደን በነበሩ ጊዜ ለስደተኞች የመመለስ ጥሪ ምላሻቸው ፈጣን በመሆኑ ነበር፡፡ “ኢትዮጵያ ከመጣችሁ እጃችንን ዘርግተን እንቀበላችኋለን” በማለት ጋብዘዋቸው ነበር፡፡ ንጉሡ በጉብኝታቸውም ጊዜ የተፈጠረውን ተዓምር ተከትሎ በርካታ ጃማይካውያን ወደዚህች የተስፋ ምድር የመመለስ ጉጉታቸውን አንሮታል፡፡

ያኔ በስደታቸው ዘመን በገቡላቸው ቃል መሠረትም አፄ ኃይለስላሴ ወደ ኢትዮጵያ ለሚመጡ ጃማይካውያን ሻሸመኔን ሰጧቸው፡፡ ከጃማይካ ጉብኝታቸው በፊትና በኋላም በርካታ ራስታዎች ወደሻሸመኔ መጉረፍ ጀመሩ፡፡ ይሁን እንጂ የተሰጣቸውን መሬት ሳያለሙትና ሳይስፋፉ የመንግስት ለውጥ ተደረገና የተሰጣቸው መሬት በደርግ ተወረሰ፡፡

ከዚያ በኋላ ባለው ጊዜ ቀድመው የመጡት በሻሸመኔ በድህነትና በዘመዶቻቸው ድጎማ ኑሯቸውን መግፋት ሲችሉ፤ ሊመጡ በዝግጅት ላይ የነበሩትም ሀሳባቸውን ቀየሩ፡፡ ከ35 ዓመታት በላይ ዛሬ ድረስ እዚያው ሻሸመኔ ያሉና ቦታውን ሳይለቁ የኖሩ ቁጥራቸው አነስተኛ ቢሆንም “ስጦታችንን በክብር እንጠብቃለን” ብለው ይኖራሉ፡፡

በጠቅላላ በዓለም አገራት ያሉና ዛሬም ድረስ ወደተስፋይቱ ምድር የመመለስ ጉጉት ያላቸው ራስታዎች ደግሞ ቁጥራቸው በአሁኑ ሰዓት ግማሽ ሚሊዮን እንደሚደርስ ይገመታል፡፡ ሃይማኖቱም ከዓለም ሃይማኖቶች ተርታ ተሰልፎ ይገኛል፡፡ ከሻሸመኔ ጋር በተያያዘ ያለው



ሁኔታም አንዳች እልባት ላይ ሳይደርስ በእንጥልጥል እንዳለ አለ፡፡ ነገር ግን የብዙዎች አቋም ቦብ ማርሌይ እንዳለው “HOLD ON TO WHAT YOU HAVE GOT” ስጦታችሁን ጠብቋት የሚል ነው፡፡ እናም የሙጥኝ ብለዋል፡፡የሆነው ሆኖ የዚህ ሁኔታ ዋናው የታሪክ መነሻ የዓድዋ ድል ነው፡፡ የጥቁር ህዝቦች ኩራት ስለሆነም ያንን የየካቲት 23ቱን ድል መሠረት በማድረግ መላው የዓለም ጥቁር ህዝብ ወሩን “The BLACK HISTORY MONTH” በማለት ሁሌም እያከበሩት ይገኛል፡፡ ስለዚህ ኢትዮጵያ የተስፋይቱ ምድር ሆነች፡፡ በዚህ ማን ይከፋዋል? “ጃ ራስተፈሪያን” ብሎ መቀበል ነው፡፡



ራስተፈሪያውያን ከጃንሆይ ጋር “ጃ”ሲባባሉ

*አብዮቱ ሲያብጥ*

የ1953ቱ የመፈንቅለ መንግስት ሙከራ ላይ ምንም እንኳ ተማሪዎች ፈራ ተባ ያለ አቋም ይዘው የነበረ ቢሆንም፤ ከክሽፈቱ በኋላ ግን ዙፋኑ ሊደፈር እንደሚችል ተረድተዋል፡፡ ጄኔራል መንግስቱ ንዋይ ከሽንፈቱ በኋላ “የለኮስነው እሳት እራሱ አይጠፋም” እንዳለውም ከዚያ ጊዜ በኋላ አገዛዙን የሚቃወሙ አካላት ጠፍተው አያውቁም፡፡ ከእነዚህ አካላት ውስጥም የዩኒቨርሲቲው ማኅበረሰብ በቀዳሚነት ይጠቀሳል፡፡

ከ1953 ዓ.ም በፊት በነበሩት ጊዜያቶች ተማሪዎቹ ኀብረታቸውም ሆነ አጀንዳቸው የዩንቨርሲቲያቸውን ጊቢ በማዘመንና በተለያዩ የጊቢው ዝግጅቶች ላይ በየዘርፉ በመሳተፍ እውቀታቸውን በራሳቸው ጥረት ለማዳበር መጣርን መሠረት ያደረገ ብቻ ነበር፡፡

ከ1954 ዓ.ም ጀምሮ ግን ምልከታቸው ከራሳቸውና ከጊቢያቸው አልፎ ወደ ኅብረተሰቡ ማተኮር ጀመረ፡፡ በየዓመቱ የኮሌጅ ቀን

ይከበርበት በነበረው ዕለት ይቀርቡ የነበሩ የውዳሴ ግጥሞችም ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ትችት እያካተቱ መነበብ ጀመሩ፡፡ በዚህም መንግስት ክፉኛ ተቆጥቶ በ1954 ዓ.ም የተማሪዎችን አስተባባሪዎችና አባላት ከትምህርት እንዲታገዱ እስከመወሰን ደረሰ፡፡

በ1956 ዓ.ም የኢትዮጵያ ዩንቨርሲቲ አገልግሎት የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ከትምህርት ጊዜያቸው ውስጥ አንዱን ዓመት በገጠሪቱ ኢትዮጵያ እንዲያሳልፉ ወስኖ ተግባራዊ ሲሆንም፤የተማረው አካል የገጠሩን ማኅበረሰብ ህይወት እንዲገነዘብ አደረገው፡፡ከዚህም ባለፈ ይህ ተግባር በየግዛቱ ያሉ የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎችንና የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችን በማቀራረብ ረገድም የራሱ አስተዋፅኦ ነበረው፡፡

ከተጠቀሰው ዘመን በኋላ ባሉት ተከታታይ ዓመታት ለተማሪዎች የመጀመሪያ ፍላጎትና የትግል ዘዴ ሆኖ የታያቸው ሀሳባቸውን የሚገልፁበትና ለሌሎችም የሚያሰራጩበት ነፃ መድረክ መፍጠር ነው፡፡ለዚህም የፕሬስ ውጤት ብቸኛ አማራጭ ነበርና የራሳቸውን መጽሔት የሚያዘጋጁበትን ሁኔታ ማመቻቸትና ነፃ ማኅበራትን ማቋቋም ጀመሩ፡፡

ቀደም ሲል የነበረው የተማሪዎች ምክር ቤት ማኅበር አደረጃጀቱ ነፃ ያልነበረና በኮሌጁ ዲን ቁጥጥር ስር የነበረ ነው፡፡ በልሳን ደረጃ ዩ.ሲ ኮልስ (የዩንቨርሲቲ ኮሌጅ ጥሪ) እና ኒውስ ኤንድ ቪውስ (ዜናና አስተያየት) የተባሉ መጽሔቶችም ፖለቲካ ውስጥ የማይገቡና የዩኒቨርሲቲውን የበላይ አካላትና የአስተዳደር እንዲሁም የመማር ማስተማሩን ሂደት የሚተቹ ጽሁፎች አልፎ አልፎ የሚቀርቡባቸው የነበሩ ናቸው፡፡

በዚህ መሠረት ከ1954 ዓ.ም ጀምሮ በስውርም፣በገሃድም ነፃ የተማሪዎች ማኅበር እየተቋቋሙ ልዩ ልዩ የተቃውሞ ድምጾች መደመጥ ጀመሩ፡፡የጃንሆይን አገዛዝ በመቃወም ረገድ ከፍተኛ ተፅዕኖ የፈጠረው በ1956 ዓ.ም የተቋቋመው "ክሮኮዳይል" ወይም "አዞ" የተባለው ቡድን ነው፡፡ የኢምፔሪያሊዝምን ክፉ ገፅታ በመተንተንና የማርክሲዝምን ጽንሰ ሀሳብ በማጥናከሸት ረገድም ሆነ፤ የንጉሡን አገዛዝ የሚቃወሙትን አካላት ተቃውሟቸው የከረረ ሆኖ እንዲቀጥል በማድረግ ረገድ፤እንዲሁም ኢትዮጵያ ከጃንሆይ አገዛዝ በኋላ ለጠበቃት ተከታይ መዘዝና አገሪቱ ዛሬ ላለችበት ቅርፅና ይዘት ሁሉ አዞዎቹ የአንበሳውን ድርሻ ይይዛሉ፡፡

የተማሪዎች ነፃ ማኅበር ምስረታ ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶም በአገር ውስጥና በውጭ አገር አገዛዙን ለመቃወም የተመሠረቱ መሰል ቡድኖች አላማቸውን በጋራ ማራመድ ቀጥለዋል፡፡ እነርሱም፤

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ማኅበር (አ. አ. ዩ. ተ. ማ.)

- የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር በሰሜን አሜሪካ (ኢ.ተ.ማ.ሰ.አ)
- የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር በአውሮፓ (ኢ.ተ.ማ.አ)
- የኢትዮጵያ ተማሪዎች ዓለም አቀፍ ማኅበር (ኢ.ተ.ዓ.አ.ማ) የሚባሉ ናቸው፡፡ እነዚህ ማኅበራት የየራሳቸውን መጽሔቶችና የንድፈ ሃሳብ ልሳኖችን መሠረቱ፡፡

የኢትዮጵያ ተማሪዎች ዓለም አቀፍ ማኅበር የአህጉር ቅርንጫፍ የሆነው የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ማኅበር "ታገል" የተሰኘ መጽሔትን፣ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር በሰሜን አሜሪካ "ቻሌንጅ"ን፣ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር በአውሮፓ ደግሞ የ"ታጠቅ" እና የ"ትግላችን" መጽሔቶችን መስርተው እንቅስቃሴያቸውን አጎልብተው ቀጠሉ፡፡

በተለይ "ቻሌንድ" እና "ታጠቅ" የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ የጋራ የንድፈ ሃሳብ መጽሔቶች ሆኑ፡፡ የድርጅትና የርዕዮት ዓለም የበላይነቱን አረጋግጦ የነበረው ግን "ታገል" ወይም "Struggle" የሚለው መጽሔት ሲሆን፤ የግራ ክንፍ የበላይነቱንም የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ማኅበር ነበር የያዘው፡፡

በውጭ አገር ያሉትና እንደ ዋና አስተባባሪ ማኅበራት የሚቆጠሩት አንድ ዓላማ የነበራቸው ማኅበራትም በስተመጨረሻ በመገንጠል ጉዳይ ተከፍለው በጠላትነት ሲዋረፉ ኖረው፤ ከአብዮቱ በኋላም የእነርሱ የመረረ ጥላቻ ወደ ኢትዮጵያም ተዛምቶ ብዙ እልቂት አስከተለ፡፡ ነገር ግን በዚያ ወቅት በተለይ ልሳኖችን በማሰራጨት በኩል የውጮቹ የተጫወቱት ሚና ከፍተኛ ነበር፡፡

በእነዚህና በሌሎች መሰል የፖለቲካ ትግል ዘዴዎች በመጠቀም ዋና ዋና ማኅበራቱና ንዑሳን ቡድኖች፣ በአገር ውስጥና በውጭ አገር ያሉት ሁሉ በጋራ ይፋ ያደረጉት አቋማቸው በኢትዮጵያ ተማሪዎች ዓለም አቀፍ ማኅበር አባላትና መጽሔቶች ሲገለፅ፤"የኢትዮጵያ ህዝብ ላጋጠመው የስርዓት ችግር መፍትሄው የፖለቲካ ጥገና ሳይሆን አብዮታዊ የስርዓት ለውጥ እንደሆነ፤መሬት ላራሹ የሚለውን የፖለቲካና የኢኮኖሚ ጥያቄ እስከመጨረሻው ማስተጋባት፣ ኢምፔሪያሊዝምና ፊውዳሊዝም የኢትዮጵያ ህዝብ ዋና የመደብ ጠላቶች እንደሆኑና ይህን መሰሉን አገዛዝ ለመገርሰስ የፖለቲካ ትግሉን እስከመጨረሻው መቀጠል" የሚል ነው፡፡

እነዚህን አቋሞች ከኢትዮጵያ ውጭ ያሉ ታጋዮች አቅልለው ቢገልጿቸውም ለአገር ውስጥ የተግባር ተፋላሚዎች ግን እጅግ ፈታኝ ነበሩ፡፡ ምንም ቢሆን ግን የአገር ውስጥ ተማሪዎች ከመተግበር ወደኋላ አላሉም፡፡ የመጀመሪያውን የከረረ ተቃውሞ በ1957 ዓ.ም ተገበሩት፡፡ "መሬት ላራሹ" ብለው የአዲስ አበባን ጎዳና አጥለቀለቁት፡፡ ከፀጥታ

አስከባሪዎች ጋር መጋፈጡ ቀላል ያልነበረ ቢሆንም፤ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ በየዓመቱ ተማሪዎች ሰልፍ እየወጡ ስርዓቱን መቃወማቸውን ቀጠሉ፡፡

ለአመፅ ወደ ጎዳና የሚወጡበት መፈክርም በተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ላይ በሚታዩ በደሎች መነሻነት ነው፡፡ በዚህም ብቻ ሳይሆን በየሰበብ አስባቡ ሰልፍ ለመውጣት ዝግጁ ነበሩና በጎ እና ተራማጅ የሆኑ ተግባራትንም ከመቃወም አልቦዘኑም፡፡

በ1958 ዓ.ም መንግስት ድሆችን በአዲስ አበባ ሾላ አካባቢ ባዘጋጀው መጠለያ አስፍሮ እርዳታ ሲሰጣቸው የነበሩትን ዜጎች "የሾላ እስረኞች ናቸው" የሚል ስያሜ ሰጥተውና ይህንኑ መነሻ አድርገው ነበር ሰልፍ የወጡት፡፡

በ1959 ዓ.ም የሲቪክ መብቶችን የሚመለከት የሕግ ረቂቅ ለፓርላማ ሲቀርብ ተማሪዎች "የሲቪክ መብቶችን ለመገደብ ነው" ብለው ወደ ጎዳና ወጥተው ተቃወሙ፡፡ በ1960 ዓ.ም የቬትናምን ህዝብ ፀረ-አሜሪካ አቋም መያዝ ደግፈው ሰልፍ ወጡ፡፡ በዚያው ዓመት ማለቂያ ላይ በዩንቨርሲቲው ጊቢ ይካሄድ የነበረውን የባህል ፌስቲቫል (ፋሽን ሾው) "የኢምፔሪያሊዝም ነፀብራቅ ነው" በሚል ተቃውመው ሰልፍ ወጡ፡፡ በ1961 ዓ.ም "የትምህርት ስርዓቱ ይሻሻል" በሚል ያነሱት አመፅ ከዩንቨርሲቲው አልፎ በየግዛቱ ያሉ የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎችን አዳረሰ፡፡

ቀስ በቀስ እንቁላል በእግሩ ይሄዳል እንዲሉ በ1962 ዓ.ም የመጀመሪያ ወራት ተማሪዎቹ "ብሔር ብሔረሰቦች የራሳቸውን እድል በራሳቸው የመወሰን መብታቸው (እስከመገንጠል) መረጋገጥ አለበት!" ብለው በመወሰናቸው የጃንሆይ መንግስት ክፉኛ ተደናግጦ በተማሪዎቹ ላይ ጠንከር ያለ ጥቃት ለመሰንዘር ተገደደ፡፡ በዚያን ጊዜ ወደ ፊት እንደምናገኘው በመንግስት ጋዜጦች አማካኝነት መንግስት የፀረ ተማሪ ፕሮፓጋንዳ ዘመቻ ካካሄደና ካስጠነቀቀ በኋላ ነበር እርምጃ የወሰደው፡፡

ይህ የራስን እድል በራስ መወሰን የሚለው ጉዳይ በ1962 ዓ.ም በአደባባይ ይውጣ እንጂ ቀደም ካለው ጊዜ ጀምሮ የ"ጀብሃ" ዓላማ የነበረና ከ1961 ዓ.ም ፊት ለፊት በማይጋፈጠው "አዞ" በተሰኘው ቡድን አማካኝነት ወደ ዩኒቨርሲቲው እንዲሰርፅ የተደረገ ነው፡፡ አዞዎቹ እንደማንኛውም ተማሪ ሆነው በስውር ስለሚንቀሳቀሱ በሚያሰርጿቸው ድብቅ የጀብሃ ጥያቄዎች ምክንያት ሌሎች አገዛዙን ከመቃወም አንፃር ብቻ ሆ ብለው ሰልፍ የሚወጡና የጀብሃን ዓላማ የማይደግፉት ተማሪዎች ነበሩ፤ የመንግስት የቅጣት እርምጃ ሰለባ የሚሆኑት፡፡

ፕ/ር ላጲሶ ይህን ጉዳይ ሲገልፁት፤ "በዘመኑ በአገር ውስጥና በውጪው ዓለም ስርዓቱን ለመጣል የሚታገሉት አካላት አስከፊው የፊውዶ ቡርዣ ስርዓት ላይ አስቀድሞ የመሣሪያ ትግል በመክፈቱ ጀብሃ ተራማጅ



ቡድን እንደነበር በመገመት ከ1954-1961 ድረስ የአንድነት ድጋፍ ይሰጡት ነበር፡፡ ነገር ግን ታሪክና ጊዜ በኋላ እንዳሳየው የጀብሃ ዓላማ ፀረ-ኢትዮጵያ ከሆኑ አካባቢ አገሮች የመሣሪያና የገንዘብ እርዳታ አግኝቶ የኤርትራን ክፍለ ሀገር ከኢትዮጵያ ቆርጦ የዓረቡ ዓለም አካል ማድረግ ነበር፡፡ ከ1954-1961 ድረስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የ"አዞ" ማኅበር በሚል ህቡዕ ድርጅት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ማኅበር (አአዩተማ) አመራር ውስጥ ጀብሃን በስውር አሰራር የሚደግፉ ግለሰቦች ነበሩ" በማለት ነው፡፡

ይህን የጀብሃን የመገንጠል ዓላማ በሰሜን አሜሪካ ያለው የተማሪዎች ማኅበር ለረጅም ጊዜ መርምሮ በ1961 ዓ.ም በነሐሴ ወር በፊላደልፊያ ከተማ ባካሄደው 17ኛው ጉባኤ ላይ ዓላማውን የሚነቅፍ አቋም ወሰደ፡፡ ምክንያቱም የጀብሃ አቋም "የኤርትራን ህዝብ የማይወክል፣ በኢምፔሪያሊዝምና በፊውዳሊዝም የጋራ ጠላቶቻቸው ላይ የኢትዮጵያ የብሔረሰቦችንና የሠርቶ አደሩን ህዝብ መደባዊ የትግል አንድነት የሚያዳክም አድሃሪ ኃይል ነው" በሚል አወገዘ፡፡ ይህን የሰሙት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ማኅበር ውስጥ ያሉት የጀብሃ ደጋፊዎች ማለትም "አዞዎቹ" በፊላደልፊያ የተወሰደውን አቋም "የብሔር ትምክህተኝነት መገለጫ ነው" ብለው የነቀፋ መልስ ሰጡ፡፡ በዚህም ሳይወሰኑ ለፊላደልፊያው አቋም ምላሽ ይሆን ዘንድ በህዳር 7 ቀን 1962 ዓ.ም በማኅበሩ መጽሔት በታገል ቅጽ 5 ቁጥር 2 ላይ "የብሔረሰቦች ጥያቄ በኢትዮጵያ" በሚል ርዕስ "አብዛኛው የኢትዮጵያ ማኅበረሰቦች በማኅበራዊ የእድገት ደረጃቸው ብሔሮች ስለሆኑ ከጨቋኙ ስርዓትና መንግስት የመገንጠል መብታቸው የተጠበቀ ነው" በማለት ጠንካራ አቋም በመውሰዳቸው የታህሳስ 1962 የመንግስት ቁጣና ርምጃን እንዲከሰት አደረጉ፡፡

ጽሁፉ በሕዳር 7 በታገል መጽሔት ከወጣበት ጊዜ ጀምሮም መንግስት ለሁለት ሳምንታት ያህል የኃይል እርምጃ ከመውሰዱ በፊት የተማሪዎችን አቋም የሚያጣጥል የማስ ሚዲያ ዘመቻ ከፍቶ ተማሪዎችንም እያስጠነቀቀ ቆየ፡፡

ህዳር 19 ቀን 1962 ዓ.ም መንግስት በ"አዲስ ዘመን" ጋዜጣ ላይ ጉዳዩን አስመልክቶ ተከታዩን ጽሁፍ አትሞ አወጣ፡፡ የጽሁፉ ርዕስ "ከመጠኑ አለፈ" የሚል ነው፡፡

"ገና በማደግ ላይ ያሉ አገሮች ከሚመኙት የኢኮኖሚ፣የፖለቲካና የማኅበራዊ ኑሮ የስልጣኔ ደረጃ ለመድረስ ከተፈጥሮ ሐብት፣ከሰው ጉልበትና ከካፒታል ሌላ፤ እውቀት፣ኅብረት እና ፀጥታው የተጠበቀ መንግስት የፀና አቋም እንዲኖር አስፈላጊ ነው፡፡ሠላምና ፀጥታ ሲታጣ፣ ስርዓትና ሕግ ሲጣስ በህይወትና በንብረት ላይ የሚያስከትለውን ጥፋት

ለመገንዘብ የሩቅ ምሳሌ መሻት አያስፈልግም፡፡ ባለፉት ወራቶች ውስጥ በጥቂት ተማሪዎች አነሳሽነት አልፎ አልፎ ፀጥታ የሚያደፈርስ በህዝብ፣ በህይወትና ንብረት ላይ አደጋ የሚያደርስ ሁከት እየተፈጠረ ጥፋተኞቹ ከሕግ ፊት እየቀረቡ ቅጣታቸውን እንዲቀበሉ መደረጉ ይታወሳል፡፡

ጥቂቶቹ ተማሪዎች የኢትዮጵያን አንድነት በሚጠሉ የባዕድ ተንኮለኞች ጋር በመተባበር በአገሪቱ ውስጥ ፀጥታ ለማደፍረስ፣ ለሠላማዊው ህዝብ ሠላም ለመንሳት ያደረጉት ጥፋት በትዕግስትና በይቅርታ ታልፎ ሳለ ሰሞኑን ጥቂቶች የዩንቨርስቲ ተማሪዎች የሚያሳዩት ተግባር ሕገወጥ ከመሆኑም አልፎ መንግስት ከዚህ ቀደም እንዳደረገው ሁሉ በትዕግስት ከማይታለፍበት ደረጃ ደርሷል" ይላል፡፡

ቀጥሎም በማግስቱ ህዳር 20 ቀን 1962 ዓ.ም "ፍሬ ቢስ ሙከራ" በሚል ርዕስ በዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ ላይ ተከታዩን ጽሁፍ መንግስት አውጥቷል፡፡ "የኮሚኒዝምን አይዲኦሎጂ እናስፋፋለን የሚሉት ጥቂት የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች በየጊዜው በሚያወጡት መጽሔታቸውና በሚበትኗቸው ወረቀቶች የህዝብ ፀጥታና ሠላማዊ ኑሮ ለማደፍረስ መሞከራቸው ተደጋግሞ ተገልጧል፡፡ የባዕድን ፍልስፍና በመከተል የአገሪቱን ነዋሪ ስርዓትና ባህል ለመሻር መሞከር ከንቱነት ነው፡፡

ኢትዮጵያ እንደሌሎች መንግስቶች በሕገ-መንግስት ትመራለች፡፡ሕገ-መንግስቱም ግልፅና ቀና ነው፡፡ከሕገ-መንግስቱ ውጪ የሆነ ሁሉ ሕጋዊ አይደለም፡፡ ያስከስሳል፡፡ያስቀጣል፡፡ሕገ-መንግስቱን የሚሳደብ፣የሚፃረር፣ የሚተናኮልና የሚቃረን የመንግስት ጠላት ነው፡፡ ህዝብ አምኖ የተቀበለውን ስርዓት ለመሻር ባዕድ አሳብ የመሰንዘር፣የቆየውንና የኖረውን ልማድ ሁሉ የሚያንኳስስ፣ሃይማኖትን የሚያቀል፣አባቶችን የሚያዋርድ፣የተደነገጉትን ሕጎች የማይታዘዝ፣በአጉል ትምክህትና ትዕቢት የሚመራ ብቻ ስለሆነ አሳቡና ዝንባሌው አደገኛ ነው፡፡"

በዚህ ዓይነቱ ዘመቻ መንግስት ለህዝቡ አቋሙን በተደጋጋሚ ከገለፀና ተማሪዎችንም ካስጠነቀቀ በኋላ ተማሪዎቹም ከተግባራቸው ለመታቀብ ስላልሞከሩ ታህሳስ 19 ቀን 1962 ዓ.ም ቀደም ሲል እንዳየነው የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ማኅበር ፕሬዝዳንት የነበረውን ጥላሁን ግዛውን ጨምሮ ከ20 በላይ ተማሪዎች በግርገሩ ተገደሉ፡፡ ዩንቨርሲቲውም ላልተወሰነ ጊዜ ተብሎ ተዘጋ፡፡ የታገል መጽሔት ህልውናም አከተመ፡፡ በዚህ ጊዜ ነው ገሚሱ የጀብሃ ደጋፊዎች የነበሩት የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ወደ ትጥቅ ትግሉ አምርተው ከጀብሃ ጋር የተቀላቀሉት፡፡

The crocodile society ወይም የ"አዞ" ማህበር በስውር የትግል ስልቱ እየተጠቀመ ረጅም መንገድ የመጓዙን ያህል፤ በማኅበሩ ስም የሚከናወኑትን አመጾች አጋግሏል፡፡ መንግስት የአገር ውስጡን የተማሪ



ማኅበር ከበተነው በኋላም ገሚሶቹ በርሃ ቢገቡም የቀሩት ደግሞ የመንግስት ተፅዕኖ ያስመረራቸው መስለው ያንኑ የአዞ ዓላማና ተግባር፤ እንዲሁም ምስጢራዊ የትግል ስልትና አሰራራቸውን ይዘው በልዩ ልዩ መንገዶች ወደ አሜሪካና ወደ አውሮፓ ተሰደው በኢተማአ እና በኢተማሰአ ውስጥ ተቀላቀሉ፡፡

በነሐሴ ወር 1962 ዓ.ም ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ማኅበር አባላት ጥቂቶቹ የአዞ ማኅበር አሰራር ኢንጂነር በነበረው በብርሃነ መስቀል ረዳ መሪነት አንድ የኢትዮጵያ መንገደኞች አውሮፕላን ጠልፈው ወደ ሱዳን ካርቱም ገቡ፡፡ ከካርቱም ወደ አልጀሪያ በመሄድም በብርሃነ መስቀል መሪነት ራሳቸውን የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር በሰሜን አፍሪካ ብለው ሲሰይሙ ቁጥራቸው 8 ያህል ነበር፡፡

ወደ አውሮፓና ወደ አሜሪካ የፈለሱት የቀድሞው የአአዩተማ አባላትና የአልጀሪያው ቡድንም በኢትዮጵያ አብዮትና የብሔረሰብ ጥያቄዎችን በሚመለከቱ ጉዳዮች ተመሳሳይ አቋም የነበራቸው ሲሆን፤ በአገር ውስጥ ከቀሩት አባላትና አመራር ጋርም የትግል አንድነታቸው እንደፀና ነበር፡፡

የሰሜን አሜሪካው ቡድን በፊላደልፊያ የወሰደውን አቋም የአውሮፓው ቡድን ሳይቀበለው የቀረና ከአገር ውስጡ ቡድን ጎን ተሰልፎ ያወገዘበት ሁኔታ ተፈጥሮ የነበረ ቢሆንም፤ በስተመጨረሻ ግን የአልጀሪያው ቡድንና ሸሽተው የሄዱ አባላትና አመራር መልሰው በአዉሮፓው ቡድን የሂስ ዘመቻ ሲከፍቱበት እናያለን፡፡

የተማሪዎች ዓለም አቀፍ ስርጭትን ተከትሎም በአውሮፓና በአሜሪካው ቡድን ገብተው የተቀላቀሉ የጀብሃ ዓላማ አራማጆች ሁኔታውን አወሳሰቡት፡፡ ወደ አሜሪካ የተጓዙት የአገር ውስጥ ማኅበሩ አባላትና አመራር በነሐሴ ወር 1962 ዓ.ም በዋሽንግተን ዲሲ በጆርጅ ዋሽንግተን ዩኒቨርሲቲ በተካሄደው 18ኛው የኢተማሰአ ጉባኤ ላይ ተገኝተው የ17ኛውን የፊላደልፊያ አቋም "አደገኛ የሆነ የብሔር ትምክህተኝነት ነበር" በማለት የውግዘት መግለጫቸውን ደግመው አሰሙ፡፡ ሲቀጥሉም በኢትዮጵያ አብዮቱን ለማስነሳት ጊዜው መድረሱን በመጠቆምና የላቲን አሜሪካ ታጋዮችን ፊደል ካስትሮንና ቼጉቬራን በመጥቀስ እነሱ ያካሄዱትን አይነት የትጥቅ ትግል በኢትዮጵያ ለመጀመር "ፋኖ ተሰማራ እንደካስትሮ እንደቼጉቬራ" በማለት ከሌሎች መሰል መፈክሮች ጋር በታላቅ ጩኸት መሸለል ጀመሩ፡፡ የኢተማሰአ አባላትንና አመራሮችንም "የወንበር ላይ ምሁር" ብለው ዘለፏቸው፡፡

እነዚሁ ፎካሪዎች ከጉባኤው በኋላ በነበሩ 12 ወራቶች በሰሜን አሜሪካ የሚገኙትን ቅርንጫፍ ማኅበራትና አባላት በመቀስቀስና